# የደብረ ነጐድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሰራረትና ቁሳዊ ባህል ጥናት

በ

ተስፋዬ ተገኝ

(GSR/2299/01)

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲ ፋክልቲ

የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የካቲት 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የደብረ ነጐድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሰራረትና ቁሳዊ ባህል ጥናት

በ

ተስፋዬ ተገኝ

(GSR/2299/01)

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲ ፋክልቲ የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያ

የቀረበ

አማካሪ

ዮናስ አድማሱ (ዶ/ር)

የካቲት 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የደብረ ነጐድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሰራረትና ቁሳዊ ባህል ጥናት

በ

ተስፋዬ ተገኝ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲ ፋክልቲ
የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| ዮናስ አድማሱ | Yonas Admassu |
| አማካሪ | ፊርማ |
| | |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |
| | |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# ምስጋና

በመጀመሪያ ጥናቱ እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ረቂቁን በማረምና በተለያዩ ጊዜያት ሙያዊ አስተያየትና ምክር በመስጠት ለረዱኝ አማካሪዬ ዶክተር ዮናስ አድማሱ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የቃልም ሆነ የጽሑፍ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ ግለሰቦች፣ እንዲሁም ለደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣ ለገዳሙ አበምኔት፣ ለአባ ኪዳነ ቃልና ለገዳሙ የካህናት ማሰልጠኛ መምህራን በያሉበት ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ወንድሜ ብርሃኑ አድማሱና ቢንያም ብርሃኑ በገንዘብና በሞራል ከመደገፍ በተጨማሪ ለዚህ ደረጃ እንድበቃ የእናንተ አስተዋጽኦ ጉልህ ነውና በልቤ ውስጥ የተለየ ቦታ አላችሁ፡፡

ባለቤቴ ዘቢባ እንድሪስ ከኔ ልታገኚ የሚገባሽን ፍቅርና ድጋፍ ሳትሽ፣ ልጅ የማሳደጉን ኃላፊነት ብቻሽን በመወጣት ለትምህርቴ ትኩረት እንድሰጥ አድርገሻልና ሳመሰግንሽ እወዳለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ላይ የተካሄደ ሲሆን፤ የገዳሙን አመሰራረት፣ የገዳማውያኑን የእለት ተእለት ህይወት፣ አለባበስና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ቁሶች መመርመር አብይ ትኩረቱ ነው፡፡

ጥናቱን ከግብ ለማድረስ ሶስት ጊዜ የመስክ ምርምር የተካሄደ ሲሆን፤ ለ25 ቃል አቀባዮች ቃለ መጠይቅ ቀርቧል፡፡ በገዳሙ ማዕቀፍ ውስጥ የቆሎ ተማሪዎች የሚገኙ ቢሆንም በጥናቱ ትኩረት የተደረገው በምንኩስና ተወስነው በሚኖሩ ገዳማውያንና በገዳሙ ሰራተኞች ላይ ነው፡፡ ለምንኩስና ወደ ገዳሙ የሚመጡ መናንያን ከመመንኮሳቸው በፊት የአመክሮ ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡ ከመነኮሱ በኂላም የክህነት ስልጣንንና "ድንግልነት"ን መሰረት በማድረግ ገዳሙን እንዲያገለግሉ ይደረጋል፡፡

የገዳማውያኑ ምግብ ዳቤና እንጀራ ሲሆን፤ ለዳቤውም ሆነ ለእንጀራ ዝግጅቱ የተወሰነ ፕሮግራም አለ፡፡ ንፍሮ በገዳሙ ተዘውታሪ ምግብ ባይሆንም አልፎ አልፎ የሚመገቡነት ሁኔታ አለ፡፡

ገዳማውያኑን በሚያደርጉት ቆብ፣ በሚለብሱት ቀሚስ፣ በቅናተ ዮሐንስና ሥጋ ማርያም አማካይነት በአመክሮ ያሉና የመነኮሱ መሆናቸውን፤ በሚደረግላቸው የግንዘት ስርዓት ደግሞ በዓለም የኖሩ፣ ደናግልና በክህነት ስራ ላይ የነበሩ መነኮሳት በማለት መክፈል ይቻላል፡፡ ልብሳቸውና ቆባቸው ጥቁር፣ ቢጫ እና ወይባ ወይም አፈር የተነከረ ነው፡፡ ገዳማውያኑ የሚለብሱት ቀሚስ፣ የሚያደርጉት ቆብ፣ ስጋ ማርያምም ሆነ ቅናተ ዮሐንስ እንዲሁም ለጸሎት የሚጠቀሙበት መቁጠሪያ፣ የግንዘት ስርዓቱ ሁሉ ተምሳሌታዊ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ጥናቱ በይሁንታ ክፍሉ ጠቅላይ ቤተ ክህነት፣ የሐገረ ስብከቱ ጽህፈት ቤት እንዲሁም መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ገዳሙንና ገዳማውያኑን ሊደግፏቸው እንደሚገባ በመጠቆም ተጠናቋል፡፡

# ማውጫ


አርዕስት ገጽ

ምስጋና ---------- ሀ

አጠቃሎ ---------- ለ

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ ---------- 1

1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ---------- 1

1.2 የጥናቱ ዓላማዎች ---------- 2

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታዎች ---------- 3

1.4 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ---------- 3

1.5 የጥናቱ ወሰን ---------- 6

1.6 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ---------- 7

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳን ---------- 9

2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ---------- 9

2.1.1 የገዳምና ገዳማዊ ህይወት አጀማመር ---------- 9

2.1.1.1 የገዳምና ገዳማዊ ህይወት አጀማመርና መስፋፋት በኢትዮጵያ ---------- 12

2.1.1.2 የገዳም ኑሮ አይነቶች በኢትዮጵያ ---------- 17

2.1.2 ቁሳዊ ባህል ---------- 20

2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ---------- 23

2.2.1 ለመጀመሪያ ዲግሪ የቀረቡ ጥናቶች ---------- 23

2.2.2 ለሁለተኛ ዲግሪ የቀረቡ ጥናቶች ---------- 27

ምዕራፍ ሶስት

የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሰራረት፣

የስራ ክፍፍልና አይነት ---------- 32

3.1 የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሰራረት ---------- 32

3.2 የስራ ክፍፍልና አይነት ---------- 37

3.2.1 ተግባር ቤት ---------- 39

3.2.2 ግብርናና ሌሎች ተግባራት ---------------------------------------------------------- 41
ምዕራፍ አራት
የገዳማውያኑ የአመጋገብ ስርዓት፣ አለባበስ እና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸው ቁሶች ---------------------------------------------------------------------------------------------- 46
4.1 የገዳማውያኑ የአመጋገብ ስርዓት ---------------------------------------------------- 46
4.2 የገዳማውያኑ አለባበስ ------------------------------------------------------------------ 53
4.2.1 ቀሚስ ------------------------------------------------------------------------------ 53
4.2.2 ቆብ -------------------------------------------------------------------------------- 56
4.3 ገዳማውያኑ በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸው ቁሶችና ግንዘት ------------- 58
4.3.1 ገዳማውያኑ በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸው ቁሶች ------------------ 58
4.3.1.1 ቅናተ ዮሐንስና ስጋ ማርያም -------------------------------------- 58
4.3.1.2 አስኬማ ----------------------------------------------------------------- 60
4.3.1.3 መቁጠሪያ -------------------------------------------------------------- 61
4.3.1.4 መስቀል ----------------------------------------------------------------- 65
4.3.1.5 በትረ መስቀል ---------------------------------------------------------- 66
4.3.2 የመነኮሳት ግንዘት --------------------------------------------------------------- 67
ምዕራፍ አምስት
ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች -------------------------------------------------------------- 69
5.1 ማጠቃለያ ------------------------------------------------------------------------------- 69
5.2 የይሁንታ ሀሳቦች ---------------------------------------------------------------------- 70
ዋቢ ጽሑፎች ----------------------------------------------------------------------------------------- 72
አባሪዎች
አባሪ -1- ከካሴት የተገለበጡ ቃለ መጠይቆች ------------------------------------------------- 1
አበሪ -2- ከገዳሙ የተሰበሰቡ አፈ ታሪኮች -------------------------------------------------- 35
አባሪ -3- ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው ሰዎች ዝርዝር ------------------------------------------ 46
አባሪ -4- ከገዳሙ የተወሰዱ ፎቶዎች --------------------------------------------------------- 48

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ "የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሰራረትና ቁሳዊ ባህል ጥናት" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች የተዋቀረ ነው። የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን አጠቃላይ ሂደት የሚያስተዋውቅ ሲሆን፤ በውስጡም የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ አላማዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታዎች፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ የጥናቱ ወሰን እንዲሁም በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው የሚሉ ርዕሶችን ይዟል።

ምዕራፍ ሁለት የክለሳ ድርሳን ክፍል ነው። በዚህ ምዕራፍ ሁለት ንዑስ ርዕሶች ተካተዋል። የመጀመሪያው ርዕስ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት የቀረበበት ክፍል ሲሆን፤ በሁለተኛው ርዕስ ደግሞ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ተዳሰዋል።

ምዕራፍ ሶስት በጥናቱ ተተኳሪ የሆነው ገዳም የአመሰራረት ሁኔታና የሥራ ክፍፍል የተፈተሸበት ክፍል ነው።

ምዕራፍ አራት ደግሞ የገዳሙ መነኰሳት የእለት ተእለት እንቅስቃሴ፣ አለባበስና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸው ቁሶች እንዲሁም በገዳሙ የሚገኙ ቁሶችን ተአምራዊነት አስመልክተው የሚነገሩ አፈ ታሪኮች ትንተና የተደረገበት ክፍል ነው። መነኰሳቱ በየእለቱ የሚያከናውኑት የጸሎትና የአመጋገብ ስርዓት፣ ለጸሎቱም ሆነ ለምግብ እደላው የተመደበው ሰዓትና መጠን ትንታኔ የተሰጠው በዚሁ ክፍል ነው።

ምዕራፍ አምስት ደግሞ የጥናቱን ማጠቃለያና ይሁንታ ይዟል። በመጨረሻም የዋቢ ጽሑፎች ዝርዝርና የተለያዩ አባሪዎች ቀርበዋል።

### 1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

በሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ላይ ይህን የጥናት ወረቀት እንዳቀርብ ካነሳሱኝ ምክንያቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ለጥናት የተመረጠው ገዳም የተመሰረተበትን ሁኔታ የማጥናት ፍላጎት ስላደረብኝ፣
- ገዳሙ "በመካከለኛው የታሪክ ዘመን (በ13ኛው ክፍለ ዘመን)" ለምንኩስና ህይወት ማበብ፣ ለገዳማት ምስረታ እና መስፋፋት መነሻ መሆኑ ቢታመንም[1] በመንግሥትም ሆነ በሚመለከታቸው አካላት የእድሜውን ያህል ትኩረት አለማግኘቱ፤ እንዲሁም ከ1985 ዓ.ም በኋላ ለሀገረ ስብከቱ የተመደቡት ሊቀ ጳጳስ ተረስቶ የነበረውን የወንዶች ገዳምና ከናካቴው ጠፍቶ የነበረውን ቤተ ደናግል እንደገና የመሠረቱበት ሁኔታ ትኩረቴን ስለሳበው፣
- የገዳማውያኑን የአመጋገብ ስርዓትና የእለት ተእለት እንቅስቃሴ፣ አልባሳታቸውንና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ቁሶች አስመልክቶ የተደረገ ሰፊ ጥናት አለመኖሩ፣
- በገዳማውያኑ የሚነገሩት አፈ ታሪኮች በተለይም ቁሳቁሶቹን አስመልክቶ የሚነገሩት አፈ ታሪኮች እስካሁን ድረስ ተሰብስበው አልተቀመጡም። በዚህ ጥናት እነዚህን አፈ ታሪኮች ለመሰብሰብ ተሞክሯል። በገዳማውያኑ የሚነገሩ አፈ ታሪኮችን ሰብስቦ ማስቀመጥ ሌሎች አጥኚዎች በየጊዜው በአፈ ታሪኮቹ ላይ የሚታየውን የይዘት ለውጥ በጥልቀት እንዲመረምሩ ሊያነሳሳ ይችላል የሚሉት ለጥናቱ አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች ናቸው።

## 1.2 የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት የሚገኘውን የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሠራረትና ቁሳዊ ባህል ማጥናት ሲሆን፤ ዝርዝር ዓላማዎቹም፡-

- የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት (የወንዶች እና የሴቶች) ገዳም የአመሰራረት ሁኔታ በአጭሩ መቃኘት፣
- በገዳማቱ የሚኖሩ መነኰሳትን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ እና አመጋገብ ሁኔታ መመርመር፣

[1] መንግስቱ ጎበዜና አሳምነው ካሳ፣ 2000 ዓ.ም፣ 90።

- የገዳማውያኑን አለባበስና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ቁሶች መፈተሽና ተምሳሌታዊ መሆናቸውን ማሳየት፣
- በገዳሙ የሚገኙ ቁሳ ቁሶችን አስመልክቶ የሚነገሩ አፈ ታሪኮችን መሰብሰብ የሚሉት ናቸው።

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ይህ ጥናት በሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ላይ መደረጉ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት በአጥኚው ይታመናል።

- ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለሌሎች መረጃውን ለሚፈልጉ አካላት በመረጃ ሰጪነት ሊያገለግል ይችላል።
- አንድ ህዝብ እምነቱን ጠብቆ ለማቆየትና ለተከታዮቹ ለማስተላለፍ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ አፈ ታሪክ ነው። በመሆኑም በገዳማውያኑ የሚነገሩትን አፈ ታሪኮች ሰብስቦ ማስቀመጡ ስለገዳማውያኑ ሁኔታ ለማወቅ ያለው አስተዋጽኦ የጎላ ነው። ስለሆነም በአንድ ወቅት በገዳማውያኑ ላይ ጥልቅ የምርምር ስራ ማድረግ ለሚሹ አጥኚዎች ይህ ጥናት የገዳማውያኑንና የገዳሙን ሁኔታ ሊያሳይ እንደሚችል ይታመናል።
- በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍልም ሆነ በሌሎች የትምህርት ክፍሎች በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ለማድረግ ለሚሹ ቀጣይ አጥኚዎች እንደ መነሻ ሊያገለግል ይችላል።
- ወደፊት ስለገዳሙ አጠቃላይ ሁኔታም ሆነ ይህን ገዳም ከሌሎች ገዳማት ጋር በንጽጽር ማጥናት ለሚፈልጉ አጥኚዎች ይህ ጥናት እንደመነሻ ሊያገለግል ይችላል።

## 1.4 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

ጥናቱ በዋነኛነት በመስክ መረጃ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ለመስክ ጥናት የሚያገለግሉ የተለያዩ ዘዴዎች በቅንጅት ይሰራባቸዋል። ፈቃደ አዘዘ፣ “የመስክ ምርምር በሦስት ልዩ ልዩ መንገዶች ሊካሄድ ይችላል። እነዚህ ሦስት መንገዶች ምልከታ

(Observation)፣ ኢንተርቪው (Interview) እና መጠይቅ (Questioner) ናቸው" (1991፣ 90) በማለት ይገልጻሉ፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢም ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም በመሄድ በምልከታና በቃለ መጠይቅ አማካይነት ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ ምልከታው የገዳማውያኑን እንቅስቃሴ፣ አለባበስና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ቁሶች ለመቅረጽና ለመዘገብ ያስቻለ ሲሆን፤ ቃለ መጠይቁ ደግሞ ስለ ገዳማውያኑ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ እንዲሁም በገዳሙ የሚገኙ ቁሶችን ተአምራዊነት በሚመለከት በገዳማውያኑ የሚነገሩ አፈ ታሪኮች ለመዘገብ አስችሏል፡፡ በምልከታው በወንዶችም ሆነ በሴቶች ገዳም ያሉ ተግባር ቤቶች የሥራ ሁኔታ፣ የገዳማውያኑ የልማት እንቅስቃሴ ወዘተ. የታዩ ሲሆን፤ ለአበምኔቱ (ለሴቶች እመምኔት)፣ ለመጋቢዎች፣ ለጓል (ዕጓል) መጋቢዎች፣ ለተቋሙ መምህራኖች እና በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ለተሠማሩ አርድእቶች፣ ለሊቀ ረድኦች፣ ለገበዞች እና ለደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ወዘተ. ቃለ መጠይቅ ቀርቧል፡፡

ጥናቱ በዋነኛነት ከመስክ በሚገኝ መረጃ ላይ ቢመሰረትም ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት ከልዩ ልዩ ቤተ መጻሕፍት ገዳምንና ገዳማውያንን የሚመለከቱ ጽሑፎችን ተመልክቻለሁ፡፡ እንዲሁም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰሩ የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ላይ ዳሰሳ አድርጌያለሁ፡፡

የመስክ ሥራው በዋነኛነት የተጀመረው ከክፍለ ትምህርቱ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት በተጻፈልኝ የትብብር ደብዳቤ መሰረት፣ ከጠቅላይ ቤተ ክህነቱ (ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም) ለደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት የትብብር ደብዳቤ በማስጻፍ፤ እንዲሁም ከሀገረ ስብከቱ ጽህፈት ቤት ለገዳሙ ተመሳሳይ የትብብር ደብዳቤ (የካቲት 02 ቀን 2002 ዓ.ም) በማስጻፍ ነው፡፡

ከጠቅላይ ቤተ ክህነትና ከሀገረ ስብከቱ የተጻፉት የትብብር ደብዳቤዎች በገዳሙ አስተዳደር በኩል መልካም አቀባበል እንዳገኝ ረድተዋል፡፡ በተጨማሪም ደብዳቤዎቹን ለገዳሙ አበምኔት መምህር አባ ፍቅረ ዮሐንስ ገብረ ህይወት ከሰጠሁ በኋላ በማግስቱ የመስክ ስራውን ስጀምር የሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ አገኘኋቸው፡፡ ከእሳቸው ጋርም የካህናት ማሰልጠኛውን እና የቤተ ደናግሉን የሽመና እንቅስቃሴ ስንመለከት በርካታ መነኮሳት አይተውኝ ነበር፡፡ ይህም በገዳሙ ያለችግር ለመንቀሳቀስና በገዳማውያኑ ዘንድ አመኔታ እንዳገኝ ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሮልኛል፡፡ አበምኔቱንም ሊቀ ጳጳሱ እንዲተባበሩኝ

ስላሳሰቧቸው ለመስክ ሥራው መሳካት ለቃለ መጠይቅ ከመተባበር ጀምሮ በካህናት ማሰልጠኛው መምህራን መኖሪያ ቤት እንዳርፍ በመፍቀድ ተባብረውኛል፡፡

በዚህ መሰረት የመጀመሪያው የመስክ ምርምር ከየካቲት 04 ቀን 2002 ዓ.ም እስከ የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ተካሂዷል፡፡ በዚህ ወቅት ከሁለቱም ገዳም (የሴትና የወንድ) በአስተዳደር መዋቅራቸው መሰረት ከአበምኔቱ/እመምኔቷ፣ ከመጋቢ.ው/ዋ፣ ከሊቀ ረድዕ፣ ከሐሬቶች፣ ከቄሰ ገበዝ፣ ከሊቀ አበው፣ ከንል (ዕንል) መጋቢዎች፣ ከአርድእቶችና እና ከመነኰሳት ማሰልጠኛው መምህራን ወዘተ. በአጠቃላይ ከሃያ አምስት ቃል አቀባዮች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ አማካይነት ሰፋ ያለ መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

በመስክ ምርምሩ ወቅት የተገኙትን መረጃዎች በየርዕሱ በማስገባበት ወቅት የተጓደሉ ነጥቦችንና ግልጽ ያልሆኑ ነገሮችን ለማሟላት ዳግም የመስክ ምርምር ለማካሄድ ከመጋቢት 19 እስከ ሚያዝያ 10 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ በገዳሙ በመገኘት የተጓደሉ ነገሮችን ለማሟላት ችያለሁ፡፡ እንዲሁም ከሐምሌ 01/2002 እስከ ሐምሌ 30/2002 ዓ.ም ለሶስተኛ ጊዜ ወደገዳሙ በመሄድ የመስክ መረጃዎቹን የተሟሉ ለማድረግ ችያለሁ፡፡

በሁለተኛው ዙር የመስክ ምርምር ወቅት በቃለ መጠይቁና በምልከታው የተረሱ፣ የተዘለሉና ያልተብራሩ መረጃዎችን ለማስተካከል እንዲሁም በመጀመሪያው ዙር የመስክ ምልከታ ወቅት ያልተስተዋሉ ነገሮች ሊካተቱ ችለዋል፡፡ በሶስተኛው ዙር ደግሞ ለአጠቃላይ ስራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በሚገባ ለማጠናቀር ተችሏል፡፡ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በይበልጥ በመቅረጸ ድምጽና በማስታወሻ አማካይነት ቢሆንም አልፎ አልፎ በቪዲዮ ካሜራና በፎቶ ግራፍ ጠቃሚ መረጃዎችን ለመያዝ ተሞክሯል፡፡ መቅረጸ ድምጹ ከገዳማውያኑ ጋር የተደረጉትን ቃለ መጠይቆች ለመያዝ ያገለገለ ሲሆን፤ ለዚህም ስምንት የቴፕ ካሴቶች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ማስታወሻው ደግሞ ድምጻቸው በቴፕ ካሴት እንዲቀረጽ ፈቃደኛ ያልሆኑ ገዳማውያን የሚሰጡትን መረጃ ለመያዝና በምልከታው ወቅትም የተለያዩ ክንውኖችን መዝግቦ ለመያዝ አስችሏል፡፡

የገዳማውያኑን አልባሳት፣ የመቁንን አይነትና የመሳሰሉትን በቃለ መጠይቅ ብቻ ሳይሆን የፎቶ ግራፍና የቪዲዮ ካሜራ መሳሪያዎችን በመጠቀም ለመያዝ ተሞክሯል፡፡ ይሁንና ገዳማውያኑ አንድም ለትህትና በሌላም በኩል በዘመናዊ መሳሪያዎች ምስላቸው ከተቀረጸ የተለያዩ ሰዎች ያዩታል በማለት አብዛሃኛዎቹ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ ስለሆነም

እነዚህን መሳሪያዎችን መጠቀም በሚፈቀድበት ቦታ በመጠቀም ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በተፈጥሯዊ አውዳቸው ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡

በዚህ ሁኔታ የተሰበሰቡት የመስክ መረጃዎች ወደ ጽሁፍ ተገልብጠው በሚመለከታቸው ርዕስ ከተመደቡ በኋላ ከካልኣይ መረጃዎች ጋር በማጣጣም በገላጭ (Descriptive) የምርምር ዘዴ ተተንትነዋል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ኢትዮጵያ የብዙ አብያተ ክርስቲያናት ባለቤት እንደሆነች ሁሉ በርካታ ገዳማትና ገዳማውያን የሚገኙባት አገርም ናት፡፡ እነዚህ ገዳማትም በአገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች የተገደሙ ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳም በየገዳማቱ የሚገኙት ገዳማውያን የአመጋገብ ስርዓት፣ የጸሎት፣ የገዳማቱ አስተዳደራዊ መዋቅርና የስራ ክፍፍል ወዘተ. ልዩነት ይኖራቸዋል፡፡ የገዳማቱ የአመሠራረት ሂደትም የተለያየ ታሪካዊ እና አፈ ታሪካዊ መነሻ ይኖራቸዋል፡፡ ከነዚህ ገዳማት መካከልም የሐይቅ ደብረ ነጎድጓድ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ተጠቃሽ ነው፡፡

ይህ ጥናትም በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት፣ በተሁለደሬ ወረዳ በሚገኘው የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም የአመሠራረት ታሪክና ቁሳዊ ባህል ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ ከገዳም ሥሪት አንጻርም የአንድነት (የንፍሮ) ገዳም በሚባለው ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ የሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ማለት የወንዶች እና የሴቶች ቤተ ደናግልን ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ሰፊ ሽፋን የተሰጠው ለወንዶች ገዳም ነው፡፡ ይህም አንድም የሴቶቹ ገዳም ከናካቴው ጠፍቶ የነበረና በቅርቡ እንደገና የተመሰረተ ስለሆነ ሁለቱን ገዳማት በንጽጽር ለማጥናት አመቺ ባለመሆኑ ነው፡፡ በሌላም በኩል የሁለቱም ገዳማት መተዳደሪያ ደንብ ተመሳሳይ በመሆኑ ሁለቱ ገዳማት የጎላ ልዩነት አይታይባቸውም፡፡ በመጠይቁ ግን የሁለቱም ገዳማት አባላት ተካተዋል፡፡

በዚህ ጥናት መነኩሴ ሲባል ምንኩስና ያላቸው ወንድ መናንያንን የሚያመለክት ሲሆን፤ ሴቶችን በተመለከተ መነኩሲት ወይም መነኮሳይያት (ለብዙ ቁጥር) ተብሏል፡፡ መነኮሳት ሲባል ደግሞ ምንኩስና ያላቸው ሴትና ወንድ መናንያንን ያመለክታል፡፡

ገዳማውያን ሲባል ግን በአጠቃላይ በገዳማቱ የሚኖሩ ምንኩስና ያላቸውም ሆነ በአመክሮ ላይ ያሉትን ያጠቃልላል።

## 1.6 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው

በጥናቱ ወቅት የሥራውን ሂደት ሊገቱ የሚችሉ ችግሮች አጋጥመውኝ ነበር። ከነዚህም መካከል የወንዶቹ ገዳም አበምኔት መረጃ ለመስጠትም ሆነ ሌሎቹ ገዳማውያን እንዲጠየቁ ፈቃደኛ አለመሆናቸው አንዱ ነበር። ይሁንና ቀድሞ የማውቃቸው በገዳሙ የካህናት ማሰልጠኛ የሚያስተምሩ መምህራን ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ጋር ወደገዳሙ ከመሄዴ በፊት እንድተዋወቅ አድርገውኝ ነበር። ሊቀ ጳጳሱም ቅዳሜና እሁድ በተለይ አቢይ የጾም ወቅቶችን በገዳሙ በተሰራላቸው የ"መንበረ ጵጵስና" ቤት ያሳልፋሉ። ጠዋት ተነስተውም የካህናት ማሰልጠኛውንና የእናቶች ቤተ ደናግልን እንቅስቃሴ የመመልከት ልማድ እንዳላቸው አስቀድሞ ተነግሮኝ ነበር። እኔም የመስክ ምርምሩን የጀመርኩት ሊቀ ጳጳሱ በገዳሙ የሚገኙበትን ቀን ጠብቄ ስለነበር ወደካህናት ማሰልጠኛው ሲሄዱ ስላገኘኋቸው ከእሳቸው ጋር የማሰልጠኛውን ተማሪዎችና የቤተ ደናግሉን የልማት እንቅስቃሴ ተመለከትኩ። ይህም በገዳማውያኑ ዘንድ አመኔታ እንዳገኝ ያደረገ ይመስለኛል።

ወደወንዶች ገዳም ስንገባም አበምኔቱን ስላገኘናቸው ሊቀ ጳጳሱ የምፈልገውን መረጃ በመስጠት እንዲተባበሩኝ ስላሳሰቧቸውና እኔም የገዳሙ ታሪክ መጠናቱ ለገዳሙ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል በተደጋጋሚ በመንገር በእሳቸው በኩል የነበረው ችግር ሊቀረፍ ችሏል። እንዲሁም የገዳሙ ሙዚየም አስጎብኝ የሆኑት አባ ፍቅረ ማርያም ዓለማዊ ትምህርት የተማሩ ስለሆኑ የጥናቱን አላማ ተገንዝበው ገዳማውያኑን ለቃለ መጠይቅ እንዲተባበሩኝ በማግባባት ለስራው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

በሴቶች ቤተ ደናግል በኩል ደግሞ እማሆይ እህተ ማርያም ኪሮስ በቤተ ደናግሉ ያሉ ገዳማውያንን በማግባባትና እሳቸው ሲጠየቁ እንዲያዩ በማድረግ መነኮሳይያቱ ለቃለ መጠይቁ ተባባሪ እንዲሆኑ አድርገዋል። ይሁንና አንዳንድ ገዳማውያን "ቪዲዮውና ፎቶ ግራፉ በመገናኛ ብዙሃን የሚተላለፍ ነው። ይህ ደግሞ ቤተሰቦቻችን ያለንበትን ቦታ እንዲያውቁ ያደርጋል" በሚል ስጋት ያንገራገሩ ቢሆንም ፎቶ ግራፉም ሆነ ቪዲዮው

ለጥናት ስራው ፋይዳ ሲባል ብቻ የሚከናወን እንጂ በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ እይታ የማይውል መሆኑን በማስረዳት ፈቃደኛነታቸውን ለማግኘት ተችሏል።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

ይህ የክለሳ ድርሳን ክፍል ሁለት ርዕሶችን የያዘ ነው። የመጀመሪያው ርዕስ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት የሚቀርብበት ክፍል ነው። ሁለተኛው ርዕስ ደግሞ የተዛማጅ ጥናቶች ዳሰሳ የተካሄደበት ነው።

### 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

በዚህ ስር ሁለት ንኡስ ርዕሶች ይቀርባሉ። የመጀመሪያው ክፍል የገዳምና የገዳማውያን ምንነትና የዚህ አይነቱ ህይወት አጀማመርና የመስፋፋት ሂደት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እና በኢትዮጵያ የሚሉ ርዕሶችን ይዟል። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ቁሳዊ ባህልን በተመለከተ ከተለያዩ መጻሕፍት የተገኙ ሀሳቦች የሚቀርቡበት ነው።

#### 2.1.1 የገዳምና የገዳማዊ ህይወት አጀማመር

"ገዳም"[2] የሚለው ቃል የምናኔ[3] ቦታን የሚያመለክት ሲሆን፤ "ገዳማውያን" ማለት ደግሞ በዚህ ቦታ የሚኖሩ ሰዎችን ያመለክታል። ገዳም ብዙሃኑ ህዝብ ከሚኖርበት አካባቢ የራቀና ዓለማዊ ህይወትን የሚያመላክቱ እንቅስቃሴዎች የማይታይበት ቦታ ነው። ሀብተማርያም ወርቅነህም ገዳም፣ "በመሰረቱ ምድረ በዳ ማለት ነው፤ እንዲሁም ጫካው የበዛበት፣ ድምጸ አራዊት ግርማ ሌሊቱ የበዛበት ቦታ ሁሉ ወይም ቅጠል፣ ዛፍ የሌለበት፣ የምንም ድምጽ የማይሰማበት ቦታ ሁሉ" (1956፣ 72) ነው ይላሉ።

---

[2] ገዳም "መነኮሳት ከአለማዊ ኑሮ ተገልለው በሃይማኖታዊ ስርዓትና ደንብ እየተዳደሩ የሚኖሩበት ቤተ ክርስቲያን ያለበት ቦታ" ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1993፣ 507)።

[3] ምናኔ "የዓለምን ነገር፣ ተድላ ደስታን ንቆና ትቶ ከሰው በመለየት በዱር፣ በጫካ ወይም በገዳም መኖር" ማለት ነው (ዝኒ ከማሁ፣ 56)።

በዚህ ግርማ ሌሊቱ፣ ድምጸ አራዊቱ በበዛበትና ምድረ በዳ በሆነ ቦታ የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ ገዳማውያን ወይም መነኮሳት የሚባሉ ሲሆን፤ ከላይ በተጠቀሱት ቦታዎች ከሥጋዊ ሀብት፣ ደስታና ድሎት በአጠቃላይ ከዓለማዊ ህይወት ተገልለው፣ በሃይማኖታዊ ስርዓትና ደንብ መሰረት የሚኖሩ ናቸው። "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ" ገዳማዊ የሚለውን ቃል እንደሚከተለው ይገልጸዋል።

> የሳመ የጣመ ሳይቀምስ፣ የሞቀ የደመቀ ሳይለብስ፣ ጤዛ ልሶ፣ ድንጋይ ተንተርሶ፣ ድምጸ አራዊትን፣ ግርማ ሌሊትን ታግሶ፣ ከዓለማዊ ኑሮ ርቆ፣ ከሥጋዊ ግብርና ተድላ ደስታ ተጠብቆ፣ በእለታዊ ኑሮው ሁሉ ከሰው ሽክምንነት ተላቆ፣ ራሱን በራሱ እየረዳ ዘወትር በጾምና በጸሎት፣ በገድልና ትሩፋት ተጠምዶ የሚኖር የእግዚአብሄር ሰው ማለት ነው (1997፣ 22)።

በአጠቃላይ ገዳማዊ ማለት "ስለ እኔ ብሎ ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እህቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል፤ የዘላለም ህይወትንም ያገኛል" (ማቴ፡ 19፣29) የሚለውን አምላካዊ ቃል ተከትለው ሀብት ንብረትን፣ ወዳጅ ዘመድን ትተው፣ ከዓለማዊ ህይወት ተገልለው የሚኖሩ መነኮሳትን ያመለክታል።

ገዳማዊ ህይወት (ምንኩስና) ከተጀመረ ብዙ ዘመናት እንዳስቆጠረ የተለያዩ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ። በብሉይ ኪዳን ዘመን በብህትውና የሚኖሩ እንደ መልከ ጸዴቅና ኤልያስ ያሉ አንዳንድ ቅዱሳን ነበሩ። ሄኖክም ልጆች ከወለደ በኋላ እንዲህ ያለው ህይወት ለመንፈሳዊ ህይወቱ አጥጋቢ ሆኖ ስላላገኘው የብህትውና ኑሮ ጀምሯል (ያሬጋል፣ 1993፣ 185)። ሄኖክ በዚህ ዓለም ሚስት አግብቶ፣ ልጅ ወልዶና ንብረት አፍርቶ የእግዚአብሔርን መንገድ በመከተል ይኖር እንደነበር በዘፍጥረት፣ 5፣ 21-24 ላይ ተጠቅሷል። ያሬጋል አበጋዝ ደግሞ በዘመነ ብሉይ፣ "ሄኖክ የዚህን ዓለም ህይወት ከጀመሩ በኋላ (ሃብት ንብረት አፍርቶ፣ ሚስት አግብቶና ልጆች ወልዶ መኖር ከጀመሩ በኋላ) ለሚመንኑና ለሚመነኩሱ ሰዎች አብነት ሆኗል። ምንም እንኳ ብህትውና ከቀድሞ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም ምንኩስና ግን በሐዲስ ኪዳን የተጀመረ የህይወት መንገድ ነው" (1993፣ 185) ይላል።

ደስታ ተክለ ወልድ ባህታዊ ማለት "ባተሌ፣ ብቸኛ፣ ከሰው ተለይቶ በበኣት (ዋሻ) ተከቶ፣ ዘግቶ ለብቻው በዱር በገደል፣ በተራራ የሚኖር መናኝ" (1962፣ 262) ነው

ይላሉ። ምንኩስና ደግሞ በንጽህናና በድንግልና ሁኖ በጸሎት፣ በስግደት፣ በትምህርት በአገልግሎት ተወስኖ መኖር ማለት ነው። የሁለቱ ልዩነት ደግሞ ብህትውና ከሰው ተለይቶ በብቸኝነት መኖር ሲሆን፤ ምንኩስና ግን ከሌሎች መነኮሳት ጋር በገዳማዊ አገልግሎት የሚኖርበት ህይወት ነው።

ከሶስተኛው እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ምናኔ፣ ምንኩስና እና ገዳማዊ ህይወት በግብጽ፣ በሶሪያ፣ በፍልስጥኤም እና በሊባኖስ በርሃዎች የተስፋፋበት ወቅት መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ (ያረጋል፣ 1993፣ 188-189፤ ዳንኤል፣ 1998፣ 7-9)። የምንኩስና ህይወት ዋና ማዕከልም ግብጽ ነበረች (ያረጋል፣ 1993፤ ዳንኤል፣ 1998)።

ገዳማዊ ህይወት ስርዓት ባለው መንገድ በአባ እንጦንስ አማካይነት የተጀመረ ሲሆን፤ የእሱ ደቀመዝሙር የሆነው ጳኩሚስ ደግሞ ይህን ህይወት ወደ ተሻለ ደረጃ አሸጋግሮታል (ሉሌ፣ 1958፣ 60-61)። ጳኩሚስ ገዳማውያኑ የሚተዳደሩበትን ህግና ስርዓት ከማውጣቱም በላይ ገዳማውያኑ በእለት ተእለት ህይወታቸው የሚከተሏቸውን ሃይማኖታዊ ደንቦችንና ጋርዮሻዊ ኑሮን አስተዋውቋል (Knowles, 1966; 3; Chadwick, 1968; 6)። ስለሆነም የምንኩስና ህይወት መስራቹ ቅዱስ እንጦንስ ሲሆን፤ የመነኮሳት የአንድነት ህይወት (የጋራ ሥራ፣ የጋራ ማዕድ፣ የጋራ ጸሎት ባጠቃላይ ጋርዮሻዊ ህይወት) መስራቹ ደግሞ ጳኩሚስ ነው።

ገዳማዊ ህይወት በዚህ ሁኔታ ተጀምሮ የተስፋፋ ሲሆን፤ "በገዳም ህግና ስርዓት መሰረት ወንድና ሴት መናንያን በአንድ ገዳም ውስጥ በጋራ መኖር፣ በጋራ መጸለይ፣ በጋራ መስራት እና መመገብ፣ በአጠቃላይ በአንድ ገዳም ውስጥ የጋርዮሽ ኑሮ እንዲመሩ አይፈቀድም" (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ፣ 1997፣ 22)። ይሁን እንጂ ወንድና ሴት መናንያን በአንድ ጳድቅ መጠሪያ ገዳም ለየብቻ መኖርና ገዳማዊ ህይወታቸውን መምራት ይችላሉ። (ለምሳሌ በአቡነ ኢየሱስ ሞአ ስም በሚጠራው ገዳም ወንድና ሴት መናንያን ለየብቻ ይኖራሉ።) የወንዶች መናንያን ገዳም ከላይ በተጠቀሱት አባቶች እንደተጀመረ ሁሉ በሴቶች ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የአባ ጳኩሚስ እህት በሆነችው ማርያም አማካይነት በዚሁ ዘመን ተጀምሯል (ሉሌ፣ 1958፤ ያረጋል፣ 1993)።

### 2.1.1.1 የገዳምና የገዳማዊ ህይወት አጀማመርና መስፋፋት በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የክርስትና እምነት በይፋ የመንግስት ሃይማኖት በመሆን የተሰበከ ቢሆንም በሐዋርያት ስራ፣ 8፣ 27-39 ላይ እንደሚታየው ከዚህ ዘመን በፊት፣ የንግስት ህንደኬ[4] ጃንደረባ[5] ለስግደት ኢየሩሳሌም ደርሶ ሲመለስ፣ ጋዛ አካባቢ በፊሊጶስ አስተማሪነት፣ በክርስትና ሃይማኖት አምኖና ተጠምቆ ከተመለሰ በኋላ የክርስትና እምነትን በቤተ መንግስት እና በአካባቢው ማስተማሩና መስበኩ ይነገራል (ሉሌ፣ 1958 እና 1997፤ ተክለ ጻድቅ፣ 1966፤ ሥርግው፣ 1972 እና ጎርጎርዮስ፣ 1974)። ዓመቱን በተመለከተ አብዛኛዎቹ በ34 ዓ.ም (ጎርጎርዮስ፣ 1974፣ 22፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ፣ 1997፣ 13፤ መንግስቱ ጎበዜና አሳምነው ካሳ፣ 2000፣ 51) እንደሆነ ሲጠቅሱ ሉሌ መልአኩ ደግሞ በ35 ዓ.ም ነው ይላሉ (1958፣ 24)። ዓመቱን በተመለከተ የተለያዩ አመለካከቶች ቢኖሩም ሃይማኖቱ ከስርዓተ ጥምቀትና ከወንጌል ትምህርት ጋር የተዋወቀው በአንደኛው ክፍለ ዘመን መሆኑን ሁሉም ይስማሙበታል።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖትን ከስርዓተ ጥምቀቱና ከወንጌል ትምህርት ጋር ቀድማ ብትቀበልም በሀገሪቱ ጳጳስ ስላልነበር ስርዓተ ቁርባን እና መሰል የቤተ ክርስቲያን ስርዓቶችን በወጉ ሳታከናውን እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ቆይታለች። ስለሆነም በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ወደኢትዮጵያ የገባውና የተሰበከው የክርስትና እምነት የበለጠ ሳይጠናከርና ሳይስፋፋ እስከ አራተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ቆይቷል። በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ ከፍሬምናጦስ መምጣት በኋላ ደግሞ ሃይማኖቱ በተሻለ ሁኔታ ሊስፋፋ ችሏል (ሥርግው፣ 1972፤ ጎርጎርዮስ፣ 1974፤ Kaplan, 1982; መንግስቱ ጎበዜና አሳምነው ካሳ፣ 2000)።

---

[4] ህንደኬ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ንግስት እንደነበረች መንግስቱ ጎበዜ እና አሳምነው ካሳ (2000፣ 51-53) ገልጸዋል። በሐዋርያት ስራ ምዕ.8፣ ቁ.27ላይም ሕንደኬ የኢትዮጵያ ንግስት መሆኗ ተጠቅሷል።

[5] ጃንደረባ የሚለውን ቃል ደስታ ተክለ ወልድ "የንጉስ ባለሟል፤ በዥሮንድ፣ የገንዘብ ሹም፤ በተፈጥሮ ትእምርተ ተባዕት ያነሰው፣ የጎደለው፣ ብልቱ የሸንብራ አፍንጫ የሚያክል ሰው፤ ስለጽድቅ በፈቃዱ ከሴት የራቀ" (1962፣ 399) በማለት ገልጸውታል።

ፍሬምናጦስ ወደኢትዮጵያ ከወንድሙ ኤዲስዮስ (ሲድራኮስ) ጋር የመጣ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ የተጀመረውን የክርስትና ሃይማኖት ይበልጥ ለማስፋፋትና ለማጠናከር በሀገሪቱ ጳጳስ መኖር እንዳለበት ያምን ነበር (መንግስቱ ጎበዜን አሳምነው ካሳ፣ 2000፣ 55)። በመሆኑም በዘመኑ የጵጵስና ማዕረግ ከሚሰጥባቸው ሀገራት ጳጳስ ለማምጣት ከሁለቱ ወንድማማች ነገስታት ኢዛናና ሳይዛና ፈቃድና ትእዛዝ ተቀብሎ ወደ እስክንድርያ ሄደ። እዚያ ሲደርስም በኢትዮጵያ ያለውን የክርስትና ሃይማኖት ለአቡነ አትናቴዎስ በማስረዳት ለሀገሪቱ ጳጳስ እንዲሾምላት ጠይቋል። አቡነም የሀገሪቱን ቋንቋና ባህል ቀድሞ የሚያውቀው እሱ መሆኑን ስለተገነዘቡ የጵጵስና ማዕረግ ሰጥተውት በ330 ዓ.ም ተመልሷል (Parrinder, 1969፤ ሥርግው፣ 1972፤ ጎርጎርዮስ፣ 1974፤ Kaplan, 1982 እና ሉሌ፣ 1997)። ከዚያም ሁለቱን ነገስታት አስተምሮ አጥምቋቸዋል፤ "አብርሃና አጽብሐ" ብሎም የክርስትና ስም አውጥቶላቸዋል።

ፍሬምናጦስ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያው ጳጳስ ነው። ከጵጵስናው በኋላ ስሙ "አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን" ይባል ነበር። ይህ ሰው በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሰሩ በማድረግ፣ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የክህነት ሹመት በመስጠት፣ ለምእመናኑም የንስሐ አባት እንዲኖር በማድረግና ከተለያዩ ቋንቋዎች በርካታ መጻሕፍት ወደ ግዕዝ ቋንቋ በመተርጎም ለሃይማኖቱ መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል (መንግስቱ ጎበዜን አሳምነው ካሳ፣ 2000፣ 56)።

ክርስትና በጃንደረባውም ሆነ በፍሬምናጦስ አማካይነት ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ሃይማኖቱን ቀድመው የተቀበሉት ነገስታቱና ተከታዮቻቸው ናቸው። ጃንደረባው ንግስት ህንደኬን፤ ፍሬምናጦስ ደግሞ ሁለቱን ወንድማማች ነገስታት ሃይማኖቱን እንዲቀበሉ አድርገዋል። በተቀረው ዓለም ያለው ሁኔታ ግን ከዚህ የተለየ ነው። ማለትም በሌላው ዓለም ሃይማኖቱን አስቀድመው የሚቀበሉት አብዛኛዎቹ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙት (ተራው ህዝብ) የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው (ሥርግው፣ 1970፣ 5፤ Kaplan, 1982; 48)። ስለሆነም በኢትዮጵያ ነገሥታቱና ተከታዮቻቸው የክርስትና ሃይማኖትን ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል ቀድመው መቀበላቸው ሃይማኖቱ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ በፍጥነት እንዲስፋፋና ስር እንዲሰድ አድርጎታል። ይህንን ሁኔታ መንግስቱ ጎበዜና አሳምነው ካሳ ሲያስረዱ፤

ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ወደ አገሩ ተመልሶ መጀመሪያ የክርስትናን እምነት ያስተማረው ለንግሥት ህንደኬ ነበር፡፡ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በቅዱስ ፍሬምናጦስ አማካይነት አምነው የተጠመቁት አብርሃና አጽብሐ (ኢዛናና ሳይዛና) የተባሉት ሁለት ወንድማማቾች ነገሥታትም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መሰረት መጣልና መስፋፋት ታላቅ አስተዋጽኦ በማድረጋቸው ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው (2000፣ 53) ይላሉ፡፡

የክርስትና ሃይማኖት የመስፋፋት ሂደትን ስናይ፤ በኢትዮጵያ ከላይ (ከነገሥታቱና መኳንንቱ) ወደታች (ወደተራው ህዝብ) የወረደ ሲሆን፤ በሌላው ዓለም ደግሞ ከተራው ህዝብ ወደላይ እንደሆነ ከላይ ከቀረበው ሃሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ለሃይማኖቱ ስር መስደድና የመስፋፋት ሂደት የራሱ የሆነ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ጎን ይኖረዋል፡፡ ምክንያቱም ነገስታቱና ተከታዮቻቸው ሃይማኖቱን ቀድመው ሲቀበሉ ካላቸው ተሰሚነትና ተቀባይነት አኳያ ሃይማኖቱ በአጭር ጊዜ በተራው ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ከታች ወደላይ (ከተራው ህዝብ ወደነገስታቱና ተከታዮቻቸው) ከሆነ ግን ሃይማኖቱ ተቀባይነት የማግኘቱና ስር የመስደዱ ጉዳይ እምብዛም አጥጋቢ ላይሆን ይችላል፡፡

በሀገራችን የክርስትና እምነት በሁለቱም ሰዎች (በጃንደረባውና በፍሬምናጦስ) አማካይነት ቢተዋወቅም ለእምነቱ መስፋፋትና መጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት በአምስተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ከተለያዩ ቦታዎች (ከሶርያ፣ ከታናሿ እስያ ወዘተ.)፣ በሁለተኛው የኢትዮጵያ ጳጳስ በአባ ሚናስ ጊዜ፣ በንጉስ አልዓሜዳ ዘመነ መንግስት የመጡት ዘጠኙ ቅዱሳን (ተሥዓቱ ቅዱሳን) ናቸው፡፡ ወደ ኢትዮጵያ የመጡትም በአርዮስ ኑፋቄ ከተፈጠረው ሁከት ለመሸሽ ሲሆን፤ ኢትዮጵያን የመረጡትም በዚያ ጊዜ ነጻ የክርስቲያን ሀገር መሆንዋን በመስማታቸው እንደሆነ ይነገራል (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ፣ 1997፣ 23)፡፡

እነዚህ ቅዱሳን በ480 ዓ.ም ከመጡ በኋላ ለምንኩስና ህይወትና ለገዳማት መስፋፋት መሰረት እንደጣሉ በብዙ ምሁራን ይታመናል (ሉሌ፣ 1958 እና 1997፤ ሥርግው፣ 1972፤ ጎርጎርዮስ፣ 1974 እና Kaplan, 1982)፡፡ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ዘጠኙ ቅዱሳን ባንድ ወገን ከሁለት ባህርዮች ለመሸሽ፤ በሌላውም ወገን ክርስትናን በአንድ ባህርይ መንገድ በወገናቸው በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ለማስፋፋት ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸውን ጠቅሰው ዘመኑም ከ460-470 ዓ.ም ነው ይላሉ (1966፣ 346)፡፡

እነዚህ ቅዱሳን አክሱም ከገቡ በኋላ ቤተ ቀውጢን በተባለው የእንግዶች ማረፊያ (ትምህርት ቤት) ሆነው የህዝቡን ቋንቋ፣ ባህልና ወግ ወዘተ. አጥንተዋል፡፡ ከዚያም ስብከተ ወንጌል ለማስፋፋትና ገዳማት ለመመስረት ከአክሱም በመነሳት በየአቅጣጫው ተሰማርተዋል (ሉሌ፣ 1997፣ 29)፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች የክርስትና እምነትን መስበክና በአባ ጳኩሚስ የተጀመረውን ስርዓተ ምንኩስና እና አተገባበሩን ማስፋፋት ጀመሩ፡፡ ቅዱሳኑ በተለያዩ ቦታዎች ገዳማትና አብያተ ክርስቲያን ከማቋቋማቸውም በተጨማሪ የምንኩስና ስርዓትን በማስፋፋትና የተለያዩ መጻሕፍትን (መጽሐፍተ ብሉያት፣ ሐዲሳት፣ መጽሐፍተ ሊቃውንትና መጽሐፍተ መነኮሳት ወዘተ.) ወደ ግእዝ ቋንቋ መልሰዋል (ሥርግው፣ 1970፤ ታደሰ፣ 1972 እና Kaplan, 1982)፡፡ ባህሩ ዘውዴ (1998፣ 35) በኢትዮጵያ በርካታ ገዳማትና ቤተ ክርስቲያኖች የተመሰረቱት ከ1270-1527 እንደሆነ፤ በዚህ ወቅትም የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ የሐይቅ፣ የጣና፣ የዝዋይና የደብረ ሊባኖስ ገዳማት እንደተመሰረቱ ይገልጻሉ፡፡

እነዚህ ቅዱሳን በኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖትን በተለይ በአንድ ባህርይ በተዋህዶ መንገድ በያውራጃው ተበትነው በአትና ገዳም እያቋቋሙ ሃይማኖቱ እንዲስፋፋ አድርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብም ለነዚህ ቅዱሳን በስማቸው ታቦት እያስቀረጸና ቤተ ክርስቲያን እያሰራ "ብጹዓን፣ ቅዱሳን" አድርጎ ያከብራቸዋል፡፡

አባ አረጋዊ በደብረ ዳሞ የመሰረቱት ገዳም ለወንድ እንጂ ለሴት መናንያን አይደለም፡፡ ወደዚህ ገዳም ከወንድ በስተቀር እንስት መናንያን መግባት አይችሉም፤ በተጨማሪም እንስት የሆኑ እንስሳት ወደዚህ ገዳም አይገቡም፡፡ ሉሌ መልአኩ ይህን ሁኔታ ሲያብራሩ "በስለትም ሆነ በሌላ ምክንያት ከዶሮ በስተቀር እንስት የሆኑ እንስሳትም ወደ ገዳሙ እንዲመጡ አይፈቀድም" (1997፣ 30) ይላሉ፡፡ ስለዚህ ለሴት መናንያንም በሴት መነኮሳይያት አማካይነት ገዳማት ይቋቋሙ ነበር፡፡ ሴት መነኮሳይያት የምንኩስና ህይወታቸውን የሚመሩበት ገዳም በግብጽ በአባ ጳኩሚስ እህት አማካይነት እንደተመሰረተ ሁሉ በኢትዮጵያ ደግሞ በአባ አረጋዊ እናት ደብረ ዳሞ ገዳም ስር የእንስት መናንያን ገዳም ተመስርቷል፡፡ "ለሴቶች መጸለያ የሚሆን የአባ አረጋዊ እናት ቅድስት አድና ከተራራው ግርጌ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነችውን የኪዳነ ምሕረትን የሴት ገዳም መስርታለች" (ሉሌ፣ 1997፣30)፡፡

ጠቅለል ባለ ሁኔታ ኢትዮጵያ በጃንደረባው አማካይነት የክርስትና ሃይማኖትን ከተዋወቀች በኋላ በፍሬምናጦስ አማካይነት ደግሞ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ለመተግበር የሚያስችለውን ማዕርገ ጵጵስና አገኘች፡፡ በዘጠኙ ቅዱሳን አማካይነት ደግሞ ገዳማት ተቋቁመው ገዳማዊ ህይወት በሀገራችን ከመጀመሩም በተጨማሪ ለምእመናን መመሪያና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መፈጸሚያ የሚጠቅሙ መጻሕፍት ወደ ግእዝ ቋንቋ ተተርጉመዋል፡፡ ይህ ደግሞ ሃይማኖቱ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገና እየተጠናከረ መሄዱን አመላካች ነው፡፡

ይሁንና ዘጠኙ ቅዱሳን በአክሱምና በአካባቢዋ ገዳማት ቢመሰርቱም እነሱ ከመሰረቷቸው ውጪ እስከ አስራ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በኢትዮጵያ አዳዲስ ገዳማት አልተቋቋሙም ነበር፡፡ ከዘጠኙ ቅዱሳን በኋላ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ገዳማት የተመሰረቱትና የምንኩስና ህይወት መስፋፋት የጀመረው ከአስራ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ነው፡፡

በዚህ ዘመን ገዳማዊ ህይወትን ለማስፋፋት የቅዱሳኑን ፈለግ የተከተሉት አቡነ ኢየሱስ ሞዓ ናቸው፡፡ እሳቸው የመነኮሱትና የተማሩት ከዘጠኙ ቅዱሳን መካከል አንዱ በመሰረቱት የደብረ ዳሞ ገዳም ነው፡፡ ሉሌም ይህን ሃሳብ በማጠናከር "በአክሱም አካባቢ ተወስኖ የኖረውን ገዳማዊ ኑሮ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲሰራጭ ያደረጉት አባ አረጋዊ በመሰረቱት ደብረ ዳሞ ገዳም ስርዓተ ምንኩስናን ሲማሩና በተግባር ሲፈጽሙ የነበሩት አባ ኢየሱስ ሞዓ ናቸው" (1997፣ 65) ይላሉ፡፡

የሉሌን ሀሳብ በመደገፍ መንግስቱ ጎበዜና አሳምነው ካሳ ስለ አቡነ ኢየሱስ ሞአ የሚከተለውን አስፍረዋል፡፡

> በዘጠኙ ቅዱሳን የተጀመረው ይኸው ገዳማዊ ህይወት ከ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ይበልጥ ተስፋፍቶ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ለዚህ ሁሉ መሰረት የሆነው አስቀድሞ በተገለጸው የደብረ ዳሞ ገዳም አበምኔት በነበሩት አባ ዮሐኒ እጅ የመነኮሱትና ያገለገሉት አባ ኢየሱስ ሞዓ ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ መጥተው የመሰረቱት የአንድነት ገዳም ነው፡፡ የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም በመካከለኛው ዘመን በአገራችን ለምንኩስና ህይወት ማበብና ለገዳማት መስፋፋት ዋነኛ ማዕከል ሆኖ ያገለገለ ነው (2000፣ 89-90)፡፡

አቡነ ኢየሱስ ሞአ ከደብረ ዳሞ ገዳም ምንኩስና ከተቀበሉ በኋላ ወደሐይቅ እስጢፋኖስ መጥተው በመሰረቱት ገዳም በርካታ ገዳማውያንን አፍርተዋል። ከነዚህም መካከል አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ አቡነ ኂሩተ አምላክ፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ አቡነ ጸሎተ ሚካኤል፣ አባ ዘኢየሱስና አባ አሮን ዘዳሬት ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ መንፈሳዊ አባቶች በተጨማሪ እንደ አጼ ይኩኖ አምላክ የመሳሰሉ የሀገር መሪዎችም በገዳሙ ተምረዋል (ተክለ ጻድቅ፣ 1966፤ ሥርግው፣ 1969፤ ታደሰ፣ 1972፤ Kaplan, 1982፤ ያረጋል፣ 1993 እና ዳንኤል፣ 1999)።

በአጠቃላይ በአቡነ አረጋዊ የተመሰረተው የደብረ ዳሞ ገዳም በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ገዳም ከመሆኑም በተጨማሪ ለገዳማዊ ህይወት መመስረትና መስፋፋት ፈር ቀዳጅ ሆኖ ለብዙ ጊዜ አገልግሏል። በመካከለኛው ዘመን ደግሞ በአቡነ ኢየሱስ ሞዓ የተመሰረተው የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ አንድነት ገዳም ለምንኩስና ህይወት ማበብና ለገዳማት መስፋፋት ማዕከል በመሆን አገልግሏል።

## 2.1.1.2 የገዳም ኑሮ ዓይነቶች በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስር የሚተዳደሩት የእምነት ተቋማት የተለያየ ስያሜና ተግባር አላቸው። አባ ጎርጎርዮስ ስያሜዎቹን በተመለከተ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስሪት ሶስት ክፍል አለው። ይኸውም የገዳም፣ የደብር እና የገጠር ስሪት ነው" (1974፣ 198) ይላሉ። እነዚህ ስሪቶችም በሀገሪቱ ያሉ የእምነት ቦታዎችን ለመለየትና ለመመደብ ወይም የእምነት ቦታዎቹን ምንነትና ዓይነት እንዲሁም ተግባራቸውን ለማወቅ ያስችላሉ። ከስሪቶቹ አንዱ ገዳም ሲሆን፤ ይህም በሁለት ይከፈላል። አንደኛው ክፍል የአንድነት ገዳም ሲባል ሁለተኛው ደግሞ የቁሪት ገዳም ይባላል (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ፣ 1997፣ 23)። አባ ጎርጎርዮስ ደግሞ በኢትዮጵያ የሚገኙት የገዳም አይነቶች የንፍሮና የሕግ ተብለው ይከፈላሉ ይላሉ (1974፣ 188)። በአባ ጎርጎርዮስ አከፋፈል መሰረት የንፍሮ ገዳም የሚባለው የአንድነት ገዳምን ይተካል ወይም ያመለክታል።

በአንድነት (የንፍሮ) ገዳም ውስጥ የሚኖሩ ገዳማውያን በጋራ ይሰራሉ፣ በጋራ ይመገባሉ፣ በጋራ ይጸልያሉ፤ በአጠቃላይ የአንድነት ገዳም፣ ገዳማዊ አገልግሎት በህብረት የሚከናወንበትና ገዳማውያኑም በህብረት የሚኖሩበት ነው። በዚህ የገዳም

አይነት ውስጥ ገዳማውያኑ የእለት ጉርሳቸውንም ሆነ ሌሎች ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት በጋራ ይሰራሉ፤ ሰርተው ያገኙትንም በህብረት ይጠቀማሉ። በዚህ ስሪት የግል ሀብትና ንብረት ማፍራት፣ ከሌሎቹ ገዳማውያን የተለየ መመገብ ወዘተ. አይፈቀድም። ይህን በሚመለከት "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ" የተሰኘው መጽሐፍ የሚከተለውን አስፍሯል።

> በዚህ አይነቱ ገዳም ምንም አይነት የግል ንብረት ይዞታ አይፈቀድም። ያለ ጸሎትና ተግባር ስራ ፈት ሆኖ መቀመጥም በጥብቅ የተከለከለ ነው። ያለ በቂ ምክንያት እና ያለ ገዳሙ ማህበር ፈቃድ ከገዳሙ ማህበር ወጥቶ መዘዋወርም አይፈቀድም። አመጋገብንም በሚመለከት የገዳሙ ቀኖና የሚፈቅደውን የምግብ አይነትና መጠን ተላልፎ መመገብ ክልክል ነው (1997፣ 23)።

በአንድነት ገዳም ውስጥ ስራና ጸሎት የገዳማውያን የዘወትር ተግባር ናቸው። ገዳማውያኑ ደከመን፣ ሰለቸን ሳይሉ ያገለግላሉ። ይሁንና ለብዙ ጊዜ አገልግለው የደከሙ አረጋውያንና ህመምተኞችን ለይቶ የመጦርና የመንከባከብ ልማድ አለ። ነገር ግን አረጋውያኑም ሆነ ህመምተኞቹ እንዲያርፉ የሚደረገው በገዳሙ ማህበረሰብ ፈቃድ እንጂ በእነሱ ፍላጎት አይደለም። ምክንያቱም ገዳም ከመገልገል ይልቅ ማገልገል የሚስተዋልበት፤ የዓለማዊና ስጋዊ ፍላጎት ጨርሶ የማይታይበት ቦታ ነው። ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍም ከዚህ ሀሳብ ጋር ሳይጣላ "አቅመ ደካማ እንኳ ቢሆን ማህበሩ ድካሙን አይቶ ከስራ ነጻ እንዲሆን ካላደረገው በስተቀር እሱ ራሱ ደክሜአለሁ ልረፍ ብሎ አያርፍም፤ ልረፍ ብሎም አይጠይቅም" (ዝኒ ከማሁ፣ 24) ይላል።

ጠቅለል ባለ ሁኔታ የአንድነት ገዳም፣ ገዳማውያኑ ሙሉ ጊዜያቸውን በገዳማዊ አገልግሎትና በጸሎት የሚያሳልፉበት ነው። የስራም ይሁን የጸሎት ጊዜ በገዳሙ አማካይነት የሚወሰን ሲሆን፤ ከዚህ ስርዓት ውጪ ገዳማውያኑ በፈለጉት ጊዜ መስራት ወይም ማረፍ፣ ሲያሻቸውም ከገዳሙ መውጣትና መግባት አይችሉም። ማንኛውም እንቅስቃሴ ገዳሙ ባስቀመጠው ስርዓት የሚከወን እንጂ በገዳማውያኑ የሚወሰን አይደለም። ነገር ግን በገዳሙ ከሚሰጠው ስራ አብዝቶ መስራት፤ ራስን በጸሎትና ስራ ማድከም ይችላሉ፤ የገዳም ኑሮ ራስን ለስራና ለጸሎት ዝግጁ አድርጎ መኖርን ይጠይቃልና።

ገዳማውያኑ በራሳቸው ፈቃድ ሰርተው፤ ሲደክማቸው ማረፍ፤ በፈለጉበት ወቅትም መግባትና መውጣት የሚችሉበት የገዳም አይነት የቁሪት ገዳም ይባላል። በዚህ የገዳም ስሪት ውስጥ ገዳማውያኑ በሰሩት መጠን የግል ሀብትና ንብረት ማፍራት ይችላሉ። ሀብተማርያም ወርቅነህ፤ በዚህ ገዳም የሚኖሩ መነኮሳት በፈለጉት ጊዜ በግላቸው እየሰሩ፣ የግል ጥሪት፣ የግል ሀብት፣ የሚያፈሩና በዚያም የሚተዳደሩ ናቸው። በተጨማሪም በዚህ ገዳም ለመኖር የሚፈልጉት መነኮሳት ራስ የመውደድና ልዩ ችሎታ ያላቸው ናቸው ካሉ በኋላ ገዳማውያኑ ከውጪ ርዳታም ሆነ ሌላ ነገር ቢያገኙ ወዲያው ተከፋፍለው የሚለያዩ መሆናቸውን ይገልጻሉ (1956፣ 74)።

የአንድነት ወይም የንፍሮ ገዳም የሚሰራው "በአንድ በገለልተኛ ቦታ ተወስኖ በተጋድሎ ህይወቱን ያሳለፈ ጻድቅ ባረፈበት የታሪክና የሃይማኖት ቦታ" (ጎርጎርዮስ፣ 1974፣ 188) ነው። የህግ ገዳም ደግሞ ስሪታቸው እንደአድባራት ሆነው በቤተ ክህነት ወይም በመንግስት ትእዛዝ ገዳም ተብለው እንዲጠሩ የተሰየሙ ቦታዎችን ያመለክታል። አባ ጎርጎርዮስም፣ "የሕግ ገዳማት ገዳም ሊባሉ የቻሉበት ምክንያት ገዳም ተብለው እንዲጠሩ በባለስልጣን በመታዘዙ እንጂ በገዳማት ስርዓት የሚመሩ አይደሉም" (1974፣ 189) በማለት የሕግ ገዳማት ከአንድነት ወይም ከንፍሮ ገዳማት የሚለዩ መሆናቸውን ገልጸዋል ።

በሌላም በኩል በኢትዮጵያ የምናኔ ህይወት ታሪክ ውስጥ ከላይ ከተጠቀሱት የገዳም አይነቶች በተለየ ሁኔታ የሚኖሩ መናንያን አሉ። እኒህ መናንያን ከአንድነት ገዳማት ርቀው በሚገኙ አስፈሪ ጫካዎችና ዋሻዎች በብቸኝነት የሚኖሩ ናቸው። መናንያኑም እጅግ አስፈሪና ከነሱ መልካም ፈቃድ ውጪ እንደማይታዩ ይታመናል። ያረጋል አበጋዝ፣ በዚህ አይነት ሁኔታ የሚኖሩ ገዳማውያንን ሲገልጽ "በብሉይ ኪዳን ዘመን በብሕትውና የሚኖሩ እንደ መልከ ጼዴቅና ኤልያስ ያሉ አንዳንድ ቅዱሳን ነበሩ" (1993፣ 185) ይላል። "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ" በበኩሉ

> ከአንድነት ገዳማት ርቀው በሚገኙ አንዳንድ ጫካዎችና ዋሻዎች እንደ መልከ ጼዴቅና እንደ ዮሐንስ መጥምቅ የተለየ አለባበስና አስፈሪ ግርማ ሞገስ ያላቸው ባሕታውያን የሚከሰቱበት ጊዜ አለ። እነዚህ አይነቱ ባሕታውያን በህብረተሰቡ አጠራር "ግሑሳን" ይባላሉ። "ግሑስ" ማለት ከሰው ርቆ የሚኖር ስውር ባሕታዊ ማለት ነው። እነዚህ ግሑሳን

ባሕታውያን ራሳቸውን ግልጽ ለማድረግ ካልፈለጉ በቀር ማንም ሰው ፈልጎ ሊያገኛቸውም ሆነ ሊያያቸው አይችልም (1997፣ 24-25) ይላል።

ጠቅለል ባለ ሁኔታ በአንድነትም ይሁን በቁሪት የገዳም ስሪት ውስጥ በርካታ መናንያን ይገኛሉ። መናንያን የሚኖሩባቸው ቦታዎችም ገዳማት ይባላሉ። ገዳማት፣ ወንዶች ከሴት ርቀው፣ ሴቶችም ከወንድ ርቀውና ንጽህናቸውን ጠብቀው በድንግልናና በምንኩስና የሚኖሩባቸው ቦታዎች ናቸው። ገዳማት የቅዱሳን አባቶችና እናቶች መፍለቂያ ከመሆን አልፈው እድሜ ጠገብ የሆኑ የሀገር ቅርሶች እንዳይበላሹና እንዳይጠፉ ተጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፊያ ማዕከልም ናቸው። ገዳማት፡-

ለህብረተሰቡ የቀለም፣ የትርጓሜ መጻሕፍት፣ የቅርጻ ቅርጽና ስዕላ ስዕል ስነ ኪነት ትምህርት፣ የቅርሳ ቅርስ ቤተ መዘክርና ቤተ መጻሕፍት ወዘተ. በመሆን በአገሪቱ ሰፊ አገልግሎት ሲሰጡ የኖሩና ያሉ በመሆናቸው የገዳማቱ መኖር ለኢትዮጵያ ህዝብ የሰጠው ጥቅም በዋጋ ሊተመን የሚችል አይደለም (ዝኒ ከማሁ፣ 32-33)።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ በርካታ ገዳማት (የአንድነት ወይም የቁሪት) ይገኛሉ። ገዳማቱ የእምነት ማዕከል ከመሆን አልፈው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ ጠቀሜታ አላቸው። እነዚህ ገዳማት በቱሪዝም ዘርፍም የገቢ ምንጭ በመሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ።

### 2.1.2 ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህል በፎክሎር ስር ከሚጠኑ ዘርፎች መካከል አንዱ መሆኑን ፈቃደ አዘዘ በ"የስነ ቃል መምሪያ" ላይ ጠቅሰዋል። ቁሳዊ ባህል የአንድ ህዝብ የዘመናት የኑሮ ውጣ ውረድ፣ የሥራና የፈጠራ ውጤት መዘክሮች፣ የስልጣኔ እና የታሪክ አሻራ ማሳያ ናቸው። እንዲሁም ስለ ሰው ዘር አመጣጥ፣ ስለተጓዘበት የለውጥና የእድገት ሂደት፣ ስላጋጠሙት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶች ወዘተ. አመላካች ናቸው።

ቁሳዊ ባህል የሰው ልጅ ለመኖር በሚያደርገው ውጣ ውረድ ውስጥ የፈጠራቸው፣ በጊዜ ብዛት ያሻሻላቸው፣ ራሱን ከተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋዎች ለመከላከል (ሐፍረተ አካሉን ለመሸፈን ብሎም ከቁርና ሐሩር ለመከለል፤ እንስሳትን

ለማደንና ከነሱም ጥቃት ለመከላከል፤ የእለት ተእለት እንቅስቃሴውን ቀና ለማድረግ ወዘተ.) የፈጠራ ክህሎቱን ተጠቅሞ ያዘጋጃቸው፣ በእጅ የሚዳሰሱ፣ በአይን የሚታዩ ግዙፍነት ያላቸው ቁሶች ናቸው። እነዚህ ቁሶች የብሔር ብሐረሰቦች የመገልገያ እቃዎች፣ አልባሳት፣ ሃይማኖታዊ ስርዓትን ማከናወኛ ወዘተ. ናቸው።

ፈቃደ አዘዘ በ"የስነ ቃል መምሪያ" መጽሐፋቸው ቁሳዊ ባህል የሚያጠናቸውን ጉዳዮች ሲገልጹ፤

> ቁሳዊ ባህል በዓይን የሚታየውን፣ በእጅ የሚዳሰሰውን፣ ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ፣ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሰራር፣ የቅመም አቀማመም ብልሃትን፣ የልብስ፣ የቤት፣ የአጥር ወዘተ. አሰራርን፣ ሰዎች ልዩ ልዩ ሥራዎችን የሚያከናውኑባቸውን መሣሪያዎችንና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል ማለት ነው (1991፣ 15) ብለዋል።

Prown የተባሉት ሰው ደግሞ "Material culture is the study through artifacts of the beliefs-values, attitudes, and assumptions-of apopular community or society at agiven time" ወይም "ቁሳዊ ባህል በአንድ የተወሰነ ጊዜ የነበረ ማህበረሰብ ወይም ህብረተሰብ እምነት፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብና እውቀትን የሚያመላክቱ የእደ ጥበብ ውጤቶችን የሚያጠና ነው" ብለዋል (Sorce: http:/ www. jostor.org/stable/1180761/ pp.1)።

ስለዚህ ቁሳዊ ባህል የሰው ልጅ በእለት ተእለት ህይወቱ የሚጠቀምባቸውን ቁሶች የሚያጠና ነው። እነዚህ ቁሶች ሰዎች የእለት ጉርሳቸውን ለማሟላት ሲሉ የሚሰሯቸው፤ እንዲሁም ለአካላቸው መሸፈኛ የሚሆኑ ልብሶች፣ የማጌጫ ቁሶች፣ ሃይማኖታዊ ተግባራትን ማከናወኛ ነገሮች፣ በአጠቃላይ የሰው ልጅ በእለት ተእለት ህይወቱ የሚጠቀምባቸው ናቸው። የሰው ልጅ ለራሱ መኖሪያ ቤት እንደሚሰራ ሁሉ ለሃይማኖታዊ ስርዓቱ ማከናወኛ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ይሰራል፤ ለቤቱ ማሳመሪያ ልዩ ልዩ ጌጣጌጥ እንደሚያዘጋጅ ሁሉ ለመንፈሳዊ ህይወቱም እንዲሁ ያደርጋል። በአጠቃላይ ሰዎች ዓለማዊውንም ሆነ መንፈሳዊ ህይወታቸውን ለማሳለጥ የሚያገለግሉ ቁሶች ይሰራሉ፤ በእነሱም እየተገለገሉ ይኖራሉ።

ፊቃደም ሆኑ Prown የቁሳዊ ባህል ጥናት የሰው ልጅ በሚሰራቸው ነገሮች ላይ የሚያተኩር መሆኑን ያሳያሉ። በተለይ Prown "Material culture embraces the class of objects known as artifacts-objects made by man or modified by man. It excludes natural objects. Thus, the study of material culture might include a hammer, a plow, a microscope, a house, a painting, a city. It would exclude trees, rocks, fossils, Skeletons. " ወይም "ቁሳዊ ባህል ሰው ሰራሽ ወይም በሰው የተሰሩ የእደ ጥበብ ውጤቶችን እንጂ ተፈጥሮአዊ ነገሮችን አያካትትም። ስለሆነም የቁሳዊ ባህል ጥናት የሚያካትተው የመዶሻ፣ የማረሻ፣ የማይክሮስኮፕ፣ የቤት፣ የቀለም፣ የከተማ አሰራርን ነው። ስለዛፍ፣ ድንጋይ፣ ቅሪተ አካል፣ አጽም የመሳሰሉትን አያካትትም" ይላሉ (Sorce: http:/ www. jostor.org/stable/1180761/ pp.2)።

"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ" የተባለው መጽሐፍ ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸውን ቁሶች በሚመለከት፤

> ከቅድመ ክርስትና ጀምሮ ሐውልቶችን ቀርጾ የመትከል፣ ታላላቅ ቤተ መንግስቶችን፣ መቃብረ ነገሥታትን በማነጽ፣ ከብረት፣ ከነሐስ፣ ከመዳብ፣ ከአልማዝ ከመሳሰሉትም ክቡራት ማእድናት እያነጠሩ ቤተ መንግስትን የማሳመር፣ የማስጌጥ ጥበብ ዳብሮባት በነበረችው የአክሱም ከተማ በይበልጥ የሥጋዊና መንፈሳዊ ጥበብ ምንጭ የሆነው የክርስትና እምነት ከገባበት እለት ጀምሮ አቡነ ሰላማ ከእስክንድርያ ይዘዋቸው የመጡ ቅዱሳት መጻሕፍትና ንዋየ ቅዱሳትን መሰረት ያደረጉ የእደ ጥበብና የስነ ጥበብ እውቀት በይበልጥ እያደጉና እየዳበሩ ሄዱ (1997፣ 58) ይላል።

አቡነ ሰላማ የጵጵስና ማዕረግ ተሰጥቷቸው ሲመለሱ ሃይማኖታዊ ተግባራትን ለማከናወን የሚረዱ በርካታ ቁሶች ይዘው መጥተዋል። እነዚህ ቁሶች የከበሩ አልባሳት፣ ንዋየ ቅድሳት፣ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ተግሳጻትና የቤተ ክርስቲያን ጌጣጌጥ፣ መስቀልና ጽንሐሕ ሲሆኑ፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በእነዚህና ሌሎች ቁሶች ስትገለገል ኖራለች።

ከዚህ ሀሳብ በመነሳት አቡነ ሰላማ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጳጳስ ብቻ ሳይሆኑ ለቤተ ክርስቲያኗም ቁሳዊ ባህልን በማስተዋወቅ ቀዳሚ ነበሩ ማለት ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በቅርስነት የምትጠቅሳቸው ቁሶች፣

ከአለት ተፈልፍለው የታነጹ አብያተ ክርስቲያናት፣ ከጥርብ ድንጋይ የታነጹ አብያተ ክርስቲያናት፣ ቅዱሳት የብራና መጻሕፍት፣ የጳጳሳትና የካህናት የእጅ መስቀሎች፣ ከእብነበረድና ከእጽ የተቀረጹ ልዩ ልዩ ንዋየ ቅድሳት፣ የቁርባን ጻሕልና ጽዋ፣ የሕጽበት ሰንና ብርት፣ የዝማሬ ከበሮ፣ ጽናጽልና መቋሚያ፣ አዋጅ መንገሪያና መጥሪያ ደወልና ቃለ አዋዲ (ቃጭል)፣ ልብሰ ተክህኖና ጽንሐሕ፣ መሶበ ወርቅና ማህተም፣ የወግና የባህል እቃዎች ናቸው (ዝኒ ከማሁ፣ 58-59)፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ስርዓት ማከናወኛ ቁሶች ናቸው፡፡ እነዚህ ቁሶች ደግሞ ንዋያተ ቅድሳት ይባላሉ፡፡ ንዋያተ ቅድሳት ማለት ቅዱስ፣ ንጹህና ሰማያዊ የሆነው የእግዚአብሔር ስም የሚመሰገንባቸው፣ ስርዓተ አምልኮት የሚፈጸምባቸው የተለዩና የከበሩ የቤተ ክርስቲያን ንብረቶች ወይም ሀብቶች ናቸው፡፡ የንዋያተ ቅድሳቱ አይነትና ቅርጽ እግዚአብሔር ለሙሴ ባሳየውና መጠናቸውንም ለክቶ በሰጠው መሰረት (ዘጸ፡ 24 -28) የሚሰሩ ናቸው፡፡

ንዋያተ ቅዱሳቱ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከመዋላቸው በፊት ሜሮን (ቅብዓ ቅዱስ) ይቀባሉ፤ ስርዓተ ጸሎትም ይደረግላቸዋል፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት የሚተላለፍባቸው ቁሶች ስለሆኑም በቤተ ክርስቲያኑ የተለየ የማስቀመጫ ቦታ ይዘጋጅላቸዋል፡፡ ንዋያተ ቅዱሳቱ የሚሰሩት ምሳሌነታቸውንና የሚሰጡትን አገልግሎት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ የተለያዩ መልኮችን በማውጣትና በማስዋብ ነው፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር ለመጀመሪያና ለሁለተኛ ዲግሪ ማማሟያ የቀረቡ አስር ያህል ተዛማጅ የጥናት ስራዎች ቅኝት ተደርጎባቸዋል፡፡ አቀራረባቸው በሁለት የተከፈለ ሲሆን፤ የተከፈሉትም የተሰሩበትን ደረጃ (ለመጀመሪያ ዲግሪና ለሁለተኛ ዲግሪ) መሰረት በማድረግ ነው፡፡

### 2.2.1 ለመጀመሪያ ዲግሪ የቀረቡ ጥናቶች

በዚህ ጥናት የታዩት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች አምስት ሲሆኑ፤ በቅደም ተከተል አንዱ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል፣ አራቱ ደግሞ ለቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የቀረቡ ናቸው።

ስለሺ መንግስቱ (1998) ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል "A History of Dima Giyorgis Monastery from Foundation to 1974" በሚል ርእስ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርቧል። የጥናቱ ትኩረት የዲማ ጊዮርጊስ ገዳምን ታሪክ ከምስረታው ጀምሮ እስከ 1974 ድረስ ማቅረብ ነው። በጥናቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳም፣ ደብር እና ገጠር የተሰኙ ስሪቶች እንዳሏት እና ብዛታቸውንም ጠቅሷል። ዲማ ጊዮርጊስ በምስራቅ ጎጃም ከሚገኙ ጥንታዊ ገዳማት መካከል አንዱ ሲሆን፤ በአባ ተከስተ ብርሃን በአካባቢው የክርስትና ሃይማኖት ከመስበኩ በፊት እመውላድ (Emäwlad) የምትባል ጣኦት ማህበረሰቡ ያመልክ እንደነበርና አባ ተከስተ ብርሃን ካረፉ በኋላም በእሳቸው እግር አባ ቶማስ የተባሉ አባት እንደተተኩ ያብራራል። እንዲሁም አባ ቶማስ ወደ ዲማ ከመጡ በኋላ የጊዮርጊስን ጽላት ከአጼ ይስሐቅ ዘንድ አምጥተው በመትከል ዲማን በገዳምነት እንዳቀኗት ጥናቱ ያሳያል።

ዳንኤል ሀይሉ (1999) "Founders of Ethiopian Monasticism" በሚል ርዕስ ለቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ጥናት አቅርቧል። የጥናቱ አላማ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማዊ ህይወት ምስረታ ማሳየት ቢሆንም በገንዘብ እጥረት ምክንያት የሁሉንም ገዳማት የምስረታ ሁኔታ ማካተት እንዳልቻለ ጠቁሟል። ዳንኤል በኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖት በፍሬምናጦስ አማካይነት ስለመስፋፋቱ በርካታ አጥኚዎች የሚስማሙ ቢሆንም በምንኩስና ህይወት ጀማሪዎች ላይ ግን የተለያየ ሀሳብ መኖሩን ጠቅሷል። አንዳንድ ሰዎች ምንኩስናን በኢትዮጵያ የጀመሩት ጻድቃን (ከዘጠኙ ቅዱሳን መምጣት በፊት በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል ለክርስትና ሃይማኖት መስፋፋት አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ የሚነገርላቸው) የሚባሉት ናቸው ሲሉ ገሚሶቹ ደግሞ አባ ዮሐኒና አባ ሊባኖስ ናቸው እንደሚሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ ዘጠኙ ቅዱሳን ከመምጣታቸው በፊት በሱዳን ጠረፍ አካባቢ በሙስሊሞች የጠፋ ገዳም መኖሩን ጠቅሰው ዘጠኙ ቅዱሳን ለኢትዮጵያ ምንኩስናን አስተዋዋቂ አለመሆናቸውን ያነሳሉ ይላል። ይሁን እንጂ ይህን ሀሳብ እነማን እንዳሉ የጠቀሰው ነገር የለም። ዳንኤል፤

እነዚህ ሰዎች ለሃሳባቸው ማስረገጫ ያቀረቡት መረጃ አለመኖሩን ጠቁሞ በኢትዮጵያ የምንኩስና ህይወትን ያስተዋወቁት ዘጠኙ ቅዱሳን ናቸው ይላል። ለማስረጃም በተለያየ ቦታ የመሰረቷቸውን ገዳማትና ያበረከቱትን አስተዋጽኦ (መጻህፍት ስለመተርጎማቸው፣ ቤተ ክርስቲያንና ገዳም ስለመመስረታቸው ወዘተ.) ዘርዝሯል።

መዝገቡ ካሳ (2001) "The Mystical Experience of the Monastic Life in the Traditional Context of the Ethiopian Orthodox Tewahido Church" በሚል ርዕስ ለቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ጥናት አቅርቧል። ጥናቱ የተካሄደው በተመረጡ አምስት ገዳማት ላይ ነው። በጥናቱ የተካተቱት ገዳማትም ምስካዬ ህዙናን መድሃኔ ዓለም[6]፣ ሰበታ ቤተ ደናግል፣ ደብረ ሊባኖስ፣ ሐይቅ እስጢፋኖስና ማህበረ ሥላሴ ናቸው።

መዝገቡ፣ በአምስት ምእራፍ ባደራጀው ጥናት ከላይ የተጠቀሱትን አምስት ገዳማት የተመለከተ ሲሆን፤ አበይ ትኩረቱ የገዳማውያኑንና የገዳሙን ታሪክ በአጭሩ መቃኘት፣ በቅዱሳን አባቶች እንደተጻፉ የሚታመንባቸውን የምንኩስና ህጎችና ደንቦች ገዳማውያኑ ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረጓቸውና በነዚህ ህጎችም ህይወታቸውን አስገዝተው መኖራቸውን መመርመር ነው።

ሌላው "A Brief History of Debra Hayq Saint Stephen Abuna Iyesus Moa Communal Monastery in South Wollo" በሚል ርዕስ ለቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ጥናታዊ ጽሁፍ ያቀረበው ኃይለሚካኤል ወልደ ተክለ ኃይማኖት (2005) ነው። የጥናቱ ዓላማም ስለ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ አንድነት ገዳም ታሪክ መዘገብ እና ገዳሙ የሚያካሂደውን ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ መመርመር ነው። ኃይለሚካኤል፤ በኢትዮጵያ ገዳማዊ ህይወት ከዘጠኙ ቅዱሳን ጋር ተያይዞ በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ እንደተጀመረና ቅዱሳኑ በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች ገዳማት የመሰረቱ መሆናቸውን ጠቅሷል። በእነዚህ ገዳማት በርካታ

---

[6] አባ ተክለማርያም፣ አጼ ኃይለ ስላሴ በስደት እንግሊዝ አገር በነበሩበት ጊዜ ከኢየሩሳሌም አስመጥተው ይጠቀሙበት የነበረው የዴር ሱልጣን መድኃኔ ዓለም ታቦት አገር ሰላም ከሆነ በኋላ ነሐሴ 23 ቀን 1933 ዓ.ም ወደኢትዮጵያ መጥቶ አባ ኃይሌ ብሩክ በተባሉ መነኩሴ አማካይነት ሚያዝያ 27 ቀን 1935 ዓ.ም ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ብለው እንደሰየሙት ገልጸዋል (1963፣ 24-36)።

መናንያን ስለምንኩስና ህይወት የተማሩ ሲሆን፤ ከነዚህ መካከል አቡነ ኢየሱስ ሞአ ከደብረ ዳሞ ገዳም ምንኩስና ተቀብለው የራሳቸውን ገዳም እንደመሰረቱ ጠቁሟል።

ኃይለሚካኤል በአምስት ምእራፍ ባደራጀው ጥናት፤ ስለ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳምና ደብረ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አመሰራረት፣ ስለ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጣቸውና ታሪካዊ ዳራቸው፣ ስለ አቡነ ኢየሱስ ሞአ ወደ ሐይቁ መምጣት፣ ስለ ገዳሙ ትምህርታዊ እንቅስቃሴና አሁን ስለሚገኝበት ነባራዊ ሁኔታ፣ ስለዘጠኙ ቅዱሳን አመጣጥ፣ ስለመሰረቷቸው ገዳማትና ስለህልፈታቸው ዘግቧል።

"Investigation of Ancient Christianity in South Wollo" በሚል ርዕስ ለቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረበው ዘውዴ ገብረ እግዚአብሔር (2007) ነው። በጥናቱ፣ ደቡብ ወሎ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለክርስትና እምነት መስፋፋት ማዕከል የነበረች መሆኗንና የተለያዩ ነገስታትም በተለያዩ ጊዜያት የክርስትና ሃይማኖትን ለማስፋፋት የተጠቀሙባት መሆኗን ጠቅሷል። የጥናቱ ትኩረት በደቡብ ወሎ አካባቢ የሚገኙ ታላላቅ ገዳማት እና አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ መዘገብና ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴያቸውን መመርመር ነው።

ጥናቱን ከግብ ለማድረስ በደቡብ ወሎ ከሚገኙ 18 ወረዳዎች ሰባቱን (ተሁለደሬ፣ ሳይንት፣ ተንታ፣ ወረኢሉ፣ ደብረሲና፣ ከላላና ወግዲን) መርጦ ታሪካዊ (ከተመሰረቱበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያሉና ሰፊ ታዋቂነት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ወይም ገዳማት) እና አርኬዎሎጂካዊ (በተለያዩ ምክንያቶች ጠፍተው የነበሩና በቁፈራ የተገኙ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ገዳማት) በማለት በሁለት ከፍሏቸዋል። ተሁለደሬ፣ ሳይንት፣ ተንታና ደብረሲና ወረዳን በታሪካዊ፤ ወግዲ፣ ወረኢሉና ከላላን ደግሞ አርኬዎሎጂካዊ በማለት መድቧቸዋል። ታሪካዊ ብሎ የዘረዘራቸው ርእሰ አድባራት ተድባበ ማርያም፣ አትሮንስ ማርያም፣ ተንታ ሚካኤል፣ ጀፋ መድሃኔዓለም፣ ምስካበ ቅዱሳን እና የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ናቸው። በተጨማሪም በሰባቱ ወረዳዎች ስለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት አመሰራረትና የመስራቾቹን ታሪክ በአጭሩ ቃኝቷል።

### 2.2.2 ለሁለተኛ ዲግሪ የቀረቡ ጥናቶች

በዚህ ስር የሚታዩት አምስት ጥናቶች ሲሆኑ፤ አራቱ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረቡ ናቸው። አንዱ ደግሞ ለታሪክ ትምህርት ክፍል የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ ነው።

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ከቀረቡት ጥናቶች መካከል የታደሰ አይችሉህም ጥናት (1999 ዓ.ም) አንዱ ነው። ጥናቱ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የምንኩስና ስርዓትና የእለት ተእለት ህይወት ከትእምርታዊነቱ አንጻር፤ በዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳማት" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው።

ታደሰ፣ በመረጣቸው ሁለት ገዳማት በተለያዩ አውዶች የሚታየውን የጸሎት ስርዓትና ክንውን፣ የገዳማውያኑን አለባበስ፣ የአመጋገብ ስርዓት፣ የስራ ድርሻቸውንና የአስተዳደር መዋቅር፣ እንዲሁም በገዳማቱ ውስጥ በጉልበታቸው እያገለገሉ የሚኖሩትን፣ ደጅ ጠኚዎችን (ምንኩስና እስከሚፈቀድላቸው ድረስ በአመክሮ የሚቆዩትን)፣ ከተለያየ አካባቢ መጥተው ቀሪ ህይወታቸውን በገዳማቱ አሳልፈው እዚያው ለመቀበር በሚሄዱ አረጋውያን ወዘተ. ዙሪያ ጥናቱን በንጽጽር አካሂዷል።

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን ዘመን በሚመለከት ሁለት ሃሳቦች እንደሚነሱ ጠቅሶ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስሪት በሶስት እንደሚከፈልም ገልጿል። ምንኩስና በራስ ፈቃድ የሚገባበት የህይወት መስመር በመሆኑ ህገ ፈቃድ መባሉን፣ በጥናቱ የተመለከታቸው ገዳማት አስተዳዳሪዎች ስያሜ መለያየቱን፣ የገዳማቱ የአስተዳደር መዋቅር አበምኔት፣ መጋቢ፣ ሊቀ ረድእ፣ ገበዝ፣ ጸሐፊና እቃ ቤት በተሰኙ አካላት መደራጀታቸውን፣ ገዳማዊው በምንኩስና ጸንቶ ከኖረ በኋላ በእረፍቱ ጊዜ የሚደረግለት ግንዘትና ጸሎተ ፍትሃት ከዓለማዊው ህዝብ የሚለይ መሆኑን በማጠቃለያው ገልጿል።

ለዚሁ ትምህርት ክፍል በ 2000 ዓ.ም ወርቁ ከተማ "የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ የጨፋ መድሃኔዓለም ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማርያምና ቅድስት ሰሎሜ[7] የሴቶች

---

[7] ሰሎሜ፣ ማርያም ኢየሱስን ከሄሮድስ ግድያ ለማዳን ይዛው ወደግብጽ በተሰደደችበት ጊዜ አብራት የነበረች መሆኗን በሪሁን ከበደ (1983፣ 32) የዋልድባ ገዳም ታሪክ በተሰኘው መጽሐፋቸው ገልጸዋል።

አንድነት ገዳም አመሰራረት ፎክሎራዊ ገጽታ" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርቧል፡፡ ጥናቱ የገዳሙን የአመሰራረት ሁኔታና በገዳሙ ውስጥ በፈለቀው ጸበል፣ ጸበል የማጥመቅ ስነ ስርዓትና በገዳሙ የሚኖሩ መነኩሳት የሚፈጽሙትን ፎክሎራዊ ገጽታ (የልማት እንቅስቃሴ፣ አመጋገብ፣ የጸሎት ጊዜ ወዘተ.) ማሳየት አቢይ አላማው ነው፡፡ ገዳሙ በተመሰረተበት አካባቢ ከአህመድ ግራኝ ወረራ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ስነ ቃሎች መኖራቸው፣ ምናልባት ከወረራው በፊት በአካባቢው ቤተ ክርስቲያን ወይም ገዳም ተመስርቶ እንደነበር የሚያረጋግጡ የድንጋይ መስቀሎች መገኘታቸው፣ በገዳሙ ውስጥ በፈለቀው ጸበልም የክርስትና እና የእስልምና እምነት ተከታዮች እኩል ሲጠቀሙ መታየታቸው፣ መነኮሳቱም በገዳሙ ውስጥ የሚፈጽሟቸው ልዩ ልዩ ፎክሎራዊ ተግባራት መኖራቸውና ሌሎች ድርጊቶችም ሲፈጸሙ መስተዋላቸው ትኩረቱን ስለሳበው ይህን ርዕስ ለጥናቱ መምረጡን ገልጿል፡፡

ወርቁ ከተማ፤ ገዳሙ የአካባቢውን ህብረተሰብ ለልማት በማነሳሳት ለሚያካሂደው እንቅስቃሴ፣ ወላጅ አልባ ህጻናትን ለማሳደግ ለሚያደርገው ጥረት እና የተለያዩ ማህበራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ ለሚያደርገው ጥረት በመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ሊታገዝ እንደሚገባ ጠቁሟል፡፡ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች በጸበሉ ስፍራ የሚያከናውኑት በጸበል የመጠመቅ ድርጊት ምናልባትም ሁለቱን ወገኖች በወንድማማችነትና እህትማማችነት ፍቅር ካስተሳሰሯቸው በርካታ ምክንያቶች መካከል አንዱ ሊሆን እንደሚችል በጥናቱ ተጠቅሷል፡፡

ፍሬህይወት ባዩ (2000 ዓ.ም) "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርባለች፡፡ የጥናቷ አቢይ አላማ የንዋያተ ቅድሳቱን ሃይማኖታዊ (ስለንዋያተ ቅድሳቱ ምንነት) እና ፎክሎራዊ (ንዋያተ ቅድሳቱን ከሃይማኖታዊ አገልግሎታቸው፣ ምሳሌያቸውና ቀኖና) ገጽታ መመርመር ነው፡፡ ንዋያተ ቅድሳት የሚባሉትም የቤተ ክርስቲያኑ ህንጻ፣ የጳጳሳት ልብሶች፣ የቤተ ክርስቲያኑ የውስጥ ክፍሎች፣ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች ሁሉ መሆናቸውን ዘርዝራለች፡፡ ለስራዋም በሁለት ሀገረ ስብከቶች የሚገኙ አራት ቤተ ክርስቲያኖችን (ከአርሲ ዞን ሐገረ ስብከት፣ ከሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ በቆጂ ደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስና ሌሙ ማርያምን፣ ከአዲስ አበባ ሐገረ ስብከት ደግሞ ርዕሰ አድባራት እንጦጦ ማርያምንና ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስን) መርጣለች፡፡ ፍሬህይወት፣ ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደርበት ህግ አንድ ሆኖ ሳለ በተለያዩ ቦታዎች

የሚያገለግሉ ካህናት ስለአንድ ነገር የተለያየ ምላሽ እንደሚሰጡ፣ የተጻፈው ህግና የሚተገበረው እንደሚለያይና ቀድሞ የማይታወቁ፣ በአማኙ ዘንድ ግን እየተዘወተሩ የመጡ ንዋያተ ቅድሳት (ለምሳሌ የልብስ ተክህኖ ቀለምና አሰፋፍ፣ የህንጻ ቤተ ክርስቲያኑ የውስጥና የውጪ ቅርጽ ወይም አሰራር፣ የጉልላት መለያየት ወዘተ.) መኖራቸውን በጥናቷ ጠቁማለች፡፡

ሰለሞን ደርቤ (2000 ዓ.ም) "የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል አከባበር" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ጥናት አቅርቧል፡፡ ጥናቱ በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል አከባበር ላይ የተመሰረተ ሲሆን አብይ ትኩረቱ በክብረ በዓሉ ወቅት የሚታዩ ሃይማኖታዊ ክንውኖችን መፈተሽ ነው፡፡ ሰለሞን፤ በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል ላይ፣ በበዓሉ ተሳታፊዎች ከሃይማኖታዊ ተግባራት ውጪ ሌሎች ሀገር በቀል የአምልኮ ስርዓቶች እንደሚከናወኑ ጠቁሟል፡፡ በዝቋላ አቦ ክብረ በዓል የአከባበር ገጽታዎች ላይ ለሃይማኖታዊ ስርዓቶች እንደሚታየው ሁሉ በክብረ በዓሉ ተሳታፊዎችና በአካባቢው ነዋሪዎች ሀገር በቀል የአምልኮ ስርዓቶች መፈጸማቸው ክብረ በዓሉ ለሃይማኖት መቻቻል ምሳሌ ሲሆን እንደሚችል ገልጿል፡፡

ሰለሞን፣ ትኩረት ያደረገው በዝቋላ አቦ በሚታየው የበዓል አከባበር ሁኔታ ላይ ሲሆን፤ በተወሰነ ደረጃ ስለ ዝቋላ ደብረ ከዋክብት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም አመሰራረትና የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የህይወት ታሪክ፣ እንዲሁም የገዳሙን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ የመሰረተ ልማት አውታሮች፣ የእስካሁን ጉዞና የወደፊት ርዕይ ለማሳየት ሞክሯል፡፡

በመጨረሻ የምናየው የማስተርስ ጥናት ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል "The Ethiopian Claim on The Monastery of Der Es-Sultan in Jerusalem, 1850s - 1994" በሚል ርዕስ በጥጋብ በዜ (2001) የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ትኩረት የዴር ሱልጣን ገዳም ከ1850ዎቹ ጀምሮ እስከ 1994 ድረስ ባሉት ወቅቶች ያጋጠመውን ውጣ ውረድና መሰናክሎች ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ገዳም ኢትዮጵያ በኢየሩሳሌም ካሏት ሰባት ገዳማት መካከል አንዱና ረጅም እድሜ ያለው መሆኑን ጠቁሞ ዴርሱልጣን ማለት የንጉስ ገዳም ወይም ደግሞ ደብረ ስልጣን ማለት ነው ይላል፡፡ ገዳሙ የሚገኘው ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ቀራኒዮ አካባቢ መሆኑንም ጠቁሟል፡፡

ለማጠቃለል፣ በዚህ ክፍል የተዳሰሱት ጥናታዊ ጽሑፎች በገዳምና ገዳማውያን ዙሪያ ስለሚያተኩሩ ከእኔ ጥናት ጋር የሚቀራረቡ ቢሆንም ባነሱት ርዕሰ ጉዳይና የአላማ ስፋትና ጥበት ልዩነት አላቸው፡፡ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡት ጥናቶች አቢይ ትኩረታቸው ስለገዳሙ መስራችና ስለገዳሙ የምስረታ ታሪክ፣ ገዳሙ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ጥናታቸውን እስካቀረቡበት ወይም እስከቀነበቡበት ዓመት ድረስ ያሳለፈው ውጣ ውረድ፣ በኢትዮጵያ የምንኩስና ህይወት ስለተጀመረበት ዘመን እና ስለጀማሪዎቹ፣ የምንኩስና ህይወትን በኢትዮጵያ አስተዋወቁ የሚባሉት ሰዎች (ዘጠኙ ቅዱሳን) ሃይማኖቱን ለማስፋፋትና የምንኩስና ህይወት እንዲለመድ ስላደረጓቸው ጥረቶች፣ እነዚህ ቅዱሳን ስለመጡበት ሀገር፣ በኢትዮጵያ ስለመሰረቷቸው ገዳማት፣ ስለክብረ በዓላታቸው ወዘተ. የሚተነትኑ ናቸው፡፡ ከአምስቱ የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር ቀረቤታ ያለው የኃይለሚካኤል ጥናት ሲሆን፤ ቀረቤታቸውም ሁለቱም በአንድ ገዳም (በአቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም) ላይ ያተኩሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ይሁንና የኃይለሚካኤል ጥናት ስለገዳሙ የአመሰራረት ታሪክ፣ ስለአስተዳደራዊ መዋቅሩ፣ ስለአቡነ ኢየሱስ ሞአ ወደሐይቁ መምጣት ወዘተ. ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የእኔ ጥናት ደግሞ የገዳሙን የምስረታ ሁኔታ በመጠኑ የሚመለከት በመሆኑ ከኃይለሚካኤል ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ነገር ቢኖርም የእኔ ጥናት የገዳማውያኑን የእለት ተእለት እንቅስቃሴና የአመጋገብ ሁኔታ እንዲሁም በገዳሙ የሚገኙ ቁሳቁሶችን ተአምራዊነት አስመልክቶ ስለሚነገሩ አፈ ታሪኮች፣ ስለገዳማውያኑ አለባበስና በሰውነታቸው ላይ ስለሚያደርጓቸው ቁሶች የሚመረምር በመሆኑ ከኃይለሚካኤልም ሆነ ከሌሎቹ ጥናቶች ጋር የተለየ ያደርገዋል፡፡

በሁለተኛ ዲግሪ የተሰሩት ጥናቶች አብዛኛዎቹ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረቡ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል የታደሰ አይችሉህም ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የቅርብ ዝምድና አለው፡፡ ሁለቱም ጥናቶች በተለያየ ርዕስ በገዳማውያኑ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ላይ የሚያተኩሩ በመሆናቸው የሚመሳሰሉ ቢሆንም የእኔ ጥናት የገዳማውያኑን አልባሳትና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ቁሶች እንዲሁም በገዳሙ የሚገኙ ቁሳቁሶችን ተአምራዊነት አስመልክቶ የሚነገሩ አፈ ታሪኮችን ማካተቱ ከታደሰ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡ የወርቁ ከተማ ጥናት ደግሞ ትኩረቱ በገዳሙ በፈለቀው ጸበልና ጸበል በማጥመቅ ሂደት ላይ ሲሆን፤ ስለገዳሙ ምስረታ የሚነገሩ አፈ ታሪኮችን በመቃኘቱ ከዚህ ጥናት ጋር መጠነኛ ዝምድና አለው፡፡ ይሁን እንጂ

የገዳማውያኑን አጠቃላይ እንቅስቃሴና የእለት ተእለት ህይወት እንዲሁም የአፈ ታሪኮቹን ይዘት አይመለከትም። ወርቁ ስለገዳማውያኑ የአመጋገብ ስርዓትና የጸሎት ጊዜ ያነሳው ነገር ቢኖርም ለጸበልም ሆነ በሃያ አራት ሰዓት አንድ ጊዜ ለሚሰጡት መቁነን የሚሰባሰቡት በደወል መሆኑን ከመግለጽ ያለፈ ዝርዝር አላቀረበም። በዚህ ጥናት ግን እኒህ ጉዳዮች በስፋት ይታያሉ።

የፍሬህይወት ባዩ ጥናት በሁለት ሀገረ ስብከቶች በሚገኙ አራት ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ በሚገኙ ንዋየ ቅድሳት ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰልበት ነጥብ አለ። ፍሬህይወት የዚህ ጥናት አንዱ ክፍል የሆነውን አልባሳት በመመልከቷ ብንመሳሰልም በገዳም ያሉ መነኮሳት ካህን እንዲሆኑ (በገዳም የቅዳሴ ስርዓት ማከናወን የሚችሉ) ማሟላት ያለባቸውን ሁኔታ እንዲሁም የገዳማውያኑን አልባሳት ባለማካተቷ እንለያያለን። በዚህ ጥናት ውስጥ የመነኮሳቱ አልባሳት፣ በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸው ቁሶች እንዲሁም የእለት ተእለት ህይወት ስለሚዳስስ ሁለቱን ጥናቶች ልዩ ያደርጋቸዋል። ሰለሞን ደርቤ ደግሞ ለጥናት የመረጠውን ገዳም መስራችና የምስረታ ታሪክ በመዳሰሱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰልበት ነጥብ ቢኖርም አቢይ ትኩረቱ በክብረ በዓል (Festival) ላይ እንጂ በገዳማውያኑ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ላይ አይደለም። የእኔ ጥናት ደግሞ በገዳማውያኑ የእለት ተእለት ህይወትና እንቅስቃሴ ላይ ይበልጥ ማተኮሩ ልዩነታቸውን ያሰፋዋል። በመጨረሻ የታየው የጥጋብ በዜ ጥናት ነው። ይህ ጥናት የዴር ሱልጣን ገዳም ከ1850 እስከ 1994 ድረስ ያለውን ታሪካዊ ሂደት የሚፈትሽ ነው። ይህ ጥናት በገዳም ታሪክ ላይ በመመስረቱ ከእኔ ጥናት ጋር የሩቅ ተመሳስሎ አለው። የጥጋብ ትኩረት በቀነበበው ዓመት ውስጥ ገዳሙ ያሳለፈውን ውጣ ውረድ ማሳየት ነው። የእኔ ጥናት ደግሞ የገዳሙን ምስረታ በአጭሩ መቃኘት፣ የገዳማውያኑን የእለት ተእለት ህይወት መዳሰስና መመርመር በመሆኑ ልዩነታቸው ጉልህ ነው።

በአጠቃላይ ከዚህ ጥናት በፊት በተለያዩ አጥኝዎች ተሰርተው በዚህ ክፍል ዳሰሳ የተካሄደባቸው ጥናቶች ስለገዳም ምስረታና ስለገዳማውያን፣ እንዲሁም በገዳሙ መስራቾች ዙሪያ ስለሚያጠነጥኑ ከእኔ ጥናት ጋር ቢመሳሰሉም፣ የእኔ ጥናት ስለገዳማውያኑ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ እና የገዳማውያኑን አልባሳት እንዲሁም በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ቁሳ ቁሶች የሚመረምር መሆኑ ጥናቱን ከሌሎቹ የተለየ ያደርገዋል።

# ምዕራፍ ሶስት

# የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሰራረት፣ የሥራ ክፍፍልና አይነት

ይህ ምእራፍ በሁለት ንዑሳን ርዕሶች የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ንዑስ ርዕስ የገዳሙ የአመሰራረት ሁኔታ በአጭሩ የሚቀርብበት ክፍል ነው። በዚህ ስር ስለ ወንዶችና ሴቶች ገዳም አመሰራረትና ስለ ገዳማቱ የመልሶ ግንባታ ሂደት ይቀርባል። በሁለተኛው ንዑስ ርዕስ ደግሞ የገዳሙ የስራ ክፍፍልና አይነት ይቀርባል።

## 3.1 የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሰራረት

የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ከደሴ ወደ ወልዲያ በሚወስደው ዋና መንገድ ላይ ከምትገኘው የሐይቅ ከተማ በስተቀኝ በኩል 3.75 ኪ.ሎ ሜትር ገደማ ላይ ይገኛል። በክልል ሶስት ቱሪዝም ቢ.ሮ (1986) መጣጥፍ መሰረት ገዳሙ ከአዲስ አበባ 433.75 ኪ.ሎ ሜትር እና ከደሴ 33.75 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል።

የሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ባለበት ደሴት እና በአካባቢው የክርስትና ሃይማኖት የተሠበከው፣ በዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ በንጉሠ ነገሥት አጼ ድል ናኦድ (ነአድ) ዘመነ መንግሥት፣ በአቡነ ሰላማ ዘአዜብ ሁለተኛ አማካይነት ነው (አባ ፍቅረ ዮሐንስ፣ ካሴት ቁ.1፣ Side A)። አቡኑ ከአክሱም ተነስተው በአፋር በኩል አድርገው ህዝቡን እያስተማሩና እየባረኩ የሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አሁን ከሚገኝበት ደሴት በምስራቅ አቅጣጫ ወደ ሚገኘው "ድማሞ" ተራራ (ደብረ እግዚአብሔር) አካባቢ ደረሱ። በተራራው ላይም ሆነው ወደ ሐይቁ በመመልከት በደሴቱ ውስጥ ስለሚኖሩ ሰዎች ሁኔታ መጠየቅ ጀመሩ። ገድለ አቡነ ኢየሱስ ሞአ ይህን በሚመለከት ሲያብራራ የሚከተለውን ይላል።

አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ጳጳስ ሆኖ ከመጣ በኋላ ሁለተኛ ሰላማ ዘአዜብ የሚባል ጳጳስ በአዳል ምድር በኩል መጣ። ቦታዎቹን እየጎበኘ ሐይቅ

ደረሰ፡፡ ደሴቲቱንም አይቶ ወደዳት፡፡ ሁኔታዋንም ሲመረምር ህዝቡ ለአውሬው እንደሚሰግዱ ሰዎች ነገሩት፡፡ ከዚህ በኋላ መስቀሉን አንስቶ ሰማይና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር ፈቃድ በደሴቲቱ ላይ በባረከ ጊዜ አውሬው ጠፋ፡፡ የደረሰበትም አልታወቀም (2001፣ 33)፡፡

በደሴቲቱ ይኖሩ የነበሩት ሰዎች እንደ ፈጣሪ ለሚያመልኩትና ለሚሰግዱለት አውሬ (ዘንዶ) ወተት፣ ደም እና የላም ሥጋ ባሉጥ በሚባል ትልቅ ዛፍ ሥር በሚገኝ የድንጋይ ገንዳ (ገበላት) ይሰጡት ነበር፡፡ አቡነ ሰላማ ዘአዜብ ይህን ነገር እንደሰሙ በመስቀላቸው ደሴቷን ሲያማትቡባት አውሬው (ዘንዶው) መጥፋቱ ይነገራል፡፡ ጳጳሱም ይህን ካደረጉ በኋላ ወደ አክሱም ተመልሰዋል (ዝኒ ከማሁ፣ 33)፡፡

አክሱም ደርሰውም ለአጼ ድል ናኦድ ሐይቅ የምትባል ደሴት እንዳገኙና ደሴቷንም እንደወደዷት፤ በአካባቢው የፈጸሙትንም ነገር አስረዷቸው፡፡ ንጉሡም ከጳጳሱ ጋር ወደ አካባቢው መጥተው በቅድሚያ በድማሞ ተራራ ላይ ለእሳቸው ቤተ መንግስት እና የእግዚአብሔር አብን ቤተ ክርስቲያን አሠሩ፡፡ በመቀጠልም ወደ ደሴቱ ገብተው አሁን የገዳሙ ቤተ ክርስቲያን ካለበት ቦታ ላይ በ862 ዓ.ም ቤተ ክርስቲያን አሠሩ፡፡ በውስጡም የማንን ታቦት እናስገባ በማለት ንጉሡ ከባለሟሎቻቸውና ከሠራዊታቸው ጋር፣ ጳጳሱም ከሊቃውንቱና ከካህናቱ ጋር ሆነው መንፈሳዊ ውይይት ማካሄድ ጀመሩ (ዝኒ ከማሁ፣ 33-34)፡፡

በዚህ ጊዜም "ቆራ" የምትባል እንስሳ ሁለት ታቦት እንደተሸከመች ከባህሩ ዳር ቆማ ስትጮህ ሰሚት፡፡ ህዝቡም ቆራይቱ ከባህሩ ዳር ቆማ ባዩዋት ጊዜ ወደ እሷ ቀርበው የተሸከመችውን ታቦት ከላይዋ ላይ አወረዱ፡፡ ታቦቱን በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ታዘው የላኩት መሆኑን የሚገልጽ ጽሑፍ እንደተገኘ አባ ፍቅረ ዮሐንስ (ካሴት ቁ.1፣ Side A) ገልጸዋል፡፡ ታቦቶቹ የቅዱስ እስጢፋኖስ እና የቅዱስ ጊዮርጊስ ሲሆኑ ጳጳሱም ታቦተ ጊዮርጊስን ከሐይቁ በስተሰሜን ሲተክሉ የእስጢፋኖስን ታቦት ደግሞ አሁን ካለበት ደሴት ላይ በተሠራው ቤተ ክርስቲያን አስገቡ፡፡ ንጉሡም ለቤተ ክርስቲያኑ መገልገያ የሚያስፈልገውን ንዋየ ቅዱሳት አሟልተው፣ ሦስት መቶ ያህል ሊቃውንትና ካህናት እንዲያገለግሉ ማድረጋቸው እና ቦታውን ደብረ ነጎድጓድ ብለው እንደሰየሙት ይነገራል (አባ ፍቅረ ዮሐንስ፣ ካሴት ቁ.1፣ Side A)፡፡

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሴቶችና ወንዶች ሳይለያዩ ቦታው በደብርነት ብቻ ለአራት መቶ አመታት ያህል ሲያገለግል ቆይቷል። በኋላም በአቡነ ኢየሱስ ሞአ አማካይነት ቦታው የአንድነት ገዳም ለመሆን ቻለ።

ከላይ እንደተጠቀሰው በሐይቅ ደሴት ላይ ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተው በአጼ ድል ናኦድ ዘመነ መንግስት በ862 ዓ.ም ነው። መሥራቾቹ በዘመኑ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ሰላማ ዘአዜብ ሁለተኛ እና ንጉሠ ነገሥቱ ናቸው። በተጨማሪም በደብርነት ሲያገለግል የነበረውን ቤተ ክርስቲያን ወደ ገዳምነት እንዲቀየር ያደረጉት በአሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን የመጡት አቡነ ኢየሱስ ሞአ ናቸው (ዳንኤል፣ 1999፣ 9-11)። አቡነ ኢየሱስ ሞአ ይህንን ቦታ ለገዳምነት የመረጡበትን ምክንያት የገዳሙ አበምኔት ሲገልጹ፣

> ቅዱስ ኡራኤል የመድኃኔ አለምን ደም ለዓለም ሁሉ ሲረጭ ይህችን ቦታ ግን በተለየ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በእጁ ለቅልቋታል። ስለሆነም ይህች ቦታ ከሌላው አካባቢ በተለየ ሁኔታ መቀባቷ የተቀደሰች መሆኗን ያመለክታል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ይህች ቦታ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ቅዱሳን አባቶች መሬቷን እንደ ሰፌድ አንስተው አስባርከዋታል። ከነዚህ መካከልም በቀዳሚነት የባረኳት አቡነ ሰላማ ዘአዜብ ሁለተኛ የተባሉት ጳጳስ ናቸው። ከዚያም አባ ቢንያሚ፣ ሦስቱ ወንድማማቾች ወይም ሠለስቱ አኃው፣ አቡነ ኢየሱስ ሞአ፣ አባ በግዑ፣ አባ ተክለ ሃይማኖት እና አቃቤ ሰዓት ሰረቀ ብርሃን ባርከዋት አልፈዋል (አባ ፍቅረ ዮሐንስ፣ ካሴት ቁ. 7፣ Side B) ይላሉ።

በሌላም በኩል ለገዳሙ መቋቋም እንደመነሻ ሊጠቀስ የሚገባው አቡነ ኢየሱስ ሞአ በደብረ ዳሞ ገዳም ማዕርገ ምንኩስና ከተቀበሉ በኋላ በመልአኩ ገብርኤል አማካይነት የተነገራቸው መልእክት ሊሆን ይችላል። ይህም በገድል መጽሐፋቸው (2001፣ 35) እንደሰፈረው መልአኩ ገብርኤል ከእግዚአብሄር ተልኮ ደብረ ዳሞን ለቀው ወደ ምስራቅ እንዲሄዱ፤ እዚያም ዙሪያዋን በውሃ የተከበበች ደሴት እንደሚያገኙ፤ ስሟም ደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ እንደምትባል፤ ይህች ሐይቅም ለእርሳቸው የተፈቀደችና ክፍላቸው መሆኗን ከነገራቸው በኋላ ወደ ሐይቁ መጥተው ገዳሙን ሊመሰርቱ ችለዋል የሚለው ነጥብና አባ ፍቅረ ዮሐንስ ያቀረቡት ሃሳብ ለገዳሙ መመስረት እንደምክንያት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

የአቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም በሁለት ይከፈላል፤ የወንዶችና የሴቶች በሚል። በደሴቱ መሐል ያለው የወንዶች መነኰሳት አንድነት ገዳም ሲሆን፤ ከደሴቱ ውጪ ደግሞ የሴቶች መነኰሳይያት አንድነት ገዳም (ቤተ ደናግል) ይገኛል።

የወንዶች ገዳም የተመሰረተው በአቡነ ኢየሱስ ሞአ አማካይነት በአጼ ይኩኖ አምላክ እርዳታ ነው። ይኩኖ አምላክ ከመንገሡ በፊት በሐይቅ እስጢፋኖስ ደብር፣ ከአቡነ ኢየሱስ ሞአ ጋር ይማር ነበር። አቡነ ኢየሱስ ሞአም ከደሴቱ ዓለማውያን ምእመናን ወጥተው ቦታው የመናንያን መነኰሳት መኖሪያ እንዲሆን ምኞት ያላቸው መሆኑን ዘወትር ያሳስቡት ነበር። ይኩኖ አምላክም የአባቱ መንግሥት ከተመለሰለት ምኞታቸውን እውን ለማድረግ ቃል መግባቱን የገድል መጽሐፋቸው (2001፣ 39) ያስረዳል።

ይኩኖ አምላክ በትረ መንግሥቱን ከተረከበ በኋላ አቡነ ኢየሱስ ሞአን ለመጠየቅና በረከት ለመቀበል ወደ ደሴቱ መጣ። አቡኑም ደሴቲቱ የመናንያን መነኰሳት መኖሪያ ትሆን ዘንድ ዓለማውያን ምእመናንን ከደሴቱ አስወጥቶ ሌላ ቦታ እንዲያሰፍራቸው ጠየቁት። ይኩኖ አምላክም ቃላቸውን ተቀብሎ "እናንተ ዓለማውያን ምእመናን ከዚህ ውጡና በእኔ ከተማ ከእኔ ጋር ትኖራላችሁ። የምትፈልጉትንም ሁሉ እሰጣችኋለሁ፤ አደርግላችኋለሁ። ይቺ ደሴት የመነኰሳት ገዳም ልትሆን ይገባል። እናንተ ግን ከእኔ ጋር መኖር ይገባችኋል ብሎ አዘዘ" (ዝኒ ከማሁ፣ 43)።

ከዚህ በኋላ ዓለማውያኑ ምእመናን ከደሴቱ ወጡ። ከወጡት መካከል ፈቃደኛ የሆኑት ንጉሡን ተከትለው ሲሄዱ የተወሰኑት ደግሞ በአምባሰል ወረዳ ተንኮርባ በሚባል አካባቢ በቅዱስ እስጢፋኖስ ስም ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ተቀምጠዋል። በእድሜ አዛውንት የሆኑት እንስት ምእመናን ደግሞ አሁን የመነኰሳይያት ገዳም ካለበት ቦታ ላይ በአቡነ ኢየሱስ ሞአ አስባርከው በማስገደም ስርዓተ ምንኩስና ተቀብለው ከሐይቁ ዳር መኖር ጀመሩ። አቡነ ኢየሱስ ሞአም ፍላጎታቸው ተሳክቶላቸው ደሴቱን የወንድ መናንያን ገዳም እንዲሆን አደረጉ (ዝኒ ከማሁ፣ 44)። ለገዳሙ የሚያስፈልጉ ነገሮችን (ለምሳሌ የመተዳደሪያ መሬት፣ የመገልገያ ቁሳቁሶች ወዘተ.) እንዲሟሉ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ንጉሡም የፈለጉትን በማድረግና ርስት በመስጠት ረድተዋቸዋል። ይሁንና ዓለማውያን ምእመናን ሲባል ሁለቱንም ጾታዎች ያጠቃልላል። ከደሴቱ ዓለማውያን ሴቶች እንዲወጡ ሲደረግ ወንዶችም አብረው ይውጡ አይውጡ የተገኘ ማስረጃ የለም።

የሴቶች አንድነት ገዳም (ቤተ ደናግል) ደግሞ አጼ ይኩኖ አምላክ ለአቡነ ኢየሱስ ሞአ በገቡት ቃል መሠረት ዓለማውያን ምእመናን (በተለይ ሴቶች) ከደሴቱ ከወጡ በኋላ የተመሠረተ እንደሆነ ቀደም ብሎ ተጠቅሷል፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙት አብዛኛዎቹ የእንስት መናንያን ገዳማት የሚመሠረቱት ከተለያዩ ቦታዎች ለምናኔ በሚሄዱ ሴቶች አማካይነት ሲሆን፤ የሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ ቤተ ደናግል የተመሠረተው ቀድሞ በደሴቱ ውስጥ ይኖሩ በነበሩ ምእመናን አማካይነት ነው (ዝኒ ከማሁ፣ 44)፡፡

አቡነ ኢየሱስ ሞአ ደብር የነበረውን ቦታ ገዳም እንዳደረጉት ሁሉ መንፈሳዊ ትምህርት ቤትም አቋቁመዋል፡፡ በከፈቱት ትምህርት ቤት አማካይነት በርካታ ቅዱሳን አባቶችን ሥርዓተ ምንኩስና ያስተማሩና ያመነኰሱ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል አቡነ ተክለሃይማኖት፣ አባ ጸሎተ ሚካኤል፣ አቡነ ኂሩተ አምላክ፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ አቡነ አሮን፣ አቡነ ገብረ ናዝራዊ፣ አቡነ ህዝቅያስ፣ አቡነ እስትፋስ ክርስቶስ፣ አባ በግዑ፣ አቡነ ዮሴፍ ወዘተ. የመሳሰሉ ታላላቅ ቅዱሳን ይጠቀሳሉ፡፡ አጼ ይኩኖ አምላክም ከመንገሣቸው በፊት እየተማሩ ያደጉት በዚሁ ገዳም ነው (መንግስቱ ጎበዜና አሳምነው ካሳ፣ 2000፣ 91፤ ገድለ አቡነ ኢየሱስ ሞአ፣ 2001፣ 48-49)፡፡

የሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም በዚህ ሁኔታ ተመስርቶ ጠንካራ የሃይማኖት ማዕከል ሆኖ እስከ ግራኝ አህመድ ወረራ ድረስ ቆይቷል፡፡ በግራኝ አህመድ ወረራ ደግሞ ከተለያዩ ነገሥታት የተበረከቱለት ንዋየ ቅድሳት፣ የወርቅ ቁሳቁሶች፣ ዘውዶች እንዲሁም ሌሎች ንብረቶች ተወስደውበታል፡፡ ይሁንና ንብረቶቹ ቢዘረፉም እንደ ሌሎቹ የአገራችን አድባራትና ገዳማት ገዳሙ አልተቃጠለም፤ መነኰሳቱም አልተገደሉም ሲሉ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1966፣ 390) ያብራራሉ፡፡ አያይዘውም "የእስጢፋኖስ ገዳም በመበዝበዝ ብቻ የዳነው መምህሩ ከግራኝ ጋር በመስማማታቸው ነው፡፡ ግራኝም ሁሉን ሲያቃጥል ይኸን ገዳም ሊያተርፍ የፈቀደው በዚህ ደሴት በምርኮኝነት በኖረው በአውራይ ሐብር አራድ ምልጃ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም" (ዝኒ ከማሁ፣ 391) ይላሉ፡፡ ይሁንና ከግራኝ አህመድ ወረራ በኋላ የወንዶች ገዳም የነበረው ታዋቂነትና የመነኰሳቱ የአንድነት ኑሮ የተዳከመ ሲሆን፤ የሴቶች ቤተ ደናግል ደግሞ ሙሉ በሙሉ ጠፍቶ ነበር፡፡ እንደ አቡነ አትናቴዎስ እምነት ከሞት የተረፉት መነኰሳት በየቦታው በመሰደዳቸውና ለረጅም ዘመናት ገዳሙን ጠብቀው

ያቆዩት የአካባቢው ተወላጆችም ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ መናንያንን አናስገባም ማለታቸው ለገዳማቱ መዳከም በምክንያትነት የሚጠቀሱ ናቸው[8]።

ከዚህ በኋላ በ1985 ዓ.ም ብጹእ አቡነ አትናቴዎስ የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ከመጡ በኋላ ባደረጉት ከፍተኛ ጥረት የሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ የወንዶች አንድነት ገዳም ዳግም ትንሳኤ አግኝቶ ወደ ቀድሞው ሁኔታ ሊመለስ ችሏል። ከዘረፋ የተረፉት የገዳሙ ቁሳዊ ሃብቶችም ሙዚየም ተዘጋጅቶላቸው እንዲቀመጡ ተደርገዋል። ቤተ ክርስቲያኑም አስፈላጊው እድሳትና ጥገና ተደርጎለታል። በርካታ የመነኩሳት ቤቶችም ተገንብተው መነኩሳቱ እርስ በርስ እየተረዳዱ ይኖራሉ። የቆሎ ተማሪዎችም ከተለያዩ አካባቢዎች እየመጡ "የአብነት ትምህርት" ይማራሉ (አባ ፍቅረ ዮሐንስ፣ ካሴት ቁ.2፣ Side A)። ሙሉ በሙሉ ጠፍቶ የነበረውን ቤተ ደናግም በአዲስ መልክ ተመስርቶ ከተለያዩ አካባቢ የመጡ መነኩሳይያት የአንድነት ኑሮ መምራት ጀምረዋል። በተጨማሪም አንድ የካህናት ማሰልጠኛ ተቋም ተቋቁሞ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

## 3.2 የሥራ ክፍፍልና አይነት

ገዳማት የጸሎትና የስግደት በአጠቃላይ የመንፈሳዊ ህይወት ቦታ ብቻ ሳይሆኑ የሥራ ቦታም ናቸው። ሥራ ለገዳማውያን የህይወታቸው አንዱ ክፍል ነው። ስለሆነም ገዳም እያንዳንዱ እንደ ችሎታውና ዝንባሌው በተለያየ ተግባርና አገልግሎት አስተዋጽኦ የሚያደርግበት ቦታ ነው። ስለዚህ ዓለመ ምንኩስናን መርጦ በገዳም የሚኖር ገዳማዊ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይል በተመደበበት ቦታ ማገልገል ይኖርበታል። ወደ ማኅበሩ ሲቀላቀልም ሆነ ሲመነኩስ ከሚገባው ቃል ኪዳን አንዱ በታዘዘበት ቦታ መስማራትና መስራት ነውና። "እንደ ማኅበሩ ሕግ የቆመውን ቁረጥ፣ የተጋደመውን ፍለጥ ቢሉኝ በትህትና ታዝዤ እፈጽማለሁ። ነፍሴን ለእግዚአብሔር ሥጋየን ለማኅበር ሰጥቻለሁ" (ፊልጶስ፣ 1961፣ 23) ይላል።

በተጨማሪም በገዳማት ውስጥ መነኩሳት "ያልሠራ አይብላ" እንዲሉ እርስ በርሳቸው እየተረዳዱ በጉልበታቸው በሚያፈሩት አሳባ የሚኖሩ በመሆናቸው የሥራ

---

[8] የሐገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አቡነ አትናቴዎስ የካቲት 04 ቀን 2002 ዓ.ም በገዳሙ ውስጥ ባሰሩት የ"መንበረ ጵጵስና" ቤት በረንዳ ላይ ባገኘኋቸው ቀን የነገሩኝ ነው።

ባህል በማኅበረ መነኰሳቱ ዘንድ የዳበረ ነው። ይህን ሀሳብ በማጠናከር ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል የሚከተለውን ብሏል።

> መስራት እየቻለ የማይሠራ ሰው የክፋቶች ሁሉ ማደሪያ ይሆናል። እጆቹን ከተግባረ እድ፣ አይኖቹን ከአንብቦ መጻሕፍት፣ ጆሮዎቹን ከሰሚዓ ወንጌል ወነገረ ቅዱሳን፣ ሕዋሳቱን ከጣእመ ቅዳሴ ሕሊናውን ከተዘክሮተ እግዚአብሔር ያልለየ ሰው በዚህ ዓለም ካለው ጾብዓ አጋንንትና መሥርገተ ዓለም በዚያኛው ዓለም ካለው መከራ ሲኦል ይተርፋል ሰይጣንም ሆነ ክፉ ሰው ወደርሱ አይቀርበውም። የክብር ባለቤትም ይሆናል (1999፣ 18-19)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ "ስንፍናን አስወግዳችሁ በትጋትና በሙሉ ልብ ጌታ ኢየሱስን አገልግሉ" (ሮም.12፥ 11) እንዳለው ገዳማውያኑ ሰውነታቸውን ለድካም፣ ነፍሳቸውን ለጸሎት በመስጠት ቀን በተግባረ እድ፣ ሌሊት በጸሎት ተግተው ይኖራሉ። እንዲሠሩ በተሰጣቸው ጊዜና ቦታም ሲወጡና ሲወርዱ ይውላሉ።

በሐይቅ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም የሚኖሩ መነኰሳትም ሆኑ መነኰሳይያት በተለያየ መስክ ተሰማርተው ይውላሉ። የሥራ ስምሪቱ በሊቀ ረድኡ የሚመራ ሲሆን፤ በአርድእቶች ምርጫ ወይም ፍላጎት የሚሰራ ሥራ የለም። ስለሆነም ይህ ሥራ አይመቸኝም፣ ይህን አልሰራም ሳይሉ በተመደቡበት ቦታ ይሰማራሉ። ይሁን እንጂ ለብዙ ጊዜ በአንድ ቦታ በመስራታቸው ምክንያት የሚሠሩት ሥራ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ የሚቀንስ ከመሰላቸው የገዳሙን ስርዓት ጠብቀው ሥራው እንዲቀየርላቸው መጠየቅ ይችላሉ። የበላይ ኃላፊዎቹ ምክንያቱን ካመኑበት ሥራውን ይቀይሩላቸዋል (አባ ገብረ ኢየሱስ፣ ካሴት ቁ.3፣ Side A)። ይህ የሚደረገው በቋሚ ስራ ለተሰማሩ አርድእቶች ብቻ ነው። ለምሳሌ በተግባር ቤት ብዙ ጊዜ ያገለገለ ኀል መጋቢ ለጸሎትም ሆነ ለሌላ ትሩፋት ካልተመቸውና ምክንያቱም አስተዳደሩን ካሳመነ ሌላ ስራ እንዲሰራ ይደረጋል። ለቋሚ ሥራዎች (ለተግባር ቤት፣ ለጫኝነት፣ ለወፍጮ ቤት፣ በጀልባ ለማስጎብኘትና ለመሳሰሉት) የሚመጥኑ ገዳማውያንን የሚመድቡት አበምኔቱና መጋቢው ናቸው። ከዚህ ውጭ ግን ሊቀ ረድኡ መጋቢው በሚያወጣለት እለታዊ የሥራ ዝርዝር መሠረት አርድእቶችን ከፋፍሎ ያሰማራል።

በገዳማቱ በርካታ የሥራ ዘርፎች (መጋቢ፣ ሊቀ ረድዕ፣ ጸሐፊ፣ እቃ ቤት ወዘተ.) ያሉ ሲሆን፤ በአስተዳደር መዋቅሩ ውስጥ ያሉት የሥራ ዘርፎች ለሌሎቹ

መሰረት ናቸው። እነሱም ከአበምኔቱ ጀምሮ እስከ እቃ ቤት ድረስ ያሉት ናቸው። ከዚህ በታች በገዳማቱ ካሉት ተግባራት ውስጥ ተግባር ቤት (ወፍጮ ቤት፣ እንጨት ፈለጣ፣ ጫኝነት ወዘተ.) እና ግብርና (ከብት እርባታ፣ ዶሮ እርባታ፣ የአትክልት ልማት ወዘተ.) የተሰኙትን የሥራ ዘርፎች እንመለከታለን። ከነዚህ ውጭ ያሉት የሥራ ዘርፎች አይታዩም። ይሁንና ጠቀሜታቸውን ከማሳነስ አኳያ አለመሆኑ ልብ ሊባል ይገባል። እነዚህን ተግባራት ለማጉላት የተፈለገው ግብርና የገዳማቱ ከፍተኛ የገቢ መሠረት ከመሆኑ አንጻር እና ተግባር ቤት ደግሞ ለገዳማውያኑ ህልውና ወሳኝ በመሆኑ ነው።

### 3.2.1 ተግባር ቤት

ተግባር ቤት በገዳሙ መጋቢ አማካይነት የሚመራ የሥራ ዘርፍ ነው። ተግባር ቤቱ የገዳማውያኑ የእለት ተእለት ምግብ የሚዘጋጅበት ሲሆን፤ አዘጋጆቹ ደግሞ "ኀል (ዕኀል) መጋቢ" ይባላሉ። "ዕኀል መጋቢ የመጋቢው ረዳቶች፣ የመጋቢው ልጆች እንደማለት ነው" (አባ ኪዳነ ቃል፣ ካሴት ቁ. 8፣ Side A)። ኀል (ዕኀል) መጋቢዎች ለገዳማውያኑ እለታዊ ፍጆታ የሚሆን ምግብ የሚያባስሉና ከፋፍለው የሚያቀርቡ ናቸው። በሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም በሴቶቹም ሆነ በወንዶቹ ገዳም ሁለት ሁለት ተግባር ቤቶች ያሉ ሲሆን፤ አገልግሎታቸውም አንዱ ዳቤና እንጀራ እንዲሁም ንፍሮና ወጥ ይዘጋጅበታል። ሁለተኛው ደግሞ የመጠጥ (ጠላ) ማዘጋጃ ነው። ለሁለቱም ተግባር ቤቶች አራት ኀል መጋቢዎች ይመደባሉ። ሶስቱ በምግብ ቤት፣ አንደኛው ደግሞ በመጠጥ ቤት ያለውን ተግባር ይከውናሉ። ከምግብ ቤት ሰራተኞቹ ውስጥ ሁለቱ ለዳቤና እንጀራ አንዱ ደግሞ ለንፍሮና ወጥ የተመደቡ ናቸው (አባ ገብረ ኢየሱስ፣ ካሴት ቁ.2፣ Side B)።

በገዳማቱ ዳቤና እንጀራ እንዲሁም ማባያ ወጥ ዘወትር ይዘጋጃል። ጠላ ደግሞ ለዓመት ክብረ በዓሎችና ለጾም ፍቺዎች ይጠመቃል። "በዚህ ገዳም ጠላ የሚዘጋጀው ለባለወልድ፣ ለቦታው ባለቤት ለአቡነ ኢየሱስ ሞአ፣ ለእስጢፋኖስ፣ ለእመቤታችን፣ ለትንሳኤ ወዘተ. ነው" (አባ ሀብተ ስላሴ፣ ካሴት ቁ. 3፣ Side A)። የዓመት ክብረ በዓል የሚባሉት የእስጢፋኖስና የአቡነ ኢየሱስ ሞአ ክብረ በዓል ናቸው። እነሱም መስከረም 15 የእስጢፋኖስ አጽም የፈለሰበት፣ ግንቦት 26 አቡነ ኢየሱስ ሞአ የተወለዱበትና ኅዳር 26 ደግሞ ያረፉበት ቀናት ናቸው።

ለተግባር ቤቶቹ እህል የሚቀርበው ከተግባር ቤቱ መጋዘን በመጋቢው አማካይነት ነው። መጋቢው ለዳቤም ሆነ ለእንጀራ ወይም ለጠላ የሚሆነውን እህል አውጥቶ እንዲፈጭና እንዲቀመጥ ያደርጋል። ዓል መጋቢዎቹ ደግሞ ለአንድ ቀን የሚበቃቸውን ያህል እያወጡ ያቦካሉ (አባ ገብረ ኢየሱስ፣ ካሴት ቁ.2፣ Side B)። የሚቦካው ከመቶ ሃምሳ ዓመት በላይ እንዳገለገለ በሚነገርለት የእንጨት ገበታ ነው። ዱቄቱ ገበታው ላይ ተደርጎ ውሃ እየተጨመረበት በደንብ ከታሸ በኋላ በሚፈለገው መጠን መቅጠን ወይም መወፈሩን አረጋግጠው ወደ በርሚል ይገለብጡታል።

ጋገራ በሥራ ቀን (ከሰኞ እስከ አርብ ድረስ) ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት በኋላ፣ በበዓል ቀናት (ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ በወርሃዊ በዓሎችና በበዓለ ሃምሳ) ደግሞ ከምሽቱ አምስት ሰዓት አካባቢ ይጀመራል (አባ ሀብተ ስላሴ፣ ካሴት ቁ.3፣ Side A)። በበዓል ቀናት ከቅዳሴ በኋላ መቁነን ስለሚሰጥ ምግቡ ቀደም ብሎ መዘጋጀት አለበት። በሌሎቹ ቀናት ግን በተለመደው ሰዓት ስለሚቆነን ቀስ ተብሎ ቢዘጋጅም ይደርሳል ተብሎ ይታመናል። እንጀራም ሆነ ዳቤ ከምጣዱ ሲወጣ እንዲበርድ እንደ አልጋ በተዘጋጀ እንጨት ላይ ለትንሽ ደቂቃ ይዘረጋል። የመቁነን መስጫ ሰዓት ከመድረሱ በፊትም አንዱ ዳቤ ለስምንት ይሸነሸናል። የሚቆነነው እንጀራ ከሆነ ለአንድ ሰው አንድ ይሰጣል (አባ ገብረ ኢየሱስ፣ ካሴት ቁ.2፣ Side B)።

ምግቡ ከተባሰለና ከተቆረሰ በኋላ ለአርድእት በሥራ ቀን ሁለት ጊዜ (በሰባት ሰዓትና ወደማታ) ለካህናትና ለአረጋውያን ደግሞ ከዘጠኝ ሰዓት በኋላ ይሰጣል። ብዙውን ጊዜ በሰባት ሰዓት የሚሰጠው ምሳ ተብሎ ስለሚታሰብ አንድ ቁራሽ ዳቤ ነው። ለካህናትና ለአረጋውያን ግን ዳቤ ብቻ በሚጋገርበት ቀን ካልሆነ እንጀራ ይቆነናሉ። ምክንያቱም ለአረጋውያንና ለካህናት የሚቆነነው በ24 ሰዓት አንድ ጊዜ ነው። አባ ፍቅረ ዮሐንስ አርድእት ሁለት ጊዜ የሚሰጥበትን ምክንያት ሲገልጹ፣

> አርድእቶች በስራ ቀን ምሳ አላቸው። ያም በስራ ቀን ስራ ሲሰሩ ስራው ክብደት ስላለው አርድእቶች ምሳ ካላገኙ አንደኛ ስራውን ያስቀራል፤ ሁለተኛም የአገልግሎት ጊዜያቸውን ይቀንሳል። ምክንያቱም ሰባትና ስምንት አመት የሚያገለግል አርድእት በጾም የሚሰራ ከሆነ አንድ አመትም አያገለግልም። ምክንያቱም ስጋው እየደከመ ስለሚሄድ ከስድስት ሰዓት በኋላ መስራት አይችልም፤ ውሃ ጥምም ያስቸግረዋል። የበዓል

ቀን ሆኖ ስራ የማይሰራበት ከሆነ ግን ሁሉም ዘጠኝ ሰዓት ይመገባሉ (ካሴት ቁ.1፣ Side B) ይላሉ።

ሌላው በተግባር ቤት የሚሠራው ወጥ ሲሆን፤ ለበሽተኞችና ለጉልበት ሰራተኞች ለዳቤ ማባያ፣ እንዲሁም እንጀራ ሲቆነን ለሁሉም ይሰጣል።

በሐይቅ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ንፍሮ የዘወትር ምግብ አይደለም። በፊት ለነበሩ ገዳማውያን መደበኛ ምግባቸው እንደነበረ ቢነገርም አሁን ግን የእንጨት ችግር ስላለ በመደበኛነት አይዘጋጅም። ይሁንና የቆሎ ተማሪዎችን ስራ ሲያሠሩ (ማለትም የቆሎ ተማሪዎች በሳምንት አንድ ቀን ለገዳሙ የጉልበት አስተዋጽኦ ማድረግ ስለሚጠበቅባቸው)፣ በአብይ ጾም ወቅት (በተለይ እሮብና አርብ) እንዲሁም በአቡነ ኢየሱስ ሞአ የዓመት ክብረ በዓል ወቅት በወንዶች ገዳም ንፍሮ ይቀቀላል። አባ ሀብተ ስላሴ "ንፍሮ የመቀቀሉ ድርሻ ወጥ የሚሰራው ኋል መጋቢ ነው" (ካሴት ቁ.3፣ Side A) ይላሉ። ኋል መጋቢው ውሃውን ይጥድና እስኪፈላ ድረስ ተለቅሞ የተሰጠው እህል ውስጥ ባጋጣሚ ሳይታይ ያለፈ ልቃሚ ካለ ይመለከታል። ውሃው ሲፈላም መጀመሪያ በቆሎውን ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ስንዴውን ይጨምራል። ንፍሮ መደበኛ መቁነን ስላልሆነ ብዙውን ጊዜ ከሌሊቱ አሥር ሰዓት በኋላ ይቀቀላል። ከበሰለ በኋላ ከጎላው ድስት ወደ ገቡቴ እየተቀነሰ በመቁነን መስጫ ቤት ይቀመጣል። ሰዓቱ ሲደርስም ለቆሎ ተማሪዎችም ይሁን ለገዳማውያኑ አንድ አንድ ጭልፋ ከትንሽ ዳቤ ጋር ይታደላል። ለክብረ በዓል ታዳሚዎች የተዘጋጀ ከሆነ ደግሞ የበዓሉ ስነ ስርዓት ሲያልቅ በገዳሙ ዋና በር አካባቢ ለተሰበሰቡ እንግዶች እንዲያዳርስ ተደርጎ በጭልፋ ይታደላል። የንፍሮው ውሃ ከውስጥ ደዌ ይፈውሳል ተብሎ ስለሚታመን ብዙውን ጊዜ ለገዳማውያኑ ይሰጣል።

በቤተ ደናግሉ ተግባር ቤት ንፍሮ የሚዘጋጅበት ወቅት በውል አይታወቅም። ይሁንና ወደ ግሸን ደብረ ከርቤ የሚሄዱ ምእመናን ሲሄዱ ወይም ሲመለሱ ገዳሙን ሳያዩ ስለማያልፉ ለበረከት እያሉ ንፍሮ ያዘጋጃሉ። እንዲሁም ለኪዳነ ምህረት ክብረ በዓል ወቅት አንዳንድ ጊዜ ለመዘከሪያ ንፍሮ ያዘጋጃሉ። ብዙውን ጊዜ ግን በዳቦ ነው የሚዘክሩት። ይህን በተመለከተ እሙሃይ ስነ ማርያም "የእንጨት ችግር ስላለ ንፍሮውን ወደ ዳቤ ለወጥነው" (ካሴት ቁ.3፣ Side B) ይላሉ። ጠላ ደግሞ በአንድ ኋል መጋቢ የሚዘጋጅ ሲሆን፤ የሚዘጋጀውም በገዳሙ ከሚመረቱ በቆሎ፣ ዳጉሳና ገብስ ነው።

ወደ ተግባር ቤቶቹ የሚገባ ገዳማዊም ሆነ እንግዳ ጫማውን ያወልቃል። ብዙዎቹ ገዳማውያንም ከቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ እስከ ተግባር ቤቶቹ ድረስ አውልቀው ይሄዳሉ። ተልእኳቸውን ፈጽመው ሲመለሱም ካወለቁበት አካባቢ ሲደርሱ ያደርጋሉ። ጫማ የሚወለቅበት ምክንያትም ተግባር ቤቶቹ በየእለቱ እንደ ቤተ ክርስቲያን ስለሚታጠኑና በተግባር ቤቶቹ የሚሠሩ ኅል መጋቢዎችም ዘወትር ጸሎት እያደረጉ የሚሠሩባቸው ቦታዎች ስለሆኑ ነው። ጸሎት የሚደረግባቸው ቦታዎች ደግሞ የተቀደሱ ስፍራዎች ናቸው ተብሎ ስለሚታመን በጫማ አይረገጡም።

## 3.2.2 ግብርናና ሌሎች ተግባሮች

የቀድሞ ነገሥታት ለገዳማት መተዳደሪያ ሰፋፊ መሬት ይሰጡ ነበር። አንዳንዶቹ ነገሥታትም ከገቢያቸው ሲሶውን ያህል ይሰጡ ነበር ይባላል። በአሁኑ ጊዜ ግን የገዳማቱ መተዳደሪያ የነበረው መሬት በደርግ ጊዜ በወጣው አዋጅ ተወስዶባቸዋል። የሐይቅ ገዳምም (የወንዶች) እንደ ሌሎቹ ገዳማት በተለያዩ መንግስታት የተሰጠውን መሬት ተነጥቋል። ይሁንና በደሴቱ ውስጥ እና በመግቢያው አካባቢ ያለው መሬት አልተነካበትም።

ቤተ ደናግሉ ግን በግራኝ አህመድ ወረራ ሙሉ በሙሉ ጠፍቶ ስለነበር ቦታውን ገበሬዎች ይዘውት ነበር። እንደገና ሲቋቋምም ገበሬዎቹ የያዙትን መሬት በስምምነት ቢመልሱላቸውም በቂ መሬት የለውም። በአጠቃላይ በሁለቱም ገዳማት በግብርና ብቻ ለመተዳደር የሚያስችል መሬት የለም። የእናቶች ገዳም ያላቸውን መሬት የተወሰኑ ቋሚ አትክቶችን (እንደ ፓፓያ፣ ሙዝ፣ ብርቱካን ወዘተ.) እና የጓሮ አትክልት (ቲማቲም፣ ጎመን፣ ሰላጣ ወዘተ.) ለገበያና ለራሳቸው ፍጆታ ያለማሉ። ከዚህ በተረፈ በሐይቁ ዳር ባላቸው ትንሽ መሬት ላይ አንድ ዓመት ማሽላ፣ አንድ ዓመት ገብስ፣ አንድ ዓመት በቆሎ ይዘራሉ (እሙሃይ ስነ ማርያም፣ ካሴት ቁ.4፣ Side A)።

ወንዶቹ ደግሞ በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ያለውን መሬት (በተለይ አሁን ያሉት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ከመጡ ወዲህ) ቡና፣ ማንጎ፣ አቡካዶ፣ እና ብርቱካን ያለሙበታል። የሐይቁን ዙሪያ ደግሞ ፓፓያ፣ ሙዝ፣ ሸንኮራ አገዳ ወዘተ. እና በቆሎን ጨምሮ የተለያዩ ሰብሎች እያፈራረቁ ለመዝራት ይጠቀሙበታል። የወንዶቹ ገዳም አንድነቱ ተዳክሞ በነበረበት ጊዜ መነኰሳቱ መሬቱን ተከፋፍለው እያረሱ ይጠቀሙበት

ነበር። የገዳሙ አንድነት እንደገና ሲመሰረት በግላቸው ይዘውት የነበረውን ለዘመዶቻቸው እየሰጡ ወደ አንድነቱ ስለገቡ ገዳሙ አሁን ስምንት ሄክታር ገደማ የሚገመት መሬት አለው (አባ ተስፋ ስላሴ፣ ካሴት ቁ.5፣ Side B)። ይሁንና በዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴና በመስኖ ስለሚጠቀሙ፣ እንዲሁም ገበያ ተኮር የሆኑ አትክልቶችን ስለሚያመርቱ ራሳቸውን ለመቻል የሚያበቃ ገቢ ያገኛሉ። የገዳሙ አንድነት ሲመሰረት አረጋውያን መነኩሳት በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ያለው መሬት የቅዱሳን አጽም ያረፈበት ስለሆነ መታረስ የለበትም ስላሉ ከግብርና ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር ከላይ የተጠቀሱትን በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ቋሚ አትክልቶች እንዲለሙ አድርገዋል (ዝኒ ከማሁ)። በገዳሙ መግቢያ አካባቢ ያለውን መሬት ደግሞ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ጤፍ የመሳሰሉ ሰብሎችን እያፈራረቁ ይዘሩበታል።

ወንዶቹ ገዳማውያን ያላቸውን የሚታረስ መሬት በሦስት ጥማድ በሬዎች የሚያርሱ ሲሆን፤ በቋሚ አትክልቶች የተሸፈነውን መሬት ደግሞ በዶማ ይኮተኩታሉ። የዘሩት ሰብልና የተከሏቸው አትክልቶች ምርት ተሰብስቦ እስከሚነሳ ድረስ ውሃ ማጠጣት፣ መኮትኮት፣ አረም ማረምና ወፍ መጠበቅ የመሳሰሉት ሥራዎች የአርድእቶች የእለት ተእለት ሥራዎች ናቸው። ገዳሙ ከሐይቁ በሁለት ሞተሮች አማካይነት ውሃ እየሳበ በትልቅ የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ በመሙላት ያሉትን ቋሚ አትክልቶች ያጠጣል። በሐይቁ ዳር ለሚዘሩ ሰብሎች ደግሞ በመስኖ ይጠቀማል። በአረም ወቅትና በአጨዳ ጊዜ የሰው ሃይል ስለሚያስፈልግ ከካህናቱ መካከል ፈቃደኛ የሆኑት አርድእቶቹን ያግዟቸዋል። ሰብሉ ከተሰበሰበ በኋላ ደግሞ ቃርሚያውን ከብቶቻቸው እንዲለቅሙ ካደረጉ በኋላ እንደገና ያርሱታል። ገዳሙ በዙሪያው ያለውን ሐይቅ በመጠቀም እንጂ የዝናብ ውሃን ብቻ ጠብቆ አያመርትም።

በተጨማሪም በገዳሙ የከብት እርባታ ይካሄዳል። የከሱ በሬዎችን እየገዙ ለአራት ወር ያህል አድልበው ይሸጧቸዋል። እስከሚሸጡም ድረስ ያርሱባቸዋል። መነኮሳቱ ለከብቶቹ ቀለብ ከዚያው ስለሚያገኙ ወጪ የለባቸውም። ስለሆነም ከብት ሲረክስ ይገዛሉ፤ የተወሰነ ወር ቀልበው ሲወደድ ይሸጣሉ። ከበሬዎቹ በተጨማሪ ላምና በግ ያረባሉ። ከላሞቹ የሚገኘውን ወተት እስካሁን ለገበያ አቅርበው ባይጠቀሙም ወተቱ ለአረጋውያንና ለታመሙ ገዳማውያን ይሰጣል። ለሌሎቹ ገዳማውያን አጠራቅመው የሚያድሉበት ጊዜ እንዳለም አባ ተስፋ ስላሴ (ካሴት ቁ.5፣ Side B) ይገልጻሉ።

የወንዶች ገዳም ከቅርብ ጊዜ (በ1996 ዓ.ም) ወዲህ የዶሮ እርባታ ጀምሯል። ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ አባቶች "ቦታው የቅዱሳን አጽም ያረፈበት ስለሆነ የዶሮዎቹ ቆሻሻ አጽማቸውን ያረክሳል" እያሉ ቢቃወሙም ካለው ገቢ አንጻር እርባታው አለመቋረጡን የገዳሙ የልማት ኃላፊ የሆኑት አባ ተስፋ ስላሴ (ካሴት ቁ.5፣ Side A) ይናገራሉ። ስለሆነም ከኮምቦልቻ የግብርና ምርምር ማዕከል የአንድ ቀን ጫጩቶችን በማምጣት ያሳድጋሉ። ዶሮዎቹም የሥጋና የእንቁላል ተብለው ይለያሉ። ከዶሮዎቹ የሚገኘውን እንቁላልና የስጋ ዶሮዎቹን ለአካባቢው ተጠቃሚ በማቅረብ የገቢ ምንጫቸውን ያዳብራሉ። የዶሮ እርባታውን ለማስፋፋትም የእንቁላል ማስፈልፈያ ኢንኩዩቤተር ለመጠቀም ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን አባ ተስፋ ስላሴ ይናገራሉ። ዶሮዎቹን የሚንከባከቡት በቋሚነት የተመደቡ አርድእቶች ሲሆኑ ግማሾቹ እንቁላል ይሰበስባሉ፤ ለዶሮዎቹ ምግብና ውሃ ይሰጣሉ። የተወሰኑት ደግሞ ከሐይቁ ዓሳ በማምጣት ቀቅለው ያቀርባሉ።

ከቋሚ አትክልቶች የሚገኘውን ምርት ገዳሙ በአካባቢው በከፈተው ሱቅ ለገበያ የሚያቀርብ ሲሆን፤ አንዳንዴም ወደ ከተማ ይጭናሉ። ሱቁ በየእለቱ የሚቀርበውን አትክልትና የተለያዩ ሸቀጦች ለጎብኝዎች፣ ለጸበልተኞችና ለአካባቢው ማኅበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል። የወረዳውም ሆነ የዞኑ ግብርና ባለሙያዎች ለገዳሙ የልማት እንቅስቃሴ ከፍተኛ ድጋፍ የሚያደርጉ ሲሆን፤ አዳዲስ ምርቶች ሲመጡም በገዳሙ መሬት ላይ አባዝተው ለገበሬው ያከፋፍላሉ (ዝኒ ከማሁ፣ Side B)።

ከላይ እንደተገለጸው ቤተ ደናግሉ በቂ የእርሻ መሬት የለውም። ስለዚህ የሀገረ ስብከቱ አስተዳዳሪ ከተለያዩ በጎ አድራጊዎች ባገኙት ገንዘብ የሽመና ማሽንና የስፌት መኪናዎች በመግዛትና በገዳሙ አካባቢና በሐይቅ ከተማ የወፍጮ ቤት በመክፈት መነኮሳይያቱ ራሳቸውን እንዲችሉ አድርገዋል። ምርታቸውን ለገበያ የሚያቀርቡበት ሱቅም በሐይቅና በደሴ ከተማ ተከፍቶላቸዋል (እማሆይ ስነ ማርያም፣ ካሴት ቁ. 4፣ Side A)። በቤተ ደናግሉ ያለውን ሥራ ሊቀ ረዷ ተቆጣጥራ ታሰራለች። አርድእቶቹም ምድባቸውን ስለሚያውቁ የሥራ ደወል ሲደወል ወደ ሥራቸው ይሰማራሉ። ምክንያቱም ሽመናውንም ሆነ ልብስ ስፌቱን የሚሠሩት የሰለጠኑ አርድእቶች ናቸው። ስለዚህ በየቀኑ ስምሪት አያሻቸውም። ስልጠና ያልወሰዱ አርድእቶች ደግሞ የጓሮ አትክልት ይንከባከባሉ፤ በተጨማሪም ቀለም በማቅለም ለሽማኔዎቹ ግብአት ያቀርባሉ (እማሆይ ወለተ ስላሴ፣ ካሴት ቁ.3፣ Side A)። የሽመና ሥራው ከገቢ ምንጭነቱ

ባሻገር በአመት አንድ ጊዜ የሚቆነነውን የመነከሳይያት መጎናጸፊያ ልብስ ይሸፍናል። በተጨማሪም ልብሳቸው የሚሰፋው በቤተ ደናግሉ ልብስ ሰፊዎች ነው።

ገዳማቱ በማር ምርት በኩልም ዘመናዊ ቀፎዎችን በመጠቀም ከፍተኛ ገቢ ማግኘት ጀምረዋል። በተጨማሪም የወንዶቹ ገዳም በአቅራቢያው ያለውን ገደላማ ቦታ ከቀበሌ ማኅበር ተረክቦ ደን በማልማት አካባቢው ልምላሜ እንዲኖረው ከማድረጉም በላይ የቆሎ ተማሪዎች መኖሪያ ቤት ችግር ለመቅረፍ ችሏል። ለገዳሙ ተግባር ቤት ማገዶና ለሽያጭ በማቅረብም ከፍተኛ ጥቅም እያገኙ ነው። በአሁኑ ወቅት ከመንፈሳዊ ተግባራት በተጓዳኝም አረጋውያንና ወላጅ የሌላቸውን ህጻናት ለመርዳት የሚያስችል ማዕከል ለማቋቋም እየተንቀሳቀሱ ናቸው።

በአጠቃላይ "መነኰሳት ሠርተው እንጅ ለምነው መብላት የለባቸውም" ተብሎ ስለሚታመን የሐይቅ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም መነኰሳትና መነኰሳይያት ከመንፈሳዊ ተግባራት ጎን ለጎን ራሳቸውን በራሳቸው በመርዳት ይተዳደራሉ። እነዚህ ተግባራትም በርካታ አርድእት የሚሰማሩባቸው ሲሆኑ ከነዚህ ውጪ ለገዳሙ ህልውና አስፈላጊ የሆኑ በርካታ ተግባራት በቋሚ አርድእቶች ይሰራሉ። ለምሳሌ ወፍጮ ቤት፣ እንጨት ፈለጣ፣ በሞተር ማስጎብኘት፣ እህል መልቀምና ማሰጣጣት የመሳሰሉት ሥራዎች በቋሚ አርድእቶች ይከወናሉ። እነዚህ አርድእቶች በተግባር ቤት የሚዘጋጀው ዳቤም ሆነ እንጀራ፣ ንፍሮም ሆነ ወጥ እንዲሁም የሚጠመቀው ጠላ በወቅቱ እንዲዘጋጅ የሚያደርጉ ናቸው።

# ምዕራፍ አራት

## የገዳማውያኑ የአመጋገብ ስርዓት፣ አለባበስና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸው ቁሶች

በዚህ ምዕራፍ ሶስት ንኡሳን ርዕሶች ተካተዋል። የመጀመሪያው ርዕስ የገዳማውያኑን የአመጋገብ ሁኔታ የሚመለከት ነው። ሁለተኛው ርዕስ ደግሞ የገዳማውያኑ የአለባበስ ሁኔታ የታየበት ክፍል ሲሆን፤ በሶስተኛው ርዕስ ደግሞ ገዳማውያኑ በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውና የሚይዟቸው ቁሶች ይታያሉ።

### 4.1 የገዳማውያኑ የአመጋገብ ስርዓት

የኢትዮጵያ ገዳማት የተገደሙበት ቦታና የአገዳደማቸው መነሻ ታሪክ የተለያየ ነው። ገዳማቱ በተለያየ ቦታ እንደሚገኙ ሁሉ ውስጣዊ ስርዓታቸውና አተገባበራቸውም ይለያያል። ለምሳሌ የምግብ አይነትና የምግብ ሰዓት፣ "ሕርመት"[9] እና "ክፈለ ሕብስት"[10] የአንዱ ገዳም ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበት ባህሪ ይኖረዋል። ለምሳሌ የማኅበረ ስላሴው ከደብረ ሊባኖስ፣ የዋልድባው ከደብረ ቢዘን፣ ወዘተ. አንዱ ከሌላው የሚለይበት ሁኔታ ይኖረዋል (የሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ የወንዶች ገዳም መተዳደሪያ ደንብ፣ 1987፣ 3)። ስርዓቱ እና ህጉም ለመነኮሳቱ በመሆኑ መነኮሳቱ ለ"ገድል"[11] እና

---

[9] ሕርመት፡- ከምግብ መለየት፤ ቀን እኽል ሳይቀምሱ ውሎ ማታ አንድ ጊዜ ጥሬ መብላት፣ ውሃ መጠጣት ማለት ነው (ደስታ ተክለ ወልድ፣ 1962፣ 527)።

[10] ሕብስት፡- ለዝክር፣ ለማህበር፣ ... የሚጋገር ዳቦ፣ ፀዲቅ፤ እንደ ድፎ ወፈር ሳይል የተጋገረ ክብ ዳቦ ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ 1993፣ 8)።

[11] ገድል፡- ሰማዕታት ስለክርስቶስ እጅ እግራቸውን ለሰንሰለት፣ ዐይናቸውን ለፍላት ሰጥተው በሰውነታቸው የፈፀሙት መንፈሳዊ ትግልና ግድያ፤ ፃድቃን የመዓልት ሐሩር የሌሊት ቁር ታግሰው ዳዋ ለብሰው፣ ደንጊያ ተንተርሰው፣ ጨዛ ልሰው ያደረጉት ስግደት ፆም ፀሎት፣ ትሩፋት መልካም ስራ ኹሉ ነው (ደስታ ተክለ ወልድ፣ 1962፣ 236)።

"ትሩፋት"[12] እንዲያመቻቸው አድርገው ይወስናሉ እንጂ ስለ ስርዓታቸውና የውስጥ ደንባቸው ማንንም ላያማክሩ ይችላሉ (የሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ የወንዶች ገዳም መተዳደሪያ ደንብ፣ 1987፣ 3)።

የገዳማውያን የምግብ አይነት ከገዳም ገዳም የሚለያይበት ባህርይ ቢኖረውም በሁሉም ገዳማት ምግቡ ተራ (የጥራት ደረጃው ዝቅተኛ የሆነ) እንደ ገዳማውያኑ አባባል "ለቁመተ ስጋ ያህል" (ነፍስን ለማቆየት ያህል) ነው። በየገዳማቱ የተለመደው ምግብ ከተለያዩ ቅልቅል እህሎች የሚዘጋጅ ንፍሮ፣ ዳቤ፣ ቋርፍ[13] እንዲሁም በተራ ወጥ የሚበላ እንጀራ ነው።

የሐይቅ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ወንድ ገዳማውያን ባላቸው መሬት ከቋሚ አትክልቶች ጎን ለጎን በቆሎ፣ ማሽላና ስንዴ የመሳሰሉ ሰብሎችን እያፈራረቁ ያመርታሉ። የሚያገኙትንም አላባ ባብዛኛው አስፈጭተው ዳቤና እንጀራ የሚመገቡ ሲሆን፣ ንፍሮም የሚበሉበት ወቅት አለ። ንፍሮ የሚቀቅሉት በገዳሙ ያሉ የቆሎ ተማሪዎችን ልማት ሲያሠሩ፣ ለዝክር እና በሰባቱ የጾም ወቅቶች (ዐቢይ ጾም፣ ጾመ ሐዋርያት፣ ጾመ ነቢያት፣ ጾመ ፍልሰታ፣ ጾመ ገሃድ፣ ጾመ ነነዌ እና ጾመ ድኅነት) ውስጥ እሮብና አርብ ነው። የሚዘጋጀውም ከበቆሎ፣ ከስንዴና ከሌሎች ጥራጥሬዎች ቅልቅል ሲሆን፣ ከበቆሎ ብቻ የሚዘጋጅበት ወቅትም አለ። በእናቶች ገዳም ግን አንደኛ ካላቸው መሬት የሚያገኙት ምርት የዓመት ቀለባቸውን ስለማይሸፍን፣ ሁለተኛ እህሉ ቢገኝም ማገዶው ችግር ስለሆነ ንፍሮ የሚያዘጋጁበት ቀን በውል የታወቀ አይደለም። እማሆይ ስነ ማርያምም፣ በእንጨት ችግር የተነሳ ንፍሮውን (የንፍሮውን ፕሮግራም) ወደ ዳቤ እንደለወጡት ይናገራሉ (ካሴት ቁ.3፣ Side B)። ይህ ማለት ግን በፊት ዳቤ አይመገቡም ማለት ሳይሆን ንፍሮ የሚያዘጋጁበትን ወቅት በዳቤ መለወጣቸውን የሚያመለክት ነው።

---

[12] ትሩፋት፡- የበዙ፣ የተረፉ የነፍስ ስራዎች (ደስታ ተክለ ወልድ፣ 1962፣ 236)።

[13] በሪሁን ከበደ፣ በዋልድባ ገዳም የሚኖሩት መነኮሳት ምግባቸው ቋርፍ ይባላል። በፊት ጣብሴ፣ ገመሎና ሳዳ የተባሉ የዛፍ ስሮች በገዳሙ ምግብ ሆነው ይበሉ ነበር። ይሁን እንጂ ገመሎውንና ሳዳውን የዱር አራዊቶች ስለሚሻሟቸው ሙዝ የተባለውን አትክልት በማልማት መመገብ ጀምረዋል (1983፣ 116-117) ይላሉ።

በሁለቱም ገዳማት የሚዘወተሩት ምግቦች ዳቤና እንጀራ ናቸው። ዳቤ ከበቆሎ፣ ከስንዴ፣ ከማሽላና ከመሳሰሉት እህሎች የሚዘጋጅ ሲሆን፤ እንጀራ ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት እህሎች ጋር ጤፍ ተቀላቅሎበት ይዘጋጃል። የዳቤውም ሆነ የእንጀራ ፕሮግራሙን በተመለከተ በገዳማቱ ሰኞ፣ እሮብና አርብ የዳቤ ፕሮግራም ሲሆን፤ ማክሰኞ፣ ሐሙስ፣ ቅዳሜና እሁድ ደግሞ የእንጀራ ፕሮግራም ነው (እማሆይ እህተ ማርያም፣ ካሴት 2፣ Side A)። በዚህ ፕሮግራም መሰረት ምግቡ በየገዳማቸው (የወንድና የሴት) ተግባር ቤት ይዘጋጃል።

የምግብ ሰዓት ሲደርስ ሁሉም ገዳማውያን ከተግባር ቤት ድርሻቸውን በመውሰድ በየበአታቸው ይመገባሉ። ይህን ሀሳብ በማጠናከር አባ አምደ ሥላሴ፣ "የምግብ ደወል ሲደወል ከአበምኔቱ/እመምኔቷ ጀምሮ ሁሉም ገዳማውያን ከተግባር ቤት መቁነናቸውን ወስደው ይመገባሉ"[14] ይላሉ። ይሁን እንጂ በመስክ ምልከታ ወቅት ለአበምኔቱ (እመምኔቷ) የተለየ ምግብ የሚያዘጋጅና ውሃ የሚያቀርብ እንዳላቸው አጥኚው ተመልክቷል። ሌሎቹ መነኰሳት ግን ከተግባር ቤት ድርሻቸውን እየተቆነነ በየበአታቸው ይመገባሉ። "መቁነን በገዳም ለመነኰሳት ወይም ለመናንያን የሚሠጥ ድርሻ ነው" (ሥርግው፣ 1981፣ 62)። ከበአታቸው መውጣት ለማይችሉ ደካማዎችና ህመምተኞች፣ በቋሚ ሥራ ለተሠማሩ አርድእቶች፣[15] በማኅበረ መነኰሳቱ ተፈቅዶላቸው ለዘጉ አባቶች (በአንድነት ገዳም መዝጋት የሚቻለው በማኅበረ መነኮሳቱ ሲፈቀድ ብቻ ነው። አባ ፍቅረ ዮሐንስ፣ ካሴት ቁጥር 7፣ Side B) እና አረጋውያን መቁነናቸው በያሉበት ይሄድላቸዋል።

የመቁነን ሰዓቱ ከሰኞ እስከ አርብ ባሉት ቀናት ከሰባት እና ከዘጠኝ ሰዓት በኋላ ነው። በሰባት ሰዓት የሚመገቡት በሥራ ላይ የተሠማሩ አርድእቶች ሲሆኑ፤ መቆየት ከፈለጉም መቁነናቸውን እቤታቸው ወስደው ማስቀመጥ ይችላሉ። ካህናትና አረጋውያን ደግሞ ከዘጠኝ ሰዓት በኋላ መቁነን ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም አርድእቶች ከሥራ መልስ (ከአሥራ አንድ ሰዓት በኋላ) ይቆነናሉ። አርድእቶች ምሳ የሚሰጣቸው የሚሰሩት የጉልበት ሥራ (እርሻ፣ አትክልት ኩትኮታ፣ ወፍጮ ቤት ወዘተ.) ወይም

---

[14] በመጀመሪያው የመስክ ስራ አባ አምደ ስላሴን በቤታቸው ሳናግራቸው የነገሩኝ ነው።

[15] አርድእት፡- ሰራተኛ፣ ረጅ፣ ገዳሙን በጉልበት የሚረዱ፣ የሚያገለግሉ ማለት ነው (እማሆይ ስነ ማርያም፣ ካሴት ቁ.3፣ Side B)።

ውጣ ውረድ ያለበት በመሆኑ በሥጋ መድከም የተነሳ ሥራው እንዳይታጎል ወይም ሳይሰራ እንዳይቀር ተብሎ ሲሆን፤ በዚህ ሰዓት የሚሰጠው መቁነን አብዛኛውን ጊዜ ዳቤ ነው (አባ ፍቅረ ዮሐንስ ካሴት ቁ. 1፣ Side A)። ለአርድእቶች እራት፣ ለካህናትና አረጋውያን ደግሞ ከዘጠኝ ሰዓት በኋላ የሚቆነነው እንጀራ ነው። ይህ ሁኔታ ሰኞ፣ እሮብና አርብን አያጠቃልልም። ምክንያቱም በነዚህ ቀናት የሚዘጋጀው ዳቤ ብቻ ነው።

ገዳማውያኑ ከቅዳሴ በኋላ (ጠዋት) እህልና ውሃ የሚቀምሱት ቅዳሜ፣ እሁድና ከትንሳኤ በኋላ ባሉት ሃምሳ ቀናት (በበዓለ ሐምሳ) ውስጥ ብቻ ነው። በነዚህ ቀናት ከቅዳሴ በኋላ መቁነን ይታደላል። ይሁንና አርድእቶችም ሥራ በማይሠሩበት የበዓል ቀንና በሕማማት ጊዜ የሚመገቡት (መቁነን የሚሰጣቸው) በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ነው። በቀን ሁለት ጊዜም ሆነ አንድ ጊዜ መመገብን በተመለከተ ፍትሐ ነገሥት የሚከተለውን ይላል።

> የምግብ፣ የመጠጥ፣ የልብስ ልክ እንዲህ ይሁን። ለማኅበሩ ፈጽሞ የምድር አራሾች ቢሆኑ በአንድ ቀን ሁለት ጊዜ መብላት ይገባቸዋል። መጀመሪያ በስድስት ሰዓት፣ ሁለተኛ በአሥራ ሁለት ሰዓት። ገበሬዎች ባይሆኑ ግን አንድ ጊዜ ይበቃቸዋል። በዘጠኝ ሰዓት ወይም በአሥራ ሁለት ሰዓት (1992፣ 114)።

ሁሉም መነኮሳት በተመደበላቸው ጊዜ መቁነናቸውን ከተግባር ቤት ተቀብለው በየበአታቸው ይመገባሉ። ይህ የሆነበት ምክንያት መመገብ በሚፈልጉበት ጊዜ በነጻነት እንዲመገቡ ታስቦ ነው። እማሆይ ስነ ማርያምም “የድርጎ ደወል ሲደወል ሁሉም እንጀራም ሆነ ዳቤ ከነወጡ ወደየቤታቸው ይወስዳሉ። ከዚያ የራበው በልቶ ወደስራው ይሄዳል። የቻለ ደግሞ ከስራ ሲመለስ ማታ ይበላል ይላሉ” (ካሴት ቁ. 3፣ Side B)። ነገር ግን ከሁዳዴ ጾም ፍቺ ጀምሮ እስከ ዳግም ትንሳኤ ድረስ እና በሌሎቹም የጾም መፍቻ ወቅቶች ጠቅላላ መነኮሳቱ የቆሎ ተማሪዎችን ጨምሮ በአንድ አዳራሽ ይመገባሉ። አቀማመጣቸውም ባላቸው የክህነት ደረጃና እድሜ መሠረት ነው። ለምሳሌ አበምኔቱና ሐሬቶች (ሐሬቶች በአባቶች ተመርጠው ገዳሙ የቀለብ፣ የአሰራር፣ የስርዓተ ገዳም፣ የመንፈሳዊ ሂደት፣ ስለ በጀት፣ ስለ ልማት ወዘተ. የሚመክሩ ናቸው። አባ ፍቅረ ዮሐንስ፣ ካሴት ቁ. 1፣ Side A) አንድ ላይ፣ ካህናት በአንድ ረድፍ፣ ምንኩስና ኖሯቸው በአርድእትነት የሚያገለግሉ ለብቻቸው፣ በአመክሮ ላይ ያሉት ለብቻቸው፣ የቆሎ ተማሪዎችም እንዲሁ በተዋረድ ይቀመጣሉ። ይህ ሁኔታ በዓለማውያኑ ዘንድም

ይታያል። በተለይ በፊትና አሁንም ቢሆን በገጠር አካባቢ (በአሁኑ ጊዜ በከተማ አካባቢ ሁሉም ለየብቻው ሰሀን ይዞ ይመገባል።) አዋቂ ወይም ትልቅ ሰው እና ህጻናት አብረው አይመገቡም። እንደውም ለልጆች የሚሰጠው ከትልልቆቹ የተረፈው ላይ የሚበቃቸውን ያህል ተጨምሮ ነው። ይህ ሁኔታ አንድም በጋራ መመገብን ወይም በአንድ ማዕድ መቅረብን በተመለከተ በገዳማውያኑም ሆነ በዓለማውያኑ ዘንድ የተወሰነ ስርዓት መኖሩን ያሳያል። በሌላም በኩል ትንሽ ትልቁን ማክበር እንዳለበት ያመለክታል። በገዳማውያኑ ዘንድ ከአቀማመጣቸው ውጭ የተዘጋጀው ነገር ለሁሉም እኩል ይሰጣል። ማለትም መጠኑም ሆነ አይነቱ ልዩነት አይኖረውም። በዓለማውያኑ ዘንድ ግን ለትልልቆቹ የሚዘጋጀው ወጥ ከትንንሾቹ (ከልጆቹ) የተለየ ሊሆን ይችላል።

ገዳማውያኑ በጋራ በሚመገቡባቸው ቀናቶች እርድ (ሥጋ) ይኖራል። ሥጋው የሚሰራው ከሽሮ ጋር ተቀላቅሎ ነው። በነዚህ ቀናት ጠላም ይኖራል። ከጾም መፍቻ ቀናት ውጭ በምንም ምክንያት ለገዳማውያኑ ሥጋ አይዘጋጅም፤ በአንድነትም አይመገቡም።

በአንድ ላይ የሚመገቡበት ምክንያት የጾም መፍቻ ወቅቶች ከሌሎቹ ወቅቶች ተለይተው የሚከበሩ በመሆናቸው ሁሉም ገዳማውያን ቀኑን በጋራ እንዲያከብሩት ታስቦ ነው። እማሆይ ስነ ማርይምም ገዳማውያኑ የጾም መፍቻ ወቅቶችን በጉጉትና በተለየ ሁኔታ እንደሚያከብሯቸው ገልጸዋል (ካሴት ቁ.4፣ Side A)። አባ ኪዳነ ቃልም፣ በአንድነት ለመመገብ መነሻው ሐዋርያት ናቸው። ቅዱሳን ሐዋርያት ተሰባስበው ማዕዳቸውን እየቆረሱ ለጸሎት ይተጉ ነበር። ማዕዱ እንደ መሰብሰቢያ፣ የአንድነታቸው፣ በህብረት የመጸለያቸው መሰረት ነው። ስለዚህ በህብረት መመገብ ለገዳም አንዱ መሰረት ነው (ካሴት ቁ.8፣ Side B) ይላሉ።

በገዳማቱ ምግብ የሚያዘጋጁት ኋል (ዕኋል)[16] መጋቢዎች ናቸው። አባ ኪዳነ ቃል መነኮሳቱ በተለምዶ "ዕ"ን እየተው ኋል መጋቢ ይላሉ እንጂ ትክክለኛው አጠራር ዕኋል መጋቢ ነው ይላሉ። (ካሴት ቁ.8፣ Side B)። ዕኋል መጋቢዎቹ የሚኖሩት ከተግባር ቤቱ አቅራቢያ በሚሰጣቸው በኣት ሲሆን፤ የምግብ ማብሰያ ፕሮግራማቸውም በሁለት የተከፈለ ነው። ከሰኞ እስከ አርብ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት በኋላ እስከ ጠዋቱ አንድ ሰዓት

---

[16] ዕኋል:- ልጅ፤ ወይፈን፤ ደቦል፤ ጠቦት፤ ጡት የተወ፤ ያደገ፤ ራሱን የቻለ ማለት ነው (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ 1948፣ 683)።

ወይም እስከሚጨርሱ ድረስ ሲሆን፤ ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በበዓለ ሃምሳ ቀናት ደግሞ ከምሽቱ ስድስት ሰዓት እስከ ጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ነው (አባ ሀብተ ስላሴ፣ ካሴት ቁ.3፣ Side A)። በስድስት ሰዓት መጀመር ያስፈለገው ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም ከትንሳኤ በኋላ ባሉ ሃምሳ ቀናት ከቅዳሴ በኋላ መነኰሳቱ መመገብ ስለሚችሉ መቁነኑ አስቀድሞ መዘጋጀት ስላለበት ነው። በሌላዎቹ ቀናት መቁነን የሚሰጠው በሰባትና በዘጠኝ ሰዓት ስለሆነ ሌሊት ከስምንት ሰዓት በኋላ ቢጀምሩ ይደርሳል ተብሎ ይታመናል። ይሁን እንጂ መቁነን ሶስት ሰዓት በሚሰጥበት ጊዜ የሚቆነነው በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ነው። የቆሎ ተማሪዎች ከጾም መፍቻ ቀናት ውጪ ከገዳሙ መቁነን አያገኙም። ምክንያቱም ትምህታቸውን ሲጨርሱ ወደመጡበት ስለሚመለሱ በገዳሙ የአንድነት ማህበር ውስጥ እንደ ገዳማውያን አይቆጠሩም።

ኅል (ዕኅል) መጋቢዎቹ መጋቢው የሚሰጣቸውን ዱቄትም ሆነ ጥራጥሬ ተጠቅመው በገዳማውያኑ መጠን የእለት ምግብ ያበስላሉ።። ለምሳሌ በወንዶች ገዳም ሰማንያ አምስት ያህል ገዳማውያን አሉ። ለእነዚህ ገዳማውያን መጋቢው ለእንጀራ እና ለዳቤ የሚሆን እህል አስፈጭተው ያቀርቡላቸዋል። ኅል (ዕኅል) መጋቢዎቹ ደግሞ ገዳማውያኑን ሊያዳርስ በሚችል ሁኔታ በቁና እየለኩ ያወጣሉ። ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ በገዳም እንግዳ ስለማይጠፋ በአባላቱ ልክ ብቻ ዳቤም ሆነ እንጀራ አይዘጋጅም። ይህን በተመለከተ አባ ሀብተ ስላሴ "መጋቢው በማህበሩ ውስጥ ያለውን ቁጥር እለት በእለት ይነግሩናል። እኛ ደግሞ እንግዳ ማስተናገጃ ብለን 10 ወይም 15 ያህል ትርፍ ጨምረን እናዘጋጃለን" (ካሴት ቁ.3፣ Side A) ይላሉ። ለዳቤ የሚወጣው ዱቄት ያለ እርሾ ለ 24 ሰዓት ይቦካና ይጋገራል። እንጀራ ደግሞ ተቦክቶ ሶስት ቀን ከቆየ በሁዋላ አብሲት ወይም የፈላ ውሃ ይደረግበታል። አብሲቱ ከቀዘቀዘ በኋላም ይጋገራል (ዝኒ ከማሁ)። ቡኮው ሶስት ቀን ስለመቆየቱም ሆነ ያለ እርሾ ስለመቦካቱ ጋጋሪዎቹ የሚሰጡት ምክንያት የለም። በተለምዶ የሚደረግ ስለሆነ ያንኑ ተከትለው ይኳሃሉ። ዳቤ ዘወትር በሥራ ቀን ከአስር በላይ እንጀራ ደግሞ ከዘጠና በላይ ይጋገራል። ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በበዓል ቀናት አርድእቶች በቀን አንድ ጊዜ ስለሚቆነኑ መጠኑ ሊቀንስ ይችላል።

ኅል (ዕኅል) መጋቢዎቹ ከበኣታቸው ወደ ተግባር ቤት ለማባሰል ሲገቡ ጸሎት እያደረጉ ነው። ገብተውም በተግባር ቤቱ ባለው የአቡነ ተክለ ሃይማኖት መደገፊያ (አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዚህ ገዳም ተግባር ቤት ምግብ ያበስሉ ነበር ተብሎ

ይታመናል) እንደሆነ በሚታመነው እንጨት ፊት ለፊት ቆመው ይሳለሙና አንድ ጊዜ አቡነ ዘበሰማያት ብለው ሶስት ጊዜ ይሰግዳሉ። ከዚያ ወደ መጋገሪያው ቀርበው 12 አቡነ ዘበሰማያትና 9 ሰላም ለኪ ካደረሱ በኋላ መጋገር ይጀምራሉ። ስግደቱም ሆነ መሳለሙ የሚዘጋጀው ምግብ በረከት ይኖረዋል፤ አብሳዮቹም የጻድቁን ብርታት ያገኛሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው። በተግባር ቤቱ በተስፋ ድርጅት አማካይነት ሦስት ምጣድ የሚይዝ ዘመናዊ ምድጃ ተሰርቶላቸዋል። ከሁለቱ ጋጋሪዎች አንዱ በውጭ ሆኖ እንጨት እየቆሰቆሰ ምጣዱን ያሰማል። ምጣዱ ከምድጃው ላይ የማይነሳ ሲሆን፤ በአንድ ጊዜ ሁለት ምጣድ ይጠቀማሉ። ሦስተኛው ምድጃ የወጥና ንፍሮ ማብሰያ ነው። እንደ ኅል መጋቢዎቹ እምነት ሦስት ምድጃ መሆኑ "የሥላሴን ሦስትነት፣ በአንድ ተግባር ቤት መሆኑ ደግሞ አንድነታቸውን ያሳያል" (አባ ሀብተ ስላሴ፣ ካሴት ቁ.3፣ Side A) ይላሉ።

ምግብ በዚህ መልኩ ከተባሰለ በኋላ ተግባር ቤቱ በካህናት ይታጠናል። ከዚያ የምግብ ሰዓት ሲደርስ ደወል ይደወላል። መጋቢው ወይም ኅል መጋቢዎቹ በተግባር ቤቱ መስኮት በኩል ለሚመጡ ገዳማውያን መቁነኑን ያድላሉ። ገዳማውያኑም መቁነናቸውን ተቀብለው "ቤተ እግዚአብሔርን ያስፋልን" በማለት አመስግነው ይሄዳሉ። በጋራ በሚበላበት ጊዜ ደግሞ የምግብ ደወል ሲደወል ገዳማውያኑ በአንድ አዳራሽ ይሰባሰባሉ። ኅል መጋቢዎቹ ከተግባር ቤት እንጀራም ሆነ ዳቤ ያለውን ወስደው በተቀመጡበት በትሪ ያቀርባሉ። ከዚያ ወጥ ካለ እየተደረገላቸው በአንድነት ይመገባሉ። ጠላም አንድ አንድ ኩባያ ይሰጣቸዋል። ጠላ በጾም መፍቻ ቀናት እንዲሁም በክብረ በዓላት ለዝክር ካልሆነ በቀር ዘወትር አይጠመቅም። በአንድነት ሲመገቡ ከመነኮሳቱ ችሎታ ያላቸው በየተራ እየተነሱ ዜና አበውንና መጽሐፈ መነኮሳትን፣ እንዲሁም ሌሎች መጻህፍት በንባብ ያሰማሉ።

የገዳሙ መተዳደሪያ ደንብ፣ የምግብ ደወል ሲደወል ከአበምኔቱ ጀምሮ ሁሉም ገዳማውያን በአንድ አዳራሽ ተሰብስበው እንደሚመገቡ ይገልጻል (1987፣ 12)። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ገዳማውያኑ ከጾም መፍቻ ወቅቶች ውጭ በጋራ አይመገቡም። ስለዚህ ሁሉም መቁነናቸውን ወደየቤታቸው ወስደው በሚፈልጉት ሰዓት፣ የሚፈልጉትን ያህል ይመገባሉ። አንዳንዶቹ የተሰጣቸውን ጨርሰው ሊመገቡ ይችላሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ለሚሰሩት ትሩፋት ይመቻቸው ዘንድ ስጋቸውን ቀጥተው ከተሰጣቸው ግማሹን ሊመገቡ ይችላሉ (አባ ኪዳነ ቃል፣ ካሴት ቁ.8፣ Side B)።

በገዳማቱ ተግባር ቤቶች በየቀኑ ከሚነደው እንጨት የሚገኘው አመድ "እምነት" ነው ስለሚባል አይደፋም። ስለሆነም የተግባር ቤት ሰራተኞች ምድጃው ሲሞላባቸው አመዱን በማዳበሪያ እያደረጉ ያስቀምጡታል። አመዱ ሲዛቅ ቁርጥራጭ እንጨቶችና ከሰል መሳይ ጉማጆች ተለቅመው ወደ እርሻ ይጣላሉ። ከገዳማቱ የሚገኘው አመድ በተለይ በወንዶቹ ተግባር ቤት አቡነ ተክለ ሃይማኖት አገልግለውበታል ስለሚባል ለገዳማውያኑ፣ ለጉብኝት ለሚመጡ አማኞች (በተለይ ከአዲስ አበባና ከሌላ ቦታ ለግሸን ደብረ ከርቤ ክብረ በዓል ለሚመጡ እንግዶች) እና በገዳማቱ የሚከበሩ ክብረ በዓላትን ለማክበር ለሚመጡ ምእመናን ትንሽ ትንሽ እየተቆነጠረ ይሰጣል። በገዳሙ ለፀበል የሚመጡ ፀበልተኞችም ከ"ተፀበሉ" በኋላ ስለሚቀቡትና አንዳንዱም በጥብጠው ስለሚጠጡት አገልግሎቱ ብዙ ነው።

## 4.2 የገዳማውያኑ አለባበስ

ይህ ርዕስ በሁለት ንዑሳን ርዕሶች የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ርዕስ ገዳማውያኑ በሚለብሷቸው ልብሶች (ቀሚስ) አይነትና አሰፋፍ ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ሁለተኛው ርዕስ ደግሞ ገዳማውያኑ በራሳቸው ላይ በሚያደርጉት ቆብ አይነትና አሰፋፍ ላይ ያተኩራል።

### 4.2.1 ቀሚስ

ገዳማውያን በአለባበሳቸው ከዓለማውያን ሰዎች ይለያሉ። አለባበሳቸው እርቃናቸውን ለመሸፈን እንጂ ለጌጥ አይደለም። የገዳማውያን ልብስ (ሴትም ትሁን ወንድ) ቀሚስ ነው። የሴቶቹ ቀሚስ ወገባቸው ላይ ጠበብ ያለ ሲሆን፤ የወንዶቹ ግን ወጥ ወይም ልቅ ነው። በገዳም የሚኖሩ መናንያን ከዓለማውያኑ የሚለዩት በልብሳቸው መናኛነት ነው። አባ ፍቅረ ዮሐንስም "መነኮሳት በማዕዳቸው መቅለልና በልብሳቸው አዳፋነት ወይም ቀላልነት፣ መታወቅ አለባቸው። መነኮሳት ከዓለም መለየታቸው የሚታወቀው በአለባበሳቸውና በአመጋገባቸው ነው" (ካሴት ቁ.8፣ Side A) ይላሉ።

የገዳማውያን ልብስ (ቀሚስ) ጥቁር፣ ቢጫ እና ወይባ ወይም አፈር የተነከረ ነው። ይሁን እንጂ አሁን አሁን ወይባ ወይም አፈር ያልተነከሩ ልብሶችን መልበስ

እየተለመደ ነው። ለዚህም ምክንያቱ በገዳም የሚለበሱ የልብስ አይነቶች (ወይባ ወይም አፈር የተነከሩ የሚመስሉ) በገበያ ስለሚገኙ ነው። ነገር ግን አፈር ወይም ወይባ የመንከሩ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ቀርቷል ማለት አይቻልም። በመስክ በነበርኩበት ጊዜ በአበምኔቱ የተመደቡልኝ የሙዚየም አስጎብኝ አባ ፍቅረ ማርያም አዲስ ወይባ የገባ ቀሚስ ለብሰው ተመልክቻለሁ።

በገዳም የተለያየ ቀለም (ዥንጉርጉር ወይም ከአንድ በላይ ቀለም) ያለው ቀሚስ መልበስ አይፈቀድም። የቀለሙ መመሳሰል ያስፈለገውም በከተማ ዘመድ ያላቸው መነኰሳትና መነኮሳይያት ዘመዶቻቸው የተለያዩ ልብሶች ሊሰጧቸው ስለሚችሉ በገዳማውያኑ ዘንድ የልብስ መለያየት እንዳይኖር ነው። ምክንያቱም "በአንድነት ገዳም ውስጥ ምንም አይነት የግል ንብረት ይዞታ አይፈቀድም" (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ፣ 1997፣ 23)። ስለሆነም በአንድነት ገዳም ውስጥ እየኖሩ ከማህበሩ የተለየ ልብስ ወይም ቀሚስ መልበስም የተከለከለ ነው። "ከዓለም የተለዩ መነኮሳት ልብሳቸው አንድ አይነት መሆን አለበት" (አባ ፍቅረ ዮሐንስ፣ ካሴት ቁ.8፣ Side A)።

ይሁን እንጂ የመነኮሱና በአመክሮ ላይ ያሉ ገዳማውያን አለባበስ የተለያየ ነው። መነኰሳቱ ረጅምና እጀ ሰፊ ቀሚስ ይለብሳሉ። በአመክሮ ላይ ያሉ ገዳማውያን ደግሞ ከጉልበታቸው ዝቅ የሚል ቀሚስ እንዲለብሱ ይደረጋል። የሁሉም አለባበስ ሰውነትን የማያስገምትና ባትን የማያሳይ ነው።

በአመክሮ ላይ ያሉ ገዳማውያን ከጉልበታቸው ዝቅ የሚል ቀሚስ እንዲለብሱ የሚደረገው ከመመንኮሳቸው በፊት ቀሚሱን ማለትም የገዳሙን የአለባበስ ሁኔታ እንዲለምዱት ለማድረግ ነው። የአመክሮ ጊዜ የገዳሙን ኑሮ (ስራውን፣ ጾሙን፣ ጸሎቱን፣ ውጣ ውረዱን ወዘተ.) የመለማመጃ ወቅት እንደሆነ ሁሉ በዚህ ጊዜ የሚለብሱት ቀሚስም የምንኩስና ልብሱን ለመለማመድ ይረዳቸዋል ተብሎ ይታመናል (አባ ገብረ ስላሴ በላይ፣ ካሴት ቁ.6፣ Side A)። በዚህ ጊዜ ቀሚሱም ይሁን በአጠቃላይ የገዳም ኑሮ ካልጣማቸው ወደመጡበት ሊመለሱ ይችላሉ። ነገር ግን የአመክሮ ጊዜውን በጽናት አልፈው ለመነኮሳት የሚፈቀደውን ቀሚስ ከለበሱ በኋላ ወደመጡበት አይመለሱም ተብሎ ይታመናል።

የገዳማውያን ቀሚስ ከገዳሙ ለሁሉም አባላት በዓመት አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ የሚቆነን ነው። በገዳማት ብዙውን ጊዜ የሚቆነነው የጨርቅ አይነት አቡጀዲ ወይም ካኪ መሳይ ጨርቅ ነው። አቡጀዲው ነጭ ስለሆነ ወይባ ወይም አፈር ይነክሩታል።

ወይባ የመነከሩ ምስጢርም ብዙውን ጊዜ ነጭ የሚለበሰው ለደስታ፣ ለድሎትና ለመሳሰሉት ሁነቶች ነው። የገዳም ህይወት ደግሞ እነዚህን መሰል ሁኔታዎችን ንቆ የሚኖሩበት ዓለም ስለሆነ ነጭ ልብስ አይለበስም።

በአጠቃላይ ገዳማውያን መነኮሳትና መነኮሳይያት፣ ዥጉርጉር፣ ቀይ፣ ነጭ፣ የሚያብለጨልጭ ወይም የተለያየ ቀለም ያለው ልብስ አይለብሱም። አሰፋፉም ወጥ እና ሰፋ ያለ ነው። የቀለሙ ቢጫ፣ አፈር ወይም ወይባ የተነከረ መሆንም ተምሳሌታዊ ነው። ቢጫው ሰላማውያን ነን ማለት ሲሆን፣ ወይባ ወይም አፈር የተነከረው ደግሞ በዓለም ከሚኖረው ህዝብ በታች ነን፣ የተናቅን ነን፣ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ራሳችንን ጥለን እንኖራለን ሲሉ የሚለብሱት ነው። ጥቁሩ ደግሞ ዓለማውያን ለሐዘን እንደሚለብሱት ሁሉ መነኰሳትም በዓለሙ ኃጢያት አዝኛለሁ፣ በሐንዘም እኖራለሁ ሲሉ ይለብሱታል። አባ ኪዳነ ቃል፣ መነኮሳት ቢጫ መልበሳቸው ምድራዊውን ሳይሆን ሰማያዊውን ህይወት መሻታቸውን፣ ከምናየው ዓለም ይልቅ የማናየውን፣ የማናውቀውን ዓለም በተስፋ መጠበቃቸውን ያመለክታል። በተጨማሪም የልብሱ ቀሚስ መሆን ኢየሱስ በምድር ሲኖር ከእድሜው ጋር አብራ የምትረዝም (የምታድግ) ቀሚስ ይለብስ ነበር ስለሚባል ገዳማውያንም ከዚህ በመነሳት ቀሚስ ይለብሳሉ (ካሴት ቁ.8፣ Side B) ይላሉ።

በሐይቅ ገዳም አበምኔቱ ከማህበረ መነኮሳቱ ለየት ያለ ልብስ እንዲለብሱ፣ ካባና መጎናጸፊያ ኢንዲኖራቸው ይደረጋል። ቤተ ደናግሉም እመምኔቷ ከሌሎቹ ለየት ያለ መጎናጸፊያና ሹራብ እንዲለብሱ ያደርጋል። ይህም ለክብራቸው ሲባልና ከብዙ ዓለማውያን ጋር ገዳሙን በሚመለከቱ ጉዳዮች ስለሚገናኙ በዓለማውያኑ ዘንድ ከበሬታ እንዲያገኙ ታስቦ የሚደረግ ይመስለኛል። የሐይቅ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም መተዳደሪያ ደንብም "አበምኔቱ ስለገዳሙ ክብር ሲባል በገዳሙ ወጭ የተለየ የክብር ልብስ እንዲኖረው ይደረጋል። ልብሱ የክብር እንደመሆኑ መጠን ሹመቱን ተከትሎ ከመምህር ወደመምህር የሚተላለፍ ይሆናል" (1987፣ 6) ይላል።

የገዳሙ ካህናት በቅዳሴ ወቅት ዘወትር የሚለብሱትን ቀሚስ ለብሰው የቅዳሴ ስርዓት አያከናውኑም። ካህናቱ በገዳሙ ለቅዳሴ ስርዓት ማከናወኛ ተብሎ የተዘጋጀውን ነጣ ያለ የክህነት ልብስ ይለብሳሉ። ይህም ለካህናቱ በግል የሚቆነን ሳይሆን "ልብሰ ተክህኖ" ተብሎ በቤተ ክርስቲያን የሚቀመጥ ነው። ፍትሐ ነገስትም የቅዳሴ አልባሳትን በተመለከተ የሚከተለውን አስፍሯል።

ለካህናት እንደሚገባ የሚቀድሱባቸው የቅዳሴ ልብሶች ነጫጭ ይሁኑ፤ ኅቦንጉርጉር አይደለም። ጌታችንም በተገለጠ ጊዜ ልብሱ እንደ ብርሃን ነጭ ሆኖ መላእክትም ስለ ደስታ በዚህ ቀለም መልክ ለሰው ታዩ። ይኸውም ልብስ የእስራኤል ልጆች ወደ እርሱ ይመጡ ዘንድ እግዚአብሔር በተናገራቸው ጊዜ ያዘዛቸው ነው (1992፣ 135)።

በሐይቅ ገዳም ካህናት ተብለው የቅዳሴ ስርዓት ማከናወን የሚችሉት ድንግልና የክህነት ስልጣን ያላቸው መነኮሳት ብቻ ናቸው (አባ ወልደ ጊዮርጊስ ገብረ መስቀል፤ ካሴት ቁ.4፣ Side B)። የዲያቆናቱን ሥራ የሚሸፍኑት ከነዚሁ ካህናት መካከል በየተራ የሚመደቡ ደናግል መነኮሳት ናቸው። ካህናቱ በቅዳሴ ወቅት ነጭ መልበሳቸው በንጽህናና በድንግልና ሆነው እግዚአብሔርን የማገልገላቸው ምሳሌ ነው። በሌላም በኩል ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ በደብረ ታቦር ተራራ ላይ በተገለጠላቸው ጊዜ የሚያብረቀርቅ ነጭ ልብስ ለብሶ ነበር ስለሚባል ይህን ለመመሰል በቅዳሴ ጊዜ ነጭ ይለብሳሉ። በተጨማሪም ነጭ ልብስ ሰማያዊ ክብርን የሚያሳይ መሆኑን አባ ፍቅረ ዮሐንስ (ካሴት ቁ.8፣ Side A) ይገልጻሉ።

### 4.2.2 ቆብ

መናንያን ገዳም ሲገቡ በዓለም ሲኖሩ ይለብሱት የነበረውን አውልቀው (ትተው) ገዳሙ የሚያዘጋጀውን ቀሚስ እንደሚለብሱ ሁሉ በራሳቸው ላይም በገዳሙ የሚታዘዘውን ቆብ ያደርጋሉ። የመነኮሱና በአመክሮ ላይ ያሉ ገዳማውያን አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ቆብ አያደርጉም። ስለሆነም ምንኩስና ያላቸው ገዳማውያን የጨርቅ፣ በአመክሮ ላይ ያሉት ደግሞ የክር ቆብ ያደርጋሉ። ከጨርቅ የሚዘጋጀው ቆብም መሐሉ ላይ በክብ ቅርጽ ትንሽ ሽንሽን ያለውና ድፍን ነው። እንደጨርቁ መስያየት ሁሉ የአመክሮ ቆብ ሽንሽን የለውም፤ መሐሉም ድፍን ሳይሆን በትንሹ ክፍተት ያለው ነው።

የአመክሮ ቆብ መሐሉ ክፍት መሆኑ ገና በሙከራ፣ በልምምድ ወይም በፈተና ላይ ያሉ መሆናቸውን አመላካች ነው። በአመክሮ ወቅት የሚለብሱት ቀሚስ የገዳሙን ህይወት መለማመጃ እንደሆነ ሁሉ የአመክሮ ቆቡም የገዳሙን ህይወት መለማመጃ ነው። በዓለም ያሉ ሰዎችን ለምሳሌ በገጠር አካባቢ ያሉ ሴቶችን ብናይ በልጅነታቸው ከፊት ለፊታቸው ያለው ጸጉራቸው ሲቀር ሌላውን ይላጩታል። ከፍ ሲሉ ደግሞ

ከመሀል ላይ ያለውን አስቀርተው ዙሪያውን ይላጫሉ። ሲታጩ ወይም ሲያገቡ ደግሞ ሙሉውን ተላጭተው እንዲያድግ ያደርጋሉ። ይህ ሁኔታ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ቢለያይም የማህበረሰቡ መገለጫ በሆነባቸው አካባቢዎች የተለመደ ነው። ህጻናት ወይም ያላገቡ ሴቶች ሙሉ ጸጉራቸውን እንደማያሳድጉ ሁሉ የገዳም መናንያንም ገዳም ስለገቡ ብቻ የጨርቅ ቆብ አያደርጉም። የዓለማውያኑ የጸጉር አሰራር እድሜንና ጋብቻን መሰረት ያደረገ እንደሆነ ሁሉ የገዳማውያኑ ቆብም የአመክሮ ጊዜን መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ነው።

የክር ቆብ አድርጎ የአመክሮ ጊዜውን ያጠናቀቀ መናኝ የምንኩስና ህይወቱንም በገድልና ትሩፋት መምራት ይችላል ተብሎ ይታመናል። አባ ወልደ ኢየሱስ ወልደ ሚካኤልም፣ የክር ቆብ ያለው መናኝ ቢከፋው ወይም የገዳሙ ኑሮ ባይመቸው ወደመጣበት ተመልሶ ሊሄድ ይችላል። የአመክሮ ጊዜውን ጨርሶ የጨርቅ ቆብ ያደረገ መናኝ ግን የትም ሊሄድ አይችልም ተብሎ እንደሚታመን ይገልጻሉ (ካሴት ቁ.4፣ Side B)። ምክንያቱም ገዳማውያኑ፣ በአመክሮ ጊዜው በገዳም ያሉትን አስቸጋሪ ሁኔታዎችና ፈተናዎች በሙሉ ተቋቁሞ የተወጣ መናኝ በምንኩስና ጊዜው ይበልጥ ለቱርፋትና ገድል ይዘጋጃል እንጂ ወደመጣበት ተመልሶ አይሄድም የሚል አመለካከት አላቸው።

አንዳንድ መነኮሳትም ለሥራ እንዲያመች በማለት የክር ቆብ ሊለብሱ ይችላሉ። ይሁን እንጂ እንደ አመክሮዎቹ መሐሉን ክፍት አያደርጉትም። የገዳማውያን ቆብ ከገዳሙ የሚቆነንና በቀለም ከቀሚሳቸው ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ በአሰፋፉ (ክፍት ወይም ድፍን መሆን) እና በአይነቱ (የጨርቅ ወይም የክር መሆን) የተለያየ ነው።

ገዳማውያን በራሳቸው ላይ የሚያደርጉት ቆብ የአክሊለ ሶክ (የእሾህ አክሊል) ምሳሌ ነው። የቆቡ መሸንሸንም በማቴዎስ ወንጌል "የእሾክ አክሊልም ጎንጉነው በራሱ ላይ ደፉበት፤ በቀኝ እጁም መቃ አስያዙት ..." (ማቴ. 27፣ 29)፤ እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል "ወታደሮቹም የእሾክ አክሊል ጎንጉነው በኢየሱስ ራስ ላይ አደረጉ ..." (ዮሐ.19፥ 2) እንዳለው ኢየሱስ ሲሰቀል አይሁዳውያን የሾኽ አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ ደፍተውበት ነበር። ስለሆነም የቆቡ መሸንሸን የእሾኽ አክሊሉን መጎንጎን መመሰያ ነው። በገዳሙ የክህነት አገልግሎት የሚሰጡ ካህናት ሲመነኩሱ በራሳቸው ላይ የሚደረግላቸው ቆብ ሁል ጊዜ የማይወልቅ ቢሆንም በቅዳሴ ጊዜ ግን ገዳሙ ለመቀደሻ ያዘጋጀውን ቆብ ይጠቀማሉ።

## 4.3 ገዳማውያኑ በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸው ቁሶችና ግንዘት

በዚህ ርዕስ መነኮሳቱ በሰውነታቸው ላይ (ከልብሳቸው ውስጥና ከልብሳቸው ላይ) የሚያደርጓቸውን ቁሶችና ሲያርፉም የሚደረግላቸው የግንዘት ሁኔታ ይዳሰሳል።

### 4.3.1 ገዳማውያኑ በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸው ቁሶች

በዚህ ክፍል መነኰሳትና መነኰሳይያት ከቀሚሳቸው ውስጥ (በሰውነታቸው ላይ) እና ከቀሚሳቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ቁሶች እንመለከታለን። ገዳማውያኑ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሸከመውን መስቀል በአንገታቸው፣ የተገረፈበትና የተጎተተበት ገመድ አምሳል የሆነውን ጠፍር ወይም ሰንሰለት በወገባቸውና በአንገታቸው እንዲሁም የጸሎት ማድረሻ መቁጠሪያቸውን ወዘተ. በአንገታቸው ወይም በእጃቸው ላይ ያደርጋሉ። ቀጥሎ እነዚህን ቁሶችና ተምሳሌታዊነታቸውን፣ እንዲሁም በነዚህ ቁሶች አማካይነት እንደተፈጸሙ የሚታመንባቸውን አፈ ታሪኮችን እናያለን።

#### 4.3.1.1 ቅናተ ዮሐንስና ስጋ ማርያም

ገዳማውያኑ ምንኩስና ሲቀበሉ ከአመክሮ ቆብና ቀሚስ የተለየ ቆብና ቀሚስ እንደሚሰጣቸው ሁሉ በዚህ ወቅት ስጋ ማርያም እና ቅናተ ዮሐንስ የሚባሉ ቁሶች ይሰጣቸዋል። አባ ገብረ ስላሴ በላይም፣ ቅናተ ዮሐንስና *ሥጋ* ማርያም ከሦስት ክር ተፈትለው የሚዘጋጅና በምንኩስና ወቅት ለመንኲሹ ወይም ለመንኲሿ የሚሰጡ መሆናቸውን ጠቅሰዋል (ካሴት ቁ.7 Side A)። *ሥጋ* ማርያም ገዳማውያኑ እንደ ማተብ በአንገታቸው ላይ የሚያደርጉትና እስከ ደረታቸው አካባቢ የሚደርስ ነው። ቅናተ ዮሐንስ ደግሞ ከስጋ ማርያም የሚረዝም ሲሆን፤ በአንገታቸው ገብቶ እስከ ወገባቸው የሚደርስና እንደ ዝናር ወይም መታጠቂያ የሚጠመጠም ክር ነው። ሁለቱም ከልብስ ውስጥ የሚደረጉ ቁሶች ናቸው።

በአንገታቸው ላይ የሚደረገው *ሥጋ* ማርያም ምሳሌነቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ከነፍሷ ነፍስ፣ ከስጋዋ ስጋ ነስቶ መወለዱን ማመልከቻ ነው።

በወገባቸው ላይ የሚታሰረው ቅናተ ዮሐንስ ደግሞ መጥምቁ ዮሐንስ ጥርጊያውን አቅኑ፤ ንስሐ ግቡ ሲል ይታጠቀው የነበረው ጠፍር ምሳሌ ነው (አባ ፍቅረ ዮሐንስ፣ ካሴት ቁ. 8፣ Side A)።

አንዳንድ መነኮሳት መከራና ስቃይን ለማብዛት ሲሉ ክሩን በሰንሰለት ወይም በጠፍር ይቀይሩታል። ሰንሰለቱ በሙቀት ጊዜ ይሞቃል፤ አየሩ ሲቀዘቅዝ ደግሞ ይቀዘቅዛል። ይህ ደግሞ መነኮሳቱ ምቾት እንዳይሰማቸው ስለሚያደርጋቸው ሁል ጊዜ ለጸሎት ትጉ እንዲሆኑ ያስችላል። ጠፍሩም ቢሆን በሰውነታቸው ላይ ለረጅም ጊዜ ሲቆይ በላብ አማካይነት ስለሚቆረፍድና ስለሚደርቅ ድሎት ይነሳል። በመሆኑም ዘወትር ፈጣሪን ብቻ እያሰቡ ለመኖር ያስችላል ብለው ያምናሉ። ይህም የገዳም ኑሮ ድሎት ያለበትና እንቅልፍ የሚወደድበት አለመሆኑንም ያመለክታል።

ሲመነኩሱ የሚሰጣቸውን የተገመደ ክር በሰንሰለት ወይም በጠፍር መቀየራቸው ሰውነትን ለማድከም ይረዳል ከማለት ውጪ ሰንሰለትም ሆነ ጠፍር ስለመጠቀማቸው ገዳማውያኑ የሚሰጡት ምክንያት የለም። እንደውም አንዳንዶቹ "በገዳሙ ያሉ አረጋውያን አባቶች አድርገው ስላየሁ እኔም የእነሱን አርኣያ በመከተል ሰንሰለት ወይም ጠፍር አድጌያለሁ ይላሉ።" የሰንሰለቱ መጠንም ተመሳሳይና እኩል አይደለም። አንዳንዶቹ ወፍራምና ረዥም ሰንሰለት የሚያደርጉ ሲሆን፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ቀጠን ያለ ሰንሰለት እንደሚያደርጉ ተመልክቻለሁ። ለምሳሌ የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ስራ አስኪያጅ የሆኑት አባ ገብረ ስላሴ በላይ በጣም ቀጠን ያለና ከመዳብ የተሰራ ሰንሰለት ማድረጋቸውን አሳይተውኛል።

ገዳማውያኑ አብዛኛውን ጊዜ በአንገታቸው ላይ የሚያደርጉት ሰንሰለት ሲሆን፤ በወገባቸው ላይ ደግሞ ጠፍር ወይም ሰንሰለት ያደርጋሉ። ይሁንና የሚያደርጉት ሰንሰለትም ሆነ ጠፍር በተለይ በአንገታቸው ላይ ያለው እንዳይታይ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። ይህ ደግሞ የገዳማውያን ህይወት የታይታ አለመሆኑንና ትህትናቸውን ያመለክታል። በአመክሮ ላይ ያሉ ገዳማውያን ሥጋ ማርያምና ቅናተ ዮሐንስ ባይሰጣቸውም ራሳቸውን ለማድከምና የኢየሱስን መከራና ስቃይ ለማሰብ ሲሉ ሰንሰለት ወይም ጠፍር በወገባቸው ላይ ያደርጋሉ። በወገባቸው ላይ የሚያደርጉት ሰንሰለትም ሆነ ጠፍር እንደ ቅናተ ዮሐንስ አይቆጠርም። ምክንያቱም እነዚህ ቁሶች የአመክሮ ጊዜያቸውን ለጨረሱ ገዳማውያን ብቻ የሚሰጡ ናቸው። ይህንን ቁስ ለምን አደረጋችሁ

ተብለው አይወቀሱም ወይም አይቀጡም፡፡ ነገር ግን እንደመነኮሳት በአንገታቸው ላይ ማድረግ እንደማይችሉ አባ ገብረ ስላሴ በላይ ገልጸዋል (ካሴት ቁ.7፣ Side A)፡፡

አንዳንድ መነኮሳት ሰውነታቸውን ለማድከምና ምቾት እንዳይኖረው ለማድረግ የተለያዩ የስቃይ መሳሪያዎችን (ቁሶችን) ለምሳሌ በቆባቸው ውስጥ እሾህ፣ በመታጠቂያቸው ላይ ደግሞ እንደመጋዝ ጥርስ ያላቸው ብረቶችን ያደርጋሉ፡፡ አባ ሀብተ ስላሴ መነኮሳቱ እነዚህን ቁሶች በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጉ ከሆነ የተጋድሎና የትሩፋት ፍቅር ያላቸው መሆኑን ያመለክታል ይላሉ (ካሴት ቁ.3፣ Side A)፡፡

### 4.3.1.2 አስኬማ

አስኬማ[17] ገዳማውያኑ ለምንኩስና ደረጃ ሲበቁ ከሚሰጣቸው ቀሚስ፣ ቆብ፣ ቅናተ ዮሐንስና ስጋ ማርያም በኋላ የሚሰጥ ቁስ ነው፡፡ ይህ ቁስ እንደ ቅናተ ዮሐንስና ስጋ ማርያም ከልብስ ስር የሚደረግ ነው፡፡ አስኬማ የሚሰጣቸው (ማድረግ የሚችሉት) ገዳማውያን በገዳማውያኑ አባባል "የበቁና ፍጹማን" እንደሆኑ የሚታመንባቸው መነኮሳት ናቸው፡፡ ስለሆነም ገዳማውያኑ የአመክሮ ጊዜያቸውን ጨርሰው በገዳሙ አባቶች እንዲመነኩሱ ሲፈቅድላቸው የሚመነኩሱ ቢሆንም በዚህ ጊዜ አስኬማ አይሰጣቸውም፡፡ አስኬማ የሚሰጠው ከምንኩስና በኋላ መነኮሳቱ በሚፈጽሙት ትሩፋትና ገድል፣ በገዳማዊ እንቅስቃሴያቸው ብቃትና ፍጹምነት ወዘተ. በገዳማውያኑ ተገምግመው ከበአታቸው ሳይወጡ በጸሎትና ስግደት ተወስነው መኖር የሚችሉ መሆናቸው ሲታመን ነው፡፡ ለዚህ ደረጃ የሚመጥኑ መነኮሳትን የሚመርጡትም የገዳሙ አባቶች ናቸው፡፡ አስኬማ የተሰጣቸው መነኮሳት ከበአታቸው ሳይወጡ በፀሎትና ስግደት ተወስነው ቀሪ ህይወታቸውን ያሳልፋሉ፡፡ አባ ፍቅረ ዮሐንስም አስኬማ ያደረገ መነኩሴ ከገዳሙ ሳይወጣ በገድል እንደሚኖር ጠቅሰዋል (ካሴት ቁ.8፣ Side A)፡፡ ኪ.ዳነ ወልድ ክፍሌም፣ "ካስኬማ በኋላ ባህታዊ መሆን፣ መዝጋት፣ አጽንኦ በአት ነው እንጂ ከገዳም መውጣት፣ ወዳለም መግባት ክልክል ነው" (1948፣ 109) ይላሉ፡፡

---

[17] አስኬማ፡- በቁሙ ልብሰ ምንኩስና፤ ከቀሚስ፣ ከቅናት፣ ከቆብ በኋላ በመጨረሻ የሚለበስ፤ የፍጻሜ ምንኩስና ምልክት ነው (ኪ.ዳነ ወልድ ክፍሌ፣ 1948፣ 109)፡፡

አስኬማ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበላቸው አስራ ሶስቱ ህማማት መስቀል ልክ ተደርጎ ከጠፍር የሚሰራ ሲሆን፣ እንደ ሰደርያ ወይም ቅናተ ዮሐንስ የሚነገት፣ ሊቀ ጳጳሳት ሲሾሙ የሚያደርጉት ነው" (አባ ፍቅረ ዮሐንስ፣ ካሴት ቁ.8፣ Side A)። ይህ ቁስ መነኮሳቱ በመነኮሱበት ቦታ ወይም በሁሉም ገዳማት የሚሰጥ ቁስ አይደለም። አስኬማ የሚሰጠው በደብረ ዳሞ ገዳም ብቻ ነው። አባ ፍቅረ ዮሐንስም፣ ደብረ ዳሞ ገዳም በመጀመሪያው የቆብ አባት በአቡነ አረጋዊ የተገደመ መሆኑን ጠቅሰው የአስኬማ ቦታ ደብረ ዳሞ ገዳም ብቻ ነው ይላሉ (ዝኒ ከማሁ)። ስሆነም ገዳማቱ አስኬማ እንዲሰጥላቸው የሚፈልጓቸውን መነኮሳት ደብዳቤ አስይዘው ወደደብረ ዳሞ ገዳም ይልኳቸዋል። የደብረ ዳሞ ገዳምም በተጠየቀው መሰረት ለመነኮሳቱ አስኬማውን ሰጥቶ ወደመጡበት ቦታ እንዲመለሱ ያደርጋል (ዝኒ ከማሁ)።

አስኬማ በአስራ ሶስት ትዕምርተ መስቀል አምሳል መዘጋጀቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሞቱ ድረስ የተቀበላቸውን መከራና ስቃይ ለማጠየቅ ነው። አስራ ሶስቱ ህማማተ መስቀል፣ እጁን የኋሊት መታሰሩ፣ በገመድ መጎተቱ፣ በገመድ አስረው ወደፊትና ወደኋላ ሲጎትቱትና ሲለቁት መውደቅና መነሳቱ፣ በአይሁዶች እግር መረገጡ፣ በጲላጦስ ፊት ለፍርድ መቆሙ፣ በአይሁዶች ፊቱን በጥፊ መመታቱ፣ አይሁዶች ምራቃቸውን የተተፋበት፣ እራሱን በመቃ መመታቱ፣ የእሾኽ አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ ያደረጉበት፣ የተሰቀለበትን መስቀል መሸከሙ፣ በችንካር መቸንከሩ፣ በእንጨት መስቀል ላይ መሰቀሉ እና ተጠማሁ ሲል ሐሞት የመጠጣቱ ምሳሌዎች ናቸው።

### 4.3.1.3 መቁጠሪያ

መቁጠሪያ ለጸሎት ማከናወኛ የሚያገለግል ቁስ ሲሆን፣ ገዳማውያኑም ይህን ቁስ በአንገታቸው፣ በእጃቸው ወይም በኪሳቸው ይይዛሉ። መቁጠሪያ እንደ ቀሚስ፣ ቆብ ወይም ስጋ ማርያምና ቅናተ ዮሐንስ ለመነኮሱና በአመክሮ ላይ ላሉ ገዳማውያን ተብሎ የሚለይ ቁስ አይደለም። ስለሆነም ሁሉም ገዳማውያን በመቁጠሪያ እኩል ይጠቀማሉ። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ማርምር ማዕከል፣ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ስለ መቁጠሪያ የሚከተለውን አስፍሯል።

መቁጠሪያ አንድን የጸሎት ቃል ስንት ጊዜ መላልሰው መጥራታቸውን ለማስታወስ ይረዳቸው ዘንድ ጸሎተኞች እንደ ዶቃ በክር ሰክተው የሚይዙት፣ ቅርጹ ድቡልቡል ሆኖ መጠኑ ዳቦ ቆሎ የሚያካክል፣ ብዛቱ እንደየጸሎተኛው ፍላጎት የሚወሰን፣ ከእንጨት ወይም ከሌላ ነገር የሚዘጋጅ የጸሎት መገልገያ እቃ ነው (1993፣ 212)።

ገዳማውያኑ የሚይዙት መቁጠሪያ አብዛኛውን ጊዜ 41 ፍሬዎች (ድብልብል መሳይ ነገሮች) ያሉት ነው። ከዚህ ሌላ ባለ 64 እና 120 ፍሬ ያላቸው መቁጠሪያዎች አሉ። መቁጠሪያ ሁሉም ገዳማውያን የሚጠቀሙበት ቁስ ቢሆንም አባ ኪዳነ ቃል ገዳማውያኑን ወጣኒ[18]፣ ማዕከላውያንና ፍጹማን በማለት ከከፈሉ በኋላ ወጣኒዎቹ በ41ዱ፣ ማዕከላውያኑ በ64ቱ ፍጹማኑ ደግሞ 120 ፍሬ ባለው መቁጠሪያ እንደሚጠቀሙና ይህም ካላቸው ጊዜና ከሚሰሩት ስራ ጋር ተያያዥነት እንዳለው ይገልጻሉ (ካሴት ቁ.8፣ Side A)። በተጨማሪም ቁጥሩ የሚወሰነው ተጠቃሚው ካለው ጊዜ አንጻር እንጂ እገሌ በዚህ መቁጠሪያ ብቻ ጸሎት ማድረግ አለበት ተብሎ እንደማይወሰን ገልጸዋል።

መቁጠሪያዎቹ በአስራ ሁለት አስራ ሁለት ልክ እንዲለዩ ተደርገው ይሰራሉ። ለመለያም ከሌሎቹ አነስ ያለ ፍሬ ይደረግባቸዋል። ይህም ምን ያህል እንደቆጠሩ ለማስታወስ የሚረዳ ነው። በመቁጠሪያዎቹ መጀመሪያ ላይ ያሉት 12 ፍሬዎች አቡነ ዘበሰማያት (አባታችን ሆይ) የሚባልባቸው ናቸው። የቁጥሩ 12 መሆን የ12ቱ ሐዋርያት ምሳሌ ሲሆን፤ በእያንዳዱ አቡነ ዘበሰማያት ሶስት ሶስት ይሰገዳል። በ12ቱ መቁጠሪያ ልክ ያለው ስግደት ሲደመር 36 ይሆናል። ይህም የ36ቱ ቅዱሳት እንስት ምሳሌ ነው። ባለ አርባ አንዱ መቁጠሪያ የአዳም ሱባኤን[19] ማስታወሻ ነው። የዚህን ምክንያት አባ ኪዳነ ቃል ሲገልጹ፣ አዳም ከገነት ከተባረረ በኋላ ተጸጽቶ 40 ቀን ሱባኤ ሊያደርግ ወሰነ። ሱባኤውን ጀምሮ ሰላሳ አምስት ቀን ከቆየ በኋላ እንደገና ዲያብሎስ አሳስቶት ሱባኤውን አቋርጦ ወጣ። ከዚያም መጀመሪያም ከገነት ያስወጣሁህ እኔ ነኝ፤ አሁንም ያሳሳትኩህ እኔ ነኝ ሲለው መሬት ላይ ወድቆ ሶስት ቀን ቆየ። በዚህ ጊዜም

[18] ወጣኒ፦ የወጠነ፣ የሚወጥን፣ ዠማሪ፣ ፈላሚ ማለት ነው (ደስታ ተክለ ወልድ፣ 1962፣ 427)።

[19] ሱባኤ ለተወሰነ ጊዜ ከሰው ተለይቶ የሚደረግ ፆመ፣ ፀሎትና ስግደት፣ ቀኖና ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ 1993፣ 128)።

የገነት አእዋፍት ከገነት ፍሬ ለቅመው ሰጥተውት ሲመለሱ እነሱን ተከትሎ ሲሄድ አሁንም ገነትን መፈለግህን አልተውክም? ብሎ ዲያብሎስ ድንጋይ ጭኖበት ሶስት ቀን ቆየ፡፡ እነዚህ ቀናት ሲደመሩ አርባ አንድ ይሆናሉ፡፡ በዚህም ቀን እኔ ከልጅ ልጅህ ተወልጀ አድንሃለሁ፤ ብሎ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባለት ሱባኤ መመሰያ ነው (ካሴት ቁ.8፣ Side A)፡፡ ባለ 64 ፍሬው መቁጠሪያ ደግሞ የእመቤታችን ድንግል ማርያምን እድሜ ያመለክታል፡፡ እመቤታችን በዚህ ዓለም የኖረችው 64 አመት እንደሆነ ይታመናል፡፡ በዚህ መቁጠሪያም እንደ ባለ አርባ አንዱ መቁጠሪያ ጸሎት ይደረግበታል፡፡

ሌላው የመቁጠሪያ አይነት ባለ 120 ፍሬ ሲሆን፤ ይህም ኢየሱስ የመረጣቸው 120 ቤተሰቦች ምሳሌ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ አባ ኪዳነ ቃል፣

> ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሲያስተምር አምስት ሺህ ገበያ የሚያህል ህዝብ ይከተለው ነበር፡፡ ከነዚህ ውስጥም 120ዎቹን መረጠ፡፡ 120 የምንላቸው 12ቱ መጀመሪያ የመረጣቸው ሐዋርያት፣ 72ቱ ሐዋርያትን የሚያገለግሉ፣ የሚላኩ፣ የሚወጡ፣ የሚወርዱ አርድዕተ ሐዋርት እና 36ቱ ቅዱሳት እንስት አጠቃላይ ሲደመሩ 120 ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ ክርስቶስ ከዚያ ሁሉ ህዝብ ለእሱ አገልግሎት የመረጣቸው፣ ለተልእኮ፣ ይህንን አለም ለማስተማር፣ ለማዳን የላካቸው ቤተሰቦች ምሳሌ ናቸው (ካሴት ቁ.8፣ Side A) ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ የመቁጠሪያዎቹ ልክ 41፣ 64 እና 120 ሲሆን፤ ሁሉም ተምሳሌታዊና ሃይማኖታዊ መሰረት አላቸው፡፡ በሁሉም መቁጠሪያ 12 ጊዜ አቡነ ዘበሰማያትና እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ፣ በእንተ እግዚትነ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ የመሳሰሉት ጸሎቶች ይደረጋሉ፡፡ የመቁጠሪያው ቁጥር ከ41 ወደ 64 ወይም 120 ከፍ ሲል በ41 መቁጠሪያ የሚደረገው ጸሎቱ ተደጋግሞ ይደረጋል ወይም የጸሎቱ ቁጥር ይጨምራል፡፡ መቁጠሪያ ከተለያዩ እንጨቶች በመቅረጽ እንዲሁም በፋብሪካ ከተለያዩ ቁሶች ሊሰራ ይችላል፡፡ በሐይቅ ገዳም፣ ገዳማውያኑ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው በእንጨት ነው ከሚል እሳቤ በመነሳት ከወይራ፣ ከሎሚ፣ ከልምጭና ከመሳሰሉት እንጨቶች በተቀረጸ መቁጠሪያ እንደሚጠቀሙ አባ ኪዳነ ቃል (ካሴት ቁ.8፣ Side A) ይገልጻሉ፡፡ በሁሉም መቁጠሪያዎች ጫፍ ላይ መስቀል ይደረግባቸዋል፡፡ ተጠቃሚውም ጸሎት ከማድረጉ በፊት በመቁጠሪያው ጫፍ ላይ ባለው መስቀል መላ ሰውነቱን አማትቦ ጸሎቱን ይጀምራል፡፡

ገዳማውያኑ ጸሎት የሚያደርጉበት ሰዓት መድረሱን ለማስታወስም ደወል ይደወላል፡፡ በዚህ ወቅት ባላቸው መቁጠሪያ አማካይነት ጸሎታቸውን ያደርሳሉ፡፡ በሐይቅ ገዳም ሦስት የደወል አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም ከነሐስ፣ ከድንጋይና ከእንጨት የተሰሩ ናቸው፡፡ የነሐስ ደወሉ በሁሉም ቤተ ክርስቲያን ያለው አይነት ሲሆን፣ የሚደወለው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት (ለሥርዓተ ቅዳሴ) ነው፡፡ ይህ ደወል "ለቅዳሴ ሥርዓት አምስት ጊዜ ይደወላል፡፡ እነሱም የተጋብዖ፣ የግብር፣ የወንጌል፣ የእግዚኦታ እና የድርገት ደወል" ይባላሉ (ስንታየሁ፣ 1992፣ 28)፡፡

በተጋብዖ ጊዜ የሚደወለው ገዳማውያኑን (ምእመናንን) ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄዱ ለማንቃትና ካህናትን ለአገልግሎት ለመሰብሰብ ነው፡፡ ለዚህም ሲባል አምስት ጊዜ ይደወላል፡፡ ይህም የአምስቱ አዕማደ ምስጢር (ምስጢረ ስላሴ፣ ምስጢረ ስጋዌ፣ ምስጢረ ጥምቀት፣ ምስጢረ ቁርባን፣ ምስጢረ ትንሳኤ ሙታን)[20] ምሳሌ ነው፡፡ የግብር ደወል ምሳሌነቱ ድንግል ማርያም ከትእማን ደጅ ስትለምን ክፉ ቃል ስለመለሰችላትና ኩቲባም ኢየሱስን ነጥቃ መሬት ላይ ስትጥለው የማልቀሷ ምሳሌ ነው፡፡ የወንጌል ደወል ደግሞ ማርያም ኢየሱስን ይዛ ስትሄድ ሁለት ወንበዴዎች በበረሃ አግኝተዋት የወርቅ ጫማውን ከወሰዱ በኋላ ሲመካከሩ ልጁን ሊገድሉት ነው ብላ የማልቀሷ ምሳሌ ነው፡፡ የእግዚኦታ ደወል በቅዳሴ ወቅት አስራ ሁለት ጊዜ የሚደወል ሲሆን፤ ይህም የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ምሳሌ ነው፡፡ የድርገት ደወል ደግሞ ሥጋ ወደሙ ሲሰጥ ሰባት ጊዜ የሚደወል ሲሆን፤ ይህም የሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን (ምስጢረ ጥምቀት፣ ምስጢረ ሜሮን፣ ምስጢረ ቁርባን፣ ምስጢረ ንስሃ፣ ምስጢረ ቀንዲል፤ ምስጢረ ክህነትና ምስጢረ ተክሊል)[21] ምሳሌ ነው (ስንታየሁ፣ 1992፣ 28)፡፡

ሌላው የደወል አይነት ከረጅም ጠፍጣፋ ድንጋይ የተዘጋጀው ደወል ነው፡፡ በዚህ ደወል አማካይነት በገዳሙ የሚገኙ ገዳማውያን የጸሎት ሰዓት መድረሱን እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡ ይህ ደወል የጸሎት ሰዓቱንም (ስንት ሰዓት እንደሆነ) የሚያመለክት ነው፡፡ ለምሳሌ በሶስት ሰዓት ሶስት ጊዜ፣ በስድስት ሰዓት ስድስት ጊዜ፣ በዘጠኝ ሰዓት ዘጠኝ ጊዜ ወዘተ. የድንጋይ ደወሉ ይመታል፡፡ ሦስተኛው ደወል ደግሞ ሁለት እንጨቶችን

---

[20] የአምስቱ አዕማደ ምስጢርን ዝርዝር አባ ኪዳነ ቃል በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ግቢ ጠይቄአቸው ነግረውኝ ነው፡፡

[21] የሰባቱን አዕማደ ምስጢር ዝርዝር አባ ኪዳነ ቃል በቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ግቢ ጠይቄአቸው ነግረውኝ ነው፡፡

እርስ በርስ በማጋጨት የሚደወል ሲሆን፤ እነዚህም ሁለት አይነት ናቸው። አንደኛው ሁለቱን እንጨቶች ደዋዩ በሁለት እጁ ይዞ ቤተ ክርስቲያኑን እየዞረ የሚደውለው ሲሆን፤ አገልግሎቱ አርድእቶችን ለስራ ማስማሪያ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በተግባር ቤቱ አካባቢ ባለ ዛፍ ላይ የተንጠለጠለ እንጨት ሲሆን፤ ኋል (ዕኋል) መጋቢዎቹ ወይም መጋቢው የምግብ ማደያ (መስጫ) ሰዓት መድረሱን የሚያውጁበት ነው። ሁሉም ደወሎች የተለያዩና የተለያየ አገልግሎት ያላቸው ናቸው። ገዳማውያኑም ደወሎቹን በድምጻቸው ይለዩዋቸዋል።

## 4.3.1.4 መስቀል

መስቀል ስርዓተ ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን ለመባረክ፣ ንዋየ ቅድሳትን ለማንጻት፣ ለመቀደስና ለማክበር የሚያገለግል ቁስ ነው። በአንዳንድ አካባቢ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ደግሞ ክርስቲያን መሆናቸውን ለማመልከት በግንባራቸው፣ በአንገታቸው፣ በእጃቸውና በመዳፋቸው ላይ በመስቀል ቅርጽ ይነቀሳሉ።

ገዳማውያኑም ሆኑ ሌሎች ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ የተሰቀለበትን መስቀል አምሳል በማተብ አስረው በአንገታቸው ላይ ያደርጋሉ። በተለይ ገዳማውያኑ (የመነኮሱም ሆነ ያልመነኮሱ) በሚለብሱት ቀሚስ አንገትያ አካባቢና በኪሳቸው ላይ በመስቀል ቅርጽ የተዘጋጀ ጨርቅ ይሰፋላቸዋል። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል በአንገት ላይ ማድረግና በልብስ ላይ ማሰፋት የክርስቲያኖች መለያ ተደርጎ ይቆጠራል። ክህነት ያላቸው መነኮሳት ደግሞ በየአጋጣሚው የሚያገኟቸውን ምዕመናን እንዲሁም ክህነት የሌላቸው ገዳማውያንን ለመባረክ የሚያገለግል መስቀል በእጃቸው ይይዛሉ።

በአንገታቸው የማሰራቸው ምክንያትም ላመንኩበት እምነት አንገቴን እሰጣለሁ የማለት ምሳሌ ነው። በተጨማሪም ለኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን ፍቅር መግለጫም ነው። በእጃቸው የሚይዙት ደግሞ ምእመናንን እና የተለያዩ ሃይማኖታዊ ቁሶችን እንዲሁም የሚመገቡትንና የሚጠጡትን ለመባረክና ሰይጣንን ለማራቅ ነው።

መስቀል ከነሐስ፣ ከብረት፣ ከወርቅ፣ ከእንጨትና ከመሳሰሉት ነገሮች ሊሰራ ይችላል። ከተለያዩ ነገሮች እንደመሰራቱ ሁሉ የተለያየ ሃይማኖታዊ ተምሳሌትም አለው። የእንጨቱ መስቀል ኢየሱስ ክርስቶስ በእለተ አርብ በቀራንዮ የተሰቀለበት

መስቀል ተምሳሌት ነው። የወርቅ መስቀሉ የባህርይ ንጉስ መሆኑን፣ የመዳብ መስቀሉ የፈሰሰው ደሙን፣ የብር መስቀሉ ይሁዳ ኢየሱስን ለአይሁድ በሰላሳ ብር አሳልፎ መስጠቱን እንዲሁም የብረት መስቀሉ በመስቀል ላይ የተቸነከረበትን ብረት ያመለክታሉ።

በሐይቅ ገዳም የነበሩ መነኮሳት አባቶችም በመስቀል አማካይነት የሚያጋጥማቸውን ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ችግሮችን ይመክቱ እንደነበር የሚያመለክቱ አፈ ታሪኮች አሉ። ለማስረጃ ያህልም የሚከተሉትን እንመልከት።

በአፈ ታሪክ 8 (አባሪ 2፣ ገጽ 39) ላይ እንደተጠቀሰው በዚህ ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያን ከመሰራቱ በፊት በዘንዶ እያመለኩ የሚኖሩ ሰዎች ነበሩ። አቡነ ሰላማ ሁለተኛ የተባሉት ጳጳስ ወደአካባቢው ሲመጡ በዚህ ቦታ ላይ (በደሴቱ) ስለሚኖሩ ሰዎችና ስለዘንዶው ሁኔታ ሰሙ። ከዚያም በእግዚአብሔር ስም በደሴቲቱ ላይ በመስቀላቸው ሲያማትቡ ዘንዶው መጥፋቱን፤ ከዚያም በቦታው ላይ ቤተ ክርስቲያን እንደተሰራበት ያመለክታል።

በአፈ ታሪክ 17 (አባሪ 2፣ ገጽ 45) ላይ ደግሞ አቡነ ብስጣውሮስ አበምኔት በነበሩበት ወቅት ሁለት ወንበዴዎች ወደ ሐይቁ መጥተው ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚያቃጥሉ፣ የገዳሙን ሀብትና ንብረት እንደሚቀሙ፤ ገዳማውያኑንም እንደሚገድሉ ለአበምኔቱ መልእክት ይልካሉ። አበምኔቱም መልእክቱ እንደደረሳቸው የአቡነ ኢየሱስ ሞአን መስቀል ይዘው ወንበዴዎቹ ወዳሉበት አካባቢ ሲሄዱ ሸሽተው እንደተመለሱና አገራቸው ሲደርሱም እንደሞቱ ያትታል።

ከላይ የቀረቡት አፈ ታሪኮች አንድም የሰው ልጅ መስገድና ማምለክ ያለበት ለኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ለሌላ ፍጡር አለመሆኑን ያመለክታሉ። በሌላም በኩል በእግዚአብሔር አምነው፣ የተሰቀለበት አምሳል የሆነውን መስቀል የሚይዙ ካህናት በያዙት መስቀል አማካይነት የሚፈልጉት ነገር እንዲፈጸምላቸው እግዚአብሔርን ቢጠይቁ የሚደረግላቸው መሆኑን ያመለክታሉ።

### 4.3.1.5 በትረ መስቀል

በትረ መስቀል ገዳማውያኑ ጸሎት ከማድረጋቸው በፊት እንደ መስቀል የሚያማትቡበት፣ ጸሎት ሲያደርጉም በፊት ለፊታቸው ተክለውም መቁጠሪያቸውንና

የዳዊት መያዣቸውን የሚያንጠለጥሉበት፣ በቤተ ክርስቲያን ቆመው ሲያስቀድሱና ሲደክማቸውም ለመደገፊያነት የሚያገለግል ቁስ ነው።

በትረ መስቀል አብዛኛውን ጊዜ ከብረት የሚሰራ ሲሆን፤ ከላይ በኩል የመስቀል ቅርጽ፣ ከታች በኩል ደግሞ ሹል እንዲሆን ተደርጎ ይሰራል። ከላይ ያለው መስቀል መነኮሳቱ ባሉበት ሆነው ጸሎት ሲያደርጉ የሚያማትቡበት ሲሆን፤ ከታች በኩል ያለው ሹል ነገር ደግሞ ለመንፈሳዊ ተልእኮም ሆነ ለገዳማዊ ስራ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ እንደ ምርኩዝ የሚያገለግላቸው እና ከሚያጋጥማቸው ማንኛውም አውሬ በተለይም እባብ እራሳቸውን የሚከላከሉበት ነው። እባብ አዳምና ሔዋን የእግዚአብሄርን ትእዛዝ እንዲተላለፉና ከገነት እንዲባረሩ ያደረገው ዲያብሎስ ምሳሌ ነው። ስለዚህ መነኮሳትም ከሃይማኖታዊ ተልእኳቸው የሚያሰናክላቸውን ማንኛውንም ነገር ለመከላከል በበትረ መስቀላቸው አማካይነት ይጠቀማሉ።

## 4.3.2 የመነኮሳት ግንዘት

ግንዘት የሰው ልጅ ሲያርፍ (ሲሞት) የሚከናወን ስርዓት ነው። የሰው ልጅ በዚህ ዓለም እንዲኖር የተፈቀደለትን ጊዜ ጨርሶ በሞት ሲለይ አካሉ ታጥቦ፣ የሰውነት ክፍሎቹ በሚገባ ተገጣጥመውና ተስተካክለው፣ የእጅና የእግር ጣቶቹ በፈትል (ክር) ታስረው፣ በአዲስ ልብስ ተጠቅልሎ ይገነዛል። ይሁንና በዓለም ለሚኖሩ ክርስቲያኖችና ለገዳማውያን የሚደረገው የግንዘት ሁኔታ የተለያየ ነው። በገዳማውያኑም መካከል ቀደም ብሎ በዓለም ሲኖር ቀይቶ ከጊዜ በኋላ ለመነኮሰ፣ ለድንግል መነኩሴና ክህነት ላለው መነኩሴ የሚደረገው የግንዘት ስርዓት የተለያየ ነው።

ቀደም ብሎ በዓለም ሲኖር በህግ ማለትም ሃይማኖቱ በሚፈቅደው ስርዓት መሰረት አግብቶ፣ ወልዶና ከብዶ በአጠቃላይ በዓለም የሚኖሩ ምእመናን የሚፈጽሙትን እያደረገ ሲኖር ቀይቶ በኋላ በገዳሙ ህግ መሰረት የመነኮሰ ገዳማዊ ሁለት እጆቹን ሀፍረተ ስጋው (ብልቱ) ላይ ተደርገው ይገነዛል። ይህም በህጋዊ ጋብቻ ተወስኖ መቆየቱንና በተሰጠው አካል በዓለም ያለውን ነገር ሁሉ ሲፈጽም መኖሩን የሚያመለክት ነው።

ማቹ ድንግል መነኩሴ ከሆነ ሁለት እጆቹ አይኖቹ ላይ ተደርገው፣ በራሱ ላይ የሚያደርገው ቆብ እጥፋቱ ተተርትሮ እጆቹን እንዲሸፍን ተደርጎ ይገነዛል። ይህም ሟቹ

በዚህ ዓለም በህይወት በነበረበት ጊዜ በአይኖቹ የዚህን ዓለም ክፉ ነገሮች አለማየቱን፣ ዝሙትና የግብረ ስጋ ግንኙነት አለመፈጸሙን ያመለክታል። በሌላም በኩል ሟቹ ክህነት ያለው መነኩሴ ከሆነ እጆቹ በትዕምርተ መስቀል አምሳል ተመሳቅለው ይገነዛል። ይህም ካህኑ መነኩሴ በህይወት በነበረበት ጊዜ በነበረው የክህነት ስልጣን፣ በቤተ ክርስቲያን የክህነት አገልግሎት እየፈጸመ፣ ምእመናንንም እየባረከና እያስተማረ መኖሩን የሚያመለክት ነው።

የመነኮሳቱ በድን በአዲስ ልብስ ከተጠቀለለ በኋላ በሶስት ክር ይታሰራል። በሶስት ክር መታሰሩም የስላሴን ሶስትነት የሚያጠይቅ ነው። በተጨማሪም ሰባት ቦታ ላይ በመስቀል ቅርጽ ተቋጥሮ በሰውነቱ ላይ የሚደረግ ክር አለ። ይህ ደግሞ ሰባቱን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚያመለክት ነው። ይህ ስርዓት ሲከናወን አስራ ሁለት መብራት ይበራል። መብራት የሚበራበት ምክንያትም ከዚህ የጨለማ ዓለም ወደብርሃን ዓለም መሄዱን ለማመልከት ሲሆን፤ የመብራቱ ቁጥር አስራ ሁለት መሆኑም አስራ ሁለቱን ሐዋርያት ለመመሰል ነው (አባ ኪዳነ ቃል፣ ካሴት ቁ.8፣ Side B)። የግንዘቱ ሁኔታ ለመነኮሳይያቱም (ለሴት ገዳማዊ) ተመሳሳይ ሲሆን፤ ክህነት የሚፈቀደው ለወንዶች ብቻ በመሆኑ "ክህነት" የሚለው መነኮሳይያቱን አያካትትም።

ከዚህ በኋላ የተገነዘው በድን በሰሌን ተጠቅልሎ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይወሰዳል። በቤተ ክርስቲያንም ጸሎተ ፍትሐት ተደርጎ ይቀበራል። የገዳማውያን በድን እንደ ዓለማውያኑ በሳጥን አይቀበርም። ይህም በህይወት ሲኖሩ የዓለሙን ተድላና ደስታ ንቀው እንደኖሩ ሁሉ በህልፈታቸውም ፈራሽ ለሆነው ሰውነት ሳጥን እንደማያስፈልጋቸው ለማመልከት የሚደረግ ይመስለኛል።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳብ የሚቀርብበት ክፍል ነው።

### 5.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት የታየው የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ሲሆን፤ አቡነ ሰላማ ሁለተኛ እና በአጼ ድል ናኦድ አማካይነት በ862 ዓ.ም በሐይቁ ደሴት ላይ ቤተ ክርስቲያን የተሰራ ሲሆን፤ በ13ኛው ክፍለ ዘመን በአቡነ ኢየሱስ ሞአ አማካይነት ቦታው ወደገዳምነት ሊቀየር ችሏል።

በዚህ ገዳም በርካታ ቅዱሳን አባቶች ዓለመ ምንኩስና ተምረው በተለያዩ አካባቢዎች ገዳም በመገደም የክርስትና ሃይማኖት እንዲስፋፋና የምንኩስና ህይወት እንዲለመድ አድርገዋል። ከአጼ ይኩኖ አምላክ ዘመን ጀምሮ እስከ አስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ገዳሙ ከፍተኛ ዝና የነበረው ቢሆንም ከዚህ ዘመን በኋላ የሃይማኖት ማዕከልነቱና የአንድነት ኑሮው ተዳክሞ ነበር። ከ1985 ዓ.ም በኋላ ደግሞ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አማካይነት የወንዶቹ ገዳም የአንድነት ኑሮው የተመለሰ ሲሆን፤ የሴቶቹ ቤተ ደናግልም በአዲስ መልክ ተመስርቷል። ጥንት የነበረው የሃይማኖት ማዕከልቱ ይዘክር ዘንድም አንድ የካህናት ማሰልጠኛ ማዕከል ተቋቁሟል።

የገዳማውያኑ ምግብ ተራ ("ለቁመተ ስጋ") ሲሆን፤ ሰኞ፣ እሮብና አርብ ዳቤ፤ ማክሰኞ፣ ሐሙስ፣ ቅዳሜና እሁድ ደግሞ እንጀራ ነው። ንፍሮ በቤተ ደናግሉ የሚዘጋጅበት ወቅት በውል ባይታወቅም በወንዶች ገዳምም ቢሆን በአብይ የጾም ወቅቶች እንዲሁም ለዝክርና የቆሎ ተማሪዎችን ስራ ሲያሰሩ ካልሆነ በቀር ተዘውታሪ መቁነን አለመሆኑ በጥናቱ ታይቷል። በጉልበት ስራ የተሰማሩ አርድእቶች በስራ ቀን ሁለት ጊዜ፣ በክህነት ስራ የተሰማሩና አረጋውያን ደግሞ አንድ ጊዜ ይመገባሉ።

ምንኩስና ያላቸው ገዳማውያን በሚያደርጉት ቆብ፣ በሚለብሱት ቀሚስ፣ በቅናተ ዮሐንስና *ሥጋ* ማርያም በአመክሮ ካሉት ይለያሉ። ልብሳቸውም ጥቁር፣ ቢጫ እና

ወይባ ወይም አፈር የተነከረ ሲሆን፣ አሁኑ ወቅት ወይባ ያልተነከሩ ልብሶችን መልበስ እየተለመደ መጥቷል። ልብሰ ምንኩስና ከኢየሱስ ክርስቶስ እንደተገኘ የሚታመን ሲሆን፣ ቆቡም የእሾህ አክሊል (የአክሊለ ሶክ) ምሳሌ ነው። ስጋ ማርያምም ሆነ ቅናተ ዮሐንስ እንዲሁም ለጸሎት ማድረጊያ የሚጠቀሙበት መቁጠሪያ ሁሉ ተምሳሌታዊ ናቸው።

ገዳማውያኑ በዚህ ዓለም እንዲኖሩ የተፈቀደላቸውን ጊዜ ፈጽመው ሲያርፉም የሚደረግላቸው የግንዘት ሁኔታ በዓለም ኖረው ለመነኮሱ፣ በድንግልና ለቆዩ እንዲሁም በክህነት አገልግሎት ለነበሩ መነኮሳት የተለያየ ነው።

በአጠቃላይ ገዳሙ እድሜ ጠገብና ለሌሎች ገዳማት መመስረት መነሻ ሲሆን፣ ገዳማውያኑ በአለባበሳቸው፣ በቆባቸው፣ በሚሰጣቸው ቅናተ ዮሐንስና ስጋ ማርያም ወዘተ. መሰረት በአመክሮ ያሉና የመነኮሱ፣ በሚደረግላቸው የግንዘት ሁኔታ ደግሞ በዓለም የነበሩ፣ ደናግልና በክህነት የሚያገለግሉ መነኮሳት ብሎ መመደብ የሚቻል መሆኑን በጥናቱ ታይቷል።

## 5.2 የይሁንታ ሀሳቦች

ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ ለማቅረብ ከተከናወኑ ተግባራት ማለትም በቅድመ መስክ፣ በመስክ ላይና በድህረ መስክ ከታዩ ተግባራት በመነሳት የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበዋል።

- ገዳማውያኑ ከማንም ምንም ሳይጠብቁ፣ በጉልበታቸው ሰርተው ባገኙት አባባ ይተዳደራሉ። ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን ለመርዳትም የተለያየ እቅድ ነድፈው ይንቀሳቀሳሉ። ስለሆነም የገዳማውያኑ የተቀደሰ አላማና ተግባር ግቡን ይመታ ዘንድ መንግስትም ሆነ ሌሎች አካላት ሊረዷቸው ይገባል።
- መነኮሳቱ ከገዳማቸው ሳይወጡ መንፈሳዊ ተልዕኳቸውን ለማካሄድ እንዲችሉ የኢኮኖሚ አቅማቸውን ማዳበር ያሻል። ስለሆነም የገዳሙን ፍላጎትና ነባራዊ ሁኔታ እያጠኑ ገዳማቱ ቢረዱ፣ የተለያየ ሙያና እውቀት ያላቸውም እውቀታቸውን ለገዳማውያኑ ቢያካፍሉ መልካም ነው።
- የገዳሙን ቁሳቁስ ለመንከባከብና ለጎብኝዎች ለማሳየት እንዲመች ቁሶቹ በሙዚየም ውስጥ መቀመጣቸው ይበል የሚያስብል ነው። ይሁን እንጂ ጉብኝቱ

የሚፈቀደው ለወንዶች ብቻ መሆኑ የህብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን ሴቶች ያገለለ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሙዚየሙ አላማ አድርጎ የተነሳበትን የቅርስ ማስተዋወቅና ገቢ የማስገኘት ተግባር የሚጎዳ ነው፡፡ ስለሆነም ሙዚየሙ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል እይታ አመቺ በሆነ ቦታ ላይ ቢሰራ የተሻለ እንደሚሆን አጥኚው ያምናል፡፡

- የገዳሙ የሃይማኖት ተቋምነት እንዲዘከር ብሎም ከተለያየ ሀገረ ስብከት የሚመጡ ካህናትን ለማሰልጠን ታስቦ የተከፈተው የካህናት ማሰልጠኛ በሙሉ አቅሙ ለመንቀሳቀስ የበጀት እጥረት አለበት፡፡ በመሆኑም ጠቅላይ ቤተ ክህነት እንዲሁም የዞኑና የወረዳው ሀገረ ስብከቶች የተቀናጀ ድጋፍ ቢያደርጉ ተቋሙ የታለመለትን ግብ ሊመታ ይችላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሀብተማርያም ወርቅነህ። ድንግልናዊ ህይወት። አዲስ አበባ፣ ብርንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1956 ዓ.ም።

ሉሌ መልአኩ። አጭር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ። አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1958 ዓ.ም።

-------------- ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1997 ዓ.ም።

መንግስቱ ጎበዜ እና አሳምነው ካሣ። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቀ. 2። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፣ 2000 ዓ.ም።

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ። አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁ. 1። አዲስ አበባ፣ ያልታተመ፣ 1969 ዓ.ም።

-------------- ። አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ቁ. 4። አዲስ አበባ፣ ያልታተመ፣ 1981 ዓ.ም።

ሰለሞን ደርቤ። "የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል አከባበር።" ኤም.ኤ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2000 ዓ.ም።

ስንታየሁ አባተ። "ደወል በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት" ሐመር። አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም።

በሪሁን ከበደ። የዋልድባ ገዳም ታሪክ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ (አዘ)። ፍትሐ ነገሥት ሥጋዊ መንፈሳዊ የሕግ ምንጭ። አዲስ አበባ፣ ተስፋ ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም።

ተክለ ማርያም (አባ)። የምስካየ ኀዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም አመሰራረት ማስታወሻ። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1963 ዓ.ም።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ። የግራኝ አህመድ ወረራ። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1966 ዓ.ም።

------------ ። የኢትዮጵያ ታሪክ አክሱም - ዛጉየ። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1966 ዓ.ም።

ታደሰ አይችሉህም። "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የምንኩስና ስርዓትና የገዳማውያን የእለት ተእለት ህይወት ከትዕምርታዊነቱ አንጻር፤ በዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳማት።" ኤም.ኤ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1999 ዓ.ም።

አትናቴዎስ (አቡነ)። ገድለ አቡነ ኢየሱስ ሞአ፣ ገድለ አቡነ ብስጣውሮስ፣ ገድለ አቡነ አቢብ። አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ማተሚያ ቤት፣ 2001 ዓ.ም።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ፣ መዝገበ ቃላት ሐዲስ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948 ዓ.ም።

ወርቁ ከተማ። "የሊሙና ቢልቢሎ ወረዳ የጨፋ መድሃኔዓለም ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማርያምና ቅድስት ሰሎሜ የሴቶች ገዳም አመሰራረት ፎክሎራዊ ገጽታ።" ኤም.ኤ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2000 ዓ.ም።

የሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ የወንዶች አንድነት ገዳም። መተዳደሪያ ደንብ። ደሴ፣ ያልታተመ፣ 1987 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። መጽሐፍ ቅዱስ። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተ ክርስቲያን። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትናና ዛሬ። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1997 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል። ኣማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም።

የክልል ሶስት ቱሪዝም ቢሮ። ክልል 3 ሲጎበኝ። ባህር ዳር፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1986 ዓ.ም።

ያረጋል አበጋዝ። ፍኖተ ቅዱሳን። አዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤት የለውም፣ 1993 ዓ.ም።

ደስታ ተክለ ወልድ። ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም።

ዳንኤል ሰይፈ ሚካኤል። የሐይቅ ቅዱስ እሲጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ቤተ ደናግል። አዲስ አበባ፣ አዲስ ማተሚያ ቤት፣ 1999 ዓ.ም።

ዳንኤል ክብረት። ከበረሓው ጉያ ውስጥ። አዲስ አበባ፣ ጥቁር አባይ አታሚዎች፣ 1998 ዓ.ም።

----------- ። የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣ 1999 ዓ.ም።

ጎርጎርዮስ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ። አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐዋርያዊ ድርጅት፣ 1974 ዓ.ም።

ፈቃደ አዘዘ። የስነ ቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1991 ዓ.ም።

ፊልጶስ (አባ)። የምንኩስና ስርዓትና ብያኔ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ሊሚትድ፣ 1961 ዓ.ም።

ፍሬህይወት ባዩ። "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ፍክሎራዊ ገጽታ።" ኤም.ኤ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2000 ዓ.ም።

Bahru Zewdie. AShort History of Ethiopia and The Horn. Addis Ababa: Commercial Printing Enterprise, 1998.

Chadwick, Owen. John Cassian. Cambridge University Press, 1968.

Daniel Hailu. "Founders of Ethiopian Monasticism." Unpublished BA. Thesis, Trinity Theology College, 2001.

Hailemichael Wolde Tekle Haymanot. "A Brief History of Debra Hayq Saint Stephen Abuna Iyesus Moa Communal Monastery in South Wollo." BA. Thesis, Trinity Theology College, 2005.

Kaplan, Steven B. "The Monastic Holly Man and The Christianization of Ethiopia; 1270-1468." Unpublished Diss. Hebrew University, 1982.

Knowles, David. From Pachomius to Ignatius; A Study in the Constitutional History of the Religious Orders. London: Oxford University Press, 1966.

Mezgebu Kassa. "The Mystical Experience of the Monastic Life in the Traditional Context of the Ethiopian Orthodox Tewahido Church." Unpublished BA. Thesis, Trinity Theology College, 2001.

Parrinder, Geoffrey. Religion in Africa. London: Pall Mall Press, 1969.

Prown, Jules David. "Mind in Matter." An Introduction to Material Culture Theory and Method. http:/WWW.jstor.org/stable/1180761.

Sergew Habla Sellassie. The Church of Ethiopia: A Panorama of History and Spiritual Life. Addis Ababa, 1970.

-------------- . Ancient and Medieval Ethiopian History. Addis Ababa: United Printers, 1972.

Sileshi Mengstie. "A History of Dimma Giorgis Monastery from Foundation to 1974." Unpublished BA. Thesis, History Department, Addis Ababa University, 1998.

Tadese Tamrat. Church and State in Ethiopia. 1270-1527. Britain: Oxford University Press, 1972.

Tigab Bezie. "The Ethiopian Claim on the Monastery of Der Es-Sultan in Jerusalem, 19850s — 1994." Unpublished MA. Thesis, History Department, Addis Ababa University, 2001.

Zewdie Geber Egziabher. "Investigation of Ancient Christianity in South Wollo." Unpublished BA. Thesis, Trinity Theology College, 2007.

አባሪ -1- ከካሴት የተገለበጡ ቃለ መጠይቆች

ካሴት ቁ.1፣ **Side A**

ቃል አቀባይ 1፣ መምህር ፍቅረ ዮሐንስ (የገዳሙ አበምኔት)

ጥያቄ፡- የገዳሙ ስያሜ ምን ይባላል?

መልስ፡- የገዳሙ ስያሜ የሁሉም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስያሜያቸው ገዳም ነው የሚባሉት፡፡ ገዳም ማለት ደግሞ ከዓለም የራቀ፣ በእግዚአብሄር ቋንቋ ዱር ማለት ነው፡፡ አባታችን ቅዱሳን ከአለም ርቀው ከሰው ተለይተው ራቅ ብለው በዱር በጫካ ይኖሩ ስለነበር ያንን ስያሜ ይዞ ገዳም ይባላል፡፡ ለገዳማት የተለየ ስያሜ ይኖራቸዋል፡፡ ይህ ገዳም ሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም ደብረ ነጎድጓድ ይባላል፡፡ ገዳሙ በመጀመሪያ የያዘውን ስያሜ እንደያዘ ነው የተቀመጠው፡፡ በመጀመሪያ ገዳሙ የተመሰረተው በ9ኛው ክፍለ ዘመን በ862ዓ.ም ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን የተሰራው በአጼ ድል ነአድ በአክሱም ዘመነ መንግስት በካሌብ ሰላማ ነው፡፡ እኒህ ካሌብ ሰላማ የሚባሉት በቤተ ክርስቲያን መዝገብ ካሌብ ሰላማ የሚባል እንሰማለን፡፡ እሳቸው ምስራቁን እያስተማሩ እዚያ ማዶ ደብረ እግዚአብሐየር ላይ ሲደርሱ አሻግረው ይህን ቦታ ዙሪያውን በውሃ የተከበበ ደሴት መሆኑን ሲያዩ በዚህ አካባቢ ሰዎች ይኖራሉ? አኗኗራቸውስ እንዴት ነው? ብለው ሲጠይቁ አምልኮተ ባእድን ይዘው ዘንዶ እንደሚያመልኩ ነገሯቸው፡፡ እሳቸውም መጥተው ቦታይቱን በስመ እግዚአብሄር ስም ባርከው ተመልሰው ወደ ንጉሱ ሲደርሱ የቦታውን ሁኔታ ተናግረዋል፡፡ ሲባርኳትም ያ ዘንዶ ጠፍቷል፡፡ ንጉሱም መጥተው ደብረ እግዚአብሄር ላይ ቤተ መንግስት ሰርተዋል፡፡ ከቤተ መንግስቱ ጋም አያይዘው የእግዚአብሄር አብን ቤተ ክርስቲያን ሰርተዋል፡፡ ከዚያም እዚህ ቦታ መሰረት ጥለው፣ ቤተ ክርስቲያን አንጸው ታቦት ለማስገባት የማንን እናግባ በማለት ልዑል እግዚአብሔርን በማመለከት እየተወያዩ እያለ ቶራ የምትባል አውሬ በትከሻዋ እንደ አህያ ተጭና እመካከላቸው ተገኘች፡፡ በኋላም የቅዱስ እስጢፋኖስንና የቅዱስ ጊዮርጊስን ታቦት አግኝተዋል፡፡ ሁለቱንም ታቦት ለመጀመሪያ ጊዜ ያስገቡት እዚሁ ነው፡፡ ያንን አስገብተው ቦታውን ደብረ ነጎድጓድ ብለው ሰይመው ብዙ አገልጋዮችን አድርገው ወደ 300 ሊቃውንት በጊዜው እያገለገሉ ይኖሩ ነበር ይባላል፡፡ ነጎድጓድ ማለት ቅልቅል ማለት ነው፡፡ ነጎድጓድ ማለት ደግሞ በአባታችን ስያሜ ደረቅ ደመናና እርጥብ ደመና ተቀላቅሎ

ነጎዳ ያመጣል። ይህም ንጉስ ቤተ መንግስቱና ቤተ ክህነት አንድ ሆነው ስለመሰረቱት ደብረ ነጎድጓድ ብለው ሰይመውታል። ሁለተኛም በእለተ አርብ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል የክርስቶስን ደም አለምን ለማዳረስ ሲረጭ እዚህ ቦታ ላይ ግን በተለየ ሁኔታ ሁሉም እንዳይቀር አድርጎ ቀብቶታል ይባላል። ያን ጊዜም ነጎድጓድ ተሰምቷል ይባላል። በዚያው ቦታው ደብረ ነጎድጓድ ተባለ የሚል ነገር አለ። በኋላ ግን በአቡነ ኢየሱስ ሞአ የአስተዳዳሪዎቹ ስም አቃቤ ሰዓት ይኮኖ አምላክ የቦታውን ስም ሳይለውጥ ሰይሟል። በዚህ ቦታ የሚቀመጡ መምህራንና አስተዳዳሪዎቹ አቃቤ ሰዓት ይባሉ ነበር። አጼ ይኩኖ አምላ ከአቡነ ኢየሱስ ሞአ ጋር ሲገናኙ ወደ ደሴቲቱ ሳይገባ እሱ በበቅሎ ወደ ባህሩ ገብቶ እሳቸው በታንኳ ሆነው ነው የተነጋገሩት። በዚያን ሰዓት ስድስት ሰዓት ስለነበር ደወል ተደወለ። ይህ የምሰማው ደወል የምን ደወል ነው ብሎ ሲጠይቃቸው ለስራ፣ ለጸሎት በ12፣ በ3፣ በ6፣ በ9፣ ማታ በ12 ሰዓት፣ ሌሊት ደግሞ ለሰዓታት የሚደወል ነው። ሲሉት እንግዲያውስ ከአሁኑ ሰዓት ጀምሮ ከእርስዎ ጀምሮ በአጠቃላይ የእርስዎ ተከታዮች በሙሉ አቃቤ ሰዓት ይባሉ። አቃቤ ሰዓት ማለት ደግሞ በቤተ መንግስት እንደ አማካሪ፣ እንደ መንፈሳዊ ፍርድ ሰጪም ሆኖ አብሮ የሚቀመጥ ነው። ሲላቸው እንግዲያውስ እኔ ከደሴቲቱ አልወጣም በእኔ ምትክ ዛኢየሱስ የሚባሉ፣ ከእሳቸው ቀጥሎ የነበሩ የሳቸው ተማሪና በቅድስናም የተካኑ ስለነበሩ ዛኢየሱስን ሰጥቻለሁ። እሱ አቃቤ ሰዓት ሆኖ ይኑር። በቤተ መንግስትም በቤተ ክህነትም እያለ ይቆይ። ለመጀመሪያ ጊዜ አቃቤ ሰዓት የሚባለው ስም የተገኘው ከዚሁ ቦታ ነው።

ጥያቄ፦ በገዳሙ የሚገኙት መነኮሳት የስራ ድርሻና የአስተዳደር መዋቅር ሁኔታ ምን ይመስላል?

መልስ፦ መነኮሳት በአስተዳደራቸው ከላይ ጀምሮ አበምኔት ይባላል። ምኔት ገዳሙ ነው። አበ ደግሞ አባት ነው። አበምኔት የገዳሙ አባት ይባላል። ከአበምኔት ጀምሮ እስከታች ድረስ በተዋረድ የአመራር አካላት አሉ። የየገዳማቱ ስርአት ግን ይለያያል። እዚህ ቦታ ከአቡነ ኢየሱስ ሞአ ጀምሮ አቃቤ ሰአት ይባላል። አበምኔት መምህር ነው። ከመምህሩ ቀጥሎ አፈ አቃቤ ሰአት አፈ መምህር የሚባል አለ። ያ ደግሞ የመምህሩ ረዳትና እንደራሴ ወይም ደግሞ መምህሩ በሌለበት ጊዜ ገዳሙን የሚመራ ማለት ነው። ወይም መምህሩ ሲደክማቸው መምህሩን ተክቶ የሚሰራ ማለት ነው። ለወደፊትም መምህሩ በሚደክምበት ጊዜ

ወደመምህር ደረጃ የሚደርስ ማለት ነው። ቀጥሎ አማካሪዎች (ሀሬቶች) የሚባሉ አሉ። ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ ናቸው። እነሱ ደግሞ በአባትነታቸው፣ በእድሜያቸው፣ በእውቀታቸው ከፍ ያሉ ሆነው በማህበረ መነኮሳቱ ይመረጣሉ። ሀሬት ማለት ምርጦች ማለት ነው። ሐሬቶች ከአበምኔቱ ጋ በመሆን ስርዘተ ገዳሙን በመጠበቅና በማስጠበቅ የሚመሩ ናቸው። ማህበሩን በስራ፣ በመቅነን የሚያስተነትን መጋቢ ይባላል። መጋቢ ማለት መገበ፣ ተሾመ ማለት ነው። በማስተዳደርም በመሾምም የሚጎድለውን ነገር ለአባቶች በማቅረብ የሚመራ ይሆናል። ከእሱ ቀጥሎ ጸሐፊ፣ ገበዝ አሉ። አርድእቶችን በስራ የሚያሰማራ ደግሞ ሊቀ ረድዕ ይባላል።

የስራ ድርሻቸው ሀሬት በአባቶች ተመርጠው ገዳሙ የቀለብ፣ የአሰራር ወይም የስርአተ ገዳም፣ የመንፈሳዊ ሂደት ጉድለት ሲኖር ተሰባስበው የሚወስኑ፣ ስለ በጀት ሁኔታ፣ ስለ ልማት፣ ገዳሙን በሚመለከት ከበድ ያሉ ነገሮች ሲመጡ ተሰባስበው የሚመክሩ ናቸው። እነሱ በሚሰባሰቡበት ጊዜ ጸሀፊው ቃለ ጉባኤ ይይዛል። እነሱ ተፈራርመው የወሰኑት ውሳኔ ያልፋል። መጋቢው አጠቃላይ በገዳሙ ያሉትን ነገሮች የሚያንቀሳቅስ ነው። ለምሳሌ እንግዳ ሲመጣ ተቀብሎ እግሩን ታጥቦ ማረፊያ ቦታ ይሰጠዋል። ምግብ ይሰጠዋል። አድሮ የሚሄድ ከሆነ በማለዳ ተሰናብቶት በሰላም ካሰብክበት ያድርስህ ብሎ በጸሎት ይሸኘዋል።የሚቆይ ከሆነ ደግሞ ወደመምህሩ አቅርቦ እንዲህ ያለ ሰው መጥቷል፤ እናንተን መስይ፣ አለምን ትቼ መንኜ ልኖር ነው ብሏል ይላል። ከዚያ ለምን እንደመጣ ይጠየቃል። 1ኛ በእምነቱ፣2ኛ በምግባሩ፣ 3ኛ ወደ ገዳሙ ለመምጣት፣ ለመመነን የቻለበት ምክንያት ምንድን ነው? ተብሎ ይጠየቃል። ለምን እንደመጣ ተጠይቆ የአመክሮ ጊዜ ይሰጠዋል። የአመክሮ ጊዜ ማለት የደጅ ጥናት ጊዜ ነው። ከዚያ በስራም፣ በጸሎትም ሆነ በመንፈሳዊ ሂደቱ ክትትል እንዳለውና እንደሌለው እየተመረመረ ይሄዳል። ወደዚያ ለመሄድ የማይችል ከሆነ እሱው ራሱ እኔ ወደመጣሁበት ቦታ ልመለስ ነው። ወይም ወደሌላ ቦታ ልሄድ ነው ብሎ ጸሎት ተቀብሎ ተሰናብቶ ይሄዳል። ወይም ገዳሙ የሰውየውን ሁኔታ መዝኖ አንተ በዚህ ለመኖር አትችለውም፤ ይከብድሃል፤ በዚህ ቀንበር ለመሄድ አትችልም። ምክንያም ምናኔ ማለት በምግብ ከሰው ተቆንኖ ነው የሚኖረው። በማደሪያም ስፍራ ከሰው ነው የሚሰጠው። ልብስም እንደ መነኮሳቱ ነው የሚሰጠው። ምግብም እንደ መነኮሳቱ ነው። ስራም በተለያየ መስክ ይሰማራል። የሚሰራውም እንደ አቅሙ ነው። በጸሎት ጊዜም

ሲደወል ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣል። ይህን ይህን የማያሟላ ከሆነ፣ አቅሙ የማይፈቅድለት ከሆነ፣ የህሊና ድክመት ካለበት እንዲሰናበት ይደረጋል።

የስራ ደወል የሚደወለው ሁለት እንጨቶችን በማጋጨት ነው። ያን ጊዜ ሁሉም በየስራ መስኩ ይሰማራል። የስራ ክብደት ያለበት ወደ ጋቢው ቀርቦ እኔ የስራ ክብደት ስላለብኝ ሰው ይጨመርልኝ ይላል። የስራ ዘርፉ ብዙ ነው። በአትክልት፣ በእርሻ፣ አትክልት በመሸጥ፣ ጸሎት በማድረግ፣ በመማር በማስተማር፣ የዶሮ እርባታ፣ ንብ እርባታ፣ በከብት እርባታ የሚሰሩ አሉ። ብዙ የስራ ዘርፍ ስላለ መደበኛዎቹ በዚያው በስራ ዘርፋቸው ይሆናሉ። ምክንያቱም ስራውን ሊነጥሉት አይችሉም። ሶስት ሰዓት ሲደርስ የጸሎት ደወል በድንጋይ ይደወላል። እዚያው አቡነ ዘበሰማያት 12 ጊዜ ይደግማሉ። ከዚያ ስራቸውን እየሰሩ 6 ሰዓት እንዲሁ ይደወላል። ከዚያ ሊቀረድዕ ከመጋቢው ምሳቸውን ተቀብሎ ይመጣል። መመገቢያቸው ዘጠኝ ሰዓት ቢሆንም ስራው እንዳይደበልና እንዳይስተጓጎል ምንም ወጥ የሌለው ዳቤ ተነባብሮ አሉበት ቦታ ሆነው ይበላሉ። ካህናትና ሽማግሌዎች ግን ምሳ አይበሉም። 7፡30 ሲሆን የእንጨት ደወል ይደወላል። ከዚያ ካህናትና አረጋውያን ዳዊት ይደግማሉ፣ ውዳሴ ማርያም፣ መልክአ ኢየሱስ፣ ሳልነከ ደግመው በአንድነት በህብረት ዳቤ ወደ ሚጋገርበት ተግባር ቤት ሂደው አንዱ ካህን የሚጋግሩት ሁሉ መሬት ወድቀው ጸሎት ይቀበላሉ። ያ አባት ገዳሙን ጠብቅልን፣ በጸሎታችሁ እርዱን እያሉ ገዳሙን የሚረዱትን ባሉበት ጠብቃቸው፣ በየተሰማራንበት በሰላም አውለህ አግባን፣ እግዚአብሄር አምላክ ሆይ በረድኤትህ በበረከትህ አትለየን፣ የቅዱሳን በረከት ከእኛ ጋር እንዲሆን እመቤታችንም በቃል ኪዳኗ በጸሎቱ እዳትለየን ብሎ ጸሎት አድርጎ አቡነ ዘበሰማያት ይሰጣል። ከዚያ በኋላ መቁነኑ ይከፈትና 9፡15 ወይም 9፡30 ይሆናል ካህናትም ሽማግሌዎችም መቁነናቸውን ከመጋቢው እየተቀበሉ ቤተ እግዚአብሔርን ያስፋልን ብለው እጅ እየነሱ በየቤታቸው ወስደው ይመገባሉ። ምሳ የበሉ አርድእቶች ግን በ11 ሰዓት መጥተው ከመጋቢው መቁነናቸውን ይወስዳሉ። የመጋቢው ድርሻ ይህ ነው። ጸሐፊም ሂሳቡን፣ የሚወጣውን ገንዘብ ይቆጣጠራል። በገዳም ብዙው በእምነት ነው የሚሰራው። ቦታውም የእምነት ቦታ ስለሆነ እንደው ጽሁፍ የያዘው ተብሎ ነው። ዛሬ በዘመናችን ዘመናዊ ትምህርት የተማሩትም አብረው እየመነኑ ስለሆነ እንዳግባቡ እንዲያዝ ከእምነት ጋር ጎን ለጎን ይደረጋል። ሊቀአበው የሚባለው ደግሞ በጣም የደከመና የማይችል ካለ መቁነናቸውንና ውሃ በየጊዜው ያቀርባል።

በገዳሙ ያሉትን አስታማሚ፣ ረዳት ማለት ነው። የሽማግሌዎችን ልብስ በየቤታቸው ያጥባል፣ መቁነናቸውን እየወሰደ፣ ቤታቸውን እያጸዳ ያገለግላል።

ካሴት ቁ.1፣ Side B

ጥያቄ፡- በዚህ ገዳም ውስጥ የሚኖሩት ምን ምን ተብለው ነው የሚሰየሙት?

መልስ፡- አንድ ላይ ሲሰየሙ ማህበረ መነኮሳት ይባላሉ። የመለኮሳት አንድነት ማለት ነው ማህበር። የመነኮሱት መነኮሳት ሲባሉ ገና በአመክሮ ላይ ያሉት ደግሞ አርድእት ይባላል። አርድእት ማለት ረዳቶች፣ ረዳት ማለት ነው። እነዚያ ብዙ ደረጃ ደርሰዋል። ለምሳሌ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እዚህ ቦታ ላይ በአርድእትነት ነበሩ። እስከ 7ዓመት፣ 10 ዓመት ቆይተዋል። በሰባት አመታቸው ምንኩስና ተቀብለው ወደ ምንኩስና ቀንበር ገብተዋል። አባቶች መነኮሳትም መጀመሪያ በስራ ይፈተናሉ። የመነኮሱት መነኮሳት ይባላሉ። ከፍ ያሉት አረጋውያን ደግሞ አበው ይባላሉ። አበው ማለት አባቶች ማለት ነው። አርድእቶችም የትምህርት ጊዜ አላቸው። በበዓላት ቀንና ማታ ማታ ይማራሉ። የስራውም ጊዜ እንዳይቀርባቸው፣ ተግባረ እዱም እንዳይቀርባቸው፣ የትምህርት ጊዜያቸውን እየተማሩ እዚሁ የክህነት ትምህርት ይማራሉ።

ጥያቄ፡- የአለባበስ፣ የጸሎት፣ የአመጋገብ የመሳሰሉት ሁኔታዎች እንዴት ነው?

መልስ፡- ምግቡ የሚሰራው በአንድነት ነው። አመጋገባቸውም በአንድ ተቆንነው ነው። አርድእቶች በስራ ቀን ስራ ከዋሉ በሰባት ሰዓት ምሳ አላቸው። ያም ስራው ክብደት ስላለው አንደኛ ስራውን ያስቀራል፣ ሁለተኛም የአገልግሎት ጊዜያቸውን ይቀንሳል። ምክንያቱም ሰባትና ስምንት አመት የሚያገለግለው አርድእት በጾም እየሰራ ከሆነ አንድ አመትም አያገለግልም። ምክንያቱም ስጋው እየደከመ ስለሚሄድ ከስድስት ሰዓት በኋላ መስራት አይችልም። አካባቢው በርሃ ስለሆነ ውሃ ጥሙም ስለሚያስቸግር በገዳሙ ውሳኔ ሰባት ሰዓት ላይ ምሳ እንዲወጣላቸው ተደርጓል። የበአል ቀን ሆኖ ስራ የማይሰራበት ከሆነ ግን ሁሉም ዘጠኝ ሰዓት ነው የሚመገቡት። ሁሉም በአንድነት ጸሎት አድርገው ጸሎታቸው ሲያበቃ ወደ መቁነን ቤት ሄደው መቁነናቸው ወስደው አቆይተውም ወይም እስከማታ ድረስ አስፋፍለው የሚኖሩ አሉ። ዳቤ ዝም ብሎ ወጥ የሌለው አለ፤ እንጀራም ካለ ያንን ወስደው ይመገባሉ። ምናልባት ሲታመሙ ደግሞ እንደነግም ሆነ እንደስሲጥ እንደተልባ ያለ ነገር

ትንሽ በጥበጥ አድርገው ፈታፍተው ለአረጋውያንም እንደ ዘመናቸው ታይቶ ሲቀ አበው የሚባለው የሚያደርግላቸው ነገር ይኖራል፡፡ በአንድነት በተሰራ ቤት መመገባቸውም አንድም የአንድነት ገዳም ስርዓተ ግብሩ በአንድነት ሰርቶ በአንድነት መመገብ ነው፡፡

በአለባበስ በኩል ደግሞ ገዳማዊ አለባበስ አላቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ በገዳም ውስጥ ዳበር ያለ ወይባ የገባ ይለብሳሉ፡፡ የተለየ ነገር መልበስ አይችሉም፡፡ ስራቀሚስ ሁሉም ይለብሳሉ፡፡ በአመክሮ ላይ ያሉ ከሆነ የአመክሮ ቆብ ከክር የተሰራ ያደርጋሉ፡፡ የመነኮሱት የሚለብሱት ቆብ ዳበር ያለ የተሻሻለ ሳይሆን ሰውነትን የማያራቁት ሆኖ ያታያል፡፡ ለአበምኔቱ ካባ እንደፈረጅያም ያለ መደረቢያ ይፈቀዳል፡፡ ለአረጋውያኖቹም እንደ እድሜያቸው ደረጃ ገዳማዊ አለባበስ አለ፡፡ የሚቆነኑት አቡጀዲ ከሆነ ወይባ ይነክሩታል፡፡ ወይባ ማለት ወየብ የሚያደርግ ማለት ነው፡፡ ወይባ ከዋርካ፣ ከቀረጥ፣ የዋርካውን ቅርፊት ይልጡና ቀጥቅጠው ጸሐይ ላይ ደረቅ እንዲል አድርገው በውሃ አንፈቅፍቀው ውሃውን አጥልለው አቡጀዲውን ሲነክሩት ቀላ ያለ፣ ዳበር ያለ ይሆናል፡፡ ከገበያ የሚገዙትም ወይባ የገባ የመሰለ ነው፡፡ ከዚያም የተሻለ ልብሰ ማርያም የተባለ አለ፡፡ ያ ቢጫ አይነት ነው፡፡ መነኮሳቶች በማዕዳቸው መቅለልና በልብሳቸው አዳፋነት ወይም ቀላልነት፣ ሻካራነት መታወቅ አለባቸው፡፡ ይኸው ነው የመነኮሳት ከዓለም መለየታቸው፡፡ እንዲያውም መነኮሳት የሚታወቁት በአለባበሳቸውና በአመጋገባቸው ነው፡፡ የተሻለ ለመልበስ እነሱም አይፈልጉም፣ በገዳማዊ ህይወትም አይፈቀድም፡፡ የመነኮሳት ልብስ የሚሰጠው ከገዳሙ ነው፡፡ አቡጀዲም ሆነ እንደ ካሽመሪ ወፈር ያለ ነገር ይሰጣቸዋል፡፡ ያንን አሰፍተው ይለብሳሉ፡፡ አንዳንዶቹ አቡጀዲውን ወይም ካሽመሪውን አጠር ወይም ረዘም ያለ አድርገው ይለብሳሉ፡፡ ይህም ጨርሶ ፍላጎትን መግታት እንዳይሆን ተብሎ የሚታለፍበት ሁኔታ አለ፡፡ ይሁንና ገዳሙ የተቻለውን ያህል ልብሳቸውንና መቁነናቸውን ያዘጋጃል፡፡

ጥያቄ፡- የጸሎት ስርዓትስ እንዴት ነው? በጋራና በግል የሚጸለይ አለ?

መልስ፡- ሌሊት ደወል በተደወለ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂደው የተቻለውን ያህል ይጸልያሉ፡፡ ሰዓታት የሚቆሙ ሰዓታት ይቆማሉ፡፡ በህብረት የሚጸለይ ጸሎት ዳዊት አለ ያንን በህብረት ይጸልያሉ፡፡ የበአል ቀን በሆነ ጊዜ ዳዊት የሚዘልቅም፣ ወንጌለ ዮሐንስ፣ አርጋኖንም፣ ውዳሴ አምላክንም እንደ ራስ ፈቃዳቸው ይጸልያሉ፡፡ የማህበር ጸሎት የሚባለው በ12 ሰዓት፣ በ3 ሰዓት፣ በ6፣ በ9፣ በ12 ሰዓት አቡነ ዘበሰማያት የሚባልበት ሰዐት ነው፡፡

ጌታችን በምትጸልዩበት ጊዜ አባታችን ሆይ ብላችሁ ጸልዩ ባለው መሰረት ይጸልያሉ። የሚጸልዩት እንደ ችሎታቸው ሲሆን ችሎታቸው ዝቅተኛ ሆኖ አቡነ ዘበሰማያትና ጸሎተ እግዚትነ ማርያም ወይም እግዚኦ ማህርነ ክርስቶስ ብቻ መቁጠሪያ ይዞ ክራላይሶን እያለ እንደ ችሎታው ይቆጥራል። ጾሙንም እስከተፈቀደው ብቻ ይጾማል። ከዚያ በላይ እጾማለሁ ካለ አይከለከልም። ከዚያ ዝጋት፣ አርምሞ የሚባል አለ። ለመዝጋት የሚችለው ማህበሩ ይችላል ብሎ ፈቅዶለት፣ በጸሎት ተወስኖ ይኑር ካሉት የማህበሩን ጸሎት ተቀብሎ ይዘጋል። ሌላም ከሆነ ከማህበሩ አስፈቅዶ ይኖራል። የእርዳታ፣ የአገልግሎት ጊዜው እየደከመ ከሄደ በጸሎት ሳገልግል ፍቀዱልኝ ብሎ ይጠይቃል። ለመዝጋትም ማህበሩን እያስፈቀደ ይኖራል። በትርፍ ጊዜያቸው ግን እዚሁ ገዳሙ ውስጥ መማር፣ መጸለይ ይችላሉ።

ካሴት ቁ.2፣ **Side A**

ቃል አቀባይ 2፣ እማሆይ እህተ ማርያም ኪሮስ (ጉዳይ አስፈጻሚ)

ጥያቄ፡- በገዳሙ የሚገኙ እእናቶች የስራ ድርሻና አስተዳደር ሁኔታ ምን እእንደሚመስል ቢነግሩኝ?

መልስ፡- በገዳሙ ያለው የስራ ድርሻ ሁሉም በየሙያው ይሰራል። ሸመና የሚሰሩ አሉ፣ ጥልፍ የሚጠልፉ አሉ፣ ልብስ ስፌት የሚሰፉ አሉ፣ ወፍጮ የሚፈጩ ልጆች አሉን፣ የጓሮ አትክልት የሚያለሙ አሉ፣ ደሴ ሱቆች አሉን እዚያም ምርት የሚሸጡ አሉ። ሐይቅ ከተማ ላይ ወፍጮታቤት አለ እዚያም እናቶች ወፍጮ ያስፈጫሉ። እዚህም እገዳሙ አካባቢ ወፍጮ አለን እናቶች ለህዝቡም፣ የካህናት ማሰልጠኛውም፣ የወንዱን ገዳም እየፈጩ ያገለግላሉ።

ጥያቄ፡- የእርስዎ የስራ ድርሻ ምንድን ነው?

መልስ፡- የፀሎት ሰዓት የማህበር ጸሎት ሌሊት 10 ሰዓት ይደረሳል።እእስከ 1 ሰዓት ድረስ ኪዳን አድርሰንእእንወጣለን። ከ1 ሰዓት በኋላ ቤታቸው ሄደው ያልጨረሱትን ፀሎት ካለ ይጨርሳለሉ 2:00 ሰዓት የስራ ሰዓታችን ነው 6 ሰዓትእእንወጣለን። 6 ሰዓት የማህበር ፀሎት ይደወላል። ባለችን ቤተ ክርስቲያን ገብተን ዳዊትና ውዳሴ ማርያም ደግመን እንወጣለን። 7 ሰዓት የቤተ እግዚአብሔር ድርጎ ይደወላል 8 ሰዓት ተመልሰን ወደ ስራ እንገባለን። 11 ሰዓት እእንወጣለን። 11 ሰዓት ተኩል የማህበር ፀሎት ይደወላል የማህበር

ፀሎት ከጨረስን በኋላ 12 ተኩል ኪዳን የሚያደርሱል አባት አሉ። ከእሳቸው ውዳሴ ማርያም 2:00 ሰዓት ይጨርሳሉ። ከዚያ በኋላ የየራሳቸውን ፀሎት ያደርሳሉ መተኛት የሚፈልጉም ይተኛሉ።

ጥያቄ፡- በአጠቃላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ስንት የፀሎት ጊዜ አላችሁ? በጋራና ለየብቻቸው የምታደርሱትስ?

መልስ፡- በጋራ የምናደርገው ሦስት ጊዜ ነው። ጠዋት ኪዳን ላይ፣ 6:00 ሰዓት፣ የማታታ። በግል ግን መጽሐፉ የሚያዘን የአቀጣጠር ሁኔታታአለ የየግልም ይኖረናል። የየግሉ እንደየአቅማችን ነው። ብርቱው መፍሐፉን ሲደግም ያድራል ደካማው ደግሞ እንደአቅሙ ነው።

ጥያቄ፡- የምግቡ አይነት ምንድን ነው ?

መልስ፡- ሰኞ፣ ረቡዕና አርብ ዳቤ ነው። ማክሰኞ፣ ሀሙስ ፣ ቅዳሜና እሁድ እንጀራ ነው።

ካሴት ቁ.2፣ **Side B**

**ቃል አቀባይ 3 አባ ፍቅረ ማርያም (የገዳሙ ሙዚየም አስጎብኝ)**

ጥያቄ፡- በሙዚየም ውስጥ ተመዝገበው ያሉት ጥንታዊ ቅርሶችን በዝርዝር ቢነግሩኝ?

መልስ፡- የነገስትት ዘውድ፣ የራስቁር ብዛት 3፣ አንድ የአፄ ዮሀንስ የራስ ቁር ነው። ኩስኩስት፣ ቀርነ ማይ ብዛት 1፣ ወንጌል የአቡነ ኢየሱስ ሞአ ብዛት 1፣ ወንጌል ብዛት አንድ፣ ዳዊት ብዛት አንድ ዳዊት ብዛት አንድ፣ ኦሪት ብዛት አንድ፣ (ይህ ከተፃፈ 800 ዓመት ዕድሜ ያለው ነው።) ታምረ ማርያም ብዛት አንድ፣ (በ17ኛው ክፍለ ዘመን የተጻፈ)፣ ታምረ ማርም (በ17ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ የተጻፈ) የሁለቱ ልዩነት አንደኛው የመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ስዕልና የቅዱስ ጊዮርጊስ ያለበት ነው። የተፃፈበት ዘመንና በውስጣቸው ያለው ስዕል ነው። በ17ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የተጻፈው ታምረ ማርያም ለየት የሚያደርገው የአባቶች የትናንት ህይወት ለማሳየት ከእመቤታችን እግር ስር የወደቀ አንድ ስዕል ይታያል። ይህ ቅዱሳን አባቶች ለእመቤታችን የሚሰጡት ክብርና ከመቤታችን እግር ስር መሆናቸውን ለማሳየት ስዕላቸውን ከእግሯ ስር እንደወደቀ አድርገው ስለው ይታያል። ሁለተኛው ደግሞ በዚህ ገዳም ለቅድስና ደረጃ የደረሱ አቡነ ብስጣውሮስ

የተባሉት አባት ያስፃፉት ታምረ ማርያም ነው፡፡ በመጀረመሪያው ገጾቹ ላይ ጌታ ሲያርግ ና የጌታን ስነ ስቅለት የያዘና በውስጡ ስምንት የተለያዩ ስዕሎች ያሉት ነው፡፡

ሌላው ገድለ ሃዋርያት ነው፡፡ በ14ኛው ክፍለ ዘመን የተፃፈና በመጀመሪያው ገድ አካባቢ የቅዱስ ዮሃንስ ወንጌላዊ ስዕል የያዘ ነው፡፡ ቀጥሎ ገድል ሰዓታት ነው፡፡ ከቅዱስ እስጢፋኖስ ጀምሮ ያሉ ሰዓዕታትን የህይወት ታሪክ ሙሉ በሙሉ የተፃፈበት ነው፡፡ ቀጥሎ ያለው ገድል ሃዋርያት፣ ገድል ሰማዕታት ነው፡፡ ይህ ገድል ሰማዕታት ሙሉ በሙሉ የሰማዕትነት ህይወታቸውን አንድ ባንድ ዘርዝሮ የሚያሳይ ነው፡፡ የሁለቱ ገድለ ሰማዕታት ልዩነቱ የየሰማዕታቱ አይነትና ብዛት ስላለው ለሁለት ተከፍሎ የተለያዩ ቅዱሳን ታሪክ ስለተፃፈበት ነው፡፡ ድርሳን ቅዱሳን የሚባለው የቅዱሳን መነኩሳት፣ የቅዱሳን ባህታውያን ሙሉ ለሙሉ ህይወታቸውን፣ የተጋደሉትን ተጋድሎ፣ የደረሰባቸውን መከራ፣ የብቃት ደረጃ እና ያስተማሩትንና የመከሩትን ህይወት የተፃፈበተን ነው፡፡ ቀጥሎ የዕጅ መስቀል ብዛት 8 ነው፡፡ በዚህ ገዳም ሲያስተዳድሩ የነበሩ አበምኔቶች ሲይዟቸው የነበሩ የዕጅ መስቀሎ ናቸው፡፡ ሌላው የመጾር መስቀል ሲሆን ብዛታቸው 4 ነው፡፡ መፃረ መስቀል ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ውጪም የሚሰጡት አግልሎት የኢትዮጵያን ያለ ስልጣኔ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ አንደኛው በጎንዳር ስልጣኔ የተቀረፀ መፃረ መስቀል ነው፡፡ ሁለተኛው በአክሱም ስልጣኔ ዘመነ መንግስት የዚያ ዘመን ዲዛይን የያዘ መፃረ መስቀል ነው፡፡ ሌላው መቋሚያ ነው ብዛቱ ሁለት ነው፡፡ አበምኔት ሲይዛቸው የነበሩ መቋሚያዎች ናቸው፡፡ ሌላው በትረ መስቀል ነው፡፡ ከሁሉ ለየት የሚለው በትረ መስቀል ገዳሙን ሲመሰርቱ የነበሩት አባት የአቡነ ኢየሱስ ሞአ መስቀል ነው፡፡ የተሰራው ከነሀስ፣ ከመዳብ እንዲሁም ከሌሎች ልዩ ልዩ ማዕድናት ነው፡፡ በአሰራሩም ለየት ያለ ነው፡፡ ቀጥሎም ያለው የገበታ ስዕል ነው፡፡

ቀጥሎ ተዘርጊ የብራና ስዕል ነው፡፡ 24ቱ ካህናት ሰማይ ነው ያለበት፡ የ24ቱ ካህናት ሰዓይ ስዕልና የ40እቱ አንስሳት የብሩቤል ስዕልን ነው ያያዘው፡፡ የተሳለው በ16ኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡ በመካከሉ የሚታየው የአርባእቱ እንስሳ የኪሩቤል በአንበሳ፣ በንስር፣ በሰው፣ በላም፣ ተስለው ይገኛሉ፡፡ በመካከላቸው እግዚአብሔር አብ ተቀምጦ ይታያል፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ዙፋን መሸከማቸውን ለአርባእቱ እንስሳ የሚያመላክት ናቸው፡፡ ቀጥሎ የአቃቢ ሰዓት አቡነ ሰረቀ ብርሃን ያሰሩት አውድ ነው፡፡ ይህ አውድ ዝርግ ሰሀን አይነት

ነው። የተሰራው ከነሀስ የተሰራው በ14ኛው ክፍለ ዘመን ነው። በዙሪያው የ24ቱ ካህናት ሰማይ ስዕልና ስማቸው፣ የ12ቱ ሃዋርያት ስዕልና ስማቸው እንዲሁም በተከታታይ የእመቤታችን ስዕሎችና የጌታ ስቅለት ከውስጡ አለበት። ሌሎችም የግዕዝና የአረብኛ ፅሑፎች ይገኙበታል። ሌላው በጨርቅ ላይ የተሳለች ስዕለ ማርያም ናት። ብዛት አንድ ነው ይች ስዕል ለጌታችን ለመድሃኒታን ለእየሱስ ክርስቶች በህጻንነቱ ወቅት አንዲት ዕጌረዳ እሸሃማ ስትሰጠው ይታያል። ይህ ትርጉሙ በእለተ አርብ አክሊስ ሶክ እንደሚቀናጅ በመንፈስ ቅዱስ ታውቅ ስለነበረ ብለህ ብለህ መሰቀልህ አይቀርም ስትል በህፃንነቱ እሾህ ያለው ዕጌረዳ ትሰጠዋለች። ቀጥሎ አትሮንስ ብዛት አንድ ነው። በጣም ለየት ያለነው፣ አሰራሩ በየት ገባ በየት ወጣ ለማለት አይቻልም ልክ እንደላሊበላ ሃውልት ተፈልፈሎ የተሠራ ነው። ሌላው ከነሀስና ከቆዳ የተሰራ አትሮንስ አለ። ቀጥሎ ደግሞ አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞአ ገዳሙን ሲያስተዳድሩ በነበረበት ጊዜ ይቀመጡበት የነበረው ወንበር ነው። ሌላው ከብረት የተሰራ መቀመጫው ቆዳ የሆነ ታጣፊ የመምህራን ወንበር ነው። ሌላው ከጥንት ከእንጨት የተሰሩ ማማሰያዎች፣ ጭልፋዎች እንደገናም ክክ አልበስል ሲላቸው የሚደቁሱበት ከእንጨት የተሰሩ የወጥ እቃዎች አሉ። ሌላው የድንጋይ መስቀል ነው። ይህ የድንጋይ መስቀል አባቶችን አቡነ ኢየሱስ ሞአ ለ52 ዓመት ያህል በገዳሙ ውስጥ ገዳሙን ሲያስተዳድሩ ቀን ቀን የማስተዳደሩ ስራ ይበዛባቸው ስነበር ሌሊት ሙሉ መስቀሉን ተሸክመው ይፀልዩ ነበር።

ቃል አቀባይ 4፣ አባ ገብረ ኢየሱስ ኢየሱስ ሞአ (መጋቢ)

ጥያቄ፡- ስምዎትንና በዚህ የአቡነ ኢየሱስ ሞአ ገዳም ያለዎትን የስራ ድርሻ ቢነግሩኝ?

መልስ፡- ስሜ አባ ገብረ ኢየሱስ ኢየሱስ ሞአ ይባላል። ዕድሜዬ 42 ነው። ስራየ መጋቢ ነው። የመጋቢው የስራ ድርሻ ያለውን ነገር በመቆጣጠር መጋቢው ያለውን ነገር ሁሉ ያወጣል፣ ያወርዳል። ማህበረ መነኮሳት ሲባል አርድእትና ቀዳሾችን ያጠቃልላል። በሚጠየቀው ሰዓት ደግሞ ሰውም ቢታመም የዳቤም ሆነ ሌላ የመቁነን ስራ አለ። የመቁንን ሰዓት ትልልቅ አባቶች ከሆኑ ከ9-10 ሰዓት ደረስ ባለው ይጾማሉ። በ10 ሰዓት መቁንናቸው ይወጣል። ይህ ትልልቅ አባቶች ከሆኑ ነው። አርድዕቶች በ7 ሰዓት ምሳ ይበላሉ። ከዚያ ወደ ስራ ይሄዳሉ እንደገና ደግሞ ሁለተኛ ሰርተው ሲመለሱ 11 ሰዓት ይቆነናሉ።

ጥያቄ፡ ምግብ የሚዘጋጅበት ሰዓት መቼ ነው?

መልስ፡- ምግብ የሚሰራው ሁልጊዜ ነው፡፡ በተለይ ሌሊት ከ9 እስከ ንጋቱ 1 ሰዓት ድረስ ዳቤ የመሳሰለውን ኀል መጋዎች ያዘጋጃሉ፡፡ ምግቡ የሚዘጋጀው ሌሊትና ቀንም ሊሰራ ይሰራል፡፡ ዕሁድን ቅዳሜ ከለሊቱ 4 ሰዓት ጀምሮ ይሰራሉ፡፡ በሌላ ቀን ግን ከሌሊቱ 9 ሰዓት ጀምሮ እስከ ጧቱ አንድ ሰዓት ይሰራሉ፡፡ ከዚህ በኃላ የሚሰሩም አሉ፡፡

ጥያቄ፡- ኀል መጋቢዎች ቁጠራቸው ስንት ነው?

መልስ፡- ኀል መጋቢዎች በቤተ እግዚአብሔር ውስጥ 4 ይገኛሉ፡፡ ጠላ ቤት አንድ፣ አንድ ወጥ ቤት፣ ሁለት ዳቤና እንጀራ የሚጋግሩ ናቸው፡፡ መቁንን የሚሰጠው መጋቢው ቢሆንም መጋቢው ካልተመቸው እነሱ ይሰጣሉ ፡፡ ተረዳድተንና ተሸፋፍነን ነው የምንሰራው፡፡ ድርሻው ግን የመጋቢው ነው፡፡

ጥያቄ፡- በጋራ የሚመገቡበትና ለየብቻ የሚገቡበት ሰዓት አለ?

መልስ፡- አለ፡፡ በጋራ የምንመገብበት ከብረ በዓል በሆነበት፣ ዝክር በሆነበት ወቅት ተማሪን ጨምሮ ሁሉም በገዳሙ ያለው በአጠቃላይ ከሌላም ቦታ የሚመጣው ሁሉ በአንድነት ይመገባል፡፡ በተለይ እንደ ልደት፣ ትንሳኤን በመሳሰሉት ትልልቅ በአል ላይ ተማሪው በሙሉ አብሮ ይበላል፡፡ የትንሳኤ ጊዜ እስከ ስምንት ቀን ድረስ አብረን እንቀምሳለን፡፡ ከሌላው ወራት ደግሞ ዝክር ሲሆን ከተማሪው ጋር አብረን እንበላለን፡፡ በአዘቦቱ ቀን ግን የየራሳችንን ነው፡፡ በየቃችን ድርሻ ድርሻችን ትቆነናለች፡፡ ንፍሮም ሆነ ዳቤ ድርሻችንን ነው የምንጠቀመው፡፡

ጥያቄ፡- በቀን የሚቀርበው ምግብ ልኬት አለው? አሁን እርስዎ መጋቢ ነዎት፡፡ ለኀል መጋቢዎች የሚያቀርቡት በኪሎ ለክተው ነው? ወይስ ዝም ብለው?

መልስ፡- በኪሎ ሳይሆን በሰው መጠን ነው፡፡ ዳቤ ከሆነ አንድ ይጋገራል፡፡ ያለ 8 ተቆርሶ ይሰጣል፡፡ በመጀመሪያ እህሉ ይፈጫል፡፡ ከዚህ እንደ ሰው መጠን ተተናትኖ ያዘጋጃል፡፡ በኪሎ እንዳይተመን በየቀኑ እንግዳ ስለሚመጣ ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ እንደ እንግዳው መጠን ነው የምናዘጋጀው፡፡ እኔ እስፈጭቸ አቀርባለሁ፡፡ ኀል መጋቢዎች ለክተው የሚዘጋጁት እነሱ ናቸው፡፡

ጥያቄ፡- የአገልግሎት ዘመን የተወሰነ ነው ወይስ እስሚያደክመዎት ነው የሚሰሩት?

ካሴት 3፡ Side A

መልስ፦ ይሄ ወሰን የለውም፡፡ ሰው እስከደከመው ነው የሚሰራው፡፡ ከደከመው ያላቅሙ አይሰራም፡፡ የተወከለው ሰው እስከደከመው ይሰራል፡፡ ወደ አባቶች እኔ ደክሞኛ ሌላ ሰው ቀይሩልኝ ይላል፡፡ ከዚህ ሌላ እሰራለሁ ብሎ እንዳቅሙ ይጠይቃል፡፡

ጥያቄ፦ የመጋቢና የኀል መጋቢዎች አመራረጥ ምን ይመስላል?

መልስ፦ ስርዓቱ ኀል መጋቢ መጋቢው ከአባቶች ጋር በሙሉ ስብሰባ ሳይሆን ከአባቶች ጋር በምክክር መጋቢው ያዘዋል፡፡ የመጋቢ፣ የፀሀፊ፣ የሊቀ ረድዕ የመሳሰሉት ምርጫ ግን በሙሉ በማህበረ መነኮሳት ነው ምርጫው፡፡ በስብሰባው ይሾማሉ፡፡ ሁለት ሶስት ሰዎች ያቀርባሉ፡፡ አንዱ ይፀድቅለታል፡፡ ለአንደኛው አንተ ባለ ተስፋ ተብሎ ፀሎተ ማርያም በሞላ ማህበሩ ደግሞ ስራውን ያስረክቡታ፡፡ ስርዓቱ በሞላ ማህበሩ እከሌ አበሉን ይህን ስራ ጥለንብሃልና ፈቃድህ ይሁንልህ ይላሉ፡፡ እንቢ ማለት የለም፡፡ አቅሙ እስከፈቀደ ሰርቶ ሲደክመው አባቶች ደከመኝ ብሎ ትንሽ አትርፉኝ ይላል፡፡ ሊቀጥልም ይችላል፡፡ ወይ ይቀይሩታል፡፡

ቃል አቀባይ 5፣ አባ ሀብተ ስላሴ ወልደ አምደ ስላሴ (ኀል መጋቢ ወይም ጋጋሪ)

ጥያቄ፦ ስምዎትንና የስራ ድርሻዎትን ቢገልፁልኝ?

መልስ፦ ስሜ አባ ሀብተ ስላሴ ወልደ አምደስላሴ እባላለሁ፡፡ የስራ ድርሻዬም በማህበረ መነኮሳቱ የተግባር ቤት ውስጥ የምግብ ዝግጅት ክፍል ወይም ጋጋሪ ነኝ፡፡

ጥያቄ፦ ምን ሰዓት ነው ምግብ የሚዘጋጀው?

መልስ፦ የስራ ቀን ከሆነ ሌሊት 8 ሰዓት እንገባለን እስከ ጠዋት 3 ሰዓት ሰርተን እንጨርሳለን፡፡ ከዚያ በኋላ ትንሽ የግል ፀሎት አድርሰን የምሳ ሰዓት ሲደርስ ወደ መስተንግዶ እንሄዳለን፡፡ ከ6 ሰዓት እስከ 12 ሰዓት ስናስተናግድ እናመሻለን፡፡ አንዱ በ7 ሰዓት ይወስዳል፤ አንዱ በ9 ሰዓት ይወሰዳል፡፡

ጥያቄ፦ የምግብ አዘገጃጀት ወይም አበሳሰል ሂደቱ ምን ይመስላል?

መልስ፡- ምግብ የሚባሰለው ሁለት አይነት ነው፡፡ አንደኛው ሳሳ ያለ እንጀራ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ዳቤ ነው፡፡ የምንጋግው በመጀመሪያ በማቡኪያው እናቦካለን፡፡ ካቦካን በኋላ 3 ቀን ቦክቶ አብሲት ጥለን አብሲቱ ከቀዘቀዘ በኋላ እንጋግረዋለን፡፡ እንጀራው ከዳቤው ትንሽ ሳሳ ይላል፡፡ እንጀራው ለእራት አንድ አንድ ይቆነናል፤ ይሰጣል፡፡ ዳቤው አንድ ቀን ተቦክቶ ወዲያው እፍለኙን እንጋግራለን፡፡ ጠላ የሚያዘጋጁት ለብቻ እላይ ናቸው፡፡ ጠላ የሚዘጋጀው በዚህ ገዳም ውስጥ ለባለወልድ ለቦታው ባለቤት ለአቡነ ኢየሱስ ሞአ፣ ለእስጢፋስና ለእመቤታችን ነው፡፡ በነዚህ ጊዜ በወር ውስጥ ጠላ ይኖራል፡፡ በዚህ ጊዜ እዚህ አዳራሽ ውስጥ በአንድነት ተሰብስበን ያለቸውን ነገር እንቀምሳለን፡፡ በሌላ ወቅት ጠላ አይዘጋጅም፡፡ በነዚህ በዓላት እና በአቢይ በኣላት ወቅት ነው ጠላ የሚዘጋጀው፡፡

ጥያቄ፡- የምታዘጋጁትን ምግብ ልኩን በምንድን ነው የምታውቁት?

መልስ፡- መጋቢው በማህበሩ ውስጥ ያለውን ቁጥሩን ይነግሩናል፡፡ እኛ ደግሞ እንግዳ ማስተናገጃ ብለን 10 ወይም 15 ትርፍ እናዘጋጃለን፡፡ እለት እለት ቁጥሩን መጋቢው ይነግሩናል፡፡ ስናቦካ የዳቤው ተለክቶ ነው የሚቦካው፡፡ መለኪያ ስሃን አለን፡፡ የምንለካው እንዳይበላሽ ነው እንጂ ሌላ ነገር የለውም፡፡ እንጀራው ግን ዝም ብለን እናቦካዋለን፡፡ ቡኮው ቢቀመጥም ችግር የለውም፡፡ ስንጋግር እንመጥነዋለን፡፡ ለእነዚህ ማባያዎች ወጥ ይሰራል፡፡ ሌላ የለም፡፡

ጥያቄ፡- መቁንን የምትሰጡበት ዕቃ የተወሰነ ነው?

መልስ፡- ወጥ መለኪያ ጭልፋ አለ፡፡ እንጀራ አንዳንድ ነው፡፡ ዳቤም በሶስት ማዕዘን ይቆረጥና ይሰጣል፡፡

ጥያቄ፡- በሰውነታችሁ ላይ የምታደርጓቸው ነገሮችስ ምን ምን ይባላሉ?

መልስ፡- ይህ ቅናት ዮሐንስ ይባላል፡፡ ወደ ሚስጢሩ ስንገባ እየሱስ ክርስቶስ አይሁዶች በሰንሰለት አስረው የጎተቱበት ሲሆን ራስን ወደ ስቃይ የማስገቢያ መንገድ ነው፡፡ አንድም የምንኩስና መለያ ነው፡፡ ቆብ፣ አስኬማ፣ ቀሚስ የምንኩስና መገለጫዎች ናቸው፡፡ እነዚህን ነገሮች ጠብቆ ሰውየው በህይወቱ ማለፍ አለበት፡፡ ሌላ ሰውየው የተጋድሎ ፍቅር ያለው ከሆነ የተለያዩ የስቃይ መሳሪያዎችን መጠቀም ይችላል፡፡ አንዱ በቆቡ ውስጥ እሾህ የሚያደርግ ይኖራል፡፡ ሌላው የብረት ሰቆችን በመታጠቂቀው ላይ የሚያደርግ ይኖራል፡፡ ያ

የሰውየው ፍላጎት ነው፡፡ ከአመንኳሽ የሚሰጠው ቆብ፣ ቀሚስና አክሴማ ናቸው፡፡ እነዚህ ግዴታዎች ናቸው፡፡

**ቃል አቀባይ 6፣ አባ ገብረ መድህን ገብረ ስላሴ (ቄስ ገበዝ)**

ጥያቄ፡- የእለት ተዕለት ስራዎን ቢነግሩኝ?

መልስ፡- የእለተ ተእለት ስራው የቤተክርስቲያን ግልጋሎት እንዳይቋረጥ መከታተል ነው፡፡ እኛ ገዳም ላይ የሚያስቸግር ነገር የለም፡፡ ሌላ ደግሞ ግብዝና በጣም ከባድ ነገር ነው፡፡ እዚህ ግን ሁሉም አውቆ የሚሰራ ነው፡፡ አዝገሮው የሚሰራ የማህብሩ አባላት እስከሁን የለም፡፡ እኔም እራሱ ስሙን ነው እንጂ የያዝኩት ገበዙ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ ናቸው፡፡ ሁሉም እሳቸውን እያሰበ ነው የሚሰራው እንጂ እኔ ይኽን ቀድስ፣ ለምን ቀረህ ብዬ የምቆጣረው የለም፡፡ ሁሉም የተቻለውን ያህል ጥረት ያደርጋል፡፡

ጥያቄ፡- አለባበሳቸው አሁን በለበሱት መልክ ነው ቅዳሴ የሚገቡት ወይስ ይቀይራሉ?

መልስ፡- አለባበስ ይቀያየራል፡፡ እንኳን ለቅዳሴ ቤተክርስቲያን ስንመጣ ቀን የለበስነውን ልብስ ለብሰን መምጣት የለብንም፡፡ የሌሊት ልብስ፣ ቀን የስራ ልብስ ተለብሶ መመጣት የለበትም፡፡ ይኽን ለብሰው ከመጡ ምክንያታቸውን እጠይቃቸዋለሁ፡፡ እቆጣቸዋለሁ፡፡ ስርዓቱም ስለተለመደ የሚያደርግ የለም፡፡ የቅዳሴ ልብስ የተለየ ነው፡፡ የስራውም ይለያል፡፡ ቀሚሱም ቆቡም ራሱን የቻለ አለን፡፡ በሚያልቅበትና በሚጎልበት ጊዜ ከአበምኔቱም ሆነ ከበጎ አድጊ ሰዎችም ጋር ተመካክሬ አሟላለሁ፡፡

**ቃል አቀባይ 7፣ እማሆይ ወለተ ስላሴ (ሊቀ ረድዕ)**

ጥያቄ፡- ሊቀረድእ ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ፡- ሊቀረድእ ማለት የመጋቢ ተከታይ ማለት ነው፡ ለምሳሌ መጋቢዋን ጠይቄ እህል የለም ካሉኝ ደወል ደወየ እህሉ እንዲወጣ አደርጋለሁ፡፡ ከዚያ ማበጠሪያና የመሳሰሉት ወጥተው እህሉ ይዘጋጃል፡፡

ጥያቄ፡- የደወሉ አይነቶች ይለያያሉ? ለፀሎት የሚደወልና የስራ ደወል ይለያያል?

መልስ፦ ለስራ የሚደወለው ሁለት አስር ጉዳይ ነው። ለፀሎት የሚደውሉት ሌላ ናቸው። 6 ሰዓት 11 ሰዓት ይደውላሉ። ሁለት ሰዓት ስራ ይገባሉ፡ መነኮሳቱ ስለሚያውቁት ወደየ ስራቸው ይሰማራሉ።

ጥያቄ፦ የሊቀ ረድዕ የምርጫ ወቅት የተወሰነ ጊዜ አለው?

መልስ፦ አዎ ለምሳሌ ጥቅምት ላይ አመታዊ ሰብሰብ አለ በዚያ ጊዜ ይመጣል። ለምሳሌ አልችልም ካለ የተመረጠ ሰው በአመቱ አልችልም ካሉ ይወርዳሉ። አንድ ሰው ጧት ተመርጦ ማታ ማውረድ ያለ ነው። የቻለ ግን ብዙ ጊዜ ማገልገል ቱርፋትም ይሆንለታል።

ቃል አቀባይ 8፣ እማሆይ ስነማርያም (እመምኔት)

ጥያቄ፦ የሴቶች ገዳም እመምኔት አመራረጥና ሌሎች የስራ መዋቅሮችን ቢነግሩኝ?

መልስ፦ የሴት ገዳም እመምኔት የሚመረጠው በሃይማኖት ትንሽ ጠንከር ያለ፣ በአመለካከቱ ስፋት ያላቸው ሁኔታዎች ያስቀመጠ፣ ከራሱ በላይ ለመነኮሳትና ለቤተ እግዚአብሔር የሚያስብ መሆን አለበት። ከእመምኔቷ በታች ዋናዋና የሆኑት መጋቢ፣ ሊቀ ረድእ፣ ጸሀፊ፣ ሂሳብ ሹም፣ ተቆጣጣሪ ናቸው። መጋቢ ከእኔ ቀጥሎ ያሉ ናቸው። መጋቢና ሊቀ ረድእ በጣም ትልቅ ስራ የሚሰሩ ናቸው። ሊቀ ረድእ በመጀመሪያ ትነሳለች። ከመጋቢዋ ጋር ተመካክረው ምን ማሰራት እንዳበላቸው ይነጋገራሉ። ኋል መጋቢዎች የተግባር ቤቱ አገልጋዮች ናቸው። በእንጀራው፣ በዳቤው ሁሉ ትልቅ ስራ ይሰራሉ። ለመነኮሳቱ የሚሆነውን ሁሉ የሚያዘጋጁ ናቸው። ኋል መጋቢዎች ከመጋቢ ቀጥሎ ብዙ ስራ የሚሰሩ፣ ጭስ የሚመጨስባአው ናቸው። ዳቦ የሚጋግሩ ሰውነታቸው የሚነጥረው እነሱ ናቸው።

ጥያቄ፦ በሴቶች ገዳም ውስጥ የኪዳነምህረት ቤተ ክርስቲያን አለች። ቅዳሰውን የመሳሰለውን ማነው የሚያከናውንላችሁ?

መልስ፦ የዕለት ተግባሩን ለምሳሌ ጠዋት ጠዋት ኪዳን አለ፤ አይቋረጥም። እሱን የሚያስ ፊፅሙልን አንድ ሽማግሌ አሉ። ከቤተክርስተያኑ ፊትለፊት ከሱቅ መሸጫው በር ላይ ቤት ሰርተን አስቀምጠናቸዋል። የለት ተግበሩን(የቀን ኪዳኑን) እሳቸው ያስፈፅማሉ። እዚያው እቤታቸው ሆነው ማለት እሳቸው ከመነኮሳይቱ ጋር ሆነው የለት ኪዳን እና ሰርከ ፀሎትና

ማታ 11 ሰዓት ሁልጊዜ ያደርሳሉ። ቅዳሴ በዓላትን በተመሰለ ግን ከወንዶች ገዳም እንጠይቃለን መተው ይቀድሱልናል። ምንኩስናም ካለ መጥተው ምንኩስና ይሰስጡልናል።

ጥያቄ፡- በገዳሙ አዲስ አባል ሲመጣ ያለውን አቀባበልና እስከ ምንኩስና ደረጃ ድረስ ያውን ሂደት ቢነግሩኝ?

መልስ፡- አንድ አዲስ ገቢ አባል ከመጣበት አካባቢ በሰበካ ጉባኤ የተፃፈ መስረጃ ካላቸው ያንን እናያለን። ዝም ብለው ከገዳም የመጡ ከሆነ ብዙም ማናጠናክርባቸው እቀበላቸዋለን። ከቤታቸውም የሚመጡ እሉ እነዚህንም እቀበላለን። ማስረጃ ሳይዙ የሚመጡትን ብንቀበላቸውም ሶስት ወር ድረስ መቁንን እያገኙ ሳይቀላቀሉ ይቀመጣሉ። ከሶስት ወር በኋላ ማህበሩ መውጣት መውረዳቸውን አይቶ ብቁ ናቸው ብሎ ወደ ማህበሩ መግባት ይችላሉ ብሎ ለመጋቢዋ ይነግራል። መጋቢዋ ደግሞ ለኔ ይነግራሉ ከዚያ በኃላ ጠርቼ እኔ አነጋግራቸዋለሁ ከዚያ በኃላ ወደ አንድነቱ ይገባሉ። አንድነቱ ውስጥ ቢገቡም ቢያንስ ለሶስት ወር እኛ ከምንሰበስበው ሰብሰባ አይሳተፉም። በአንድ ላይ ስድስት ወር ሆነ ማለት ነው። ከዚያ ደግሞ መነኩሴ እስከሚሆኑ ድረስ ደግሞ ይታያሉ። እስከዚያ ድረስ መምረጥም ሆነ መመረጥ አይችሉም። ሁለመናቸው መጠናት አለበት ከአመት በኃላ ደግሞ እንደማንኛውም መጥ መምረጥም መመረጥም ይችላሉ። ምንስናውን ግን እራሳቸው ናቸው የሚወስኑት። እንዳዶች እኛ ይበቃናል እንመኩስ ይላሉ። እንቆይ ካሉን እናስድድም ሁሉንም ነገር ገምግመው አይተው የገቡበት ነገር አይቆጭም። በሰው ጉትጎታ የሆነው የሆነ ነገር ግን በሁዋላ ሊቆጭ ይችላል።

ጥያቄ፡- በአመክሮ ጊዜ ሲቆዩ መጠሪያ ስማቸው አርድእት ነው ወይስ ሌላ?

መልስ፡- አርድዕት የሚባለው ማኛውም ገዳሙ ውስጥ ያለ ሰው ነው አርድእት ማለት ሰራተኛ፣ ረጂ ማለት ነው። ብዙውን ግዜ አንዳንድ ቦታ በእርሻ ቦታ የሚሄዱትን አርድእት የሚሉ አሉ። አርድእት የገዳም ሰራተኛ ገዳሙን የሚረዳ ማለት ነው።

ጥያቄ፡- በገዳሙ ውስጥ ያለው የአመጋገብ፣ የፀሎትና የአለባበስ ስርዓት ቢነግሩኝ?

መልስ፡- በኛ ገዳም ያለው የአልባበስ ስርዓት ገዳም ውስጥ ተቀምጦ ነጭ መልበስን፣ አጊጦ መኖር አይችልም። ምክንያቱም በስራ የተዘጋጀን ሰዎች ነን። ሁልጊዜ በስራ የተዘጋጀ ወታደር ስለሆኑ የስራ ልብስ ነው የሚለብሱት በኛ ገዳም የሚለብሱት ወይባ ነው። ከዋርካ፣

ከተለያ ቀለም ተበጥብጠው ይነክሩና የዘወትር ልበስ እሱ ነው። አመጋገብ ደግሞ በፊት በአንድ ላይ ነበር የታሰበው። ግን ነገሮች ስናስባቸው ጥሩ አይሆኑም ለምን አንዱ ሊጾም ይችላል፤ አንዱ በሽተኛ ሆኖ ወደ ኋላ ሊዘገይ ይችላል። ስለዚህ አማራጭ የወሰድነው ዘጠኝ ሰዓት እንዳንል ባለዘጠኙ ሊቸገር ይችላል። ስለዚህ ልክ 7፡30 ይደወላል። ከስራ ጠዋት 2፡00 ገብተው ልክ ስድስት ሰዓት ለፀሎት ሲደወል ይወጣሉ። ከዚያ በኋላ የራበው በልቶ ወደ ስራው ይሄዳል። የቻለ ወደ ስራ ሄዶ ሲመለስ ማታ ይበላል። በጋራ ቢሆን ግን እከሌ ጾሞ እኔ በላሁ እንዳይባሉ ነው። ስለዚህ ወደቤት ይወስዳሉ። ሰኞ፣ ረቡዕና አርብ ዳቤ ከወጥ ጋር ይበላሉ። ሌላው ቀን እንጀራ ነው። በቀን አንድ ጊዜ ነው ይደጎ የሚሰጠው። ንፍሮውን እንጨት ስለሌለ ወደ ዳቤ ለወጥነው።

ጥያቄ፡- ልብሳቸው የአንዳንዶቹ ቢጫ፣ የአንዳንዶቹ ወደ ጥቁርነት የተቀየረ ነው። ይኸ ልዩነት አለው?

መልስ፡- ልዩነት የለውም ጥቁር ዝም ብለን ሁላችንም በዘወትር መልበስ እችላለን። ቢጫ በዕድሜ አረጋዊያን የሆኑት ከ50-60 ያሉት ቢጫ ቀይ ቢለብሱ ትርጉም አለው። ቢጫ የእርግና ምልክት ነው። ትልቅ የገዳም አባቶች የትልቅነት ምሳሌ ነው። ቀይ ደግሞ የሚወሰደው በክለሜዳ ነው። ጥቁር በመነኮሳት ብዙውን ግዜ የሚለበሰው አይን አያስገባም፣ ብልጭልጭ ሁኖ አይን ውስጥ አይገባም፣ ቆሻሻ ይችላል በማለት ነው። በተጨማሪ ጥቁር መልበስ የሀዘን መልክት ነው።

ጥያቄ፡- በእናንተ ገዳም በጋራ የምትመገቡበት ወቅት ካለና የፍስክ ምግብ የመሳሰሉት የሚዘጋጅ ከሆነ ቢነግሩኝ?

መልስ፡- በጋራ የምንመገብባቸው ወቅቶች በትንሳኤና በልደት ነው። በዚህ ወቅት ማህበሩ በአንድ ላይ ነው የምንመገበው። እነዚህ በጉጉት የሚጠበቁት ወቅቶች ናቸው። በልደትም የታረደው ስጋ እስካለቀ ድረስ በጋራ እንመገባለን።

ካሴት ቁ.4፣ Side A

ቃል አቀባይ 9፣ አባ ወልደ ጊዮርጊስ (ሊቀ ረድዕ)

ጥያቄ፡- የሊቀ ረድእ የስራ ድርሻ ምንድነው?

መልስ፡- አርድዕቶችን አባቶች በሰጡኝ ስራ አሰማርቶ ማሰራት ነው፡፡ ከዚያ ሦስት ሰዓት ሲሆን ፀሎት እናደርጋለን፡፡ በስድስት፣ በዘጠኝ እያረፍን ፀሎት እናደርጋለን፡፡ ከዚያ በ አስራ ሁለት ሰዓት ወደ ቤታችን እንመጣለን፡፡

ጥያቄ፡- በአርድዕትነት የሚሰማሩት ሰዎች ምን አይነት ናቸው?

መልስ፡- የቤተ ክርስትያን አገልግሎት የሌላቸው ገበሬ የሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ካህን ያልሆኑ ናቸው፡፡

ጥያቄ፡- በየቀኑ የስራ ድርሻ ከማነው የሚያገኙት?

መልስ፡- ከመጋቢውና ከመምህሩ ነው፡፡

ጥያቄ፡- በየቀኑ የሚሰሩት ስራዎች ምን ምን ናቸው?

መልስ፡- የበቆሎ፣ የፓፓያ፣ ብርቱካን፣ ሸንኮራ ኩትኮታ አረም ማረም እና እርሻ የመሳሰሉት ስራዎች አሉ፡፡

ጥያቄ፡- ሌላስ ምን ዓይነት የልማት ስራ አለ?

መልስ፡- ሽንኩርት መትከል፣ ጐመን፣ ሰላጣ፣ ቆስጣ፣ ሸንኮራ እንተክላለን፡፡

**ቃል አቀባይ 10፣ አባ ገብረ ስንበት ተክለ ሃዋርያት (የሊቀ ረድዕ ተከታይ)**

ጥያቄ፡- የሊቀ ረድዕ ተከታይ ስራው ምንድን ነው?

መልስ፡- የሊቀ ተከታይ ከአባቶች በሚወጣለት የዕቅድ ቦታ ላይ የእርሻም ሆነ የአረም ከነሱ ሊቀ ረድዕ ተቀብሎ ያመጣል፡፡ በዚያ በተቀበለው መመሪያ መሰረት እንሰራለን ማለት ነው፡፡

ጥያቄ፡- በራስዎ ላይ ያለው ቆብ ከክር የተሰራ ነው፡፡ ምንድን ነው ትርጉሙ?

መልስ፡- ይህ የአመክሮ ቆብ ነው፡፡ ይህንን ቆብ ለብሼ ለ10 ዓመት ያህል ቆይቻለሁ፡፡

ጥያቄ፡- በዚህ ገዳም ውስጥ እስካአሁን ምን ምን ሰርተዋል? ወደ ፊትስ ምን ምን ስራዎችን ይሰራሉ?

መልስ፡- አሁን የምሰራው አባቶች በሚያዙኝ ቦታ ላይ ነው የምሰራው፡፡ ወደፊት ይህን እሰራለሁ ብዬ እኔ የማውቀውና የማቅደው ነገር የለኝም፡፡ በየቀኑ የተሰጠኝን ነው የምሰራው፡፡

ጥያቄ፡- በደጅ ጥናት ወይም በአመክሮ ላይ ያሉት መነኮሳት ቅናተ ዮሃንስ፣ ስጋ ማርያም የመሳሰሉትን ነገሮች ይጠቀማሉ?

መልስ፡- ስጋ ማርያም አያደርጉም፡፡ ቅናተ ዮሃንስ ግን ያደርጋሉ፡፡ ስጋ ማርያም ከምንኩስና ጋር የሚሰጥ ነው፡፡ ቅናተ ዮሃንስ ግን ማንኛውም ገዳማዊ ለመከራ ሲባል ማድረግ ይቻላል፡፡ ስጋ ማርያም ከምንኩስና ቆብ ጋር አብሮ የሚሰጥ ነው፡፡

ጥያቄ፡- በአመክሮ ጊዜ የምታልፏቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው? ለምሳሌ እርስዎ ከመጡ ጀምሮ በአመክሮ ላይ ነው ያሉት? በነዚህ ጊዜያቶች ምን ምን ሁኔታዎችን አልፈዋል?

መልስ፡- የሚያጋጥሙን ፈተናዎች ከቀን ወደ ቀን ሊበዙ ይችላሉ፡፡ እነዚያን መታገስና ማለፍ ያስፈልጋል፡፡ ፈተናዎችን መቻል፣ አለመቻሉን ማለፍ አለማለፉን ድሮ ከመጣ በኋላ አሁን መሻሻል ማሳየቱን የሚታይበት ጊዜ ነው፡፡

ጥያቄ፡- እስከ ምንኩስና ድረስ ባለው ጊዜ የምትለብሱትንና የምትጫሙትን ማነው የሚያሟላላችሁ?

መልስ፡- በአንድነት ገዳም እስካለን ድረስ ጫማ ባይሰጥንም የምንለብሰው ልብስ ገዳሙ ነው የሚያሟላልን፡፡ በቁሪት ያለ ገዳም ከሆነ ግን የሚያስፈልውን ነገር የሚያሟለው ራሱ ነው፡፡

ጥያቄ፡- በገዳሙ ማህበር ስብሰባዎች ይካሄዳሉ? በነዚያ ስብሰባዎች ላይ በአመክሮ ላይ ያሉ ገዳማውያን ትሳተፋላችሁ?

መልስ፡- አባቶች ብቻ የሚሰባሰቡበት አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ከዚያ ውጭ ማህበሩ በጠቅላላ የሚያስፈልግ ከሆነ እንሰባሰባለን፡፡ ማህበሩ ጠቅላላውን አባላት የሚያሳትፍ ከሆነ እንሰባሰባለን፡፡ በገዳሙ ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤ በዓመት ሁለት ጊዜ ይከናወናል፡፡ በነዚያ ስብሰባዎች ላይ እንሳተፋለን፡፡

ካሴት ቁ.4፣ **Side B**

ቃል አቀባይ 11፤ አባ ወልደ ኢየሱስ ወልደ ሚካኤል (እቃ ቤት)

ጥያቄ፦ በገዳሙ ውስጥ ያልዎት የስራ ድርሻ ምንድን ነው?

መልስ፦ የገዳሙን መፅሃፍትና የመሳሰሉትን አደራ ስለተሰጠኝ የዕቃ ቤት ጠባቂ ነኝ።

ጥያቄ፦ ምንኩስና ስትቀበሉ ያለው ስርዓት ምን ይመስላል?

መልስ፦ ወደ እግዚአብሄር ፀሎት ማድረግ ነው። ከዚያ ፍታት ይፈታለትና ለ40 ቀን ይቆያል። በ40 ቀኑ 40ውን ያወጣል። ያው በቁሙ ተፈታ ማለት ነው። ከሌለውም ማህበሩ 40ውን ያወጣለታል።

ጥያቄ፦ ስጋ ማርያምና ቅናተ ዮሃንስ የሚደርገው ማን ነው?

መልስ፦ አንድ ገዳማዊ ሲመነኩስ ስጋ ማርያምና ቅናተ ዮሃንስ ይሰጠዋል። ያንን በሰውነቱ ላይ እንዳደረገ እስከለተ ሞቱ ሲያልቅ እየተቀየረ ይኖራል። ሲሞትም አብሮት ይቀበራል። ያልመነኮሰ ግን ስጋ ማርያም አያደርግም።

ጥያቄ፦ የክር ቆብና የጨርቅ ቆብ ምንድነው ልዩነቱ?

መልስ፦ የክር ቆብ ያለው ቢከፋው ትቶት ሊሄድ ይችላል። ላግባ ብሎም ሊሄድ ይችላል። የጨርቅ ቆብ ያለው ግን የትም አይሄድም።

ጥያቄ፦ በቤተክህነት ውስጥ የሚቀድሱት ደናግል ናቸው ወይስ ሁሉም ገዳማዊ ይገባል?

መልስ፦ በቤተክህነት ውስጥ የሚገቡት ደናግል የሆኑ ገዳማውያኖች ናቸው። ደናግል ያልሆኑት ደግሞ በቤተክርስቲያን ዙሪያ ሆነው ፀሎት ያደርሳሉ እንጂ መቅደስ ውስጥ አይገቡም።

ቃል አቀባይ 12፤ አባ ወልደ ጊዮርጊስ ገብረ መስቀል (ሊቀ አበው)

ጥያቄ፦ የሊቀ አበው ስራ ምንድን ነው?

መልስ፦ ሊቀአውንት ከአባቶች ሰላም ለኪና ፀሎት እንዲደግም ኃላፊነት ይሰጠኛል። ከዚያም ደካማ የሆኑ አባቶችና በሽተኞች ይሰጡኛል። እነሱ ግን በአንድ ቦታ አድርጌ ማገልግል

ስለሚቻል ልብሳቸው ሲቆሽሽ በየቀኑ ገላቸውንም እያጠቡ ከመጋቢው በመነጋገር ደካማ የሆኑ አባቶችን መንከባከብ ነው፡፡ የታመሙትንና ደካማዎችን በአንድነት ነው፡፡ በሽተኞቹ ልጆች ከሆኑ ሲድኑ ተመልሰው ወደ ስራቸው ይገባሉ፡፡ ደካማዎቹ ግን በደካማነታቸው በአንድ ቤት ሆነው የሚያስፈልጋቸውንና የሚያምራቸውን ከቤተ እግዚያብሄር እየሄድኩ እየጠየኩ በማምጣት እሰጣቸዋለሁ፡፡

ጥያቄ፡- በምንኩስና ጊዜ ቅናተ ዮሃንስ ስጋ ማርያም የተሰኙት ነገሮች ይሰጣሉ፡፡ እነዚህን ከምንኩስና በፊት መጠቀም ይቻላል ወይስ አይቻልም?

መልስ፡- ቅናተ ዮሃንስና ስጋ ማርያም መጠቀም የሚቻለው ከምንኩስና በኃላ ነው፡፡ ግን እንዳንድ አባቶች በበረሃ ያሉ መንቆር እያሉ ሰውነታቸውን ለማድከም በወገባቸው የሚታጠቁት ነገር አለ እንጂ የሚፈቀደው ከምንኩስና በኃላ ነው፡፡

ጥያቄ፡- በቅዳሴ ላይ የሚሳተፉት ደናግሎች ናቸው? በህጋዊ ሁኔታ ኑረው የመጡ መቀደስ ይችላሉ?

መልስ፡- ከዚህ ቦታ ደናግሎች ናቸው መቀደስ የሚችሉት፡፡

ጥያቄ፡- የሚቀድሱ ካህናት በቅደሴ ወቅትና በሌላው ጊዜ የሚለብሱት አንድ አይነት ነው?

መልስ፡- የመቀደሻ ልብስ ለየት ያለ ነጭ ልብስ ነው፡፡ ከቅዳሴ ሲወጡ ግን ነጩን ቀይረው የራሳቸውን ያለብሳሉ፡፡

ጥያቄ፡- ቆብን በተመለከተ ከጨርቅ የተሰራ ወይም ከክር የተሰራ የሚለብሱ አሉ፡፡ የነዚህ ልዩነት ምንድን ነው?

መልስ፡- መሀሉ ትንሽ ቀዳዳ ያለው በአመክሮ ላይ ያሉ ሰዎች የሚለብሱት ነው፡፡ ምንኩስና የተቀበሉት ግን መሀሉን ደፍነው ነው የሚለብሱት በማለት አባቶች ይነግሩናል፡፡ የክርና የጨርቅ ቆብ መሆኑ ደግሞ በአመክሮ ላይ ያሉት የክር ቆብ ይለብሳሉ፡፡ የመነኮሱት ግን የጨርቅ ቆብ ይለብሳሉ፡፡

ጥያቄ፡- በግልና በጋራ የሚደረጉ ፀሎቶች ምንድ ነው ልዩነታቸው?

መልስ፡- በጋራ የሚፀለዩት እንደ ሰዓታት የመሳሰሉት የማህበር ፀሎት ይባላሉ፡፡ ይህ በጋራ የሚደረግ ሲሆን የግል ግን በሰርክ በ3፣ 6፣ 9 በመሳሰሉት የሚደረጉ ፀሎቶች ናቸው፡፡

ቃል አቀባይ 13፣ አባ ተስፋ ወልደሃና (የገዳሙ ልማት ሃላፊ)

ጥያቄ፡- በገዳሙ ውስጥ ያለዎት ኃላፊነት ምንድን ነው? የልማት እንቅስቃሴዎቹ ምን ምን ናቸው?

መልስ፡- ኃላፊነቴ ከመጀመሪያ ጀምሮ በገዳሙ ውስጥ ያለውን የልማት እንቅስቃሴ በበላይነት መምራት ነው፡፡ የልማት እንቅስቃሴያችን ይህ አካባቢ በባህር የተከበበ ስለሆነ ከረጅም ጊዜ በፊት የዝናብ ውሃን በመጠቀም ብቻ ይሰሩ የነበሩት እኛ ከመጣን በኋላ የአትክልት ስራ ለመስራት እዚህ የነበሩት ነባር መነኩሳት ስለማያውቁት ብዙ ፈተና ገጥሞናል፡፡ የገዳሙ አስተዳዳሪ ብዙ እውቀት ያላቸውን ሰዎች እያሰባሰቡ በግድም በውድም የልማቱ ስራ እንዲጀመር አደረጉ፡፡ በመጀመሪያ የጓሮ አትክልት ተከልን፡፡ ከዚያ በኋላ ቋሚ አትክልት መትከል ጀመርን፡፡

የዶሮ እርባታ በ1996 ዓ.ም በ50 የአንድ ቀን ጫጩት ተጀመረ፡፡ በዚያ የተጀመረው ስራ በአሁኑ ሰዓት በአንድ ጊዜ እስከ 2000 ጫጩት ማስገባት ጀምረናል፡፡ ከዚያ ውስጥ እርባታው በሁለት የተከፈለ ነው፡፡ አንደኛው በየ3 ወሩ እያሳዳግን ለአካባቢው ተጠቃሚ እናሰራጫለን፡፡ ሁለተኛው የስጋና የእንቁላል ዶሮዎችን አሳድጎ ለምግብ ማቅረብ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት በዓመት 4000 የአንድ ቀን ጫጩቶችን ተቀብለን በማሳደግ ለአካባቢው ተጠቃሚ የማድረስ ችሎታ ላይ ደርሰናል፡፡ እኛ የእግዚአብሔር ፍቃዱ ከሆነ ኢንኪዩቤተር ገዝተን እዚህ አካባቢ የአንድ ቀን ጫጩት ለገበሬው ለማሰራጨት በእቅድ ላይ ነን፡፡

ጥያቄ፡- የጓሮና ቋሚ አትክልት የሚባሉት ምንድን ናቸው?

መልስ፡- የጓሮ አትክልት የሚባሉት ጎመን፣ ሰላጣ፣ ቲማቲም ናቸው፡፡ እነዚህም ለቤተ እግዚአብሄር በምግብ ከመጠቀም አልፎ ለገበያ እናቀርባለን፡፡ ከዚህ ባሻገር በቋሚ አትክልት ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ፓፓያ፣ አቡካዶ የመሳሰሉትን በብዛት እናመርታለን፡፡ ህዝቡ በብዛት አትክልት ተጠቃሚ በመሆኑ ከዚህ አካባቢ ወጥተን ለማሰራጨት አልቻልንም፡፡

ጥያቄ፦ ያገኘሁዎት በገዳሙ የካህናት ማሰልጠኛ ውስጥ ነው። በዚህ ውስጥ ያለዎት የስራ ድርሻ ምንድን ነው? የገዳሙ የካህናት ማሰልጠኛ አገልግሎት የጀመረው መቼ ነው?

መልስ፦ የካህናት ማሰልጠኛው ለ13ኛ ጊዜ እያሰለጠነ ነው። 12 ዓመት ሆኖታል ማለት ነው። ካህናቱን ከየወረዳው ሀገረ ስብከት ለህብረተሰቡ ተምረው ያስተምራሉ የሚባሉትን እየመለመሉ ይልኩልናል። እኛ ከደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት በሚመጡ ሰባኪያን ትምህርቱ እየተሰጠ ለ4ወር አሰልጥነን እንመርቃቸዋለን። እነሱም በተመረቁበት ትምህርት ህብረተቡን ያስተምራሉ፣ ያልተጠመቀውን ያጠምቃሉ፣ የተጠመቀውም ወደ ሌላ ሃይማኖት እንዳይሄድ የራሳቸውን ጥረት እያደረጉ ነው።

ጥያቄ፦ የገዳሙ በዚህ አካባቢ መኖር እና በሚያካሂደው የልማት እንቅስቃሴ ህብረተሰቡ ምን ያህል ተጠቃሚ ሆኗል ይላሉ?

መልስ፦ በልማት እንቅስቃሴው ገበሬው በጣም ተጠቃሚ ነው። ገበሬዎቹ እኛ ከመምጣታችን በፊት ምንም አትክልት አይተክሉም ነበር። ቲማቲምም የሚያውቁ አይመስለኝም። እኛ ከመጣን በኋላ እኔ ዘሩን ገዝቼ አፈላለሁ። አንድ ዓመት ከተጠቀምን በኋላ ፍሉን በነፃ እንሰጣቸው ነበር። ፍሉም ቀይስር፣ ቆስጣ፣ቲማቲም፣ ጎመን አፍልተው ለገበያ ያቀርባሉ። የገቢ ምንጫቸው እየዳበረ ሲሄድ እነሱም በስራው ላይ ትኩረት አድርገው ከጓሮ አትክልት አልፈው በባህሩ ዳር ዳር ሙዝ፣ ሸንኮራ እያለሙ ነው። ይህ ሁሉ ፍል ያለ ዋጋ እኛ የሰጠናቸው ነው። ሌላም በዶሮ እርባታ በኩል የተወሰኑ ገበሬዎችን የሶስት ወርም የሁለት ወርም ጫጩት እያመጣሁኝ እየሰጥኋቸው ነበር።

ካሴት ቁ.5፣ **Side B**

አሁን እንኳን ለገበያ ከቀረቡ እና ከተሸጡ 1500 ጫጩቶች ውስጥ ከ200 መቶ የማያንሱ ጫጩቶችን ማንም ሳያውቅ ትዳር ለሌላቸውና ምንም አጋር ለሌላቸው ሴቶች አምስት አምስት የ3 ወር ጫጩቶች በነፃ ሰጥተናል። እኛ ከእኛ አልፎ ከሌሎች አባቶቻችን አላማ ተነስተን ለዓመት ቀለብና ልብስ ካገኘን የተረፈውን ያካባቢውን ህዝብ ማገልገል አለብን። አሁንም ወደ ፊት ኢንኪዩቤተር ከገባልን አካባቢውን በዶሮ ልማት ተጠቃሚ እናደርጋለን የሚል እቅድ አለን። ሌላም አስር የከሱ በሬዎችን አስገብቼ አንዱን ገዳሙ በዓመት በዓል ወቅት እንዲጠቀምበት አድርጌ ከዘጠኙ በሬዎች በስድስት ወር 36,000 ብር

ትርፍ አግኝቻለሁ። እነዚያን ሳደልብ ሳርም አልገዛሁም። የተወሰነ ፉርሽካ ገዝቻለሁ። ከዚያ በተረፈ አገዳ ሲሸጥ የአገዳው ቁራጭ አስሬ እያበላሁ ነው ትርፍ ያገኘሁት። ስራው በጣም አድካሚ ስለሆነና መነኮሳት ብዙ ጊዜ በስራ ተጠምደው ለመስራት ስለማይፈልጉና ስራውን ስንጀምር ጥለውን ስለሚሄዱ ነው እንጂ ብዙ ስራ መስራት እንችል ነበር። ሌላም የወተት ከብት ብናረባ አካባቢው የተራቆተ ስለሆነ ወተት ለተጠቃሚ ማቅረብ እንችል ነበር። ለወደፊት እየተወያየንበት ነው። ለጊዜው አራት ዲቃላ ላሞች አሉ። እስካሁን ድረስ ወተቱን የምንጠቀምበት እኛ ነን። መነኮሳት በሌላው አካባቢ ከገቢውም አንፃር ሲታመሙ ዝም ብለው ይተዋቸዋል። ጉልበት ያለው በፀበል ይድናል። ካልዳነ ሆስፒታል ከፍሎ የሚያሳክም ገዳም የለም። እኛ ግን መነኩሴ ከታመመ እናሳክማለን።

የእርሻ እንቅስቃሴያችንን የምናካሂደው ጥንታዊ ዘዴን ተከትለን እንደ ገበሬው ነው። መሬት ሲከፋፈል ገዳሙ በአንድነት ሳይሆን በቁሪት ነበር የሚተዳደረው። እዚያ የነበሩት መነኮሳት እንደ ገበሬው ተመሩ። አሁን ወደ አንድነቱ ሲገቡ መሬቱን ለዘመዶቻቸው እያወረሱ ነው የገቡት። ስለሆነም በሬ ገዝተን እናርሳለን፤ ሲወፍሩ ደግሞ ሸጠን የከሱ በሬዎችን እንገዛለን። ስድስት ጥማድ በሬዎች አሉን። ገዳሙ የተመሰረተው በ862 ዓ.ም ነው። በአንድ ጊዜ እንኳን እስከ 800 መነኮሳት በነ አቡነ ኢየሱስ ሞአና በአቡነ ሰረቀ ብርሃን ጊዜ ነበሩ። የነዚህ ሁሉ ቁጥራቸው በርካታ መነኮሳት አፅም ያረፈው እዚሁ ነው። የነዚህ መነኮሳት አፅም አፍልሰን በቆሎ ከመዝራት ቋሚ አትክልቶች እንደ ቡናና ማንጎ የመሳሰሉትን ተክለን አፅማቸው በዚያው ባለበት እስከምፃት ድረስ ይቆይ ብለን አላረስነም። ሌላው ቀርቶ የዶሮ እርባታው እንኳን ብዙ አባቶች እባካችሁ ዶሮ አታርቡበት፤ ቦታው ብዙ አበው አፅማቸው ያረፈበት ስለሆነ ዶሮውን ወደ ውጭ ብታወጡ ይሉናል። ግን እስካሁን ዶሮዎቹን የማራቢያ ቦታ ስላጣንና ከእነሱ በሚገኘው ገቢም ገዳሙ ስለሚታገዝ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለን ነው ያለነው።

ቃል አቀባይ 14፣ አባ ገብረ ስላሴ በላይ (የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ስራ አስኪያጅ)

ጥያቄ፡- የምንኩስና ሂደት ምን ይመስላል? ወይም ምንኩስና እስከሚሰጥ ድረስ ያሉት ሂደቶች? ምን ምን ናቸው? አንድ መናኝ ገዳም ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ያሉትን ሂደቶች ቢነግሩኝ?

መልስ፦ ምንኩስና ማንም ሰው በማስገደድ የሚሰራው ስራ አይደለም። ምንኩስና ስርዓት ስለሆነ በየጊዜው እያንዳንዱ ቦታ የተለያየ የገዳም ስርዓት ይኖረዋል። ግን ትክክለኛ አባቶች እንደነገሩኝና እንዳየሁት አንድ መናኝ ከቤቱ የሚወጣበት የራሱ አመለካከት ይኖረዋል። ይህ የራሱ አመለካከት ወይም እግዚአብሔር እንደመራውና እንደፈቀደለት ነው የሚሄደው ከዚያ በኋላ ወደየገዳሙ ሲሄድ መጀመሪያ የእንግዳ ማረፊያ አለ ለ7 ቀን ወይም ደግሞ ለ3 ቀን እንደገዳሙ ስርዓት ከሰነበተ በኋላ ሊቀ አበው የሚባለው ይቀበለውና በእንግዳ ማረፊያ ይቀመጣል። ከዚያ በ3ኛው ወይም በ7ኛው ቀን ደወል ይመታል። መነኮሳቱ ይሰበሰባሉ ሰውየው በፊታቸዉ ይቆምና ለምን መጥተህ ነው ወንድማችን ብለው ይጠይቁታል። ጉብኝተህ ለመሄድ ነው ወይስ በረከት ለማግኘት ወይስ አብረህ ለመኖር ነው የመጣኸው ይሉታል። እንግዲህ አናንተን ወስዬ ለመኖር ነው ብሎ ከመለሰ የገዳሙን ችግር ይነግሩታል። የገዳም ምግቡ ከባድ ነው። ልብሱም እንደዚህ ነው፣ ስራው ብዙ ነው፣ ውጣ ውረድ አለው፣ ታዞ መኖር ነው ብለው አስፈራርተው ካለውም በበለጠ አድርገው ከገባ በኋላ እንዳይላላና ሰይጣን እንዳይፈትነው አስፈራርተው ይነግሩታል። እናንተን ያስቻለ አምላክ እንዲያስችለኝ ፀሎታችሁ ይርዳኝ ብሎ መልስ ከሰጠ ከዚያ በኋላ ይወድቅና ፀሎተ ማርያም ይደገምለታል። ፀሎተ ማርያም ተደግሞለት ከማህበሩ አንድነት ይቀላቀላል። ከዚያ በኋላ በገዳሙ ያለው ንብረት በሙሉ ንብረቱ ነው። ለገዳሙ መነኮሳት የሚሰጠው ሁሉ ለሱም ይሰጠዋል። እኩል መብት አለው። ልብስ ሲሰጣቸው ልብስ ይሰጠዋል፣ መቁነን ሲሰጣቸው መቁነን ይሰጠዋል። የሱ የሆነው ሁሉ የገዳሙ ነው። የተማረ የቤተ ክርስትያን ሰው ከሆነ በቤተ ክርስትያን፣ ገበሬ ከሆነ በእርሻ ስራ ሊሰማራ ይችላል። ብቻ በሚችለው ነገር መነኮሳቱ ያሰማሩታል። እሱም እሺ ብሎ ይሰራል። እሱም ቢሆን ሰባት ዓመት ስለሞላው ማመንኮስ ሳይሆን የሰውን ሁኔታ በዚያ ላይ ይገመገማል። መነኩሴው ፀሎት ተቀብሎ ስራ መስራት ብቻ ሳይሆን ስርዓተ ገዳሙንም ጭምር ይማራል፣ ምንኩስና ምን ማለት እንደሆነ ይማራል፣ መቼ ተጀመረ፣ ማን ጀመረው፣ በምን ተጀመረ፣ ክብሩስ ይህን ሁሉ ይማራል።

ለመነኮሳት ሕይወት ማሰሪያው የገዳሙ አበምኔት ነው። መናኙም ሰባት ዓመት ከሞላ በኋላ ጥሩ ሥነ ምግባር ከታየበት፣ ምግባሩ ሁሉ የተወደደ ከሆነ ልመንኩስ ሲል እንዲመነኩስ ይፈቀድለታል። ሲመነኩስም ሌላ ቤትና ንብረት ስለሌለው ቀሚሱም፣ ቆቡም፣ አስኬማውም ከገዳሙ ይሰጠዋል። በዚህ ሂደት ውስጥ ወደ ገዳሙ ሲገባ መነኮሳቱ ቢጫ እየለበሱ እሱ ነጭ ጋቢ አይለብስም። ስለዚህ በአመክሮው ውስጥ የሚለብሰው የክር ቆብ

መሀሉ የተቀደደ ወይም ክፍት የሆነ ነው። ይህ ያለመመንኮሱ ምልክት ነው። እሱን አድርጐ እየተለማመደ ይሄዳል። ቀሚሱም የአቡጀዲ ቀሚስ ነው። በአመክሮ ጊዜ ቆቡንና ቀሚሱን ብቻ እንዲለብስ ይፈቀድለታል።

ካሴት ቁ.7፣ Side A

ስለዚህ ይሄ መነኩሴ በመጀመሪያ መነኮሳቱ ፀሎት አድርገውለት ራሱን ይላጫል፣ ሰውነቱን ይታጠባል። አዲስ አቡጀዲ ለብሶ ይመነኩሳል። ቆቡም፣ ቀሚሱም አዲስ አቡጀዲ ነው። ከዚያ በሦስት ክር የተፈተለ ከታች ከወገቡ ጀምሮ በአንገቱ የሚዞር ቅናተ ዮሐንስ ሰጥተዋል። ከዚያ ስጋ ማርያም ያደርጋል። በአንገታችን ያለው ስጋ ማርያም ይባላል። በወገብ ላይ የሚታሰረው ቅናተ ዮሐንስ ይባላል። ስጋ ማርያምና ቅናተ ዮሐንስ ልዩነታቸው አንደኛ መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለስመ አጠራሩ ክብር ምስጋና ይግባውና በዕለተ አርብ ዓለምን ለማዳን አንገቱን የተጐተተበትን ለማሰብ ሁለተኛ ደግሞ እጁን የኋሊት አስረው አንዱ ሲስበው ሌላው ሲለቀው በጲላጦስ አደባባይ ላይ የታሰረበትን ገመድ ለማሰብ ነው። ከዚህ በኋላ እኔም እንዳንተ እንደአምላኬ ታስሬአለሁ ብሎ ቃል ገብቶ ነፍሴን ለስላሴ ስጋዬን ደግሞ ለመነኮሳት ሰጥቻለሁ ብሎ ቃል ይገባል።

ቆቡም መድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ የደፋውን አክሊለ ሶክ ለማሰብ ነው። ካህን ከሆነ፣ ወይም ምዕመን ከሆነ፣ ሴት ከሆነች፣ እያንዳንዱ የራሱ የሆነ ፀሎት አለው ስርዓተ ቅዳሴም ይደረግለታል። ከዚህ በኋላ በመነኮሰበት ቀን ስጋወደሙን ይቀበላል። ስጋወደሙ ከተቀበለ በኋላ ለአርባ ቀን በገዳሙ መነኰሳት ስር በቤቱ ዘግቶ እንዲቀመጥ ይደረጋል። ለብቻው ዳዊት እንዲደግም፣ አቁጣሮ እንዲቆጥር ይደረጋል። በእያንዳንዷ አቡነ ዘበሰማያት ሦስት ሦስት ይሰግዳል። 12 አቡነ ዘበሰማያት ሲደግም 36 ይስግዳል። ስግደቱም ክርስቶስ የወደቀውን፣ የተነሳውን እያሰበ በነግ፣ በሰለስት፣ በ6፣ በ9፣ በ11፣ በንዋን፣ ሌሊት በስድት ሰዓት አቁጣሮውን ሳያቋርጥ ያደርሳል። ይሄ ለወጣኒ (ለአርድእት) በስራ ላይ ላሉ መነኮሳት ነው። በነግ ወይም በማለዳ ተይዞ ወደ ጲላጦስ አደባባይ የሄደበትን በማሰብ፣ በሰለስት በጲላጦስ አደባባይ ቆሞ የተመረመረበትን በማሰብ፣ በስድስት ሰዓት ስቅለቱን በማሰብ፣ በዘጠኝ ሰዓት ቅድሰት ነፍሱን ከቅድስት ስጋው በፍቃዱ መለየቱን በማሰብ፣ በ11 ሰዓት የኛን ሞት ድል ያደርግ ዘንድ ወደ መቃብር የሄደበትን በማሰብ፣ በንዋም ስርሀ መዓልትን አስፈፅመህ እንዲሁ ንዋመ ሌሊቱን ያመጣህልን አምላክ ብሎ የሱን ቸርነት በማሰብ፣

እንዲሁም በመንፈቀ ሌሊት ላይ ዕለት ምፅአትን በማሰብ አስራ ሁለት አቡነ ዘበሰማያትና ዘጠኝ ፀሎተ እግዚትነ ማርያም ያደርሳል። ዘጠኙ እግዚትነ ማርያም ሲደመሩ ስልሳ አራት ይሆናሉ። ይህ ደግሞ የእመቤታችን የዚህ አለም የኖረችበት እድሜ ነው። አቡነዘ በሰማያቱ ሲደመር ክርስቶስ የተገረፈበትን ግርፋት ለማሰብ ነው።

የገዳሙ መነኮሳት አርሰው ቆፍረው ወደ ገዳሙ ለሚሄዱ እንግዶች የእኛ ነው ብለው አንሰጥም ማለት አይችሉም። ለሚመጣው ሁሉ ይሰጣሉ። በገዳሙ ዘግተው የሚፀልዩት መነኮሳትም ለገዳሙ ብቻ ሳይሆን ለአለም ሁሉ ነው የሚፀልዩት። 3ኛው ዘበአኮቴት ነው። በሽተኛ ታሞ የተኛ ሰው በገዳሙ ውስጥ ታሞ እግዚአብሔርን ማማረር እንዲህ አደረገኝ ማለት የለም። አቤት ፈጣሪዬ ከነዚያ የምትወዳቸው ወገን ጨምረኸኝ ይሆን ይህን የሰጠኸኝ እንዲህ ያደረክልኝ እያለ እዚያው የተኛበት በሽታውን ይዞ እያመሰገነ ይኖራል። የዚያም ክብር አለው። የበሽተኛው ቅጥቃጤውና ደዌው ለሱ ብቻ አይደለም በረከቱ ለገዳሙ መነኮሳት ሁሉ ነው። እነሱንም የሚያስታምሙት ሲቀ አበው የሚባል አለ።

ካሴት 7፣ Side B

አባ ፍቅረ ዮሐንስ ገብረ ህይወት

ጥያቄ፦ ይህን ቦታ ለገዳምነት ያስመረጠው ምንድን ነው ይላሉ?

መልስ፦ ይህ ቦታ ከጥንት ጀምሮ የተባረከ ነው። በታሪክ እንደምንሰማው መላኩ ኡራኤል ደመ መለኮትን ስለቀባት የእግዚአብሄር መንፈስ በላይዋ ረብቦ ይኖርባት ነበር። አቡነ ሰላማ ካልእም ይችን ቦታ ሲያዩ ላይዋ መንፈስ እግዚአብሄር ረበባት ነበር። በታች የሚኖሩት ሰዎች እንደምንድን ናቸው? ናቸው ብለው ሲጠይቁ አምልኮተ ባእዳን በላይ ግን የእግዚአብሄር መንፈስ አለባት። ከዚያ መጥተው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሲባርኩ ያ ጣኦት ጠፋ ማለት ነው። ቦታው የቅድስና ቦታ ሆነ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ተተክሎባት የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን መሰረት ተጣለ። የቅዱስ እስጢፋኖስና የቅዱስ ጊዮርጊስ ደግሞ ራሳቸው ሳይሆኑ በታምራት ነው። በመጀመሪያ ቅዱስ ኡራኤል ደሙን ቀባ። ቤተ ክርስቲያን ይሰራ በሚባልበት ጊዜ ጣኦቱ ጠፍቶ ቤተ ክርስቲያኑን ገዝም ብለው ሰርተው የማንን ታቦት እናስገባ ሲሉ በታምራት የቅዱስ እስጢፋኖስና የቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት ቶራ በምትባል አውሬ ተጭኖ በኢየሩሳሌም በርሃ

የሚገኙ ቅዱሳን የላኩት ነው የሚል ጽሑፍ ተጽፎበት መጣ። ሁለቱ ታቦቶች አንድ ላይ ሁነው ሳሉ አንድ ታምር ታየ። ባህሩ ወደ ሰማይ ይዘል ጀመር። ወደ እግዚአብሔር ሲያመለክቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከባህሩ ወዲያ ማዶ ነው የሚተከለው ቅዱስ እስጢፋኖስ ግን በዚሁ ቦታ ነው ተባሉ። ወደፊትም ቅዱስ እስጢፋኖስ ስርዓተ ማህበር ሲባል ያው የመጀመሪያው የሓዋርያት ማህበርን ይመራ ስለነበር ማህበር እንደሚመሰረት እግዚአብሔር ባወቀ የእስጢፋኖስ ታቦት እዚሁ ቆየ።

በገዳሙ ያሉ ታምራዊ ነገሮችን ስንመለከት የአቡነ ፊልጶስ ባህሩን ማንደድ፣ ከዚያ በጣልያን ጊዜ ቦምብ ቤተ ክርስቲያኑ ላይ ወደቀ፤ ቤተ ክርስቲያኑ ሳር ቢሆንም አልተቃጠለም። ሁለተኛም ሲጥል ባህሩ ላይ ጥሎ አውሮፕላኑ ባህሩን ሳይሻገር በሰማይ ላይ ነደደ። የተረፉት ጣልያኖች መጥተው ክርስቶስ ከዚህ ቦታ አለ ብለው መነኮሳቱን ሳያጠፉ ኖሩ።

አሁን በቅርብ ጊዜ እንኳን የኢህአዲግና የደርግ ጦርነት በነበረበት ጊዜ ወንዱ ተሰብስቦ እዚህ ገባ። ሴቱ ደግሞ ወዲያ ማዶ ገባ። ከዚያ መሳሪያ ተተኩሶ ላዩን በቆርቆሮው ሲገባ መሳሪያው ተንከባሎ ሰውም ሳይመታ፣ ቤተ ክርስቲያኑንም ሳያቃጥል ተቀምጦ ተገኝቷል። ይህ ሁሉ ታምር ነው። ባህሩ ራሱ አዞና ጎማሬ ሳይኖርበት አሳ ብቻ እያለ ላዩን አእዋፍ ሲንሳፈፉበት ብቻ ነው የሚገኝ። ይህ ምንያቱ ባህሩን አቡነ ፊልጶስ ካቃጠሉት ጀምሮ መርዛማ አራዊት ከዚህ የሉም። አቡነ ኢየሱስ ሞአም በቃል ኪዳናቸው አጥፍተዋቸዋል። ውሃው ታፍሶ እየተጠጣ የሚኖር፣ አልቀት ከብቶችን ከሌላ ቦታ ሲይዛቸው እዚህ ሲጠጡ ይለቃቸዋል እንጂ የማይዛቸው መሆኑ፣ ሌላ አራዊት አለመኖሩ ሁሉ እንደታምር የሚቆጠሩ ናቸው ማለት ይቻላል። ከአቡነ ኢየሱስ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ገዳሙ አለመጥፋቱ፣ አሰረ ምንኩስና አልተቋረጠም። መማሪያ መሆናቸው፣ ታሪካቸው ሳይጠፋ መገኘቱ፣ በስርዓተ ገዳም ጸንተው መገኘታቸው፣ ኢትዮጵያን ሲመሩ የነበሩ ምሁራን መማራቸው፣ ልዩ ያደርጋቸዋል።

ቦታዎችን ሰዎች በታምራት ይቀድሷቸዋል። ለምሳሌ ደብረ ሊባኖስ ጣኦት አምላኪ የነበረበት ቦታ ነበር። ያንን ጠራርገው አስወጥተው ነው ገዳም የመሰረቱት። የስርዓተ ምንኩስና አፈጻጸም እንደየ ገዳማቱ ስርዓት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ተኝቶ ስርዓተ ምንኩስና መቀበሉ ምንድን ነው ሞትኩ ሲል ነው። ጸጉሩን ሲላጭም ከዚህ ዓለም የመለየቱ

ነው። ወድቆ ደግሞ ስርዓቱ ካለቀ በኋላ አበምኔቱ ያነሳዋል። ትንሳኤ፣ ክብር አለህ፣ በክብር የምትኖር ነህ ለማለት ነው። አንዳንዶች ቆም አድርገው በዚያው ስርዓተ ምንኩስና ይፈጽማሉ።

ጥያቄ፡- መነኮሳት ከሚለብሷቸው ልብሶች ስር የሚያደርጓቸው ነገሮች ምንን የሚያመለክቱ ናቸው?

መልስ፡- ልብሳቸው ወይባ ይባላል። ደበር ያለ ነው። ወይባ ማለት ደበር ያለ ነው። ወይም እንደ ቢጫ አይነት ነው። በመሰረቱ የመነኮሳት ልብስ መሆን ያለበት ጥንት የቦታው አቅኚ ይለብሱት የነበረው ልብስ ነው መለበስ ያለበት። አንዱ ገዳም ካንዱ የሚለይበት ልብስ መኖር ያለበት ነው። የመቀደሻ ልብሶች ብዙውን ጊዜ ነጭ ነው የሚፈቀደው። ነጭ ልብስ ጽዳት ያለው ስለሆነ ወደ ብሩህ ዓለም ክርስቶስ፣ ብሩህ ክርስቶስን የሚከተሉ ስለሆነ፣ ብርሃን ለብሶ ስለተነሳ፣ ወደ ብርሃን ዓለም ስለሚወስደን፣ በብርሃን ስለሚመራን ነጭ ልብስ ይለበሳል። ከነጭ ልብስ ላይ እንደ መስቀል ያለ አንዳንድ ነገር ይደረግበታል። ይሄ ሰማያዊ ክብርን የሚያሳይ ስለሆነ ነው።

ካሴት ቁ.8 Side A

ጥያቄ፡- በህመም ለደከሙ ሰዎች የሚዘጋጀው ምግብ ለምን የተለየ ሆነ?

መልስ፡- በመሰረቱ ምግብ የምንመገበው ቁመን እንድንሄድ፣ እንድንንቀሳቀስ ነው። ካለም የተለዩ መነኮሳት ምግባቸውና ልብሳቸው አንድ አይነት፤ ሲለብሱም ባንድ ጊዜ፣ ሲመገቡም ባንድ ጊዜ ነው። እዱር የሚውሉ እንደ ስራው ክብደት ይታዘዝላቸዋል። አቅማቸው እየደከመ ሲሄድ ያንኑ ያለውን እህል ለየት አድርገው አገልግሎቱ እንዳይቀር፣ መንቀሳቀስ እንዲችል፣ እንዳይደክሙ ለማድረግ ለየት ይደረግላቸዋል። የቀድሞ አባቶች ቅጠል እየበሉ ይኖሩ ነበር። አሁንም አክርመው የሚበሉ፣ ደረቀን ብቻ የሚበሉ አሉ። የተለየ ምግብ ከዚያው ከምግቡ ማዘጋጀቱ አለማዊ ስራ መስራት ማለት አይደለም። የሚሰራላቸውም ማህበሩና መጋቢው አውቆት ነው። የሚሰራላቸውም ሲደክሙ ብቻ ነው።

ጥያ፡- ስጋ ማርያምና ቅናተ ዮሐንስ በመነኮሰበት ቦታ ይሰጣሉ?

መልስ፡- የሚያመነኩሰው አባት ስጋ ማርያምና ቅናተ ዮሐንስ ይሰጣል። ቅናተ ዮሐንስ ማለት ዮሐንስ ጠፍር ይታጠቅ ነበር። ዮሐንስ ታጥቆ ጥርጊያውን አቅኑ፣ ንስሐ ግቡ ይል ስለነበር ያ ቅናተ ዮሐንስ ይባላል። አንገት ላይ የምትደረገው ስጋ ማርያም ትባላለች። ስጋ ማርያም ማለት ጌታችን ከእመቤታችን የነሳው ስጋ ምሳሌ ማለት ነው። ከስጋዋ ስጋ፣ ከነፍሷ ነፍስ ነስቷል ማለት ነው። ቆቡ ደግሞ በእለተ አርብ ጌታችን የተቀበለው የአክሊለ ሶክ ምሳሌ ነው። ቀሚሱም ጌታችንን ያለበሱት የከለሜዳ ምሳሌ ነው። አስኬማ የሚባለው ጌታችን በተቀበላቸው 13ቱ ህማማተ መስቀል ልክ የሚደረግና ከጠፍር የሚሰራ ሆኖ እንደሰደሪያ የሚጠለቅ ነው።

ጥያቄ፡- መዝጋት ምን ማለት ነው?

መልስ፡- መዝጋት የሚቻለው በማህበሩ ፈቃድ ነው። በራሱ ፈቃድ እዘጋለሁ ካለ ማህበሩ ተሰባስቦ ስርዓተ አበው በሚባለው ያስሩታል። ነገር ግን እየረዳ ወደ አባቶች ያመለክታል። ዳዊት ልድገም፣ ልዝጋ ፍቀዱልኝ ብሎ ለመጋቢው ያመለክታል። መጋቢው ያቀርብለታል። ጉዳዩ ታይቶ ተመርምሮ ይሄ መዝጋት ይችላል፣ ጸሎት ማድረስ ይችላል፤ ፈተናውን ይቋቋማል ብለው አባቶች ካመኑበት ከማህበሩ ፊት ቀርቦ ጸሎት ይቀበላል። ጸሎት ተቀብሎ ይዘጋል እንጂ ሳያስፈቅድ መዝጋት የለም። ሳያስፈቅድ ሱባኤ የለም።

ቃል አቀባይ 15፣ አባ ኪዳነ ቃል ኪዳኔ (በስላሴ ኮሌጅ በመማር ላይ ያሉ)

ጥያቄ፡- መቁጠሪያ ምንድን ነው? አገልግሎቱስ?

መልስ፡- መቁጠሪያ አገልግሎቱ ጸሎት ነው። ብዙ የጸሎት አይነት፣ የጸሎት ክፍሎች አሉ። መቁጠሪያ የምንጠቀምበት ሁሉም መነኮሳት ጸሎታቸውን አባታችን ሆይ ወይም በግእዙ አቡነ ዘበሰማያት የተባለውን ጌታ በወንጌል ያስተማረውን ጸሎት የምናደርስበት ነው። መቁጠሪያ የተለያየ መጠን አለው። ይህም ማለት የአንድ መቁጠሪያ ብዛት 41፣ 64፣ 120 ሆነው ይዘጋጃሉ። ሰውም እንደችሎታው ይጠቀምባቸዋል። ጸሎት በመጀመሪያ ሰዓትን ማዕከል ያደረገ ነው። በገዳም ወጣኒ፣ ማዕከላዊ፣ ፍጹማን የሚባሉ አሉ። ወጣኒ የሚባሉት ጀማሪዎች ናቸው። እነሂህ ጀማሪዎች ደግሞ ብዙ ይሰራሉ፤ ጥቂት ወይም መጠነኛ ጸሎት ያደርጋሉ። ማዕከላውያኖቹ ደግሞ ብዙ ይጸልያሉ፤ ጥቂት ይሰራሉ። ፍጹማን የሚባሉት ወደ መጨረሻው ደረጃ ላይ የደረሱት ደግሞ ሙሉ ህይወታቸውን በጸሎት ያሳልፋሉ።

ዝጉሐን ወይም ባህታውያን ይባላሉ። ዘግተው በበአት፣ በዋሻ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው። እንደየብቃታቸው፣ እንደየቆይታቸው፣ እንደአገልግሎታቸው መርዘምና ማጠር የመቁጠሪያው መጠን ይወሰናል። ባብዛኛው በገዳም ብዙ ሰው የሚጠቀምበት 41 ቁጥር ያለውን አቡነ ዘበሰማያት የሚደገምበትን መቁጠሪያ ነው።

ጥያቄ:- 64፣ 120 የሚባል መቁጠሪያ አለ ይባላል። በ41 ውስጥ ደግሞ 12 ጊዜ ተቆጥሮ ይሰገዳል ይባላል። ስለዚህ ቢነግሩኝ?

መልስ:- መቁጠሪያ 41 ነው ስል በ41ዱ መቁጠሪያ ውስጥ 12 አቡነ ዘበሰማያት ወይም አባታችን ሆይ ጸሎት የሚደረስበት ነው። በያንዳንዱ አቡነ ዘበሰማያት ሶስት ሶስት ስግደት አለው። 12ቱ አቡነ ዘበሰማያት 36 ስግደት በአንድ ጸሎት አለው። ሰርክ፣ ነግህ፣ ሰለስት፣ ስድስት ወይም በዘጠኝ ሰዓት ወዘተ. ሰባት የጸሎት ጊዜያት አሉ። በነዚህ ሰባት የጸሎት ጊዜያት ውስጥ እነዚህ 12 አቡነ ዘበሰማያት እና በያንዳንዱ ሶስት ሶስት ስግደት አጠቃላይ 36ቱ አይቋረጥም። በተለይ በመነኮሳት በጣም በጥንቃቄ እነዚህ ሰዓቶች ተጠብቀው ይከናወናሉ። ይህንን ማንኛውም ሰው በገዳም ውስጥ ሲኖር ባለበት ቦታ ሆኖ የጸሎት ደወል አለ የገዳሙ መጋቢ ይህንን ደወል ያስደውላል። ወይም ሰው ይመድባል። መጋቢው ከሌለ ደግሞ እንደ መጋቢ የሚባሉ የመጋቢው ረዳቶች፣ የመጋቢው ልጆች እንደማለት ነው። እንል የሚለው ልጅ የሚለውን ትርጉም የሚይዝ ነው። እነዚህ ይህንን ሰዓት ይጠብቃሉ፤ ያስጠብቃሉ። በዚህ ሰዓት ደወል ሲደወል ለምሳሌ በሐይቅ የድንጋይ ደወል አለ። ያ የድንጋይ ደወል ሲደወል የጸሎት መሆኑን ሁሉም አርድዕት፣ ሁሉም መነኮሳት በያሉበት ቦታ ሲሰሙ በያሉበት ያለው አርድዕት ስራ ቦታ ላሉት ሊቀ አርድዕቱ የአገልጋዮቹ ኃላፊ ያጨበጭባል። በጭብጨባ ድምጽ ሲያሰማቸው ሁሉም በያሉበት በዛፍ ስር፣ በየጥላው አርፈው 12 አቡነ ዘበሰማያት፣ 41 ጊዜ እግዚኦ መሀረነ ክርስቶስ፣ በእንተ እግዚትነ ማርያም መሀረነ ክርስቶስ የሚለውን እግዚኦታም ጭምር አድርሰው ወደየስራቸው ይመለሳሉ። ይሄ በህይወት ዘመናቸው ሁሉ የማይቋረጥ የጸሎት አገልግሎት ነው። ይህንን ጸሎት ሌሎችም በከተማም ያሉ በተለያየ የስራ ቦታም ያሉ ሊያደርሱት ይችላሉ። ገደብ የለውም። መቁጠሪያ ማንኛውም ሰው አጠቃቀሙን ትምህርት ወስዶ መጠቀም ይችላል። ከእኛ ገዳም መቁጠሪያ ተዘጋጅቶላቸው የሚጠቀሙ ሰዎች እንዳሉ አውቃለሁ። በፍትሐ ነገስቱም የጸሎት ሰዓት ለሁሉም በክርስትና እምነት ላመኑት በተለይ እንደ ኢትዮጵያ

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የታዘዘ ነው፡፡ ጌታን በወንጌል ምን ብለን እንጸልይ ብለው በጠየቁት ጊዜ እንደዚህ ብላችሁ ጸልዩ ብሎ ያስተማረን ጸሎት ስለሆነ ለሁሉም የሚመለከት ነው፡፡

አርባ አንዱን እንደዚህ ካልን ስልሳ አራቱ ደግሞ በእመቤታችን እድሜ ልክ፣ እመቤታችን በዚህ አለም የኖረችው 64 አመት ነው፡፡ 64ቱ ከእመቤታችን ፍቅር የተነሳ ወጣኒዎቹ በ41ዱ ካደረሱ ማዕከላውያኑ ደግሞ በ64ቱ ለማድረስ ጊዜ ስላላቸው ነው፡፡ ቁጥሩን የምንወስነው ካለን ጊዜ አንጻር ነው እንጂ እኔም አንተም ሌሎቹም መጠቀም ይችላሉ፡፡ ነገር ግን 64 መሆኑ የእመቤታችን እድሜ ሆኖ ቅዱስ ኤፍሬም በሉቃስ ወንጌል ላይ ያለውን ሰላም ላንቺ ይሆናል ብሎ ቅዱስ ገብርኤል ያበሰራትን ብስራት ሁልጊዜ ቅዱስ ኤፍሬም እየደገመ በዚህ በእመቤታችን ፍቅር አድሮበት ምስጋናሽ እንደ እህል፣ እንደ ልብስ ሆኖኝ አንቺን ሳመሰግን በኖርኩ እያለ ይጸልይ ስለነበር በዚህ የጸሎት ሰዓት ውስጥ 64 ጊዜ የሷን እድሜ እየወሰነ ይጠቀም እንደነበር ብዙ ድርሳናት ይመሰክራሉ፡፡ ስለዚህ 64ቱ እኛም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት እመቤታችንን ለድህነታችን መሰረት የአምላክ እናት ናት ብለን እስከምናምን ድረስ በእሷ እድሜ ልክ እንቆጥራለን፡፡ አሁንም እዚህ አገልግሎት ውስጥ 12 አቡነ ዘበሰማያት እንደተጠበቀ ነው፡፡ እግዚኦ መሀረነ ክርስቶስ፣ በእንተ ማርያም መሀረነ ክርስቶስ ብለን የምንለምነው የልመናችን መጠን ከ41 ወደ 64 አደገ ማለት ነው፡፡ 41 ጊዜ የምንለምነውን 64 ጊዜ እንደግማለን ማለት ነው፡፡ ጊዜ ካለን 120 ጊዜ እንደግማለን ማለት ነው፡፡ 64 እና 120 ሲሆን የምንደግመው ያድጋል፡፡ የምንጠቀመው ቃላት፣ ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት፣ የምናስተላልፈው መልእክት አንድ አይነት ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ውስጥ እንደ አንድ አገላለጽ የሚገለጽ ነው፡፡ 41፣ 64፣ 120፣ 72፣ 36 ብለው የሚሉ አሉ፡፡ ነገር ግን 12ቱ በዚህ በ41 መቁጠሪያ ውስጥ የተካተተ ነው፡፡ 36 ብንልም እንደዚሁ ነው፡፡ 72 ብንልም በ120 ውስጥ የተካተተ ነው፡፡ ስለዚህ የምንጠቀመውን የጸሎት ክፍል ባለን መቁጠሪያ ውስጥ መጠቀም ስለምንችል አብዛኛው መነኮሳት፣ አብዛኛው ሰው የሚጠቀመውና የተለመደው 41 መቁጠሪያ ነው፡፡ አመጣጡም የአዳም ሱባኤ ነው፡፡ አዳም በስህተት ከገነት ከወጣ በሁዋላ ከሄዋን ጋር ሱባኤ ገባ፡፡ ሱባኤ የገባው 40 ቀን ሊቆዩ ነበር፡፡ በሰላሳ አምስተኛው ቀን በጠላታችን ሰይጣን ምክር ሱባኤውን አቋርጦ ወጣ፡፡ በዚህ ጊዜ ቀድሞም ከገነት ያስወጣሁህ ጥንት ጥላትህ እኔ ነኝ አለው፡፡ በዚህ ጊዜ አዳም መሬት ላይ ወድቆ ሶስት ቀን አልቅሷል፡፡ እህል ሳይቀምስ በረሃብ ሶስት ቀን

ከቆየ በሁዋላ መላእክት እግዚአብሔር ሆይ አዳም በረሃብ ሊሞት ነው። እየተራበ፣ እየተጠማ ጎስቁሎ ነው ያለው። ብለው ወደ እግዚአብሔር ልመና አቀረቡለት። በዚህ ጊዜ የገነት አእዋፍት ከገነት እጽዋት ፍሬ ለቅመው ከረሃብ ለማስታገስ ወደ አዳም አመጡለት። አዳምም አእዋፍቱን እየተከተለ ወደ ገነት ሄደ። ከዚያ በኋላ ዲያብሎስ ጠላቱ አሁንም ገነትን መናፈቅህ፣ ለማግኘት መሞከር አልተውክም ብሎ ድንጋይ ወርውሮ ጫነበት። ደሙም ደማ፣ ቆሰለም፣ አለቀሰም። በዚህ ሁኔታ ሶስት ቀን ቆይቷል። የመጨረሻውን የእንባውን ያቀረበውን መስዋእት እግዚአብሔር የተቀበለለት በዚህ ቀን ነው። ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ። አንተ በምታቀርበው ደም ከስህተትህ ወይም ፍጹም የሆነ ድህነት አታገኝም። ከልጅህ ተወልጄ የሚለውን ቃል ያገኘው በዚህ ሰዓት ሲሆን፤ 35ቱ ሱባኤ፣ ሁለተኛ በረሃብ የቆየበት ሶስት ቀን፣ ቆስሎ የቆየበት ሶስት ቀን ሲደመሩ ስድስት ቀን እና 35ቱ 41 ይሆናል። በነዚህ 41 ቀናት ልመናው፣ ለቅሶው፣ ንስሃው እግዚአብሔር እንደሚያድነው ወደዚህ አለም የክርስቶስን መምጣት ብስራት፣ ቃል ኪዳን ተቀብሎ የዳነበት ሱባኤ ስለሆነ 41 ሱባኤ ብለን የምንጠቀመው ከዚህ የተነሳ ነው። እኛም እግዚኦ መሀረነ ክርስቶስ ብለም አዳምን እንደማርከው፣ አዳምን እንዳዳንከው፣ ከነልጅ ልጆቹ ከገሃነመ እሳት ወደ ገነት፣ ወደቀድሞው ክብራቸው እንደመለስካቸው እኛንም ለመንግስተ ሰማያት አብቃን እያልን የምንጸልየው የጸሎት አይነት ስለሆነ ነው 41 የምንጠቀመው።

64ቱ እመቤታችን በዚህ ዓለም የኖረችበትን የእድሜ መጠን የሚያመለክት ነው። 72ቱ የ72ቱ አርድእት ናቸው። 120 ካልን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሲያስተምር 5000 ገበያ የሚያህል ህዝብ ይከተለው ነበር። ከነዚህ ውስጥ 120 መረጠ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን 120 የምንላቸው 12 መጀመሪያ የመረጣቸው ሐዋርያት፣ 72 አርድእት ሐዋርያትን የሚያገለግሉ፣ የሚላኩ፣ የሚወጡ፣ የሚወርዱት አርድእት የምንላቸው፣ 36ቱ ቅዱሳት አንስት ማለት 36ቱ ሴቶች እነዚህ አጠቃላይ ሲደመሩ 120 ይሆናሉ። ስለዚህ እነዚህ ክርስቶስ ከዚያ ሁሉ ህዝብ ውስጥ ለእሱ አገልግሎት የመረጣቸው ለተልእኮ፣ ይህንን ዓለም ለማስተማር፣ ለማዳን የላካቸው የ120 ሰዎች ወይም ቤተሰቦች ምሳሌ ነው።

41ዱ የአዳም ሱባኤ፣ 64ቱ የእመቤታችን እድሜ፣ 120ው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተሰቦች፣ የ12ቱ ሐዋርያት፣ የ72ቱ አርድእት፣ የ36ቱ ቅዱሳት አንስት ምሳሌ ነው። አጠቃላይ ሲደመሩ 120 ይሆናሉ። በዚህ የሚጠቀሙ ዝጉሃን የሆኑ ባህታውያን፣ በባእት

ብቻ ተወስነው ሃያ አራቱን ሰዓት ጊዜያቸውን ለጸሎት ብቻ ሰጥተወው የሚያገለግሉ አባቶች 120ውን እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ወይም አባታችን ሆይ ይጸልያሉ። ምክንያቱም ሙሉ ጊዜያቸውን ለጸሎት የሰጡ ናቸው። ይህ ሁሉ መነሻው ወንጌል ነው። 120 ቤተሰቦች እንደመረጠ የሐዋርያት ስራ ምዕራፍ አንድ፣ ሁለት፤ አባታችን ሆይ ብላችሁ ጸልዩ እንዳለ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ስድስት ላይ ይነግረናል። ስለዚህ ጸሎቱም ልመናውም በመቁጠሪያ መነኮሳት መልሰው መላልሰው የሚጸልዩት ይህንኑ ነው። አቤቱ ይቅር በለን ብለው አብዝተው መጸለይ፣ መለመን 64 ጊዜ፣ 41 ጊዜ፣ 120 ጊዜ እየደጋገሙ የሚጸልዩት የጸሎት አይነት ነው።

መቁጠሪያ የሚዘጋጀው በገዳም ባሉ ለመቅረጽ የሚችሉ አባቶች ያዘጋጁታል። ለአዘገጃጀቱ በብዛት በገዳም የምንጠቀምበት ከተለያየ እጽ ነው። ያ ማለት ከወይራ፣ ከልምጭ፣ ከርመል ከሚባል እንጨት፣ ከሎሚ ከነዚህ ከነዚህ ይዘጋጃል። ከዚህ ውጭ በፋብሪካ በተለያዩ እንጨት ያልሆኑ እንደ ዶቃ፣ በፕላስቲክ ነገሮች ተሰርቶ ገበያ ላይ ይታያል። በገዳም በብዛት ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው በእንጨት ነው ከሚል እሳቤ በእንጨት ነው የምንጠቀመው። ሐይቅም ላይ እዚያው ከገዳም ውስጥ ይዘጋጃል።

ጥያቄ፡- በገዳም ውስጥ መቁጠሪያ መያዝ ግድ ነው? የሚለያዩ ነገሮችስ አሉ?

መልስ፡- ግዴታ ነው ብለን ባናስቀምጠውም ቁጥር እስካልተሳሳትን ድረስ በእጃችን መቁጠር እንችላለን። መላልሶ መቁጠር ከተቻለ። ነገር ግን እንደ አንድ ሃይማኖታዊ መሳሪያ ነው መቁጠሪያ የሚታየው። መቋሚያ፣ መጽሐፍ፣ ከበሮ እንደምንለው መቁጠሪያም በገዳማት መነኮሳት ደረጃ እንደ አንድ የጸሎት መሳሪያ ነው። የአጋንንት ማባረሪያ መሳሪያ ነው። መቁጠሪያ ጫፉ ላይ መስቀል አለበት። መቁጠሪያ ያለ መስቀል አይዘጋጅም። ለጸሎት ሲቆሙ ጫፉ ላይ ባለው መስቀል መላ ሰውነታቸውንና ገጻቸውን አማትበው ወደ ጸሎታቸው ይገባሉ። አብዛኛው መነኮሳት መቁጠሪያ ይጠቀማሉ። ግን ባይዙ አያስወቅስም፤ አያስከስስም።

ጥያቄ፡- በአንድነት ገዳም በአንድነት መመገብና ለብቻ መመገብ ያላቸውን ልዩነት ቢነግሩኝ?

መልስ፡- በገዳማት በህብረት ወይም በአንድነት መመገብ መነሻው ቅዱሳን ሐዋርያት ተሰባስበው ማዕዳቸወውን እየቆረሱ ይጸልዩ ነበር ይባላል። ይህም ማዕዱ እንደ መሰብሰቢያ፣

የአንድነታቸው፣ በህብረት የመጸለያቸው መሰረት ነው። የግል ሐብት ንብረት ሳይኖር፣ የኔ የግሌ ሳይባል የተለያየ ስራ እየሰሩ በአንድ ላይ ይመገባሉ። አሁን አሁን ግን በእኛ ገዳም ያለው ምንድን ነው ሰዎች ለትሩፋት፣ ለሚሰሩት ስራ ይመቻቸው ዘንድ እኩል መቁነን በማንኪያም ሆነ በጭልፋ ቢደርሳቸው ያንን በበአታቸው ወስደው በሚፈልጉት ሰዓት፣ በሚፈልጉት መጠን እንዲጠቀሙ ያመቻቸው ዘንድ ወደ በአታቸው ወስደው ይመገባሉ። ያ ምንድን ነው ግማሹ ብዙ መመገብ ሊፈልግ ይችላል፤ ግምሹ ደግሞ ከፍሎ ጥቂት ሊመገብ ይችላል። የአመጋገባችን ስርዓት ስለሚለያይ አንዱ ባንዱ ላይ ተጽእኖ እናዳይፈጥር፣ ውዳሴ ከንቱ ሌላ ዘለፋ እንዳያመጣ ሁሉም በየበአታቸው ይመገባሉ።

ጥያቄ፡- ወይባ የገባ፣ ጥቁር የመሳሰሉትን አለባበሶች ቢነግሩኝ?

መልስ፡- መነኮሳት የሚለብሱት ቀሚስ ነው። ቀሚሱ የተለያየ ከለር ሊኖረው ይችላል። የቀሚሱ አመጣ ከኢየሱስ ክርስቶስ አለባበስ የተወሰደ ነው። ዛሬ ላለነው መነኮሳት መነሻችን ኢየሱ ክርስቶስ ነው። እሱም አንድ ወጥ የሆነች ቀሚስ ይለብስ ነበር። ያቺ ቀሚስ እሱ ባደገ ቁጥር አብር ታድግ ነበር ይባላል። ቀሚሱ ቢጫ ሲሆን ይህን ምድራዊ ዓለም ረስቶ፣ በሰማያዊ ነገር ተስፋ አድርጎ መኖር፣ መንግስተ ሰማያትን መጠበቅ፣ ከዚህ ከምናየው ዓለም ይልቅ የማናየውን ዓለም በተስፋ መጠበቅን ያመለክታል።አፈር ሲሆን ደግሞ ነጭ ወይም ደረጃውን የጠበቀ ልብስ በገዳም አይፈቀድም። ስለዚህ እኛ የተዋረድን ነን፣ አይገባንም፣ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ራሳችንን ጥለን አዋርደን እንኖራለን የሚለውን ያመለክታል። ልብሱ አፈርና ወይባ ሲገባ ደረጃውን ይቀንሳል። ይህም ትህትናን የሚገልጽ ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ ያደረገ፣ በዚህ ዓለም ከሁላችሁ ትንሽ የሆነ ከሁላችሁ ትልቅ ይሆናል ብሏል። ጥቁሩ ለዚህ ዓለም አልተገባንም፣ ለእኛ ይህ ዓለም መከራ ነው፣ በዚህ ዓለም ያለውን መከራ እያሰቡ መኖርን ያመለክታል።

አበሪ -2- ከገዳሙ የተሰበሰቡ አፊ ታሪኮች

አፊ ታሪክ 1

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተባሉትን ጻድቅ አባታቸው ትምህርት እንዲማሩ፤ በመንፈስ ታንጸው እንዲያድጉ ወደ እዚህ የምንኩስና ማዕከል አመጧቸው። ከዚያ በኋላ እየተማሩ እስከ ሶስት አመት ድረስ ቆዩ። በዚህ ጊዜ ፊደል እንኳን መጨረስ አልቻሉም ነበር።

ቢኋቸው ቢያደርጓቸው አልገባቸው አለ። ተሰጥኦአቸው አልሆን አለ። ከዚያ እኛ እንግዲህ ይህ ሰው ትምህርቱ አልገባውም። አባቱም ጉልበቱን እየገዙ አላስተማሩልኝም ብሎ ሊወቅሰን ነው ብለው መጥተህ ልጅህን ውሰድ ጸጋ እግዚአብሄር አላደረበትም፤ሙያ ሊያገኝ አልቻለም። ወቀርን ግን ፊደል እንኳን ሊያውቅ አልቻለም ብለው ውሰድ አሏቸው። አባታቸውም እኔ እንግዲህ አንድ ጊዜ መባእ አድርጌ ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቻለሁ። ቢማር ይማር። እንደፈቀደው ሁኖ እናንተን እያገለገለ ይኑር ብለው አልወስድም አሉ።

ከዚህ በኂላ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ምርር ብለው ከአንዲት ስእለ ማርያም ላይ አለቀሱ። እመቤቴ እኔ ከድንጋይ ነው የተፈጠርኩት? ከባልንጀሮቸ በታች ሆኘ ቃለ እግዚአብሄር የተዘጋብኝ ለምንድን ነው? ብለው ምርር ብለው እንባቸውን ስእለ ማርያሟ ላይ አፈሰሱ። ትምህርቱ ቀርቶ ይፍጭ እየተባሉ በየቀኑ ዘጠኝ ዘጠኝ ቅርጫት እህል ይፈጩ ነበር። እያለቀሱ፤ እየሰገዱ ጠዋት ማታ በዚያች ስእል ላይ ሲማጸኗት እመቤታችን ቅድስት ማርያም አሳየቻቸው። አንዳንድ ሰዎችም ጡቷን አጠባቻቸው ይላሉ። እኔ በዚህ አላምንም። ባይሆን እንኳ ከጡቷ ነጠብጣብ ላይ ኡራኤል ሰውነታቸውን ቀባቸው ይባል። ከዚህ በኂላ ዓለሙ በሙሉ ዳር እስከ ዳር ተገልጦ ብርሃን ሆናቸው። ቃለ እግዚአብሄር ብቻ ሳይሆን ዓለም በሙሉ ተገልጦ ታያቸው። ድርሰት የሚደርሱ ሆኑ። እነ ኖኅተ ብርሃን፣ መጽሐፈ ምስጢር፣ አርጋኖን፣ ሰዓታት ሁሉ የደረሳቸው መጻሕፍት እዚህ አሉ። ብዙ ታምራት ሰርተው መንኩሰው ወደ ጋስጫ ሄደው አስተምረው እዚያው ተቀበሩ።

አፈ ታሪክ 2

በሐይቅ ከተማና በገዳሙ አካባቢ ያሉ ሰዎች ከሐይቁ ውስጥ አሳ እያሰገሩ ለገበያ ያቀርባሉ። በፊት የሚያሰግሩት ወደ ደሴቱ ሳይገቡ በሐይቁ ዳር ዙሪያውን ሆነው ነበር። ቀስ በቀስ ደግሞ በደሴቱ ውስጥ ገብተው ማስገር ጀመሩ። መነኮሳቱም አሳ አስጋሪዎቹ ወደ ደሴቱ እየገቡ ሲያሰግሩ አንዳንድ እቃ ሊጠፋብን ይችላል በማለት እንዳይገቡ ከለከሉ። አስጋሪዎቹ ግን ሊሰሙ ስላልቻሉ በደሴቱ መግቢያ በር ላይ የዘበኛ ቤት ተሰራ። ቤቱ ተሰርቶ ሲያልቅም አንድ ጠባቂ ቆሞ ወደ ውስጥ የሚገቡትን ሰዎች ማንነት እንዲያጣራ ተደረገ። ይህም ለአስጋሪዎቹ አመቺ ባለመሆኑ ከአስጋሪዎቹ አንዱ የተሰራውን ቤት አቃጠለው። መነኮሳቱም እኛ አንጣላም ብለው እንደገና ሌላ ቤት ሰሩ። አሁንም ያ ሰውየ መጥቶ ቤቱን አቃጥሎት ሄደ። መነኮሳቱም እኛ ጉልበት የለንም ጉልበቱ የፈጣሪ ነው ብለው

በጣም አዘኑ። ሰማዒት በምትባለው ሥዕል ፊት ሆነውም መሪር ለቅሶ አለቀሱ። ለሰባት ቀን ያህልም በሥዕሏ ፊት ሆነው ተማጸኑ።

ከዚያ በኋላ አንድ ቀን ቤቱን ያቃጠለው ሰውየ እርሻ እያረሰ ድንገት አመመኝ ብሎ እርሻው ላይ ወደቀ። በዙሪያው እያረሱ የነበሩ ሰዎች ከወደቀበት አንስተው ወደ ቤቱ ወሰዱት። በዚያው በሽተኛ ሆኖ እንደተኛ ሳይነሳ ለሞት በቃ። መነኮሳቱም አብዛኛውን ጊዜ የከፋ ችግር ሲያጋጥማቸው በዚችው ሥዕል ፊት ይማጸናሉ። ሰማዒት ማለት የምትሰማ ማለት ስለሆነ ልመናቸንን ሁሉ ትሰማናለች።

አፈ ታሪክ 3

ገድለ አቡነ ኢየሱስ ሞአ የሚባለው መጽሐፍ የሚወጣው ለክብረ በዓልና ለአንዳንድ ጉዳዮች ነው። አንድ ጊዜ የአንበጣ መንጋ ተነስቶ የአገሩን ሰብል እና ለምለም ነገር ሁሉ እያጠፋ ወደ ሐይቁ አካባቢ ደረሰ። መነኮሳቱም መንጋውን እንዳዩ የአቡነ ኢየሱስ ሞአን የገድል መጽሐፍ ይዘው ደሴቷን በሙሉ ዞሩ። ከዚያም መጽሐፉን እንደያዙ ወደ ሐይቁ ዳር ወጡ። የአንበጣ መንጋውም ወደ ደሴቷ ሳይገባ ተመለሰ። ከአንበጣ መንጋውም አንድም ወደ ደሴቷ የገባ የለም። ይህ መጽሐፍ አሁንም በየበአሉ ይወጣል። ሁሉም ሰው የበረከቱ ተካፋይ እንዲሆን ማለትም ሴቶች ወደ ደሴቷ መግባት ስለማይችሉ ተብሎም በአመት ክብረ በዓሎች ወቅት ከገዳሙ ውጭ በሩ አካባቢ በተዘጋጀው የምእመናን መሰባሰቢያና የበአል ማክበሪያ ስፍራ አካባቢ ድንኳን ተዘጋጅቶ ይወጣል። ምእመናኑም በመጽሐፉ እየታሹ ይመለሳሉ። ከበሽታቸውም ይፈወሳሉ።

አፈ ታሪክ 4

በሐይቅ ከተማ አካባቢ የሚኖር አንድ ሀብቱ የተትረፈረፈ ባለጸጋ ነበር። የባለጸጋው አሽከር የሰውየውን ባለቤት ይዞ የአቡነ ኢየሱስ ሞአ በዓል በሚከበርበት ቀን ወደ ገዳሙ ዘወትር ይመጣ ነበር። እመቤቱን ከሐይቁ ዳር አስቀምጦም እሱ ወደ ደሴቱ የሚገባበት ታንኳ እንዲመጣለት እያደረገ ወደገዳሙ ይገባል። ከገባ በኋላም መጋቢውን እያስፈራራ ምግብና መጠጥ ይወስዳል። መጋቢውም ሰውየው በተደጋጋሚ እየመጣ ሲያስቸግረው በጣም ተማረረና ወደ አቡነ ኢየሱስ ሞአ መቃብር ቦታ ሂዶ አለቀሰ። ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥም ገብቶ የታምረ ማርያምን መጽሐፍ አንስቶ ይህ ሰውየ ዳግመኛ ከመጣ የአባቴን የኢየሱስ

ሞአን ስም አልጠራም፤ የእመቤታችንንም ታምር አላነብም አለ። ሎሌውም እንደ ልማዱ ወሩ መጥቶ ታንኳ እንዲልኩለት አዘዘ። መጋቢውም ታንኳውን ልኮ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ብቶ ማልቀስ ጀመረ። ሎሌውም በታንኳ ሁኖ ወደ ደሴቱ እየተጓዘ ሳለ ከባህሩ ውስጥ አዞ ጥቶ ዋጠው። አዞው አፉን ሲከፍትም ሰውየው በሁለት እጁ አፉን ይዞ ታየ። እመቤቲቱም መነኮሳቱን ስትሳደብ የሎሌሽ እጣ እንዳይደርስሽ ዝም ብለሽ ሂጂ አሏት። ከዚያ በኋላ ማንም ው ከመነኮሳቱ ፈቃድ ውጪ በጉልበት ምግብም ሆነ መጠጥ ለመውሰድ የሚሞክር የለም።

ፊ ታሪክ 5

አንድ በየሀገሩ እየዞረ በሌብነት የሚኖር ሰው ነበር። በየአካባቢው ያለው ሰው ብነቱን ሲያውቁበት ወደ ገዳሙ መጥቶ አጥምቁኝና የእናንተ አገልጋይ ልሁን ብሎ ጠየቀ። መነኮሳቱም ወደ ደሴቱ አስገብተው፣ በስርዓተ ጥምቀት መሰረት አጥምቀው፣ የሃይማኖት መጽሐፍት እያስተማሩት ለስድስት ወር ያህል ተቀመጠ። ሲገም ተንኮል አስቦ ስለነበር ገዳሙን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ካጠናና መነኮሳቱም እንዳመኑት ካረጋገጠ በኋላ አንድ ቀን ሌሊት ተነስቶ ከሙዳየ ምጽዋት ማስቀመጫው ውስጥ ያገኘውን ገንዘብ ይዞ ጠፋ። መነኮሳቱም በጣም አዝነው ሳይፈልጉትም ዝም ብለው ተቀመጡ።

ሰውየው ግን የወሰደው ገንዘብ ሲያልቅበት ተመልሶ ወደ ገዳሙ መጣ። መነኮሳቱ ሚተኙበት ወቅትም ወደ ደሴቱ ገብቶ የቤተ ክርስቲያኑን መስኮት ከፍቶ ገባና ንዋያተ ዱሳቱን ሰብስቦ ይዞ ሊወጣ ሲሞክር መንቀሳቀስ አቃተውና ባለበት ተገትሮ ቀረ። የእለቱ ረኛ አጣኝ ካህንም ሌሊት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሲገቡ ሰውየውን ተገትሮ ስላዩት ጮኹ። መነኮሳቱም ጩኸታቸውን ሰምተው የደሴቱን ዙሪያ ከበው ሰው እንዳይወጣ መጠባበቅ መሩ። ሲነጋም ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሂደው ሰውየውን አውጥተው ክፉኛ ገረፉት፤ እሳትም ተኩሰው ለቀቁት። የሰውየው ወሬም በሀገሩ ሁሉ ተሰማ። ከዚያ በኋላ መነኮሳቱን ማታለልና ንብረታቸውን ለመዝረፍ የሚሞክር አያጋጥምም። ሰውየውንም ገትሮ ያስቀረው ንዋያተ ቅድሳቱ ተአምር መሆኑ ስለሚነገር ለመስረቅ የሚደፍረን የለም።

ፊ ታሪክ 6

አቡነ ብስጣውሮስ አበምኔት በነበሩበት ወቅት ሁለት ወንበዴዎች ወደ ሐይቁ አካባቢ ጡ። ለአበምኔቱም ቤተ ክርስቲያንህን አቃጥለን ሀገርህን ልንወርስና ሀብትህንም ልንቀማ

መጣንብህ፤ ሰዎችህንም አንድም ሳናስቀር እንገድላቸዋለን ብለው መልእክት ላኩ። አቡነ ብስጣውሮስም መልእክቱን እንደሰሙ ለማንም ሳይናገሩ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ገብተው የአቡነ ኢየሱስ ሞአን መስቀል ይዘው ወንበዴዎቹ ወዳሉበት ስፍራ መሄድ ጀመሩ። በመንገዳቸውም የአቡነ ኢየሱስ ሞአን ስም ይጠሩ ነበር። ገጻቸውም ያያቸውን ሁሉ በጣም ያስፈራራና ያሸብር ነበር። ወንበዴዎቹም አቡነ ብስጣውሮስ መስቀል ይዘው ወደነሱ ዘንድ ሲመጡ ባዩዋቸው ጊዜ በጣም ደነገጡ። ሲቀርቧቸውም ወደ ኋላ ማፈግፈግ ጀመሩ። ከዚያም ሸሽተው ወደ መጡበት ተመለሱ። አገራቸውም እንደደረሱ ብዙ ሳይቆዩ ሁለቱም ሞቱ።

ወንበዴዎቹ ወደገዳሙ ሲመጡ ለአካባቢው ነዋሪ ከገዳሙ የሚዘርፉትንና የሚያመጡትን ንብረት እንዲሁም የሚይዙትን ግዛት ተናግረው ነበር። ባዶ እጃቸውን መጥተው ታመው የሞቱበት ሁኔታ ሲታወቅም ህዝቡ ሁሉ የነሱ ዳፋ እንዳይደርስባቸው ፈርተው ነበር። ከዚያ በኋላ እንኳን ቤተ ክርስቲያኑን የሚያቃጥልና የሚዘርፍ ቀርቶ ከነመኮሳቱ ፈቃድ ውጪ ወደ ደሴቱ ውስጥ የሚገባ ሰው አልነበረም።

አፈ ታሪክ 7

በቤተ ክርስቲያኑ እቃ ቤት አካባቢ የሚስማር ቤት አለ። በአካባቢው የነበረው የመነኮሳት ቤት በእሳት ቃጠሎ ተያያዘ። የእሳቱ ላንቃ በቤተ ክርስቲያኑ ላይ እየተላለፈ ወደዚህ መጥቶ ሌላ ቤትና ዛፍ አቃጠለ። ንዋያተ ቅድሳቱ ያሉበት ቤት እሳቱ በላዩ ላይ እየሄደበት አልተቃጠለም። ነገር ግን መነኮሳቱ ተቃጠለብን ብለው መጻህፍቱን ከቤት እያወጡ አሸሹ። እሳቱ ግን ቤቱን አልነካውም። ዘመኑም 1942 ዓ.ም ነው። ይህ በታምርነት የሚጠቀስና የሚጻፍ ነበር። በጊዜው የነበሩ አባቶች ስላለፉ ሳይታወስና ሳይጻፍ ቀረ።

አፈ ታሪክ 8

በዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሀገራችን ኢትዮጵያ ጳጳስ የነበረው አቡነ ሰላማ ሁለተኛ ይባላል። ጳጳሱ ከአክሱም ተነስቶ በአዳል መሬት በኩል ህዝቡን እያስተማረና እያጠመቀ ወደዚህ አካባቢ መጥቶ ነበር። ወደዚህ ሲመጣ ያረፈው እዚያ ማዶ ከሐይቁ ዳር በሚታየው ተራራ ላይ ነው። ተራራው ድማሞ ይባላል። አንዳንድ ሰዎችም የእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ስለተሰራበት ደብረ እግዚአብሔር እያሉ ይጠሩታል።

ጳጳሱ እተራራው ላይ ሆነው ሐይቁን እና ዙሪያውን አስተዋሉ፡፡ የሐይቁና የአካባቢው ማማር ቀልባቸውን ስቦት ስለነበር በሐይቁና በአካባቢው ስለሚኖሩ ሰዎች ሁኔታ በዙሪያቸው ያሉ ሰዎችን ጠየቁ፡፡ ሰዎቹም በሐይቁና በአካባቢው የሚኖሩ የሚያምኑት በዘንዶ እንደሆነና ለዘንዶውም እንደሚሰግዱለት ነገራቸው፡፡ በተጨማሪም ለዘንዶው ወተትና የከብት ስጋ ገብላት በተባለ ድንጋይ ላይ እንደሚገብሩ ነገሯቸው፡፡ አቡነ ሰላማም ቦታው በጣም ማርኳቸው ስለነበር ሰዎቹ ለዘንዶ በመስገዳቸው ተቆጩ፡፡ ከዚያ መስቀላቸውን ወደሐይቁ አቅጣጫ አመልክተው በስመ እግዚአብሔር ስም አማተቡ፡፡ በዚያው ቅጽበትም ዘንዶው የገባበት ሳይታወቅ ጠፋ፡፡ ከዚያ በኋላ በዚህ ገዳም ውስጥ ሚኖሩ ሰዎች ለፈጠራቸው እግዚአብሔር እንጂ ለዘንዶና ለሌላ ነገር አልሰገዱም፡፡

አፈ ታሪክ 9

በጣሊያን ወረራ ጊዜ ጣሊያኖች በአውሮፕላን በቤተ ክርስቲያኑ ላይ ሶስት ቦንቦች ወረወሩበት፡፡ ከተወረወሩት አንዱ ተምዘግዝጎ ወደ ባህሩ ውስጥ ገባ፡፡ አንዱ ደጀሰላሙ አካባቢ ወድቋል ይባላል፡፡ አንዱ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኑ ላይ አርፎ እየጠቃ ወደ መሬት ገባ፡፡ የወደቀውም በቤተ ክርስቲያኑ ደረጃ አካባቢ ስለሆነ በዚያ አካባቢ አትቀመጡ ይባል ነበር፡፡ በቅርብ ጊዜም አንድ ፈረንጅ መጥቶ ሲጃራ አጤሶ ቁራጩን ሲጥለው አካባቢው ጨሰ፡፡ ፈረንጁም ደንግጦ ትርኳሿን በእንጨት አንስቶ እዚህ አካባቢ ምን አለ? አለ፡፡ የተቀበረ ቦንብ አለ ሲሉት ይህ ካልወጣ ፈንድቶ አገር ያጠፋል፤ ብሎ ሄደ፡፡ አሁንም ድረስ ቦንቡ እንደተቀበረ ቀርቷል እንጂ አልወጣም፡፡ አንደኛው ወደ ወንዙ የወረደውን አምጥተውት ነበር፡፡ አሁን ግን የት እንደደረሰ አይታወቅም፡፡ ቦንብ የወረወረው አውፕላንም ቦንቡን ወረወውሮ ሲሄድ ባህሩን ሳይሻገር ጭስ አሳየ፡፡ ከዚያ ባህሩ ማዶ ላይ ሲደርስ ቦግ ብሎ ነደደ፡፡ ከዚያ ዛፉን እያቃጠለ ተምዘግዝጎ ወረደ፡፡ ሰውም እየሄደ የሰዎቹን ልብስ ገፏቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያኑም በዚህ ሁኔታ ታምሩን አሳይቷል፡፡ ቦታዋም አንዳዴ ትባላለች፡፡ አውሮፕላኑ ቤተ ክርስቲያኑን ባያቃጥልም በመድፈሩ ብቻ ባህሩን ሳይሻገር ታምሩን አሳይቷል፡፡

አፈ-ታሪክ 10

መምህር ጥኡመ ልሳን የሚባሉ አባት በፊት ነበሩ። ያረፉትም እዚሁ ነው። እሳቸው ገዳሙ በቁሪት በሚተዳደርበት ዘመን ይህ ገዳም እንደዚህ በቁሪት አይኖርም፤ አሁን ዘመኑ ደርሷል። ነገር ግን እኛ አናገኘውም። በእናንተ ዘመን ግን ጥንት አቡነ ኢየሱስ ሞአ እንደመሰረቱት የአንድነቱ ጊዜ ይመለሳል። አሁን በቅርብ ጊዜ አንድነቱ ይመለሳል እያሉ ትንቢት ይናገሩ ነበር። እሳቸው ባረፉ በሁለተኛው ዓመት የገዳሙ አንድነት ተመሰረተ። በተጨማሪም በዚያ ጊዜ እኛ ስናልፍ ታምር ታያላችሁ ብለው ይናገሩ ነበር። እሳቸው ባረፉ ጊዜም የባህሩ አሳ በጠቅላላ ወጣ። ሜዳው ሁሉም አሳ ብቻ ሆነ። እሳቸው በጣም ታዋቂ ሰው ስለነበሩ ለቀብራቸው ከሸዋና ከሌላ አካባቢ ሰው እየተጠራ መጥቶ ነበር። የመጣው ሰውም አሳውን እየተሸከመ ሄደ። አልችለው ብለውም በየመንገዱ ጅብ እየበላው የቀረ ሞልቷል። ይህ ትንቢት የታየው በእሳቸው ጊዜ ነው።

አፈ ታሪክ 11

አንድ ዘንዶ በገዳሙ አካባቢ እየተስለከለከ ያስቸግር ነበር። አንድ ቀን በየት እንደገባ ሳይታወቅ በቤተ እግዚአብሄር ቤት ገብቶ እወጣለሁ ብሎ ሲታገል በጣሪያው በኩል ትንሽ ሽንቁር አገኘ። በዚያች ሽንቁርም ግማሽ አካሉ እንደወጣ ከወገቡ በታች ያለው አካሉ እዚያው ቀረ። ግድግዳውም አጣብቆ ይዞት ስለነበር ጠዋት ስንወጣ ሞቶ ተንጠልጥሎ ሞራው እየተንጠባጠበ አገኘነው። ይህ የሆነውም ጻድቁ ባገለገሉበት ቦታ እና ለዘንዶው ባልተፈቀደ ቦታ ላይ በመግባቱ እሳቸው በታምራቸው እንዳጠፉት ይታመናል። የቆሎ ተማሪዎችም ዘንዶው ያለ መስሏቸው በትልቅ እንጨት ደበደቡት። እሱ ግን ሞቶ ስለነበር ሞራው ሁሉ በአፉ ይንጠባጠባል። ከዚያ አውጥተን ቀበርነው። ከዚያ በሁዋላ ዘንዶ አላየንም። እሱ ሳይሞት በፊት ግን በቤተ እግዚአብሄር እየተዘዋወረ ሲኖር በቀን ሶስት አራት ጊዜ ሳናየው አንውልም ነበር።

አፈ ታሪክ 12

አቡነ ፊሊጶስ ዘደብረ ቢዘን የተባሉት አባት ይህን ባህር አቃጥለውት ነበር። አንዳዴ ባህር የተባሉትም ለዚህ ነው። እሳቸው በዚህ አካባቢ በነበሩበት ጊዜ ከአገሩ መሳፍንት ጋር በሐሰት ወሬ የአካባቢው ሰው አጣሏቸው። መስፍኑም በሃይማኖቱ የጸና አልነበረም።

እንደፈለገው የሚኖር ነበር። ሰዎቹ የከሰሷቸውም አንተን በጸሎት ካላጠፋሁ እያሉ ያሙሃል፤ ይሰድቡሃል ብለው ነበር። መስፍኑም አስጠርቶ ሲጠይቃቸው እኔ አላልኩም። ግን ብልም አያስጸይፍብኝም፤ አንተ የቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚ እስከሆንክ ድረስ ሃይለ እግዚአብሄር ያጠፋሃል አሉት። መስፍኑም ተናዶ በቁርበት ጠቅላችሁ ከዚህ ባህር ጨምሩት ብሎ አዘዘ። እሳቸውም ፍርዱን በክብር እቀበለዋለሁ ካሉ በኋላ መጠቅለያው እስከሚዘጋጅላቸው ድረስ ወደ እግዚአብሄር አመለከቱ። ከዚያም እናንተ አሳዎች በእኔ እዳ፣ በእኔ ኃጥያት እንዳትቃጠሉ ወደ ዳር ውጡ፤ ይህ ባህር ሲቃጠል ነው ብለው አሳዎቹን አዘዙ። ለህዝቡም እነዚህ አሳዎች ወደ ዳር ከወጡ በኋላ ወደ ባህራቸው እስከሚመለሱ ድረስ ስደተኞች ስለሆኑ እነሱን ይዞ የበላ በስልጣነ አቡየ የተወገዘ ይሁን፤ የእባብ ስጋ ይሁንበት። ሲመለሱ ግን የተለመደውን ታደርጋላችሁ ብለው አወገዙ። ከዚህ በኋላ አሳዎቹ ሙልጭ ብለው ወጥተው የሐይቁን ዳር ሸፈኑት። እሳቸውንም በቅርበት ጠቅልለው ከፍ ካለ ቦታ ላይ ሆነው ጣሏቸው። ባህሩ ውስጥ ከመግባታቸው በፊትም ቁርበቱ ተፈቶ ወደቀ። እሳቸውም በእግራቸው ባህሩ ላይ ቆሙ። ከዚያም እሳት ቦግ ብሎ ባህሩ ከዳር እስከዳር በሙሉ ነደደ። እሳትና ውሃ እንዴት እንደተዋደደ ተመልከት። ውሃው ወደ እሳትነት የተቀየረው በጸሎታቸው ነው። በዚህ ባህር ውስጥ የነበሩት ጉማሬ፣ አዞና ሌላም አራዊቶችና አጋንንቶች በሙሉ ግማሾቹ አርዲቦ ሐይቅ ገቡ። ዋናው የአጋንንቶቹ አለቃ ቢሸፍቱ ሐይቅ የሚባለው ሄዶ ገባ ይባላል። አርዲቦ ሐይቅ የገቡት አሁን ማታ ማታ በዚያ አካባቢ ሰው ሲሄድ እየጠለፉ ያስገባሉ ይባላል። በዚህ ሐይቅ ግን ሙሉ ቀን ስንቦጫረቅ ብልውል ማታም ቢሆን የሚነካን የለም። ከሶስት ቀን በኋላም ከባህሩ የወጡትን አሳዎች ወደ ቦታችሁ ተመለሱ አሏቸው። እሳቸውም ሶስት ቀን በባህሩ ላይ ምንም ሳይሆኑ ቆመዋል። ባህሩ ሙሉውን ሲቃጠል እሳቸው የቆሙበት ቦታ ብቻ አልተቃጠለም።

## አፈታሪክ 13

አቡነ ፊልጶስ በጠፍር ተጠቅልለው ወደ ሐይቁ እንዲጣሉ የፈረደው መስፍን ሐይቁ ላይ በእግራቸው ሲቆሙ፤ ሐይቁም ሲቃጠል፣ አሳዎቹም ከሐይቁ ወጥተው ባየ ጊዜ እጅግ ተሸበረ። ምን ማድረግ እንዳለበት ሲያስብም አቡነ ፊልጶስን የከሰሷቸው ሰዎች በአካባቢው አልነበሩም። ከዚያ በኋላ መስፍኑ ጫማቸው ላይ ወድቆና ተለማምጦ ይቅርታ ጠየቃቸው። እሳቸውም ይቅርታውን ተቀብለው እንዲጠመቅ አደረጉት። እሱም ተጠምቆ ወደ

ሃይማኖታቸው ተመለሱ። ቤተሰቡንና ተከታዮቹን በሙሉ እንዲጠመቁ አድርጓል። እሳቸውም ከዚህ በኋላ ከዚህ ገዳም ወጥተው አለምን በሙሉ አስተምረው ደብረ ቢዘን ሄደው ገዳም ገድመው ኑረዋል። መስፍኑም ይህንን ገዳም እየተንከባከበ ይኖር ነበር።

አፈ ታሪክ 14

ይህ አካባቢ ቆላ ስለሆነ እባብ ይበዛበታል፤ ባህሩም አልቀት አለው። አልቀቱ አሁን እየደከመ ቢሆንም ጨርሶ አልጠፋም። እባቡን እንረግጠዋለን፤ ውርማም ስንመነጥር እንጨብጠዋለን። እንዳጋጣሚ ስንረግጠው ወይም ስንጨብጠው ሲያመው እጃችንን፣ እግራችንን ሊነክሰን ይችላል። የነከሰንም አይቆስልም፤ ወዲያውኑ ይድናል። የጻድቁ የአቡነ ኢየሱስ ሞአ መቃብር አፈርን ዘገን አድርገን እንለቀልቀዋለን። ባንለቀልቀውም ምንም አይሆንም። መርዝም የለውም። አልቀቱም ከብቶች ውሃ ሲጠጡ አይዛቸውም፤ ሰውንም አይነካም። እባቡ ፍዝ ሆኖ ቆይቷል። እዚህ ቦታ እባብ ያልነከሰው ሰው የለም። ነገር ግን በእባቡ ንክሻ የተጎዳ ሰው የለም። ይህ የሆነበት ምክንያት ይኩኖ አምላክ በፈረስ ሆኖ ከአቡነ ኢየሱስ ሞአ ጋር ሁኖ ይማከር ነበር። ንግግራቸውም በፊት በተማሪነቱ ጊዜ የገባላቸውን ቃል ለመፈጸም ነበር። በተማሪነቱ ጊዜ በጸሎትህ የአባቴ መንግስት ቢመለስልኝ ሲሶ መንግስት እሰጥሃለሁ ብሏቸው ነበር። እሳቸውም እኔ ሰማያዊ መንግስትን እንጂ ምድራዊ መንግስትን አልፈልግም። ነገር ግን በዚህ ቦታ ያሉ ሴቶችን አስወጥተህ ሳይከፋቸው ደህና ቦታ እንድታስቀምጣቸው። እንዳያዝኑብኝ። ርስት ጉልት እንድትሰጥልኝ። ይቺ ቦታ ግን መካነ መነኮሳት እንድትሆን ቀድሰህ ባርከህ እንድትሰጠኝ አደራ ባሉት መሰረት ያንን ለመፈጸም ነበር የመጣው።

በመጣበት ጊዜም አቡነ ከባህሩ ላለመውጣት መሃላ ስላለባቸው እሱ በበቅሎ ወደ ባህሩ ገብቶ፤ እሳቸው ደግሞ አቡነ ሂሩተ አምላክን ታንኳ እያስቀዘፉ ወደእሱ ቀርበር ነበር የሚነጋገሩት። በሚነጋገሩበት ወቅትም የበቅሎዋን እግር እባብ ተጠመጠመባት፤ አልቀቱ ደግሞ ወጋት። የሚፈሳት ደምም የውሃውን መልክ ቀየረው። አቡነ ኢየሱስ ሞአም ያንን ባዩ ጊዜ ደነገጡና “ወወረገሙ ለአልቀት ወለሃመግድ” ይላል በግእዝ። በዚህ ውሃ ውስጥና በግቢው ውስጥ የምትንቀሳቀሱ አራዊትና እባብም ሆነ አልቀት ከዛሬ ጀምሮ መርዛችሁ የረከሰ ይሁን፤ ከዛሬ ጀምሮ ጉዳት የማታደርሱ ሁኑ ብለው እባቡንና አልቀቱን ረገሟቸው። ከዚያ ጀምሮ እባብ በልቶት የሞተ፤ የተጎዳ የለም። አልቀቱም ከብት አይጎዳም። እንደውም

ላ ቦታ የያዛቸው አልቀት እዚህ ሲጠጡ ይወጣላቸዋል። እባቡና አልቀቱ ከዚህ ግቢና ሀይቅ ውጪ ሰዎችን ሊጎዱ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች እዚህ ቢመጡ ላይድኑ ይችላሉ። ነገር ን በዚህ ግቢና ሐይቅ ውስጥ ግን የገዳሙን ነዋሪዎችም ሆነ ሌሎች እንግዶችን ይተናኮሉም።

ፊ ታሪክ 15

አቡነ ተክለ ሃይማኖት የቦታው ክብር ተገልጾላቸው የመጡት በዚች (በጣታቸው ያመለከቱ) ቦታ ነው። በዚህ ሲመጡም በባህሩ ላይ በእግራቸው እየተራመዱ መጥተው ዚች ድንጋይ ስር ጽጌረዳ ነበረች ድንጋይዋ ላይ አርፈው ጫማቸውን አውልቀው ጫማቸውን አቧራ ድንጋዩ ላይ አራገፉ። በባህሩ ላይ እየተራመዱ ሲመጡ ጫማቸው ካልራሰም ነበር። አባራውም እንዳለ ነው። ይህችን ቅድስት ቦታ በጫማየ አልረግጥም ብለው ጫማቸውን አውልቀው ከድንጋዩ ላይ መታ መታ አድርገው አቧራውን አራገፉት። ጫማቸውን ያወለቁበት ቦታ ላይ ወዲያው ጽጌረዳ በቀለበት። ጽጌረዳዋም እስካሁን ድረስ ነበረች። አሁን አሁን ከብት ስለበዛ ነው ያጠፏት። ከዚያ ከአቡነ ኢየሱስ ሞአ ጋር ተገናኙ። እሳቸውም ቦታ አዘጋጁላቸው። እንደሚመጡም በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾላቸው ስለነበር አንተ ለብዙ ዓለም አባት ትሆናለህ ብለው አመነኮሷቸው። ከዚህ ቦታም ለ10 ዓመት ሳይወጡ አገለገሉ። እዚህ በነበሩበት ጊዜ እየፈጩ፣ እየጋገሩ፣ እየቀዱ፣ እየጸለዩ፣ እየቀደሱ አገልግለዋል። አቡነ ተክለ ሃይማኖት እዚህ ሆነው ከአርባራቱ ካህናተ ሰማይ ጋር ሆነው ነው መንበረ ጸባኦትን ያጠኑት። ገድላቸውም ይህን ያስረዳል።

አፈ ታሪክ 16

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በእዚህ ገዳም ብዙ ጊዜ አገልግለዋል። መቸም የቅዱሳን ብቃታቸው ይለያያል። የአቡነ ኢየሱስ ሞአ ብቃታቸው የጸሎትና የሌላ የሌላ ከፍተኛ ስራ ነው። የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደግሞ የእርድና ስጦታ አላቸው። እዚህ ሲጋግሩ፣ ወጥ ሲሰሩ፣ ንፍሮ ሲቀቅሉ የሚያማስሉትና የሚያዋህዱት በእጃቸው እየበጠበጡ ነበር። እጃቸውም እንደ ጸሐይ ያበራል እንጂ ሙቀት አይሰማቸውም።

ከእለታት አንድ ቀን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቅዳሴ ገብተው ስለነበር አቡነ ኢየሱስ ሞአ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ብቃት ከእኔ የበለጠ ነው? ወይስ ያነሰ? ብለው እጃቸውን እዚያ

ፍላት ውስጥ ሲጨምሩት በጣም ፈጃቸውና ጎዳት አደረሰባቸው። አቡነ ተክለ ሃይማኖትም መቅደስ ውስጥ ሆነው በመንፈስ አዩዋቸው። እኒህ የዋህ አባት አየ ጉድ ጉዳት ላይ ወደቁ! ብለው አዘኑ። በተቀላጠፈ ሁኔታ ቅዳሴውን ጨርሰው ቶሎ ወደሳቸው መጡ። ሲመጡም አቡነ ኢየሱስ ሞአ እጃቸውን ሸፍነው አዩዋቸው። ምን ሆነ ሲሏቸውም ምንም አልሆንኩ አሉ። ከዚያም የተሸፈነውን ጨርቅ ገልጠው አዩባቸው። አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተጎዳውን እጅ እፍ ሲሉበት ጣታቸው ሁሉ እንደ መብራት ተንቀለቀለ። እንደ ብርሃን ሆነ። በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጸሎት አቡነ ኢየሱስ ሞአ የብርሃን እጅ አገኙ።

አፈ ታሪክ 17

አቡነ ብስጣውሮስ አበምኔት በነበሩበት ወቅት ሁለት ወንበዴዎች ወደ ሐይቁ አካባቢ መጡ። ለአበምኔቱም ቤተ ክርስቲያንህን አቃጥለን ሀገርህን ልንወርስና ሀብትህንም ልንቀማ መጣንብህ፤ ሰዎችህንም አንድም ሳናስቀር እንገድላቸዋለን ብለው መልእክት ላኩ። አቡነ ብስጣውሮስም መልእክቱን እንደሰሙ ለማንም ሳይናገሩ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ገብተው የአቡነ ኢየሱስ ሞአን መስቀል ይዘው ወንበዴዎቹ ወዳሉበት ስፍራ መሄድ ጀመሩ። በመንገዳቸውም የአቡነ ኢየሱስ ሞአን ስም ይጠሩ ነበር። ገጻቸውም ያያቸውን ሁሉ በጣም ያስፈራራና ያሸብር ነበር። ወንበዴዎቹም አቡነ ብስጣውሮስ መስቀል ይዘው ወደነሱ ዘንድ ሲመጡ ባዩዋቸው ጊዜ በጣም ደነገጡ። ሲቀርቧቸውም ወደ ኋላ ማፈግፈግ ጀመሩ። ከዚያም ሸሽተው ወደ መጡበት ተመለሱ። አገራቸውም እንደደረሱ ብዙ ሳይቆዩ ሁለቱም ሞቱ።


ወንበዴዎቹ ወደገዳሙ ሲመጡ ለአካባቢው ነዋሪ ከገዳሙ የሚዘርፏትንና የሚያመጡትን ንብረት እንዲሁም የሚይዙትን ግዛት ተናግረው ነበር። ባዶ እጃቸውን መጥተው ታመው የሞቱበት ሁኔታ ሲታወቅም ህዝቡ ሁሉ የነሱ ዳፋ እንዳይደርስባቸው ፈርተው ነበር። ከዚያ በኋላ እንኳን ቤተ ክርስቲያኑን የሚያቃጥልና የሚዘርፍ ቀርቶ ከነመኮሳቱ ፈቃድ ውጪ ወደ ደሴቱ ውስጥ የሚገባ ሰው አልነበረም።

አባሪ -3- ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው ሰዎች ስም ዝርዝር


| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | እድሜ | ኃላፊነት | ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አባ ፍቅረ ዮሐንስ ገብረ ህይወት | ወ | 60 | አበምኔት | 04/06/2002 እና 01/08/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 2 | አባ ፍቅረ ማርያም ዮሐንስ | ወ | 37 | የሙዚየምአስጎብኝ | 05/06/2002 እና 04/08/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 3 | አባ ገብረ ኢየሱስ ሞአ | ወ | 42 | መጋቢ | 05/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 4 | አባ ሀብተ ሥላሴ ወልደአምደ ሥላሴ | ወ | 47 | ንዑስ መጋቢ | 11/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 5 | አባ ገብረ መድህን ገብረሥላሴ | ወ | 32 | ቄሰ ገበዝ | 14/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 6 | አባ ወልደ ጊዮርጊስ ዮሐንስ | ወ | 37 | ሊቀ ረድእ | 15/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 7 | አባ ገብረ ዋህድ | ወ | 50 | ወፍጮ ቤት | 16/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 8 | አባ ወልደ ኢየሱስ ወልደ ሚካኤል | ወ | 64 | እቃ ቤት | 18/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 9 | አባ ወልደ ጊዮርጊስ ገብረ መስቀል | ወ | 28 | ሊቀ አበው | 22/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 10 | አባ ተስፋ ስላሴ ወለወደ ሀና | ወ | 53 | የልማት ኃላፊ | 02/08/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 11 | አባ ኪዳነ ቃል | ወ | 38 | ተማሪ | 20/05/2003 ዓ.ም | አዲስ አበባ |
| 12 | አባ አምደ ሥላሴ | ወ | 72 | ሐሬት | 23/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 13 | አባ ገብረ ሰንበት ተክለ ሐዋርያት | ወ | 45 | የሊቀ ረድዕተከታይ | 24/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ብጹዕ አቡነ አትናቴዎስ | ወ | 58 | የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከቱ ሊ.ቀ ጳጳስ | 08/06/2002 እና 16/06/2002 ዓ.ም | ደሴ |
| 15 | አባ ገብረ ስላሴ በላይ | ወ | 45 | የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ዋ/ጸሐፊ | 01/08/2002 ዓ.ም | ደሴ |
| 16 | መምህር ገብረ ኢየሱስ መለስ | ወ | 30 | የካህናት ማሰልጠኛ መምህር | 30/07/2002 ዓ.ም | ደሴ |
| 17 | መምህር ላዕከማርያም ደስታ | ወ | 38 | የካህናት ማሰልጠኛ መምህር | 02/08/2002 ዓ.ም | ደሴ |
| 18 | መምህር ጥበቡ ደመቀ | ወ | 41 | የካህናት ማሰልጠኛ ርእሰ መምህር | 02/08/2002 ዓ.ም | ደሴ |
| 19 | እማሆይ ስነ ማርያም ጎርፉ | ሴ | 49 | እመምኔት | 06/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 20 | እማሆይ እህተ ማርያም ኪሮስ | ሴ | 41 | የእመምኔቷ ረዳት | 07/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 21 | እማሆይ ወለተ ህጻን | ሴ | 40 | መጋቢ | 07/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 22 | እማሆይ ወለተ ስላሴ | ሴ | 44 | ሊ.ቀ ረድዕ | 24/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 23 | እማሆይ ስርጉተ ማርያም | ሴ | 38 | እቃ ቤት | 13/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 24 | እማሆይ ወለተ መድህን | ሴ | 46 | ሊ.ቀ አበው | 21/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |
| 25 | እማሆይ ወለተ መስቀል | ሴ | 43 | ኃል መጋቢ | 24/06/2002 ዓ.ም | ሐይቅ ገዳም |


ባሪ -4- ከገዳሙ የተወሰዱ ፎቶዎች



ፎቶ -1- በገዳሙ የሚዘጋጀው ዳቤ፣ እንጀራና ወጥ




ፎቶ -2- አባ ወልደ ጊዮርጊስ ሊቀ አበው



ፎቶ -3- ገዳሙ የሚገኝበት ሐይቅ



ፎቶ -4- የቤተ ደናግሉ የሽመና እንቅስቃሴ



ፎቶ -5- 150 ዓመት እንዳስቆጠረ የሚነገርለት ማቡኪያ

## ማረጋገጫ

ይህ ቴሲስ የእኔ መሆኑንና በውስጡም የተገለገልኩባቸውን ምንጮች በሙሉ መጥቀሴን በፊርማየ አረጋግጣለሁ።

ስም፦ ተስፋዬ ተገኝ

ፊርማ ------------

የማስረከቢያ ጊዜ፦ የካቲት 2003 ዓ.ም